በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት
የርዕሰ መስተዳድርና የካቢኔ ጉዳዮች ጽ/ቤት

The Amhara National Regional state
Office of the Government and the Cabinet Affairs

ቁጥር/ Ref. No ... ዐ/ 618 ... 
ቀን / Date 16 / 10/ 2018 ዓ.ም

ለ [illegible] ቢሮ/ባለስልጣን
ባህር ዳር

ጉዳዩ፡-የተሻሻለውን የአስፈፃሚ አካላት አዋጅ ቁጥር 300/2017 ዓ/ም ስለመላክ ፣

የአማራ ክልል ምክር ቤት የተሻሻለውን የአስፈፃሚ አካላት ስልጣንና ተግባራት እንደገና ለመወሰን የወጣውን አዋጅ ቁጥር 300/2017 ዓ/ም ከሐምሌ 21 ቀን 2017 ዓ/ም ጀምሮ ስራ ላይ እንዲውል በማለት በዝክረ -ሕግ ጋዜጣ አሳትሞ ማውጣቱ ይታወቃል፡፡

ስለሆነም ተቋማችሁ ይህንን የተሻሻለውን የአስፈፃሚ አካላት ስልጣንና ተግባራት እንደገና ለመወሰን የወጣውን አዋጅ ቁጥር 300/2017 ዓ/ም ተግባራዊ እንዲያደርግና በአዋጁ መሰረት አንድ ወጥ የሆነ አሰራር እስከታችኛው አደረጃጀት እርከን ድረስ እንዲኖር በጥብቅ እናሳስባለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት

ዳንኤል ደሳለኝ ፈንቴ
የአብክመ የርዕሰ-መስተዳደር ጽ/ቤት ኃላፊ

ግልባጭ

- ለክቡር ርዕሰ መስተዳድሩ
- ለም/ጽ/ቤት ኃላፊ
  ርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት



CamScanner

30ኛ ዓመት ቁጥር 34
30th Year, No. 34

ባሕርዳር ሐምሌ 21 ቀን 2017 ዓ.ም
Bahir Dar, July 27, 2025

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት ዝክረ ሕግ

# ZIKRE HIG

## of the Amhara National Region Council in the Federal Democratic Republic of Ethiopia

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

Issued under the Auspices of the Council of the Amhara National Region

✉ 1324
ያንዱ ዋጋ 3264.62 ብር
Unit Price Birr 3264.62

## አዋጅ ቁጥር 300/2017 ዓ/ም

**በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የተሻሻለው የአስፈፃሚ አካላትን እንደገና ለማቋቋም እና ሥልጣንና ተግባራት መወሰኛ አዋጅ**

## Proclamation No. 300/2025

**The Revised Executive Organs Re-Establishment and Determination of its Powers and Duties Proclamation in the Amhara National Regional State**

## አዋጅ ቁጥር 300/2017 ዓ/ም

**በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የተሻሻለው የአስፈፃሚ አካላትን እንደገና ለማቋቋም እና ሥልጣንና ተግባራት ለመወሰን የወጣ አዋጅ**

የሕግ የበላይነትን በማረጋገጥ በክልሉ ያሉትን የመልማት ፀጋዎች ለመጠቀም እና ለዘመናት ስር ሰደው የቆዩትን የድህነት እና የግጭት አዙሪቶች በማስቀረት የትውልዶች ጥያቄ የነበረውን ብልፅግናን እውን ለማድረግ የክልሉ መንግሥት ተቋማትን ፈትሾ እንደገና ማደራጀት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የተጀመረውን መሠረታዊ የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ አፋጥኖ በክልሉ ኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ ልማትን ለማስፋፋት እና መልካም አስተዳደርን ለማስፈን የሚያግዝ እንዲሁም ክልሉ ያሉትን እምቅ ሰብዓዊ እና ቁሳዊ አቅሞች ተጠቅሞ ያሉበትን መሠረታዊ ተግዳሮቶች እንዲሻገር እና ዘላቂ ልማት እንዲረጋገጥ የሚረዳ የተቋማት አደረጃጀት መፍጠር በማስፈለጉ፤

## Proclamation No. 300/2025

**The Proclamation Issued to Re-Establish and Determine the Powers and Duties of the Revised Executive Organs in the Amhara National Regional State**

Whereas, it is necessary to review and re-organize the regional government institutions in order to utilize the development opportunities in the region by ensuring the rule of law, and eliminating the cycles of poverty and conflict that have been entrenched for centuries, thereby realizing the prosperity that generations have been asking for;

Whereas; it is needed to create an institutional structure helping to promote economic and social development, and promote good governance accelerating fundamental economic structural change commenced in the region, as well as the region to overcome its fundamental challenges by utilizing its existing human and material resources and ensure sustainable development;

ላለፉት በርካታ ዓመታት የተሸረሸሩ ጠቃሚ ክልላዊ ወጎችን፣ እሴቶችን እና ባሕሎችን መልሶ በመገንባት በሥነ ምግባር የታነፀ እና ሀገር ወዳድ ትውልድ የማፍራት ወሳኝ ተልዕኮ የሚሸከሙ ውጤታማ ተቋማትን ለመፍጠር እንዲቻል የተቋማትን አደረጃጀት እንደገና ማሻሻል የሚገባ መሆኑ ስለታመነበት፤

Whereas, it is believed that it is necessary to reform the organization of institutions in order to create effective institutions that carry the important mission of producing morally upright and patriotic generation by rebuilding important regional traditions, values, and cultures that have been eroded over the past several years;

ምርታማነትን በማሳደግ እና ቅልጥፍናን በማረጋገጥ ጥራት ያለው ኢኮኖሚ ለመገንባት እና በክልሉ ሁለንተናዊ ብልፅግናን እውን ለማድረግ የሚከናዱ ፈርጀ ብዙ የልማት እና የመልካም አስተዳደር ሥራዎች በመላ የክልሉ ሕዝብ ዘንድ ዘላቂ ቅቡልነት አግኝተው እንዲከናወኑ ለማድረግ ተቋማዊ ማሻሻያ ማድረግ ተገቢ በመሆኑ፤

Whereas, it is appropriate to make institutional reforms to build a quality economy through increasing productivity and ensuring efficiency, and to make the overall development and good governance activities undertaken to realize an overall prosperity in the region are carried out with lasting acceptance by the entire population of the region;

ለፈጣን ኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ እድገት መሠረት መሆን የሚችል አምራች ሰብዓዊ ሀብት ለማልማት እንዲሁም ሕዝብን ለማገልገል ዝግጁ የሆኑ፣ ክልሉን ለማበልፀግ ሙያዊ ኃላፊነታቸውን በብቃት የሚወጡ፣ በዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብ የተቃኙ፣ አገልጋይ እና ሥልጡን ሲቪል ሰርቫንቶችን ለማፍራት የተቋማትን አደረጃጀት እንደገና ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

Whereas, it is necessary to reform organization of institutions to produce servitude and skilled civil servants to develop productive human resources that can be a base for rapid economic and social development as well as who are ready to serve the people, capable of fulfilling their professional responsibilities to enrich the region, and imbued with democratic thinking;

የክልሉን የአስፈፃሚ አካላት አደረጃጀት፣ ሥልጣን እና ተግባራት ለመወሰን በየጊዜው የወጡ ሕጎች በፍጥነት በመለዋወጣቸው ምክንያት ወጥ የሆነ የተቋማት አደረጃጀትን ለመፍጠር፣ የተቋማት ቀጣይነትን ለማረጋገጥ እና የስያሜ ወጥነትን ለማስቀጠል ያልተቻለ በመሆኑ ይህንኑ ችግር በመቅረፍ ወጭ ቆጣቢ፣ የመፈፀም አቅማቸው ያደገ፣ በየጊዜው የማይለዋወጡ እና የተረጋጉ፣ ተቋማዊ ትውስታ ያላቸው ተቋማትን መፍጠር የሚያስችል፣ ከማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ለውጦች ጋር እየተለወጡ እና እየተሻሻሉ የሚሄዱ የተቋማትን አደረጃጀት እና ስያሜ መፍጠር የሚያስችል ሥርዓት በሕግ መዘርጋት አስፈላጊ መሆኑ ስለታመነበት፤

Whereas, it is believed that it is necessary to establish a system by law in order to create uniform organization of institutions as laws enacted to establish organization of the regional executive organs and determine their powers and duties from time to time used to be changed rapidly, enabling to create organization and nomenclature of institutions which are cost-effective, efficient, unchanged now and then and stable, which have institutional memory, and go with social and economic changes and improvements as it was impossible to ensure continuity of institutions, and maintain consistency in naming, thereby addressing this problem;

CamScanner

በሥራ ላይ ያለው የተሻሻለው የክልሉ አስፈፃሚ አካላት እንደገና ማቋቋሚያ፣ ሥልጣን እና ተግባራት መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 280/2014 በጥናት የተገኙበትን ክፍተቶች በማረም የክልሉ አስፈፃሚ ተቋማት የሥልጣን እና ተግባር ግጭት የሌለባቸው፣ ግልፅ ዓላማ ይዘው የሚሠሩ፣ ተገልጋዩን ኅብረተሰብ የሚያረካ ቀልጣፋ ውሳኔ የሚሰጡ፣ የሥራ ቀረቤታ፣ የተልዕኮ ትስስር እና የእርስ በእርስ ተመጋጋቢ ባሕሪ ያላቸውን የተበታተኑ የሥራ ዘርፎች አሰባስቦ በአንድ አስፈፃሚ አካል ስር በማጠቃለል ተግባር እና ኃላፊነታቸውን ለመወጣት በቅንጅት መሥራት እና ውጤታማነትን ማሳደግ እንዲሁም ኃላፊነታቸውን አጓድለው ሲገኙ ተጠያቂነትን ማረጋገጥ በሚያስችል እና ከሚመለከታቸው የፌደራል መንግሥት አቻ ተቋማት ጋር ተናባቢ በሆነ መልኩ እንደገና ማደረጃት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የአማራ ክልል ምክር ቤት በተሻሻለው የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሕገ መንግሥት አንቀፅ 49 ንዑስ አንቀጽ 3 (1) ድንጋጌ ስር በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል።

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የተሻሻለው የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት አስፈፃሚ አካላት እንደገና ማቋቋሚያ፣ ሥልጣን እና ተግባራት መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 300/2017 ዓ/ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፦

1/ "ቢሮ" ማለት በዚህ አዋጅ የተቋቋመ የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት አባል የተደረገ የክልሉ መንግሥት አስፈፃሚ መሥሪያ ቤት ነው፤

Whereas, it is necessary to re-organize the regional executive bodies by correcting gaps found through study in the revised Proclamation No. 280/2021 on the Re- establishment, Determination of Powers and Duties of the Regional Executive Bodies, and merging the scattered work sectors under one executive body_ in a manner such that there is no conflict of power and duties, operates with clear objectives, makes efficient decisions satisfying the user community, have work closure, mission connection and mutually supportive_ enabling to fulfill their duties and responsibilities working in coordination, increase efficiency as well as ensuring accountability when they are found failed in their responsibilities, and consistent with the relevant federal government institutions;

**Now therefore**, the Amhara Region Council, pursuant to the power vested it under Article 49, Sub-Article 3 (1) of the Revised Amhara National Regional State Constitution has issued this proclamation.

## PART ONE

## GENERAL PROVISIONS

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as "**The Amhara National Regional State Executive Organs Re-Establishment and Determination of Powers and Duties Proclamation No. 300/2025.**"

### 2. Definitions

Unless the context requires otherwise, in this Proclamation:

1/ "**Bureau**" means the executive office of the Regional Government established by this Proclamation and made a member of the Regional Government Council;

CamScanner

2/ "የቢሮ ኃላፊ" ማለት የዚሁ መሥሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ ሆኖ እንዲያገለግል በክልሉ ሕገ-መንግሥት መሠረት የተሾመ ወይም የሚሾም ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ነው፤

3/ "ምክር ቤት" ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት መስተዳድር ምክር ቤት ሲሆን እንደተገቢነቱ የየእርከኑን አስተዳደር ምክር ቤት ይጨምራል፤

4/ "ክላስተር" ማለት ለአሠራር ቅልጥፍና እና ለጋራ ዓላማ ስኬታማነት ተመጋጋቢ የሥራ ባሕርያት ያላቸው አስፈፃሚ ተቋማትን በአንድ ቡድን ውስጥ የማደራጀት ተግባር ነው፤

5/ "ኢንቨስትመንት ሆልዲንግ" ማለት በዚህ አዋጅ አንቀፅ 53 ንኡስ አንቀፅ (2) ላይ የተዘረዘሩ የመንግሥት እና የሕዝብ ሀብቶችን በአንድ ሕጋዊ ተቋም ጥላ ሥር በኩባንያ መርህ መሠረት በባለቤትነት እንዲያስተዳድር ኃላፊነት የተሰጠው የክልሉ የኢንቨስትመንት ድርጅት ነው፤

6/ "የመንግሥት የልማት ድርጅቶች" ማለት ሙሉ በሙሉ በክልሉ መንግሥት በባለቤትነት ተይዘው በማምረት፣ በማከፋፈል፣ አገልግሎት በመስጠት ወይም ሌላ ማናቸውንም ኢኮኖሚ ነክ ተግባር በመፈፀም ትርፍ ለማግኘት የተመሰረቱ ተቋማት ናቸው፤

7/ "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

8/ በዚህ አዋጅ ውስጥ የተጠቀሱ ሌሎች ቃላት ወይም ሀረጎች እንደ አስፈላጊነታቸው መስተዳደር ምክር ቤቱ በሚያወጣው የተቋማት አሠራር እና አደረጃጀት ደንቦች ሊተረጎሙ ይችላሉ፤

9/ በዚህ አዋጅ ውስጥ በወንድ ፆታ የተገለፀው ለሴትም ያገለግላል::



2/ **"Head of Bureau"** shall mean any natural person appointed or to be appointed to serve being head of such an executive office pursuant to the provisions of the Regional constitution;

3/ **"Council"** shall mean the Council of the National Regional Government including those councils at various levels as appropriate;

4/ **"Cluster"** means the act of organizing into a group of executive institutions with similar characteristics for operational efficiency and achievement of common goals;

5/ **"Investment Holding"** means a regional investment organization responsible for managing the government and public resources listed in Article 53, Sub-Article (2) of this Proclamation under the umbrella of a single legal entity in accordance with the principles of a company;

6/ **"Public Development Enterprises"** means institutions fully owned by the regional government established to make profit by producing, distributing, providing services or performing any other economic activity;

7/ **"Person"** means a natural person or given legal personality by law;

8/ Other words or phrases mentioned in this proclamation may be defined, as necessary, by procedural and organizational regulations of institutions to be issued by the Government Council;

9/ In this proclamation, what is defined in the masculine gender shall also apply to the feminine gender.

CamScanner

## ክፍል ሁለት

## ስለ ርዕሰ መስተዳድሩ፣ ምክትል ርዕሰ መስተዳድሩ እና የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት

### 3. ስለ ርዕሰ መስተዳድሩ ሥልጣን እና ተግባር

የአማራ ክልል ርዕሰ መስተዳድር ሥልጣን እና ተግባር በተሻሻለው የብሔራዊ ክልሉ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 60 ድንጋጌዎች ሥር የተመለከተው ይሆናል::

### 4. ስለ ምክትል ርዕሰ መስተዳድሩ ሥልጣን እና ተግባር

የአማራ ክልል ምክትል ርዕሰ መስተዳድር ሥልጣን እና ተግባር በተሻሻለው የብሔራዊ ክልሉ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 61 ድንጋጌዎች ሥር የተመለከተው ይሆናል::

### 5. ስለ ክላስተር አስተባባሪ ሥልጣን እና ተግባር

የክላስተር አስተባባሪዎች ተጠሪነታቸው ለርዕሰ መስተዳድሩ ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣን እና ተግባራት ይኖሯቸዋል:-

1/ ከሚመለከተው ተቋም ጋር በመሆን ለክላስተሩ አፈፃፀም መሻሻል አወንታዊ ሚና የሚጫወቱ እና የክላስተሩን ተቋማት አስተሳሳሪ ዓላማ የሚያንፀባርቁ ስትራቴጅዎችን ይቀርፃል፣ አፈፃፀማቸውን ይከታተላል፤

2/ በክላስተር ውስጥ የመንግሥት ፕሮግራሞችን እና የልማት ውጥኖችን የላቀ አፈፃፀም እንዲኖራቸው ይሠራል፤ ከሀገራዊ ፖሊሲዎች እና ክልላዊ ዕቅዶች ጋር ተጣጥመው መፈፀማቸውን ያረጋግጣል፣ ውጤታማነቱን ይገመግማል፤



## PART TWO

## THE HEAD OF GOVERNMENT, DEPUTY HEAD OF GOVERNMENT AND THE COUNCIL OF THE REGIONAL GOVERNMENT

### 3. Powers and Duties of Head of Government

Powers and Duties of the Head of Government of the Amhara National Regional State shall be those stipulated under provisions of Article 60 of the Revised Regional Constitution.

### 4. Powers and Duties of the Deputy Head of Government

Powers and duties of the Deputy Head of Government of the Amhara National Regional State shall be those stipulated under provisions of Article 61 of the Revised Regional Constitution.

### 5. Powers and Duties of the Cluster Coordinator

Cluster Coordinators, being accountable to the Head of Government, shall have the following powers and duties:

1/ Together with the relevant institution, formulates strategies that play a positive role in improving the performance of the cluster and reflect the linking objectives of the cluster institutions, and monitor their implementation;

2/ Works to ensure the best implementation of government programs and development initiatives in the cluster; ensures their implementation in line with national policies and regional plans, and evaluates their effectiveness;

CamScanner

3/ ከክላስተሩ ዓላማዎች ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን መረጃዎች እና ሪፖርቶች ይቀበላል፣ ይተነትናል፣ ለተቋማት ግብረ መልስ ይሰጣል፣ ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ያደርጋል፤

4/ ጠንካራ እና ችግር ፈቺ የክትትል እና ድጋፍ ሥርዓት በመዘርጋት የተቋማትን የተግባር አፈፃፀም ውጤታማነት ይገመግማል፤ ምርጥ ተሞክሮዎችን ቀምሮ በማስፋት በክላስተሩ ውስጥ ተቀራራቢ አፈፃፀም እንዲኖር ለማድረግ ይሠራል፤

5/ የክላስተሩን የሥራ መርሃ ግብር ያዘጋጃል፤ የክላስተሩን ስትራቴጂያዊ ጉዳዮች ለይቶ ያቅዳል፤ ግቦች እና ዓላማዎች ግልፅ እና ሊደረስባቸው የሚችሉ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤

6/ የክላስተሩ ተቋማት የተቀናጀ የገጠር እና የከተማ ልማት ጽንሰ ሐሳቦችን መሠረት ያደረጉ ሥራዎችን እንዲያከናውኑ ያስተባብራል፤ ያቀናጃል፤ ውጤታማነቱን ይከታተላል፤

7/ የክላስተሩ አባል ተቋማት አመራሮች አግባብነት ያላቸውን የተቋማት ሕጎች እና የሥራ ሥነ ምግባር ደረጃዎችን አክብረው መሥራታቸውን ያረጋግጣል፤ ጉድለቶች ሲያጋጥሙ በሚመለከታቸው አካላት የማስተካከያ እርምት እንዲወሰድ ያደርጋል፤

8/ በክላስተሩ ለሚያጋጥሙ የተፈጥሮ ወይም ሰው ሠራሽ አደጋዎች ወቅታዊ ምላሽ ይሰጣል፤ የሚመለከታቸውን ተቋማት እና ባለ ድርሻ አካላትን በማስተባበር ሁኔታውን ይቆጣጠራል፤ ከክላስተሩ አቅም በላይ የሆኑ ሁኔታዎች ካጋጠሙ ለርዕሰ መስተዳደሩ ወይም ለሚመለከታቸው አካላት ያሳውቃል፤

9/ በክላስተሩ አባላት፣ ባለ ድርሻ አካላት ወይም የሥራ ክፍሎች መካከል የመገናኛ ማዕከል ሆኖ ያገለግላል፤ መልካም የሥራ ግንኙነትን እና ትብብርን ያሳድጋል፣ ያመቻቻል፤



3/ Receives and analyzes data related to objectives of the cluster, provides feedback to institutions, and reports to the relevant body;

4/ Evaluates the effectiveness of performance of institutions by establishing a strong and problem-solving monitoring and support system; and works for the existence of related performance within the cluster by formulating and expanding best practices;

5/ Prepares the cluster's work program; identifies and plans strategic issues for the cluster; and ensures that goals and objectives are clear and achievable;

6/ Coordinates, integrates, and monitors the effectiveness of cluster institutions to carry out activities based on the concepts of integrated rural and urban development;

7/ Ensures that leaders of cluster member institutions comply with relevant institutional laws and standards of work ethics; and causes corrective measures to be taken by relevant bodies when deficiencies are encountered;

8/ Provides timely response to natural or man-made disasters occurring in the cluster; monitors the situation through coordinating with relevant institutions and stakeholders; notifies to the head of government or relevant parties if situations arose are beyond the cluster's capacity;

9/ Serves as a communication center among cluster members, stakeholders or work units; promotes and facilitates good working relations and cooperation;

CamScanner

10/ መለኪያዎችን መሠረት በማድረግ የተግባር አፈፃፀምን ይተነትናል፤ መሻሻል ያለባቸው ጉዳዮችን ለይቶ በቀጣይ የሚፈቱበትን አማራጭ መንገድ ያመላክታል፤

11/ የክላስተሩን ዲጂታላይዜሽን ሥርዓት ውጤታማ ለማድረግ የዲጂታል መሠረተ ልማት ወቅታዊ፣ ደኅንነቱ የተጠበቀ እና ከክላስተሩ ግቦች ጋር የተጣጣመ መሆኑን ያረጋግጣል፤

12/ አመራሮች መሪነትን እንዲረዱ እና ለብዙኃኑ ጥቅም እንዲያውሉት፣ ጤናማ እና ጠንካራ የሥራ ባሕል እንዲፈጠር፣ ሥልጡን እና አገልጋይ ሲቪል ሰርቫንት እንዲገነባ በማድረግ ለተቋም ግንባታ ሥራዎች እና ለአገልግሎት አሰጣጥ ቅልጥፍና ልዩ ትኩረት ሰጥቶ ይሠራል፤ ይከታተላል፤ ይደግፋል፤

13/ ተቋማት ክልሉ ባሉት የመልማት ፀጋዎች እና ባሉበት ዘርፈ ብዙ ችግሮች ልክ እንዲሠሩ በማነቃቃት ለክልሉ እና ለሀገራዊ ጥቅል ምርት የሚኖራቸው አስተዋፅዖ እንዲያድግ ያደርጋል፣ ውጤቱን በየጊዜው እየገመገመ ይመራል፤

14/ የሚመለከተዉ የመስተዳድር ምክር ቤት ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ሆኖ ይሠራል፤

15/ በዚህ አንቀጽ ከንዑስ-አንቀጽ (1) እስከ ንዑስ-አንቀጽ (13) የተመላከቱት እንደተጠበቁ ሆነው የክላስተር አደረጃጀት፣ ስያሜ እና ዝርዝር የአሠራር ሥርዓት መስተዳደር ምክር ቤቱ በሚያወጣው መመሪያ የሚወሰን ይሆናል።

## 6. <u>ስለ ምክር ቤቱ ሥልጣን እና ተግባር</u>

የአማራ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ሥልጣን እና ተግባር በብሔራዊ ክልሉ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 58 ድንጋጌዎች ሥር የተመለከተው ይሆናል።

10/ Analyzes work performances based on metrics; identifies areas for improvement, and suggests alternative ways to address them;

11/ Ensures that the digital infrastructure is up-to-date, secured, and aligned with the cluster's goals to make the cluster's digitalization system effective;

12/ Works, monitors, and supports giving special attention for institution-building activities and service delivery efficiency by making leaders to understand leadership and use it for the benefit of the masses, creating healthy and strong work culture, and building skilled and servant civil servant;

13/ Stimulates institutions to work in accordance with the development opportunities and multifaceted problems of the region, thereby increasing their contribution to the regional and national gross domestic product, and periodically reviews the results;

14/ Acts as the chairperson of the relevant standing committee of the Government Council;

15/ With out prejudice to the provisions of Sub-articles (1) to (13) of this Article, organization, nomenclature and detailed operating procedures of the cluster shall be determined by a directive to be issued by the Government Council.

## 6. <u>Powers and Duties of the Council</u>

Powers and duties of the the Amhara National Regional Government Council shall be those stipulated under the provision of Article 58 of the Revised Regional Constitution.

CamScanner

## 7. የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት አባላት

1/ የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ከዚህ በታች የተመለከቱት አባላት ይኖሩታል:-

ሀ) ርዕሰ መስተዳድሩ፤

ለ) ምክትል ርዕሰ መስተዳድሩ፤

ሐ) በምክትል ርዕሰ መስተዳድር ማዕረግ የተሾሙ የክላስተር አስተባባሪዎች፤

መ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 18 ሥር የተመለከቱት ቢሮዎችን የሚመሩ የቢሮ ኃላፊዎች፤

ሠ) በርዕሰ መስተዳድሩ የሚሰየሙ ሌሎች የተቋም ኃላፊዎች::

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (1) ፊደል ተራ (መ) ድንጋጌ ሥር የተመለከተው የትኛውም የቢሮ ኃላፊ በምክር ቤቱ ስብሰባ ላይ ሊገኝ በማይችልበት ጊዜ በተለየ ሁኔታ በጽሑፍ ካልወከለ በስተቀር በሹመት ቀደምትነት ያለው ምክትል ቢሮ ኃላፊ በምክር ቤቱ ስብሰባዎች ላይ ይሳተፋል፤

3/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ-አንቀፅ (2) መሠረት ሹመቱ በተመሳሳይ ቀን የተሰጠ ከሆነ ከተሿሚዎች መካከል ሴት ካለች ቅድሚያ ለሴት ይሰጣል፤

4/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ-አንቀፅ (3) በተገለፀው መሠረት መለየት ካልተቻለ በአጠቃላይ የበለጠ የሥራ ልምድ ያለው የሚሳተፍ ይሆናል::

## 8. ስለ ምክር ቤቱ ጽሕፈት ቤት

1/ የርዕሰ መስተዳድሩ ጽሕፈት ቤት በተሻሻለው የክልሉ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 62 ንዑስ-አንቀጽ (2) ሥር በተደነገገው መሠረት የመስተዳድር ምክር ቤቱ ጽሕፈት ቤት ይሆናል፤

2/ ጽሕፈት ቤቱ የሚኖረው ዝርዝር ሥልጣን እና ተግባር ይህንን አዋጅ ተከትሎ ምክር ቤቱ በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል፤

## 7. Members of the Regional Government Council

1/ The Regional Government Council shall have the following members here bellow:

A) The Head of Government;

B) The Deputy Head of Government;

C) Cluster Coordinators assigned in the Deputy Head of Government Status;

D) Heads of Bureaus referred in Article 18 of this Proclamation;

E) Other heads of institutions to be appointed by the head of government.

2/ Whenever any one of the Head of Bureau indicated under Sub-article 1/D/ of this Article is unable to attend sessions of the council, the Deputy Head of Bureau having seniority in appointment shall so participate in such sessions provided that no other delegations have been conferred before in writing on exceptional grounds.

3/ If the appointment is made on the same date in accordance with Sub-article (2) of this Article, if there is a woman among the appointees, priority shall be given to the woman;

4/ If it is not possible to distinguish according to Sub-article (3) of this Article, the person with more general work experience shall participate.

## 8. Office of the Regional Government Council

1/ Office of the Regional Government Council shall be office of the Head of Government as indicated under provisions of Article 62, Sub-article /2/ of the Revised Regional constitution.

2/ Detailed powers and duties of the office shall be determined by a regulation to be issued by the council following this proclamation.

3/ የጽሕፈት ቤቱ ኃላፊ በቢሮ ኃላፊ ማዕረግ የሚሾም ሆኖ:-

ሀ) የምክር ቤቱን ጉዳዮች በበላይነት ያስፈጽማል፤

ለ) በምክር ቤቱ ስብሰባዎች ላይ ያለ ድምፅ በመሳተፍ ሐሳብ እና አስተያየት ይሰጣል፤

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (1) እና (2) ሥር የሰፈሩት ድንጋጌዎች በበታች የአስተዳደር ጽሕፈት ቤቶችም ሆነ ኃላፊዎቻቸው ላይ በተመሳሳይ ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል።

## 9. ስለ ምክር ቤቱ የመሰብሰቢያ ጊዜ፣ የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት እና አመራር

1/ የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት:-

ሀ) ዝርዝሩ በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣ ደንብ የሚወሰን ሆኖ መደበኛ እና አስቸኳይ ስብሰባዎችን ያካሂዳል፤

ለ) ምልአተ-ጉባዔ የሚሆነው ከምክር ቤቱ አባላት ውስጥ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት በስብሰባው ላይ ሲገኙ ይሆናል፤

ሐ) ምክር ቤቱ ውሳኔዎችን የሚያሳልፈው በተባበረ ድምፅ ይሆናል፤ በተባበረ ድምፅ መወሰን ካልተቻለ ግን ጉዳዩ በስብሰባው ላይ በተገኙት የምክር ቤቱ አባላት የአብላጫ ድምፅ ይወሰናል፤ የተሰጠው ድምፅ እኩል ከሆነ ርዕሰ መስተዳድሩ ያለበት አብላጫ ድምጽ ይኖረዋል፤

2/ የምክር ቤቱ አባላት አጀንዳ የማስያዝ መብታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ርዕሰ መስተዳድሩ:-

ሀ) ለምክር ቤቱ የመወያያ አጀንዳ ሆነው የሚቀርቡትን ጉዳዮች ይለያል፣ ይወስናል፤

ለ) የምክር ቤቱን ስብሰባዎች ይመራል፤

ሐ) ለምክር ቤቱ የመወያያ አጀንዳ ሆኖ የቀረበ ማናቸውም ጉዳይ በሚመለከተው የምክር ቤቱ ቋሚ ኮሚቴ በኩል መታየት የሚያስፈልገው ሆኖ ሲያገኘው ስብሰባውን ለሌላ ጊዜ ያስተላልፋል፤



3) To be appointed at the status of Head of Bureau, the Head of the office shall:

A)Cause the the execution of the council affairs;

B) Attends, without vote, the council sessions as well as render suggestions and opinions.

4/ Provisions of Sub-articles /1/ and /2/ of this Article hereof shall, mutatis mutandis apply to the subordinate administrative offices as well as their respective Heads.

## 9. Meeting Time, Procedure and Chairing of the Council

1) The Regional Government Council shall:

A) Details being specified in a regulation based on this proclamation, undertake ordinary and extra ordinay sessions;

B) It shall be quorum if more than half of its members are present at the meeting;

C) The council shall pass decisions in acclamation, provided that it may be by majority vote in default of same; where the votes are in tie, the opinion supported by the head of government shall be decision of the council;

2/ Without prejudice to the rights of members of the Council to submit an agenda, the Head of Government shall:

A) Identifies and decides on the agenda presented to the council;

B) Presides over the council's meeting;

C) Postpones the meeting if he finds out that a given agenda is subject for consideration by concerned standing committee of the council;

CamScanner

3/ ርዕሰ መስተዳድሩ በማይኖርበት ወይም ሥራውን ለማከናወን በማይቻልበት ጊዜ እና ሁኔታ እርሱን ተክቶ ምክትል ርዕሰ መስተዳድሩ የምክር ቤቱን ስብሰባዎች ይመራል፡፡

## 10. ስለ ምክር ቤቱ ቋሚ ኮሚቴዎች

1/ የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ኃላፊነቱን በብቃት ለመወጣት ይረዳው ዘንድ ከምክር ቤቱ አባላት መካከል የሚሰየሙ ልዩ ልዩ ቋሚ ኮሚቴዎች ይኖሩታል፤

2/ የእነዚህ ቋሚ ኮሚቴዎች ዝርዝር ተግባራት እና ኃላፊነቶች ምክር ቤቱ በዚህ አዋጅ መሠረት በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

## ክፍል ሦስት
## የክልል አስፈፃሚ አካላት ስያሜ

## 11. ስለ ቢሮ

አንድ ተቋም፡-

1/ ሥራውን በሚያከናውንበት ዘርፍ እና በተያያዥ ጉዳዮች ላይ ፖሊሲ፣ ስትራቴጂ እና ፕሮግራም የሚቀርፅ፣ ሲፀድቁም በበላይነት ተፈፃሚነታቸውን የሚመራ እና የሚያስተባብር፤

2/ በሚሠማራበት ዘርፍ ለሌላ ተቋም ስታንዳርድ በማውጣት ቁጥጥር የሚያደርግ፣ እንደ አስፈላጊነቱ ፈቃድ የሚሰጥ፣ አቅም በመገንባት እንዲሁም በተጨባጭ ፕሮግራምን ወደ ፕሮጀክትነት በመቀየር የቀን-ተቀን ሥራዎችን የሚያከናወን እና አገልግሎት የሚሰጥ፤

3/ ተጠሪ ለሆነለት ወይም እንደ አስፈላጊነቱ ከሥራው ጋር ተያያዥነት ላለው ለሌላ የክልል ተቋም ከተሰጠው ሥልጣን እና ተግባር በከፊል ቆርሶ የሚሰጥ በቢሮነት ይሰየማል፡፡

## 12. ስለ ኮሚሽን

አንድ ተቋም፡-

1/ ለቢሮ ለርዕሰ መስተዳድሩ ወይም የጥቅም ግጭት ይኖራል ተብሎ ሲገመት ለክልሉ ምክር ቤት ተጠሪ የሚሆን፤



3/ In the absence or inability of the Head of Government, the deputy Head of Government shall, in his place, preside over meetings of the council.

## 10. Standing Committees of the Council

1/ The Regional Government Council shall have various standing committees appointed from among members of the council to assist it in carrying out its responsibilities effectively;

2/ Detailed duties and responsibilities of these standing committees shall be determined by a directive to be issued by the council in accordance with this proclamatuiion.

## PART THREE
## NOMENCLATURE OF REGIONAL EXECUTIVE BODIES

## 11. About Bureau

An institution shall be nomenclatured as Bureau if it:

1/ Formulates policies, strategies and programs in the sector in which it operates and related issues, and once approved, directs and coordinates their implementation;

2/ Regulates other institutions in the sector in which it operates by issuing standards, issues licenses as necessary, carries out day-to-day operations and provides services by building capacity and pragmatically transforming programs into projects;

3/ Partially or completely delegates its powers and duties to another regional institution related to its work, as necessary.

## 12. About Commission

An institution shall be nomenclatured as Commission if it:

1/ is responsible to Bureau head of government or region council when conflict of interest is suspected;

2/ የተለያዩ መሥሪያ ቤቶችን እና ሥራዎችን የሚያቀናጅ፣ ፖሊሲን እና ስትራቴጂን የሚቀርጽ እና አፈፃፀሙን በበላይነት የሚያስተባብር፣

3/ እንደ አግባቡ ዘላቂ ለሆነ ወይም በአንዳንድ ሁኔታ በጊዜያዊነት አንገብጋቢ ለሆኑ ጉዳዮች ሊቋቋም የሚችል በኮሚሽንነት ይሰየማል፡፡

## 13. ስለ ባለሥልጣን

አንድ ተቋም፡-

1/ የቁጥጥር ሥራ ለመስራት ደረጃ የማውጣት እና በወጣው ደረጃ መሠረት መተግበሩን የሚያረጋግጥ፣

2/ ለርዕሰ መስተዳድሩ ተጠሪ የሚሆን ወይም የጥቅም ግጭት ይኖራል ተብሎ ሲገመት ለክልል ምክር ቤት ተጠሪ የሚሆን፣

3/ በዋናነት በተሰጠው የዘርፍ ሥራ ስታንዳርዶችን የማውጣት፣ ስታንዳርዶችን መሠረት በማድረግ የቁጥጥር ሥራ የሚያከናውን ወይም በሚመለከተው አካል የወጡ ስታንዳርዶችን የሚያስፈፅም፣

4/ ፈቃድ የሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች ሲኖሩ ፈቃድ የመስጠት እና የመቆጣጠር ሥራን የሚያከናውን በባለሥልጣንነት ይሰየማል፡፡

## 14. ስለ አገልግሎት

አንድ ተቋም በዋናነት ለዜጎች አገልግሎት የሚሰጥ ተቋም በአገልግሎትነት ይሰየማል፡፡

## 15. ስለ ጽሕፈት ቤት

አንድ ተቋም በዋናነት አንድን ልዩ ትኩረት የሚፈልግ ተግባር በልዩ ሁኔታ ተቋማዊ አደረጃጀት ይዞ የተለያዩ ተቋማትን ማስተባበር በሚያስፈልግበት ወቅት በልዩ ሁኔታ ጊዜያዊ ወይም ቋሚ ዓላማ ይዞ የሚቋቋም በጽሕፈት ቤትነት ይሰየማል፡፡

2/ coordinates various offices and activities, formulates policies and strategies, and coordinates their implementation;

3/ may be established on a permanent basis or, in some cases, temporarily for urgent matters, as appropriate.

## 13. About Authority

An institution shall be nomenclatured as Authority if it:

1/ issues standards for regulatory work and ensures their implementation in accordance with same;

2/ is accountable to Head of Government or, when a conflict of interest is suspected, to the Region Council;

3/ primarily issues standards in the given sector, carries out regulatory work based on standards, or causes execution of standards issued by relevant body;

4 / issues license in cases where same are required, and carries out regulatory works.

## 14. About Service

An institution that primarily provides services to citizens shall be termed as service institution.

## 15. About Office

An institution to be established having permanent or temporal objective with organizational structure primarily for an activity requiring special attention in need of coordinating various institutions shall be designated as an Office.

CamScanner

## 16. ስለ ኢንስቲትዩት

አንድ ተቋም ተጠሪነቱ እንደተሠማራበት የሥራ ዘርፍ አግባብ ላለው ቢሮ የሆነ በሥልጠና፣ በጥናት፣ በምርምር እና በማማከር አገልግሎት ላይ የሚያተኩር በኢንስቲትዩትነት ይለየማል፡፡

## 17. ስለ ኤጀንሲ

አንድ ተቋም ከሚመለከተው የመንግሥት ተቋም ወይም ድርጅት የተወሰኑ ተግባራትን እና ኃላፊነቶችን እንዲያከናውን ተግባራዊ ኃላፊነት የሚሰጠው እና ይህንኑ የተሰጠውን ተግባር በማከናወን ላይ የሚያተኩር በኤጀንሲነት ይለየማል፡፡

## ክፍል አራት

## ስለ መንግሥት አስፈፃሚ አካላት በጠቅላላው

## 18. ስለ መቋቋም

የሚከተሉት የክልሉ አስፈፃሚ አካላት በዚህ አዋጅ ተቋቁመዋል፡-

1/ የግብርና ቢሮ፤

2/ የንግድ እና ገበያ ልማት ቢሮ፤

3/ የኢንዱስትሪ እና ኢንቨስትመንት ቢሮ፤

4/ የመሬት ቢሮ፤

5/ የከተማ እና መሠረተ ልማት ቢሮ፤

6/ የውኃ እና ኢነርጂ ቢሮ፤

7/ የማዕድን ቢሮ፤

8/ የመንገድ፣ ትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ ቢሮ፤

9/ የሥራ እና ክህሎት ቢሮ፤

10/ የገንዘብ ቢሮ፤

11/ የገቢዎች ቢሮ፤

12/ የትምህርት ቢሮ፤

13/ የጤና ቢሮ፤

14/ የፍትሕ ቢሮ፤

15/ የሰላም እና ጸጥታ ቢሮ፤



## 16. About Institute

An institution shall be termed as an institute if it is responsible to a Bureau for the field of work in which it is engaged and focuses on training, study, research and consultancy services.

## 17. About Agency

An institution given practical responsibility to carry out certain functions and responsibilities from relevant government institution or organization and focuses on carrying out the assigned functions shall be called an agency.

## PART FOUR

## EXECUTIVE ORGANS OF GOVERNMENT IN GENERAL

## 18. Establishment

The following executive organs of the region are hereby established by this proclamation:

1/ Bureau of Agriculture;

2/ Bureau of Trade and Market Development;

3/ Bureau of Industry and Investment;

4/ Bureau of Land;

5/ Bureau of Urbans and Infrastructure;

6/ Bureau of Water and Energy;

7/ Bureau of Mineral;

8/ Bureau of Road, Transport and Logistics;

9/ Bureau of Labour and Skills;

10/ Bureau of Finance;

11/ Bureau of Revenues;

12/ Bureau of Education;

13/ Bureau of Health;

14/ Bureau of Justice;

15/ Bureau of Peace and Security;

CamScanner

16/ የሴቶች፣ ወጣቶች እና ማኅበራዊ ጉዳይ ቢሮ፤

17/ የፕላን እና ልማት ቢሮ፤

18/ የሲቪል ሰርቪስ እና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ፤

19/ የመንግሥት ኮሚዩኒኬሽን ቢሮ፤

20/ የባሕል፣ ቱሪዝም እና ስፖርት ቢሮ፤

22/ የእንስሳት እና ዓሣ ሀብት ቢሮ፤

22/ የኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ቢሮ

23/ የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን::

## 19. የወል ሥልጣን እና ተግባር

1/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 18 የተቋቋመ ቢሮ እና ባለሥልጣን መሥሪያ ቤት በየሥራ መስኩ:-

ሀ) የፌደራል መንግሥቱን ፖሊሲዎች እና ፕሮግራሞች መሠረት ያደረገ እና የክልሉን ነባራዊ ሁኔታዎች ያገናዘቡ ክልል አቀፍ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጅዎችን እና ሕግጋትን ያመነጫል፣ የሥራ ዕቅድ እና የማስፈፀሚያ በጀት ረቂቆችን ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፤

ለ) የክልሉን እና የፌደራሉን መንግሥታት ሕጎች እና ደንቦች በክልሉ ውስጥ በሥራ ላይ ያውላል፤

ሐ) አግባብ ካለው የክልሉ መንግሥት አካል ጋር በመመካከር የጥናት እና ምርምር ተግባራትን ያከናውናል፣ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ያጠናቅራል፣ ይተነትናል፣ ለተጠቃሚዎች ያሰራጫል፤

መ) እንደ አስፈላጊነቱ በክልሉ ውስጥ የራሱን የበታች አደረጃጀቶች ይፈጥራል፣ ሥራቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ ለብሔረሰብ፣ ለወረዳዎች እና ለከተማ አስተዳደሮች ተገቢውን ድጋፍ እና የምክር አገልግሎት ይሰጣል፤

ሠ) አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር በውስጡ የሚታዩትን የአቅም ክፍተቶች ይለያል፣ በወቅቱ የሚሞሉበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤



16/ Bureau of Women, Youth and Social Affairs;

17/ Bureau of Plan and Development;

18/ Bureau of Civil Service and Human Resource Development;

19/ Bureau of Government Communication;

20/ Bureau of Culture, Tourism and Sport;

21/ Bureau of Animal and Fishery Resources;

22/ Bureau of Innovation and Technology;

23/ Authority of Environmental Protection.

## 19. Collective Powers and Duties

1/ The bureau and authority established under Article 18 of this Proclamation, in each field of work, shall:

A) Initiate regional policies, strategies and laws based on policies and programs of the Federal Government and having due regard to the objective realities of the regional state as well as prepare work plan along with the budget proposal and implement same upon approval;

B) Implement lasws of federal and regional states and regulations throghout the region;

C) In collaboration with pertinent bodies of the region, perform research activities; collect, compile and analyze information and distribute same to users;

D) Create, as may be necessary, its subordinate structures throughout the region, follow up and monitor their activities as well as provide the appropriate support and advisory services to the nationality, wereda and city administrations;

E) In collaboration with pertinent bodies, identifies capacity gaps seen in it, facilitate conditions to fill the gaps in time;

ረ) በሀገሪቱ ውስጥ የሚካሄደውን ሁለንተናዊ ልማት ለማፋጠን እና የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታን ለማሳካት የተቀረጹ ልዩ ልዩ የማሻሻያ ፕሮግራሞች እና ፕሮጀክቶች ከመሥሪያ ቤቱ ተልዕኮ እና ፍላጎት ጋር በተጣጣመ መንገድ እንዲተገበሩ ያደርጋል፤

ሰ) ከተግባር እና ኃላፊነቱ ጋር በተያያዘ ዝርዝር የማስፈፀሚያ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፤

ሸ) ለየሥራ ዘርፉ ባለው ተገቢነት ላይ አተኩሮ የሴቶችን፣ የሕፃናትን፣ የወጣቶችን፣ የአካል ጉዳተኞችን እና የአረጋውያንን ሕገ መንግሥታዊ እኩልነት እና ሌሎች ተጋላጭ የኅብረተሰብ ክፍሎችን ሕገ መንግሥታዊ እኩልነት እና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ይቻል ዘንድ በዕቅድ፣ በፕሮግራም፣ በፕሮጀክት እና በሕጎች ውስጥ አካቶ ይሠራል፤

ቀ) በሚካሄዱት የልማት ፕሮግራሞች እና ፕሮጀክቶች ውስጥ ለአካባቢ ጥበቃ ሕጎች ተግባራዊነት ልዩ ትኩረት ሰጥቶ ይሰራል፤

በ) በሕግ መሠረት ውሎችን ይዋዋላል፣ የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ስምምነቶችን ያደርጋል፣ በስሙ ይከሳል፣ ይከሰሳል፤

2/ በዚህ አዋጅ ክፍል ስድስት ስር ወይም በየማቋቋሚያ ሕግጋት ስር በተደነገገው መሠረት ተጠሪ የተደረጉለትን አስፈፃሚ መሥሪያ ቤቶች፣ ተቋማት እና ድርጅቶች አፈፃፀም በበላይነት ይመራል፣ ሥራቸውን ያስተባብራል፣ አደረጃጀቶቻቸውን እና የሥራ ፕሮግራሞቻቸውን መርምሮ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው የክልሉ መንግሥት አካላት ቀርበው እንዲወሰኑ ያደርጋል፤

3/ በዚህ አዋጅ እና በሌሎች ሕጎች የተሰጡትን ዝርዝር ሥልጣን እና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፤



F) Causes the designed different programs and projects to be implemented in line with the ofice's mission and demand to foster the overall development and realize the democratic building system taken place in the country;

G) May issue detailed implementation directives in relation to its own duties and responsibilities;

H) Focusing on the relevance of each sector of work, works to ensure the constitutional equality and benefit of women, children, youth, people with disabilities, and the elderly, as well as other vulnerable segments of the society by incorporating them into plans, programs, projects and laws;

I) pay special attention to the implementation of environmental protection laws in development programs and projects;

J) Enter into contracts pursuant to law, own property, conclude agreements, sue and be sued in its own name;

2/ Direct the overall implementation of the executive offices, institutions and organizations made accountable to it pursuant to provisions of part six of this proclamation or their respective establishment laws; coordinates their works, causes their structures and operational programs to be decided being submitted to the pertinent regional government through examining same;

3/ Implements the specific powers and duties as are provided for it in this proclamation and other laws;

CamScanner

4/ የሥራ ክንውኑን በተመለከተ ወቅታዊ ሪፖርቶችን እያዘጋጀ ለርዕሰ መስተዳድሩ እና ለምክር ቤቱ ያቀርባል፡፡

## 20. የኃላፊዎች ተጠሪነት እና ተግባር

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 18 የተገለፁት ተቋማት ኃላፊዎች፡-

1/ ተጠሪነታቸው ለርዕሰ መስተዳድሩ እና ለምክር ቤቱ ይሆናል፤

2/ የሚመሩትን ተቋም ይወክላሉ፤ ሥልጣን እና ተግባራቱን በሥራ ላይ ያውላሉ፤

3/ ለተቋሙ በተፈቀደው በጀት እና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጭ ያደርጋሉ፤

4/ በተቋሙ ውስጥ ውጤታማ የሥራ አመራር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን ይከታተላሉ፣ ያረጋግጣሉ፡፡

## 21. የምክትል ኃላፊዎች ተጠሪነት እና ተግባር

1/ እያንዳንዱ ምክትል ኃላፊ ተጠሪነቱ ለሚመለከተው የተቋሙ ኃላፊ ሆኖ በዚሁ የበላይ ኃላፊ ተለይተው የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፤

2/ የተቋሙ ኃላፊ በማይኖርበት ወይም ሥራውን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜ እና ሁኔታ እርሱን ተክቶ ይሠራል፤

3/ ከሥራው መጠን እና ውስብስብነት የተነሣ ከአንድ በላይ የሆኑ ምክትሎች በሚኖሩበት ጊዜ የተቋሙ ኃላፊ በተለየ የጽሑፍ ውክልና የሰጠው ሰው መኖሩ ካልተረጋገጠ በስተቀር እርሱን ተክቶ ተቋሙን የሚመራው በሹመት ቀደምትነት ያለው ምክትል ኃላፊ ይሆናል፤

4/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (3) መሠረት ሹመቱ በተመሳሳይ ቀን የተሰጠ ከሆነ ከተሿሚዎች መካከል ሴት ካለች ቅድሚያ ለሴት ይሰጣል፤



4/ Submit periodic reports to the Head of government and the Council in respect of the performance of its duties.

## 20. Accountability and Duty of the Heads

Heads of institutions specified in Article 18 of this Proclamation shall:

1/ Be accountable to the Head of Government and the council;

2/ Represent the Bureau under thier leadership and implement thier powers and duties;

3/ Effect expenditures in accordance with the work program and budget approved for the institution;

4/ Put in place effective management systems in the Bureau are implemented and follow up its observance thereof.

## 21. Accountability and Duty of the Deputy Heads of Bureau

1/ Each Deputy Head of institution shall, being accountable to Head of the institution concerned, carry out such duties as are specifically assigned to him by this Head;

2/ He shall replace and act on behalf of the head of institution in his absence and inability to carry out his tasks;

3/ When there is more than one Deputy in an institution due to the requirement of the amount and complexity of work, Deputy Head of the institution having seniority in appointment, shall so lead the institution replacing him, provided that no other delegations have been conferred before in writing on exceptional ground;

4/ If the appointment is made on the same date in accordance with Sub-article (3) of this Article, if there is a woman among the appointees, priority shall be given to the woman;

CamScanner

5/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (3) እና (4) በተገለፀው መሠረት መለየት ካልተቻለ በአጠቃላይ የበለጠ የሥራ ልምድ ያለው የሚመራ ይሆናል፡፡

## 22. ስለ አማካሪዎች እና ሌሎች ባለሙያዎች

1/ የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር በሕገ መንግሥቱ የተሰጠውን ኃላፊነት በብቃት እንዲወጣ ለማድረግ ይቻል ዘንድ በተለያዩ የኃላፊነት ደረጃዎች የሚሾሙ አማካሪዎች ይኖሩታል፤

2/ የማክሮ ኢኮኖሚ ጉዳዮችን በመከታተል እና በመተንተን ለርዕሰ መስተዳድሩ ሳይንሳዊ እና ተተግባሪ የሆኑ ሐሳቦችን በማደራጀት የሚያቀርብ የማክሮ ኢኮኖሚ ቡድን ይቋቋማል፤

3/ በርዕሰ መስተዳድሩ ሲታመንበት የክልሉን የተለያዩ አስፈፃሚ አካላት የዕለት ከዕለት የሥራ እንቅስቃሴ የሚደግፉ አማካሪዎች በተለያዩ የኃላፊነት ደረጃዎች ሊሾሙ ይችላሉ፤

4/ የማክሮ ኢኮኖሚ ቡደን፣ የአማካሪዎች እና ሌሎች የርዕሰ ጉዳይ ባለሙያዎች አሠራር፣ ተግባር እና ኃላፊነት በርዕሰ መስተዳድሩ በሚወጣ መመሪያ የሚወሰን ይሆናል፡፡

## ክፍል አምስት

## ስለ ተቋማት ዝርዝር ሥልጣን እና ተግባር

## 23. የግብርና ቢሮ

በሌሎች ሕጎች አስቀድሞ የተደነገገው ወይም ወደ ፊት የሚደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ ግብርና ቢሮ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ዝርዝር ሥልጣን እና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1/ የግብርና ልማትን እና ተወዳዳሪነትን በቀጣይነት የሚያረጋግጡ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችን፣ ፕሮግራሞችን እና ሕጎችን ይቀርፃል፤ ሲፀድቁም ተግባራዊ ያደርጋል፤



5/ If it is not possible to determine the position as described in Sub-articles (3) and (4) of this Article, the person with total most work experience shall lead in such.

## 22. Advisors and Other Professionals

1/ The Head of Government shall have advisors appointed at various levels of responsibility to enable him to effectively discharge the responsibilities assigned to him by the Constitution;

2/ A macro-economic group shall be established to monitor and analyze macro-economic issues and provide scientific and practical advice to head of government;

3/ When the head of government deems it necessary, advisors may be appointed at various levels of responsibility to support the day-to-day activities of various executive bodies of the region;

4/ The procedures, functions and responsibilities of macro-economic team, advisors and other subject matter experts shall be determined by a directive to be issued by the Head of Government.

## PART FIVE

## SPECIFIC POWERS AND DUTIES OF INSTITUTIONS

## 23. Bureau of the Agriculture

Without prejudice to the existing or subsequent provision of other laws, the Regional Bureau of Agriculture shall, pursuant to this proclamation, have the following specific powers and duties:

1/ Formulate policies, strategies, programs and laws that ensure continuous development and competitiveness of agriculture; and implements them once approved;

CamScanner

2/ በክልሉ ውስጥ ፈጣን እና ቀጣይነት ያለው የግብርና ልማት እና መዋቅራዊ ለውጥን ለማረጋገጥ የረዥም፣ የመካከለኛ እና የአጭር ጊዜ መዳረሻ ግቦችን መሠረት ያደረገ የዘርፍ ዕቅድ ያዘጋጃል፤ ውጤታማ በሆነ መልኩ እንዲፈፀም ያደርጋል፤

3/ የተፈጥሮ ሀብቶችን ለማልማት የተፈጥሮ ሀብት መመናመን መንስኤዎችን በጥናት ይለያል፤ ሥነ አካላዊ እና ሥነ-ሕይወታዊ የአፈር እና ውኃ ጥበቃ ሥራዎች በስፋት እና በጥራት እንዲከናወኑ ያደርጋል፤ ውጤታማነቱን ይከታተላል፤

4/ የአፈር ለምነትን፣ ደኅንነትን እና ጤንነትን ለመጠበቅ እና ለማሻሻል የሚረዱ የአፈር ለምነት ማሻሻያ ሥራዎች እንዲከናወኑ ተገቢውን ሥርዓት ይዘረጋል፤ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

5/ ግብርና የተፈጥሮ ሀብት መሠረቱን ሳያራቁት እና ከተፈጥሮ ሀብቱ ጋር ሳይጠፋፋ እንዲዘልቅ የተፈጥሮ ሀብት ልማትን ለማሻሻል የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፤ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

6/ የግብርና ልማት በገበያ እንዲመራ እና ዘመናዊ አመራረት እንዲጎለብት ገበያ-መር የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት እና የቴክኒክ ድጋፎችን ይሰጣል፤

7/ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን ለግብርና ምርቶች የገበያ ትስስር እንዲፈጠር በማድረግ አርሶ አደሩ በጥረቱ ልክ ተጠቃሚ የሚሆንበትን ሥርዓት ያመቻቻል፤ በገበያ የሚቀርብ ማናቸውም የግብርና ምርት የጥራት ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፤ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤

8/ የግብርና አመራረት ዘይቤ ጤናማነቱ የተጠበቀ እንዲሆን በማድረግ ደኅንነታቸው የተጠበቀ እና በንጥረ ነገር ይዘታቸው የበለፀጉ ምርቶች እንዲመረቱ ሥርዓት ይዘረጋል፤ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

9/ የግብርና ምርምር ሥራዎች የዘርፉን ቁልፍ የምርታማነት ችግሮችን በሚፈታ እና የአርሶ አደሩን ፍላጎት በሚያሟላ አግባብ መሠራታቸውን ያረጋግጣል፤ በበላይነት ያስተባብራል፤



2/ Prepares a sector plan based on long, medium and short-term access goals and and cause its effective implementation to ensure rapid and sustainable agricultural development and structural change in the region;

3/ Identifies causes of natural resource depletion through research to develop natural resources; causes physical and biological soil and water conservation works to be carried out extensively and qualitatively; and monitors their effectiveness;

4/ Establishes an appropriate system to carry out soil fertility improvement works helping to protect and improve soil fertility, safety, and health; and monitors their implementation;

5/ Develops a system to improve natural resource development so that agriculture can continue to grow without depleting its natural resource base and extincting with natural resources; and monitor its implementation;

6/ Provides market-oriented agricultural extension services and technical support so that agricultural development is market-driven and modern production is promoted;

7/ Facilitates a system in which farmers benefit from their efforts through creating market linkages for agricultural products being with concerned bodies; devises a system to ensure any agricultural product offered in the market meets its quality standards; and monitors its implementation;

8/ Establishes a system to make agricultural production methods to be healthy and produce safe and nutritious products; and monitors their implementation;

9/ Ensures and coordinate agricultural research activities to be done in a way that addresses key productivity problems in the sector and meet the needs of farmers;

CamScanner

10/ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን ለአርሶ አደሩ እና በግብርና ሥራ መዋዕለ ንዋያቸውን ማፍሰስ ለሚፈልጉ ባለ ሀብቶች ተደራሽ የሆነ የግብርና እና የገጠር ፋይናንስ አቅርቦት ሥርዓት እንዲዘረጋ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤ ተገቢውን መረጃ እና ሙያዊ ድጋፍ ይሰጣል፤

11/ የሰብል ምርት እና ምርታማነትን ለማሳደግ እና የምርት ተወዳዳሪነትን ለማረጋገጥ የግብርና ኤክስቴንሽን ምክር አገልግሎት፣ የቴክኖሎጂ አቅርቦት እና ዘመናዊ የአመራረት ስልት እንዲስፋፋ ያደርጋል፤ ውጤታማነታቸውን ያረጋግጣል፤

12/ ለሰብል እና የተፈጥሮ ሀብት ልማት አስፈላጊ የሆኑ የግብርና ግብዓቶች ጥራታቸው ተጠብቆ በወቅቱ ለተጠቃሚዎች እንዲቀርቡ የፍላጎት፣ የአቅርቦት፣ የስርጭት እና የግብይት ሥርዓት ይዘረጋል፤ አፈጻፀሙን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

13/ የእፅዋት በሽታን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፤ ፀረ ሰብል ተባዮችን፣ በሽታዎችን እና አረሞችን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የማቴርያል እና የሙያ ድጋፍ ያደርጋል፤ በዘርፉ የሚደረጉ የጥናት እና ምርምር ሥራዎችን ይመራል፣ ያስተባብራል፤

14/ የእፅዋት ጤና አገልግሎትን ጥራት እና ተደራሽነት ለማሻሻል የሚያስችል ሥርዓት እና መሠረተ ልማት ይዘረጋል፤ እንደ አስፈላጊነቱ ላቦራቶሪዎች እና ክሊኒኮች እንዲገነቡ ያደርጋል፣ አቅማቸውን ይገነባል፣ ውጤታማነታቸውን ያረጋግጣል፤

15/ የግብርና ቴክኖሎጂዎች እና ግብዓቶች ምዝገባ እና ቁጥጥር፣ የምርት ጥራት፣ የዕፅዋት ጤና እና ደኅንነት ቁጥጥር ሥርዓት ይዘረጋል፤ ወደ ክልሉ በሚገቡትም ሆነ ከክልሉ በሚወጡት የዕፅዋት ዝርያዎች ላይ ቁጥጥር እንዲደረግ በበላይነት ያስተባብራል፤

10/ In collaboration with relevant body, it facilitates the establishment of an accessible agricultural and rural finance system for farmers and investors who wish to invest in agriculture, and provide appropriate information and professional support;

11/ Makes for the promotion of agricultural extension advisory service, technology provision and modern production methods to increase crop production and productivity and ensure product competitiveness, and ensures their effectiveness;

12/ Establishes a system of demand, supply, distribution and marketing so that agricultural inputs essential for crop and natural resource development to be supplied for users being their quality is maintained; follows up and controls the implementation thereof;

13/ Establishes a system to prevent and control plant diseases; provides material and professional support for the prevention and control of crop pests, diseases, and weeds; directs and coordinates research and development activities takenplace in the field;

14/ Establishes a system and infrastructure to improve the quality and accessibility of plant health services; makes for the establishment of laboratories and clinics as necessary, builds their capacity, and ensures their effectiveness;

15/ Establishes a system for the registration and control of agricultural technologies and inputs, product quality, plant health and safety; coordinates the control of plant species entering in as well as leaving from the region;

CamScanner

16/ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን የከተማ ግብርናን ውጤታማ ለማድረግ ይሠራል፤ የአተገባበር ሥርዓት ይዘረጋል፣ ውጤታማ መሆኑንም ያረጋግጣል፤

17/ የሰብል፣ የአትክልት እና ፍራፍሬ ልማት ምርት እና ምርታማነት እንዲያድግ የሚያደርጉ የመስኖ ልማት ሥራዎችን በማሳደግ ግብርናን በሂደት ከዝናብ ጥገኝነት የሚያላቅቅ ሥራ ያከናውናል፤

18/ ዓለም የደረሰበትን ዘመናዊ የግብርና ደረጃ ማማተር፣ መረዳት፣ መቅዳት እና መተግበር የሚችል ተወዳዳሪ የግብርና ልማት ኃይል እንዲፈጠር እና እንዲገነባ ተገቢውን ትኩረት ሰጥቶ ይሠራል፤

19 የግብርና ኮሜርሻላይዜሽን ክላስተር እርሻ ቅኝቱን በማሻሻል የኢንዱስትሪ ሥነ-ምግባር ለበስ ተፅዕኖ ፈጣሪ አርሶ አደሮች እንዲፈጠሩ እና ቁጥራቸው እንዲበራከት ይሠራል፣ ውጤታማነቱን ይከታተላል፤

20/ አንፃራዊ ጠቀሜታን በማስላት ስትራቴጂ የሚመራ ግብርናን ተግባራዊ በማድረግ ወሳኝ ሚና በሚጫወቱ ዘርፎች ልህቀት ለማምጣት የሚያስችል አስተማማኝ ሥርዓት ይዘረጋል፤ ውጤታማነቱን ይከታተላል፤

21/ የግብርና ሜካናይዜሽን አጠቃቀምን፣ የምርት ክምችት መሠረተ ልማት አቅርቦትን፣ እሴት በመጨመር ላይ የተመሠረተ የሥራ ዕድል ፈጠራን በማሳደግ ግብርናን ተወዳዳሪ የሚያደርግ መሠረታዊ የአሠራር፣ የምርምር እና ዕድገት ሥርዓቶችን ይዘረጋል፣ ይከታተላል፤

22/ የግብርና ፕሮጀክቶች እና ፕሮግራሞች አላስፈላጊ ድግግሞሽ ከመፍጠር ወጥተው ያመጡት ውጤት እንዲመዘን እና ከዋናው የግብርና ሥርዓት ጋር ተዋሕደው በዘላቂነት እንዲተገበሩ አስፈላጊውን ሥርዓት ይዘረጋል፣ ክትትል ያደርጋል፤

16/ Works with relevant bodies to make urban agriculture effective; establishes an implementation system, and ensures its effectiveness;

17/ Works to gradually remove agriculture from rain-dependency by increasing irrigation development activities increasing production and productivity of crops, vegetables, and fruits development production;

18/ Works to create and build a competitive agricultural development force that can seek, understand, copy, and implement the modern agricultural standards that the world has reached;

19 Works to create and increase the number of influential farmers with industrial ethics by improving the culture of agricultural commercialization cluster farming; and monitors its effectiveness;

20/ Establishes reliable system to achieve excellence in sectors playing critical role through implementing a strategy guided by comparative advantage; monitors its effectiveness;

21/ Establishes and monitors basic operational, research and development systems that will make agriculture competitive through promoting the use of agricultural mechanization, supply of production storage infrastructure, and creation of employment opportunities based on value addition;

22/ Establishes and monitors the necessary systems to ensure that agricultural projects and programs are implemented in a sustainable manner, without creating unnecessary duplication;

CamScanner

4/ የሥራ ክንውኑን በተመለከተ ወቅታዊ ሪፖርቶችን እያዘጋጀ ለርዕሰ መስተዳድሩ እና ለምክር ቤቱ ያቀርባል።

## 20. የኃላፊዎች ተጠሪነት እና ተግባር

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 18 የተገለፁት ተቋማት ኃላፊዎች፡-

1/ ተጠሪነታቸው ለርዕሰ መስተዳድሩ እና ለምክር ቤቱ ይሆናል፤

2/ የሚመሩትን ተቋም ይወክላሉ፣ ሥልጣን እና ተግባራቱን በሥራ ላይ ያውላሉ፤

3/ ለተቋሙ በተፈቀደው በጀት እና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጭ ያደርጋሉ፤

4/ በተቋሙ ውስጥ ውጤታማ የሥራ አመራር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን ይከታተላሉ፣ ያረጋግጣሉ።

## 21. የምክትል ኃላፊዎች ተጠሪነት እና ተግባር

1/ እያንዳንዱ ምክትል ኃላፊ ተጠሪነቱ ለሚመለከተው የተቋሙ ኃላፊ ሆኖ በዚሁ የበላይ ኃላፊ ተለይተው የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፤

2/ የተቋሙ ኃላፊ በማይኖርበት ወይም ሥራውን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜ እና ሁኔታ እርሱን ተክቶ ይሠራል፤

3/ ከሥራው መጠን እና ውስብስብነት የተነሣ ከአንድ በላይ የሆኑ ምክትሎች በሚኖሩበት ጊዜ የተቋሙ ኃላፊ በተለየ የጽሑፍ ውክልና የሰጠው ሰው መኖሩ ካልተረጋገጠ በስተቀር እርሱን ተክቶ ተቋሙን የሚመራው በሹመት ቀደምትነት ያለው ምክትል ኃላፊ ይሆናል፤

4/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (3) መሠረት ሹመቱ በተመሳሳይ ቀን የተሰጠ ከሆነ ከተሿሚዎች መካከል ሴት ካለች ቅድሚያ ለሴት ይሰጣል፤



4/ Submit periodic reports to the Head of government and the Council in respect of the performance of its duties.

## 20. Accountability and Duty of the Heads

Heads of institutions specified in Article 18 of this Proclamation shall:

1/ Be accountable to the Head of Government and the council;

2/ Represent the Bureau under thier leadership and implement thier powers and duties;

3/ Effect expenditures in accordance with the work program and budget approved for the institution;

4/ Put in place effective management systems in the Bureau are implemented and follow up its observance thereof.

## 21. Accountability and Duty of the Deputy Heads of Bureau

1/ Each Deputy Head of institution shall, being accountable to Head of the institution concerned, carry out such duties as are specifically assigned to him by this Head;

2/ He shall replace and act on behalf of the head of institution in his absence and inability to carry out his tasks;

3/ When there is more than one Deputy in an institution due to the requirement of the amount and complexity of work, Deputy Head of the institution having seniority in appointment, shall so lead the institution replacing him, provided that no other delegations have been conferred before in writing on exceptional ground;

4/ If the appointment is made on the same date in accordance with Sub-article (3) of this Article, if there is a woman among the appointees, priority shall be given to the woman;

5/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (3) እና (4) በተገለፀው መሠረት መለየት ካልተቻለ በአጠቃላይ የበለጠ የሥራ ልምድ ያለው የሚመራ ይሆናል፡፡

## 22. ስለ አማካሪዎች እና ሌሎች ባለሙያዎች

1/ የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር በሕገ መንግሥቱ የተሰጠውን ኃላፊነት በብቃት እንዲወጣ ለማድረግ ይቻል ዘንድ በተለያዩ የኃላፊነት ደረጃዎች የሚሾሙ አማካሪዎች ይኖሩታል፤

2/ የማክሮ ኢኮኖሚ ጉዳዮችን በመከታተል እና በመተንተን ለርዕሰ መስተዳድሩ ሳይንሳዊ እና ተተግባሪ የሆኑ ሐሳቦችን በማደራጀት የሚያቀርብ የማክሮ ኢኮኖሚ ቡድን ይቋቋማል፤

3/ በርዕሰ መስተዳድሩ ሲታመንበት የክልሉን የተለያዩ አስፈፃሚ አካላት የዕለት ከዕለት የሥራ እንቅስቃሴ የሚደግፉ አማካሪዎች በተለያዩ የኃላፊነት ደረጃዎች ሊሾሙ ይችላሉ፤

4/ የማክሮ ኢኮኖሚ ቡድን፣ የአማካሪዎች እና ሌሎች የርዕሰ ጉዳይ ባለሙያዎች አሠራር፣ ተግባር እና ኃላፊነት በርዕሰ መስተዳድሩ በሚወጣ መመሪያ የሚወሰን ይሆናል፡፡

## ክፍል አምስት

## ስለ ተቋማት ዝርዝር ሥልጣን እና ተግባር

## 23. የግብርና ቢሮ

በሌሎች ሕጎች አስቀድሞ የተደነገገው ወይም ወደ ፊት የሚደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ ግብርና ቢሮ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ዝርዝር ሥልጣን እና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1/ የግብርና ልማትን እና ተወዳዳሪነትን በቀጣይነት የሚያረጋግጡ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችን፣ ፕሮግራሞችን እና ሕጎችን ይቀርፃል፤ ሲፀድቁም ተግባራዊ ያደርጋል፤

5/ If it is not possible to determine the position as described in Sub-articles (3) and (4) of this Article, the person with total most work experience shall lead in such.

## 22. Advisors and Other Professionals

1/ The Head of Government shall have advisors appointed at various levels of responsibility to enable him to effectively discharge the responsibilities assigned to him by the Constitution;

2/ A macro-economic group shall be established to monitor and analyze macro-economic issues and provide scientific and practical advice to head of government;

3/ When the head of government deems it necessary, advisors may be appointed at various levels of responsibility to support the day-to-day activities of various executive bodies of the region;

4/ The procedures, functions and responsibilities of macro-economic team, advisors and other subject matter experts shall be determined by a directive to be issued by the Head of Government.

## PART FIVE

## SPECIFIC POWERS AND DUTIES OF INSTITUTIONS

## 23. Bureau of the Agriculture

Without prejudice to the existing or subsequent provision of other laws, the Regional Bureau of Agriculture shall, pursuant to this proclamation, have the following specific powers and duties:

1/ Formulate policies, strategies, programs and laws that ensure continuous development and competitiveness of agriculture; and implements them once approved;

CamScanner

2/ በክልሉ ውስጥ ፈጣን እና ቀጣይነት ያለው የግብርና ልማት እና መዋቅራዊ ለውጥን ለማረጋገጥ የረዥም፣ የመካከለኛ እና የአጭር ጊዜ መዳረሻ ግቦችን መሠረት ያደረገ የዘርፍ ዕቅድ ያዘጋጃል፤ ውጤታማ በሆነ መልኩ እንዲፈፀም ያደርጋል፤

3/ የተፈጥሮ ሀብቶችን ለማልማት የተፈጥሮ ሀብት መመናመን መንስኤዎችን በጥናት ይለያል፤ ሥነ አካላዊ እና ሥነ-ሕይወታዊ የአፈር እና ውኃ ጥበቃ ሥራዎች በስፋት እና በጥራት እንዲከናወኑ ያደርጋል፤ ውጤታማነቱን ይከታተላል፤

4/ የአፈር ለምነትን፣ ደኅንነትን እና ጤንነትን ለመጠበቅ እና ለማሻሻል የሚረዱ የአፈር ለምነት ማሻሻያ ሥራዎች እንዲከናወኑ ተገቢውን ሥርዓት ይዘረጋል፤ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

5/ ግብርና የተፈጥሮ ሀብት መሠረቱን ሳያራቁት እና ከተፈጥሮ ሀብቱ ጋር ሳይጣፋፉ እንዲዘልቅ የተፈጥሮ ሀብት ልማትን ለማሻሻል የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፤ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

6/ የግብርና ልማት በገበያ እንዲመራ እና ዘመናዊ አመራረት እንዲጎለብት ገበያ-መር የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት እና የቴክኒክ ድጋፎችን ይሰጣል፤

7/ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን ለግብርና ምርቶች የገበያ ትስስር እንዲፈጠር በማድረግ አርሶ አደሩ በጥረቱ ልክ ተጠቃሚ የሚሆንበትን ሥርዓት ያመቻቻል፤ በገበያ የሚቀርብ ማናቸውም የግብርና ምርት የጥራት ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፤ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤

8/ የግብርና አመራረት ዘይቤ ጤናማነቱ የተጠበቀ እንዲሆን በማድረግ ደኅንነታቸው የተጠበቀ እና በንጥረ ነገር ይዘታቸው የበለፀጉ ምርቶች እንዲመረቱ ሥርዓት ይዘረጋል፤ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

9/ የግብርና ምርምር ሥራዎች የዘርፉን ቁልፍ የምርታማነት ችግሮችን በሚፈታ እና የአርሶ አደሩን ፍላጎት በሚያሟላ አግባብ መሠራታቸውን ያረጋግጣል፤ በበላይነት ያስተባብራል፤

2/ Prepares a sector plan based on long, medium and short-term access goals and and cause its effective implementation to ensure rapid and sustainable agricultural development and structural change in the region;

3/ Identifies causes of natural resource depletion through research to develop natural resources; causes physical and biological soil and water conservation works to be carried out extensively and qualitatively; and monitors their effectiveness;

4/ Establishes an appropriate system to carry out soil fertility improvement works helping to protect and improve soil fertility, safety, and health; and monitors their implementation;

5/ Develops a system to improve natural resource development so that agriculture can continue to grow without depleting its natural resource base and extincting with natural resources; and monitor its implementation;

6/ Provides market-oriented agricultural extension services and technical support so that agricultural development is market-driven and modern production is promoted;

7/ Facilitates a system in which farmers benefit from their efforts through creating market linkages for agricultural products being with concerned bodies; devises a system to ensure any agricultural product offered in the market meets its quality standards; and monitors its implementation;

8/ Establishes a system to make agricultural production methods to be healthy and produce safe and nutritious products; and monitors their implementation;

9/ Ensures and coordinate agricultural research activities to be done in a way that addresses key productivity problems in the sector and meet the needs of farmers;

16/ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን የከተማ ግብርናን ውጤታማ ለማድረግ ይሠራል፤ የአተገባበር ሥርዓት ይዘረጋል፣ ውጤታማ መሆኑንም ያረጋግጣል፤

17/ የሰብል፣ የአትክልት እና ፍራፍሬ ልማት ምርት እና ምርታማነት እንዲያድግ የሚያደርጉ የመስኖ ልማት ሥራዎችን በማሳደግ ግብርናን በሂደት ከዝናብ ጥገኝነት የሚያላቅቅ ሥራ ያከናውናል፤

18/ ዓለም የደረሰበትን ዘመናዊ የግብርና ደረጃ ማማተር፣ መረዳት፣ መቅዳት እና መተግበር የሚችል ተወዳዳሪ የግብርና ልማት ኃይል እንዲፈጠር እና እንዲገነባ ተገቢውን ትኩረት ሰጥቶ ይሠራል፤

19 የግብርና ኮሜርሻላይዜሽን ክላስተር እርሻ ቅኝቱን በማሻሻል የኢንዱስትሪ ሥነ-ምግባር ለበስ ተፅዕኖ ፈጣሪ አርሶ አደሮች እንዲፈጠሩ እና ቁጥራቸው እንዲበራከት ይሠራል፣ ውጤታማነቱን ይከታተላል፤

20/ አንፃራዊ ጠቀሜታን በማስላት ስትራቴጂ የሚመራ ግብርናን ተግባራዊ በማድረግ ወሳኝ ሚና በሚጫወቱ ዘርፎች ልህቀት ለማምጣት የሚያስችል አስተማማኝ ሥርዓት ይዘረጋል፤ ውጤታማነቱን ይከታተላል፤

21/ የግብርና ሜካናይዜሽን አጠቃቀምን፣ የምርት ክምችት መሠረተ ልማት አቅርቦትን፣ እሴት በመጨመር ላይ የተመሠረተ የሥራ ዕድል ፈጠራን በማሳደግ ግብርናን ተወዳዳሪ የሚያደርግ መሠረታዊ የአሠራር፣ የምርምር እና ዕድገት ሥርዓቶችን ይዘረጋል፣ ይከታተላል፤

22/ የግብርና ፕሮጀክቶች እና ፕሮግራሞች አላስፈላጊ ድግግሞሽ ከመፍጠር ወጥተው ያመጡት ውጤት እንዲመዘን እና ከዋናው የግብርና ሥርዓት ጋር ተዋሕደው በዘላቂነት እንዲተገበሩ አስፈላጊውን ሥርዓት ይዘረጋል፣ ክትትል ያደርጋል፤

16/ Works with relevant bodies to make urban agriculture effective; establishes an implementation system, and ensures its effectiveness;

17/ Works to gradually remove agriculture from rain-dependency by increasing irrigation development activities increasing production and productivity of crops, vegetables, and fruits development production;

18/ Works to create and build a competitive agricultural development force that can seek, understand, copy, and implement the modern agricultural standards that the world has reached;

19 Works to create and increase the number of influential farmers with industrial ethics by improving the culture of agricultural commercialization cluster farming; and monitors its effectiveness;

20/ Establishes reliable system to achieve excellence in sectors playing critical role through implementing a strategy guided by comparative advantage; monitors its effectiveness;

21/ Establishes and monitors basic operational, research and development systems that will make agriculture competitive through promoting the use of agricultural mechanization, supply of production storage infrastructure, and creation of employment opportunities based on value addition;

22/ Establishes and monitors the necessary systems to ensure that agricultural projects and programs are implemented in a sustainable manner, without creating unnecessary duplication;

CamScanner

23/ ሜካናይዜሽን፣ ዝርያ-ዘር፣ ማዳበሪያ፣ ውኃ፣ ሥነ ምሕዳር፣ እሴት እና ስፔሻላይዜሽን መር የግብርና ልማት አብዮቶችን በማቀጣጠል አርሶ አደሩ ከድህነት እንዲላቀቅ በትኩረት ይሠራል፤

24/ የግብርና ግብዓቶች አጠቃቀም በምክረ-ሐሳቡ መሠረት እንዲሆን እና ከተበጣጠሱ ማሳዎች ልማት ጎን በጎን የኮሜርሻል አሠራርን አጣምሮ በመተግበር ምርት እና ምርታማነት እንዲያድግ ይሠራል፤

25/ የአየር ንብረት ለውጥ፣ ተባይ፣ በሽታ እና አረም በግብርናው ላይ የሚያደርሱትን ስጋት ለመቀነስ እና ለመከላከል የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ፣ በቴክኖሎጂ የታገዘ ቅኝት እና ክትትል ብሎም ውጤታማ የሆነ የመከላከያ እና የመቆጣጠሪያ አቅም እንዲገነባ ያደርጋል፤

26/ በምርምር የተገኙ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ያቀርባል፣ ያላምዳል፣ መሥራች ዝርያዎችን ያመርታል፣ እንዲመረቱ ያደርጋል፣ ያሰራጫል፤

27/ ለምግብ፣ ለአገር ውስጥ እና ለውጭ ገበያዎች እንዲሁም ለአግሮ ፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪዎች የሚቀርቡ የግብርና ምርቶችን በበቂ መጠን እና የጥራት ደረጃ እንዲመረቱ ያደርጋል፤ የምርት ብክነትን ለመቀነስ የሚረዱ አሠራሮች እና ቴክኖሎጅዎችን ጥቅም ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፤

28/ የግብርና ልማቱን ለማፋጠን፣ የኤክስቴንሽን ሥርዓቱን ለማዘመን እና ለማስፋፋት የግብርና አሠራሮችን እና ቴክኖሎጂዎችን ለማላመድ የሚረዱ የማሰልጠኛ ተቋማትን እና ማዕከላትን ያቋቁማል፣ ይመራል፤

29/ በክልሉ የሰብል እና የገጠር ቴክኖሎጂ ብዜት ማዕከላትን ያስፋፋል፣ ያስተዳድራል፣ አዳዲሶች እንዲቋቋሙ ያደርጋል፤

30/ ማንኛውንም የደን ልማት ሥራ ያከናውናል፣ ችግኝ ጣቢያዎችን ያስፋፋል፣ ሁሉን አቀፍ ጠቀሜታ ያላቸው የደን ችግኞችን ያለማል፤

23/ Works diligently to lift farmers out of poverty by igniting agricultural development revolutions led by mechanization, species-seed, fertilizers, water, ecology, value and specialization;

24/ Works to increase production and productivity through making use of agricultural inputs is based on the recommendation and implementing commercial practices in combination besides the development of fragmented farms;

25/ Causes for capacity building of early warning, technology-assisted surveillance and monitoring as well as effective prevention and control to reduce and prevent threats of climate change, pests, diseases and weeds bring on agriculture;

26/ Provides and adapts new technologies obtained through research; produces and causes for production of pioneer species and disseminates them;

27/ Makes agricultural products supplied to food, domestic and foreign markets as well as agro-processing industries to be produced in sufficient quantity and quality; causes practices and technologies helping to reduce product waste to be used;

28/ Establishes and manages training institutions and centers helping to enhance the agricultural development, to modernize and promote the extension system;

29/ Promotes and manages crop and rural technology duplication centers in the region, and causes for establishment of new ones;

30/ Carries out any forest development work, expands seedling stations, and develops forest seedlings of universal importance;

CamScanner

31/ በክልሉ የምግብ ዋስትና የሚረጋገጥበትን ሥርዓት ይዘረጋል፤ ተግባራዊ ያደርጋል፤ በገጠር የልማታዊ ሴፍትኔት እና ሌሎች የምግብ ዋስትና ፕሮግራሞችን እና ሥራዎችን ያስተባብራል፤ ይደግፋል፤ ይከታተላል፤

32/ የክልሉን የምግብ ሥርዓት ፍኖተ ካርታ፤ የምግብ እና ሥርዓተ ምግብ ፖሊሲ እና ስትራቴጅ ያመነጫል፤ ተግባራዊ ያደርጋል፤ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፣ ውጤታማነቱን ይከታተላል፤

33/ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን የምግብ እና ሥርዓተ ምግብ ሥራዎችን በትኩረት በመምራት በሰው ሕይወት እና ጤና እንዲሁም በምርታማነት ላይ አሉታዊ ጫና እያሳደሩ ያሉት የመቀንጨር፣ የመቀጨጭ እና ከሥርዓተ ምግብ መዛባት ጋር የተያያዙ ችግሮች እንዲቀረፉ ይሠራል፤

34/ ቴክኖሎጂ መር ኮመርሻል ግብርና እና ማኅበረሰብ አቀፍ አሳታፊ የተቀናጀ የገጠር ትራንስፎርሜሽን ንቅናቄ በመከተል ድህነትን በሁለት አቅጣጫ ለመቅደም እና የአነስተኛ ባለ ይዞታዎችን የግብርና ምርት ለማሳደግ ይሠራል፤

35/ በአነስተኛ ግብርና የተሠማሩ ዜጎች በራስ ጥረት እና በትብብር የተሻለ ገቢ ከማግኘት ባለፈ ለተሻለ ሕይወት እንዲተጉ ያበረታታል፣ ይደግፋል፤

36/ በክልሉ የመስኖ አውታሮችን ጥናት፣ ዲዛይን እና ግንባታ የሚመለከቱ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችን፣ ሕጎችን ያመነጫል፤ ለአፈጻፀሙ ከክልላዊ የልማት አቅጣጫዎች ጋር የተጣጣመ ዝርዝር መርሃ ግብር ያዘጋጃል፣ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

37/ በክልሉ ውስጥ በተለይም ቆላማ እና ከፊል ቆላማ በሆኑ አካባቢዎች የመስኖ አውታሮችን ግንባታ ያከናውናል፣ እንዲከናወኑ ያደርጋል፤ የግንባታ ሥራዎች ዘላቂ ጥቅም እንዲሰጡ ተገቢውን ሥራ ይሠራል፤

31/ Develops and implements a system to ensure food security in the region, coordinates, supports and monitors the development of safety-net and other food security programs and activities in rural areas,

32/ Initiates and implements the regional food system roadmap, food and nutrition policy and strategy, develops and implements system of operations in collaboration with the relevant body, and monitors its effectiveness;

33/ Works with relevant body to address stunting, malnutrition and problems related to malnutrition that are having negative impact on human life and health as well as productivity by leading focusing on food and nutrition activities;

34/ Works to eradicate poverty in two directions and increase agricultural production of smallholders by following technology-led commercial agriculture and community-wide participatory integrated rural transformation movement;

35/ Encourages and supports citizens engaged in small-scale agriculture to strive for better life through their own efforts and cooperation, in addition to earning better income;

36/ Initiates policies, strategies, and laws related to the study, design, and construction of irrigation networks in the region; prepares detailed program for its implementation in line with regional development directions, and implements upon approval;

37/ Performs and causes for performance of construction of irrigation networks in the region, especially in lowland and semi-lowland areas, carries out the appropriate work that construction works to give sustainable benefits;

CamScanner

38/ የመስኖ ውኃ ማሰባሰብ ሥራዎችን ይሠራል፣ የመስኖ ቴክኖሎጅዎች አቅርቦት፣ ስርጭት እና አጠቃቀም እንዲሻሻል ያደርጋል፤ ይከታተላል፤ ይደግፋል፤ የውኃ አጠቃቀም ክህሎትን ለማሳደግ የድጋፍ እና ማበረታቻ ሥርዓት ይዘረጋል፣ ውጤታማነቱን ያረጋግጣል፤

39/ በተቀናጀ የተፋሰስ ልማት በጥናት የተለየውን የክልሉን የውኃ ሀብት ለመስኖ አገልግሎት እንዲውል እና የመስኖ ልማት ሥራዎች እንዲስፋፉ የአነስተኛ፣ የመካከለኛ እና ከፍተኛ የመስኖ አውታሮችን የጥናት እና ዲዛይን ሥራዎች ይሠራል፣ ያሠራል፤ ዲዛይኑ በሚመለከተው አካል ሲፀድቅ ግንባታ ያከናውናል፣ በሌሎችም እንዲከናወን ያደርጋል፤

40/ በክልሉ መንግሥት አማካኝነት የተገነቡ የመስኖ ግድቦችን፣ ቦዮችን እና ሌሎች የመስኖ አውታሮችን ተረክቦ ያስተዳድራል፤ ተጠቃሚዎች እራሳቸውን በሚችሉበት ጊዜ ለእነርሱ አሳልፎ ይሰጣል፤ ከመስኖ ተጠቃሚዎች አቅም በላይ የሆነ ጥገናን ያከናውናል፤ እንዲከናውን ያደርጋል፤

41/ በፌደራሉ መንግሥት ባለቤትነት በክልሉ ውስጥ ለሚገነቡ የመስኖ አውታር ፕሮጀክቶች ድጋፍ እና ክትትል ያደርጋል፣ ሲጠናቀቁ ተረክቦ ያስተዳድራል፤

42/ የክልሉን የመስኖ ልማት ሽፋን ለማሳደግ የመስኖ አውታሮች ግንባታን የሚያቀላጥፍ የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤

43/ በመስኖ አውታሮች የግንባታ ሥራዎች ለሚሳተፉ አጋር አካላት ሙያዊ ድጋፍ ይሰጣል፤ የሚገነቡ የመስኖ አውታሮች ስታንዳርዳቸውን የጠበቁ እንዲሆኑ ተገቢውን ክትትል እና ቁጥጥር ያደርጋል፤

44/ የመስኖ ውኃ ተጠቃሚዎች ማኅበራትን ያደራጃል፣ ያሰለጥናል፣ የመተዳደሪያ ደንብ እንዲያዘጋጁ ይደግፋል፣ ይከታተላል፣ ሕጋዊ ሰውነት እንዲያገኙ ከሚመለከተው አካል ጋር ይሠራል፤

38/ Carries out irrigation water collection works, causes for the improvement of supply, distribution and use of irrigation technologies, monitors and supports them, establishes support and incentive systems to enhance water use skills, and ensures its effectiveness;

39/ Conducts and causes for conduction of research and design works for small, medium and large scale irrigation networks in order to utilize water resources of the region, identified by research in integrated basin development, for irrigation and to expand irrigation development works; carries out construction works when the design is approved by the relevant body, and causes others to do so;

40/ Takes over and manages irrigation dams, canals and other irrigation networks constructed by the regional government; hands them over to users when they are able to do so; carries out maintenance beyond capacity of users; causes it to be done;

41/ Supports and supervises irrigation network projects under ownership of the federal government in the region; manages taking over them upon completion;

42/ Establishes an operational system facilitating the construction of irrigation networks in order to increase irrigation development coverage of the region, and monitors its implementation;

43/ Provides professional support to partner parties involved in the construction of irrigation networks; makes an appropriate supervision and control to ensure irrigation networks being constructed meet their standards;

44/ Organizes and trains irrigation water users associations, supports and monitors so that they prepare bylaws, and works with relevant body hence they obtain legal personality;

45/ የተገነቡ የመስኖ ተቋማት ተፈላጊውን አገልግሎት በዘላቂነት እንዲሰጡ የመለስተኛ እና ከፍተኛ ጥገና ሥራዎችን ያካሂዳል፣ እንዲካሄዱ ያደርጋል፤

46/ ከመስኖ አውታሮች ግንባታ ሥራዎች ጋር የተያያዙ ቴክኖሎጅዎች ጥራታቸውን የጠበቁ እና ስታንዳርድ ያሟሉ እንዲሆኑ ያደርጋል፤

47/ በከፍተኛ መስኖ ፕሮጀክቶች ግንባታ ላይ ሥራውን ለማሳለጥ እንደ አስፈላጊነቱ የፕሮጀክት ጽሕፈት ቤት ይከፍታል፤ ተግባራዊ እንዲሆን ከሚመለከተው አካል ጋር በትብብር ይሠራል፤

48/ በመስኖ ተቋማት ግንባታ ፕሮጀክቶች የአካባቢው ሕዝብ ተሳታፊ እና ተጠቃሚ እንዲሆን ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

49/ በቆላማ አካባቢ ያለውን የመስኖ ልማት አቅም ለመለየት እና የአካባቢውን ኅብረተሰብ ተጠቃሚነት ለማሳደግ ጥናት እና ምርምር ያደርጋል፤ የምርምር ውጤቱ ተግባራዊ እንዲሆን ይሠራል፤

50/ በቆላማ አካባቢ ውኃን ማዕከል ያደረገ የተፋሰስ ልማት ሥራ እና የመስኖ ልማት እንዲስፋፋ ያደርጋል፤

51/ ዘመናዊ ቴክኖሎጅን በመጠቀም የመስኖ አውታር የመረጃ እና ኢንፎርሜሽን ሥርዓት ይዘረጋል፤

52/ የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች ምርታማነትን እንዲያሳድጉ እና በዘመናዊ ውኃ ቆጣቢ ቴክኖሎጂ ላይ እንዲመሠረቱ ያደርጋል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

53/ በመስኖ ዘርፍ በመንግሥት እና በግል አጋርነት ሊከናወኑ የሚችሉ የመስኖ አውታሮችን በመለየት ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፤ ሲፈቀድም የግንባታ ሥራውን ተግባራዊ ያደርጋል፤

54/ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን በክልሉ ለድርቅ ተጋላጭ በሆኑ አካባቢዎች ለእንስሳት ሀብት ልማት አስፈላጊ የሆነ ውኃ ለማቅረብ የሚያስችሉ መሠረተ ልማቶች እና የመስኖ አውታሮች እንዲስፋፉ ያደርጋል፤ ይከታተላል፤

45/ Conducts and causes for the conduction of midium and higher maintenance works to make the constructed irrigation facilities provide the required services in a sustainable manner;

46/ Makes technologies related to the construction of irrigation networks maintain their quality and meet standards;

47/ Opens a project office as necessary to facilitate the construction of major irrigation projects; works with concerned body for its implementation;

48/ Facilitates conditions for participation and benefit of local people in irrigation infrastructure construction projects;

49/ Conducts research and studies to identify potential for irrigation development in lowland areas and to increase beneficiary of to local community; works to implement results of the research;

50/ Promotes water-based basin development works and irrigation development in lowland areas;

51/ Establishes an irrigation network data and information system using modern technology;

52/ Ensures that irrigation development projects increase productivity and are based on modern water-saving technology, and monitors their implementation;

53/ Identifies irrigation networks, in the irrigation sector, that can be implemented through government and private partnerships and submits them to the relevant body; implements the construction when approved;

54/ In collaboration with relevant body, causes for the expansion of infrastructure and irrigation networks enabling to provide essential water for livestock development in drought-prone areas of the region; and monitors same;

CamScanner

55/ በእርዳታ እና በብድር የሚገኝ ለመስኖ ግንባታ እና ጥገና ሥራዎች የሚውል ፈንድ ለተፈለገው ዓላማ እንዲውል ያደርጋል፣ አፈፃፀሙን በመከታተል ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ያደርጋል፤

56/የመስኖ አውታሮች በዘላቂነት እንዲያገለግሉ ተጠቃሚዎች ስለ ወጭ፣ እንክብካቤ፣ አስተዳደር እና ጥገና ግንዛቤ እንዲኖራቸው ያደርጋል፤ ለዚሁ የፋይናስ አቅም እንዲፈጥሩ ቁጠባን ያበረታታል፣ ድጋፍ ይሰጣል፤

57/ የመስኖ ግንባታ ፕሮጀክቶች በአካባቢ እና በሰው ጤና ላይ ሊያደርሱ ሚችሉትን ጉዳት ለመቀነስ የአካባቢ ጥበቃ ሕጎችን ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

## 24. የንግድ እና ገበያ ልማት ቢሮ

በሌሎች ሕጎች አስቀድሞ የተደነገገው ወይም ወደ ፊት የሚደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ ንግድ እና ገበያ ልማት ቢሮ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ዝርዝር ሥልጣን እና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1/ የንግድ እና ገበያ ልማት ተወዳዳሪነትን በቀጣይነት ለማረጋገጥ በሀገራቱ ፖሊሲ እና ሕግ መሠረት የንግድ እንቅስቃሴ መከናወኑን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችን እና ሕጎችን ያመነጫል፤ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

2/ በክልሉ ውስጥ ብቁ እና ተወዳዳሪ የንግድ ተቋማት እንዲስፋፉ ያበረታታል፤ የጥናት፣ የሥልጠና፣ የሙያ እና የምክር አገልግሎቶችን ይሰጣል፤ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን ዘርፉ የሚታዩበት ማነቆዎች እንዲፈቱ ያደርጋል፤

3/ ዘመናዊ ቴክኖሎጅን በመጠቀም በክልሉ ውስጥ በንግድ ሥራ የሚሠማሩ አካላትን በንግድ ሕጉ መሠረት ይመዘግባል፣ ፈቃድ ይሰጣል፣ ያድሳል፣ ይሰርዛል፤

55/ Ensures that funds obtained through grants and loans for irrigation construction and maintenance works are used for the intended purpose, and reports its implementation to the relevant body

56/ Makes users are aware of the costs, care management and maintenance of irrigation networks to be used sustainably; encourages and supports savings to create financial capacity for this purpose;

57/ Iimplements environmental protection laws to reduce potential harm that irrigation construction projects may cause on environment and human health.

## 24. Trade and Market Development Bureau

Without prejudice to the existing or subsequent provision of other laws, the Regional Bureau of Trade and Market Development shall, pursuant to this proclamation, have the following specific powers and duties:

1/ Monitors and controls that trade activities are done based on the national policy and laws to continuously ensure competitiveness of trade and market development; initiates policies, strategies and laws, and implements them when approved;

2/ Encourages the expansion of competent and competitive business institutions in the region; provides research, training, professional and advisory services; together with concerned body, causes bottlenecks the sector faces to be solved;

3/ Using modem technology, registers, issues, renews, and cancels business entities engaged in business activities in the region in accordance with the Commercial Law;

CamScanner

4/ የሙያ ፈቃድ በሚጠይቁ የንግድ ሥራዎች ለሚሠማሩ አካላት ከሚመለከታቸው አካላት ተገቢውን የሙያ ፈቃድ ያገኙ መሆናቸውን በማረጋገጥ የንግድ ሥራ ፈቃድ ይሰጣል፣ ያድሳል፣ ይሰርዛል፤

5/ የክልሉን የንግድ መዝገብ ያቋቁማል፣ ያስተዳድራል፣ የነጋዴዎችን የተሟላ መረጃ ይይዛል፣ በዚህም ተገቢውን የአገልግሎት ክፍያ ይሰበስባል፤

6/ የገበያ እና የንግድ ሥራ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ያጠናቅራል፣ ይተነትናል፣ ያሰራጫል፣ በዚህም የገበያ ትስስር እንዲፈጠር ያደርጋል፤

7/ የግብይት ልማት ዘርፉን ለማጠናከር በተመረጡ መስኮች ለክልሉ የግብይት ተዋናያን የብድር፣ የትራንስፖርት እና ትራንዚት አገልግሎቶችን እንዲያገኙ ተገቢውን ድጋፍ ይሰጣል፤

8/ በክልሉ ውስጥ የንግድ አደረጃጀቶች እንዲቋቋሙ ያበረታታል፣ ድጋፍ ይሰጣል፣ የንግድ አሠራር ግንዛቤ እና ተሳትፎ እንዲዳብር ያደርጋል፤

9/ በጠቅላላ የጥራት አሠራር እና አስተዳደር እንዲሁም በድርጅቶች መካከል በውል ሊፈጠር ስለሚችል የሥራ ቁርኝት አሠራር ይዘረጋል፣ ያስተዋውቃል፤

10/ የክልሉን ምርቶች እና አገልግሎቶች ለማስተዋወቅ የሚረዱ ቋሚ ኤግዚቢሽኖች እንዲዘጋጁ ያደርጋል፣ ለሚያዘጋጁ አካላትም ፈቃድ እና ድጋፍ ይሰጣል፣ ሌሎች ክልሎች በሚያዘጋጇቸው መሰል ኤግዚቢሽኖች ላይ ይሳተፋል፤

11/ የዋና ዋና የግብርና ምርቶች እና ሌሎች ግብዓቶች የገበያ ፍላጎት ትንበያ ጥናት ያካሂዳል፣ ይቆጣጠራል፤

12/ በግብይት ረገድ የሚያጋጥሙ ችግሮችን በጥናት ይለያል፣ ሂደቱ የተቀላጠፈ እንዲሆን አሠራር ይቀይሳል፣ የግብይት ሥርዓቱን ያዘምናል፣ ይመራል፣ ያስተባብራል፤

4/ Issues, renews, and cancels business licenses to entities engaged in business activities requiring professional licenses, verifying they have obtained the appropriate professional licenses from relevant bodies;

5/ Establishes and manages the regional commercial registry; maintains complete information of merchants, and collects appropriate service fees from;

6/ Collects, compiles, analyzes and disseminates market and business information, thereby creates market linkages;

7/ Provides the appropriate support to the regional trading actors in selected areas to strengthen the marketing development sector so that they can access credit, transport, and transit services;

8/ Encourages and supports the establishment of trade organizations in the region, makes for enhancement of understanding and participation of trade practices;

9/ Develops and promotes overall quality procedure and management as well as establishes a mechanism for working relationships may be created on contract between organizations;

10/ Causes for permanent exhibitions to be organized to promote the region's products and services; provides permission and supports to the organizing bodies, and participates in similar exhibitions organized by other regions;

11/ Conducts and monitors market demand forecasting studies for major agricultural products and other inputs;

12/ Identifies problems encountered in marketing through research; designs procedures to accelerate the process, updates, directs, and coordinates the marketing system;

13/ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን ለኢንዱስትሪ እና ለግብርና ምርቶች የገበያ ማዕከላት እንዲፈጠሩ እና እንዲጠናከሩ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣ የግብይት አማካሪ ምክር ቤት እንዲቋቋም ያደርጋል፣ውጤታማነቱን ይቆጣጠራል፤

14/ የግብርናም ሆነ የኢንዱስትሪ ውጤቶች የጥራት እና የሥነ ልክ ደረጃቸው ተጠብቆ ለገበያ የሚቀርቡበትን ሥርዓት ይዘረጋል፣ ውጤታማነቱን ይከታተላል፤

15/ የኢንዱስትሪ እና የግብርና ምርቶች አቅርቦት እና በገበያ ረገድ ያላቸው አቅርቦት ቀጣይነት እና ተወዳዳሪነት አስተማማኝ ይሆን ዘንድ ያበረታታል፣ ይደግፋል፤

16/ ሕጋዊ የንግድ አሠራርን ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፤ የዋጋ ንረትን ለመከላከል የሚያስችሉ ስልቶችን በመንደፍ የገበያ ሥርዓት መረጋጋትን የሚያውኩ ድርጊቶች እና አሠራሮች ላይ የእርምት እርምጃ ይወስዳል፣ እንዲወሰድ ያደርጋል፤

17/ በክልሉ የተለያዩ አካባቢዎች የገበያ ማዕከላት እንዲጠናከሩ እና እንዲስፋፉ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊያደርጋል፣ ውጤታማነቱን ይከታተላል፤

18/ የንግድ ሥርዓቱን እና ሸማቹን ኅብረተሰብ የሚጎዱ የተለያዩ ሕገ ወጥ የንግድ እንቅስቃሴዎችን ይቆጣጠራል፣ እርምጃዎችን ይወስዳል፣ ያስወስዳል፤

19/ የሸማቹን መብት ለማስከበር የሚደረጉ እንቅስቃሴዎችን እና ለዚሁ ሲባል የሚፈጠሩ አደረጃጀቶችን ይደግፋል፣ በበላይነት ያስተባብራል፤

20/ በንግድ ውድድር እና በሸማቾች መብት አጠባበቅ ረገድ አለመግባባት ሲፈጠር አግባብ ባለው ሕግ መሠረት እንዲፈቱ ያደርጋል፤

13/ In collaboration with the relevant body, facilitates the creation and strengthening of market centers for industrial and agricultural products, establishes marketing advisory council, and monitors its effectiveness,

14/ Establishes a system that agricultural and industrial products are marketed while maintaining their quality and standard, and monitors its effectiveness;

15/ Encourages and supports the continuity and competitiveness of the supply of industrial and agricultural products and their availability in the market to be reliable;

16/ Implements legal business practices; devises strategies to prevent price inflation and takes and causes to be taken corrective action against actions and practices that disrupt stability of the market system;

17/ Establishes, implements, and monitors a system enabling to strengthen and expand market centers in various areas of the region;

18/ Controls, takes and causes action to be taken on various illegal business activities that harm the business system and the consumer community;

19/ Supports and coordinates activities to protect consumer rights and organizations created for this purpose;

20/ Ensures that disputes arising in the field of trade competition and consumer rights are resolved in accordance with the relevant laws;

CamScanner

21/ ዓይነታቸው እና የዋጋ ዝርዝራቸው በንግድ እና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር የሕዝብ ማስታወቂያ ክፍል የተገለፀ ወይም የሚገለፀ የንግድ እቃዎች እና አገልግሎቶች በክልሉ ውስጥ ስለሚሰራጩበት፣ ስለሚሸጡበት እና ከቦታ ቦታ ስለሚዘዋወሩበት ሁኔታ ይወስናል፤ እንዳስፈላጊነቱ እቃዎች ባለቁ ጊዜም እንዲተኩ ለነጋዴዎች የሥራ መመሪያ ይሰጣል፤

22/ የክልሉን የኢንዱስትሪ እና ግብርና ምርቶችን ሊገዙ የሚችሉ የሀገር ውስጥ እና የውጭ ሀገር ገዥዎችን ይለያል፣ ያቀናጃል፣ የገበያ ትስስር ይፈጥራል፤ ለዚሁ ተግባር አስመጭ እና ላኪዎች እንዲጠናከሩ ያደርጋል፣ ይደግፋል፣ ይቆጣጠራል፤

23/ ዘመናዊ የገበያ መረጃ መሰብሰቢያ ማሰራጫ ሥርዓትን ይዘረጋል፣ የገበያ መረጃ መሰብሰቢያ እና ማሰራጫ ማዕከላትን ያቋቁማል፣ የገበያ መረጃን በጊዜ እና በጥራት ይሰበስባል፣ ያቀናጃል፣ ይገመግማል፣ ያሰራጫል፤

24/ ለክልሉ የገበያ ተሳታፊዎች እና ባለድርሻ አካላት በየጊዜው በሚለዋወጠው ዓለም አቀፍ የገበያ ሁኔታ ላይ የመሳተፍ አቅማቸው እንዲጠናከር ሥልጠና እና የምክር አገልግሎት ይሰጣል፤

25/ ወደ ውጭ ለሚላኩ የክልሉ ምርቶች የገበያ ሥርዓት ይዘረጋል፣ ሥርዓት የተዘረጋላቸውን ምርቶች ያቀናጃል፣ የይለፍ ፈቃድ ይሰጣል፣ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ እርምጃ ይወስዳል፣ እንዲወሰድ ያደርጋል።

## 25. <u>የኢንዱስትሪ እና ኢንቨስትመንት ቢሮ</u>

በሌሎች ሕጎች አስቀድሞ የተደነገገው ወይም ወደ ፊት የሚደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ ኢንዱስትሪ እና ኢንቨስትመንት ቢሮ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ዝርዝር ሥልጣን እና ተግባራት ይኖሩታል፦



21/ Determines conditions under which commercial goods and services, whose types and prices are specified or to be specified public notice part in the Ministry of Trade and Regional Integration, to be distributed, sold and moved from place to place in the region; issues work instructions to traders to replace same when they are out of stock, as necessary;

22/ Identifies and integrates domestic and foreign buyers who can purchase industrial and agricultural products of the region, and creates market linkages; causes for strengthening of importers and exporters for this purpose, supports and supervises;

23/ Establishes a modern market information collection and dissemination system, establishes market information collection and dissemination centers, collects, organizes, evaluates and disseminates market information in timely and quality manner;

24/ Provides training and advisory services to the regional market participants and stakeholders to strengthen their capacity to participate in the ever-changing international market environment;

25/ Establishes a market system for the regional products to be exported, integrates the products for which the system is established, issues transit permissions, monitors, controls, takes action, and causes to be taken.

## 25. <u>Bureau of Industry and Investment</u>

Without prejudice to what has been previously or may be provided for in other laws, the Regional Bureau of Industry and Investment shall have the following detailed powers and functions under this Proclamation:

1/ የኢንዱስትሪ ልማት እና ተወዳዳሪነትን በቀጣይነት ለማረጋገጥ የኢንዱስትሪ እንቅስቃሴ በሀገሪቱ ፖሊሲ እና ሕግ መሠረት መከናወኑን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችን እና ሕጎችን ያመነጫል፣ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

2/ በክልሉ ውስጥ ብቁ እና ተወዳዳሪ የኢንዱስትሪ ተቋማት እንዲስፋፉ ያበረታታል፤ የጥናት፣ የሥልጠና፣ የሙያ እና የምክር አገልግሎቶችን ይሰጣል፤ ጉዳዩ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን ዘርፉ የሚታዩበት ማነቆዎች እንዲፈቱ ያደርጋል፤

3/ የኢንዱስትሪ ተቋማት እንዲስፋፉ በአምራች ኢንዱስትሪ የግል ዘርፉን ተሳትፎ እና ሚና ለማሳደግ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፣ የጥናት፣ የስልጠና፣ የሙያ እና የምክር አገልግሎቶችን ይሰጣል፤

4/ የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፉን በመደገፍ ረገድ ቁልፍ ሚና ካላቸው የክልሉ ወይም የፌደራሉ የከፍተኛ ትምህርት፣ የምርምር እና የፋይናንስ ተቋማት ጋር በመሆን የጋራ ዕቅዶችን አውጥቶ ይሠራል፤

5/ በአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ልማት ትኩረት የሚሰጣቸውን የጨርቃ ጨርቅ፣ የቆዳ፣ የምግብ እና መጠጥ ኢንዱስትሪዎች ያላቸውን አንፃራዊ ጠቀሜታ እና እምቅ አቅም ይለያል፤ ለአፈፃፀሙ ከክልላዊ የልማት አቅጣጫ ጋር የተጣጣመ ዝርዝር መርሃ ግብር ያዘጋጃል፣ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

6/ በክልሉ ውስጥ በአምራች ዘርፉ ለሚሠማሩ መካከለኛ እና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች አገልግሎት ሊውሉ የሚችሉ የኢንዱስትሪ መንደሮችን፣ የክላስተር ማዕከላትን፣ የኢንዱስትሪ ፓርኮችን እና ልዩ የኢኮኖሚ ዞኖችን ያደራጃል፤ እስከ መዳረሻቸው የሚዘልቅ መሠረተ ልማት እንዲሟላላቸው በማድረግ ለኢንዱስትሪ ፓርኮች ኮርፖሬሽን ያስተላልፋል፤



1/ Monitors and controls performance of industrial activity is based on the national policy and laws to ensure continuous industrial development and competitiveness; initiates policies, strategies and laws and implement same when approved;

2/ Encouragees the expansion of competent and competitive industrial institutions in the region; provides research, training, professional and advisory services; makes bottlenecks in the sector to be solved working with relevant parties;

3/ Establishes a system to increase the participation and role of the private sector in the manufacturing industry so that industrial institutions can expand, provide research, training, professional and advisory services,

4/ Develops and implements joint plans with regional or federal higher education, research and financial institutions that play a key role in supporting the manufacturing sector;

5/ Identifies the comparative advantage and potential of the textile, leather, food and beverage industries that are of interest in the development of the manufacturing sector; prepares detailed program for its implementation in line with the regional development direction, and implements it once approved;

6/ Organizes industrial villages, cluster centers, industrial parks and special economic zones that can be used for medium and high industries engaged in the manufacturing sector in the region; hands over them to industrial parks corporation after making infrastructures to be fulfilled upto their destination;

CamScanner

7/ የኢንዱስትሪ በተለይም የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ ልማትን ለማሳደግ የሚያስችሉ ምርጥ ተሞክሮ የመቀመር ተግባራትን እና አጠቃላይ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማት አቅም ግንባታ ሥራዎችን ይሠራል፤

8/ የኢንዱስትሪ ዘርፍ ልማት እና ምርታማነትን ለማሳደግ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት፣ የቴክኖሎጂ፣ የግብዓት እና የግብይት እንዲሁም በአመራረት ረገድ ድጋፍ እንዲያገኙ ያደርጋል፣ ውጤታማነታቸውንም ያረጋግጣል፤

9/ የአምራች ኢንዱስትሪያሊስቶችን አቅም ለመገንባት የሚያስችሉ ተቋማት ያደራጃል፣ ይደግፋል፤ የዕውቀት እና የቴክኖሎጂ ሽግግር ማዕከላት ሆነው እንዲያገለግሉ ያደርጋል፤

10/ የኢንዱስትሪ ምርቶች የጥራት ደረጃቸውን ጠብቀው እንዲመረቱ እና በዓለም አቀፍ ገበያ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ የሚያደርግ የአቅም ግንባታ፣ የምርምር እና ስርፀት ሥራዎች እንዲከናወኑ ሥርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤

11/ ኢንዱስትሪያሊስቶችን ለመፍጠር፣ በሥራ ላይ የሚገኙትን ለማጠናከር የሚረዳ የኢንተርፕረነርሽፕ ፕሮግራም ቀርፆ በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፣ ሥልጠናዎችን ይሰጣል፤

12/ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን ለኢንዱስትሪ በተለይም ለአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ የሚመጥን የሰው ኃይል ፍላጎት ለማሟላት የሚቻልበትን ስልት ይቀይሳል፤ የኢንዱስትሪ ግብዓት አቅርቦት ትስስር ሥርዓት እንዲዘረጋ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፤

13/ በመካከለኛ እና በከፍተኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች መካከል የተቀናጀ ትስስር እንዲፈጠር፣ ስኬታማ ሽግግሮች እንዲከናወኑ እና በዘርፉ ዘላቂ መዋቅራዊ ለውጥ እንዲረጋገጥ ለማድረግ የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

7/ Undertakes best practice formulation activities and general manufacturing industry development capacity building activities to enhance the development of the industrial sector, especially the manufacturing industry;

8/ Causes for the provision of industrial extension services, technology, input and marketing as well as to get support in production aspect to enhance the development and productivity of the industrial sector, and ensures their effectiveness;

9/ Organizes and supports institutions that will build the capacity of manufacturing industrialists; makes them to serve as centers for knowledge and technology transfer;

10/ Establishes a system for capacity building, research and indoctrination activities to make industrial products to be produced with high quality standards and to be competitive in the international market, and monitors their implementation;

11/ Designs and implements an entrepreneurship program that will help to create industrialists and strengthen those who are already in business, and provides training;

12/ In collaboration with relevant body, devises a strategy to meet needs of human power to industry_ especially to the manufacturing sector, and facilitates conditions in which an industrial input supply linkage system to be developed; implements same;

13/ Establishes a system of procedures to create coordinated linkages between medium and high-production industries, performance of successful transitions, and to ensure sustainable structural change in the sector; monitors its implementation;

CamScanner

14/ ለአምራች ኢንዱስትሪው መስፋፋት ዘላቂ ፋይዳ ያለው የአዋጭነት ጥናት እና የፕሮጀክት ትግበራ፤ ክትትል እና ድጋፍ ሥርዓት ቀርፆ ተግባራዊ ያደርጋል፤

15/ ከአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ በኩል የሚቀርቡለትን ፕሮጀክቶች ይቀበላል፤ ወደ ክላስተር ማዕከላት፣ የኢንዱስትሪ መንደሮች እና ኢንዱስትሪ ፓርኮች ሊገቡ የሚችሉትን በዓይነት ይለያል፤ የፕሮጀክት ፕላንት ሌይ አውት ይገመግማል፣ የሚያስፈልገውን የመሬት መጠን ይወስናል፤ ወደ ልዩ የኢኮኖሚ ዞኖች የሚሳቡና የሚገቡ ኢንቨስትመንቶችን ከሚመለከታቸው የፌዴራል ተቋማት ጋር በሚፈጠር ቅንጅታዊ አሠራር ይገመግማል፣ ይለያል፤

16/ የመካከለኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች የዘርፍ ማኅበራት እና የሙያ ማኅበራት እንዲቋቋሙ ያበረታታል፣ የተቋቋሙትንም እንዲጠናከሩ ያደርጋል፤

17/ የኢንዱስትሪ ፕሮጀክት ሐሳቦችን ያመነጫል፣ ተጠንተው በሥራ ላይ ሊውሉ የሚገባቸውን ይለያል፤ አግባብ ላለው የፌደራል መንግሥት አካል ያስተላልፋል፤ በክልሉ አቅም ሊፈፀሙ የሚችሉትን ደግሞ በሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፤

18/ በአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፍ የደረጃ ሽግግር የሚያደርጉ ባለሀብቶች እድገታቸው እንዲፋጠን ለማድረግ የማምረቻ ቦታ እና የመሠረተ ልማት አገልግሎት እንዲሟላላቸው ይሠራል፤ በፕሮጀክት ዝግጅትም ሆነ በአዋጭነት ጥናት ረገድ ይደግፋል፤

19/ በክልሉ ውስጥ የገጠር ኢንዱስትሪያላይዜሽንን ለማስፋፋት በየአካባቢው ያለውን የመልማት አቅም መሠረት ያደረጉ የኢንዱስትሪ ዓይነቶችን ይለያል፣ የኢንዱስትሪ መንደሮችን ያደራጃል፤ ተፈላጊው መሠረተ ልማት እንዲሟላላቸው ያደርጋል፤

14/ Designs and implements a sustainable feasibility study and project implementation, monitoring and support system for expansion of the manufacturing industry

15/ Receives projects submitted to it from the manufacturing industry sector; identifies those that can be included in cluster centers, industrial villages and industrial parks; evaluates layout of project plant and determines the amount of land required, evaluates and identifies investments to be pulled and included in special economic zones through a coordinated process created with relevant federal institutions;

16/ Encourages sector and professional associations to be established of medium-sized manufacturing industries, and makes those already established to strengthened,

17/ Generates industrial project ideas, identifies those should be studied and implemented; handsover them to the appropriate federal government body; implements those that can be implemented by capacity of the region;

18/ Works for manufacturing plot and infrastructure to be fulfilled to investors making level-shifting in the manufacturing industry sector to accelerate their growth; supports them in project preparation and feasibility studies;

19/ Identifies industrial types based on the development potential of each area to promote rural industrialization in the region; organizes industrial villages, and ensures that the required infrastructure is to be fulfilled to them;

20/ ተለይተው በተዘጋጁ የኢንዱስትሪ ቀጠናዎች አምራች ኢንዱስትሪዎች ገብተው እንዲያለሙ ይሠራል፤ የቀጠናዎቹን ወሰን እና የመሬት አጠቃቀም ለውጥ በሚመለከተው አካል እንዲመዘገብ ያደርጋል፤

20/ Works for the established manufacturing industries to develop being entered in the designated industrial zones; ensures that boundaries of zones and changes in land use are registered by the relevant body;

21/ የአገር ውስጥ ግብዓቶችን በተለይም የግብርና ምርቶችን እና የማዕድን ሀብቶችን የሚጠቀሙ የመካከለኛ እና ከፍተኛ የምግብ ነክ፣ የጨርቃ ጨርቅ እና አልባሳት፣ የቆዳ ውጤቶች፣ የኮንስትራክሽን ግብዓቶች እና መድኃኒት ንዑስ ዘርፎችን በማስፋፋት ከውጭ የሚገባ ምርት እና አገልግሎትን የመተካት እና ወደ ውጭ አገር የሚላክ ምርት እና አገልግሎትን የማሳደግ ግብ እንዲሳካ ይሠራል፤

21/ Works to achieve the goal of replacing imported products and services and increasing exports of products and services by expanding the medium and high-end food related, textile and clothing, leather products, construction inputs, and pharmaceutical sub-sectors that utilize domestic resources_ especially agricultural products and mineral resources;

22/ ኢንዱስትሪዎች በአካባቢ ጥበቃ እና ደኅንነት የተቀመጡ መስፈርቶችን እንዲያሟሉ እና ማኅበራዊ ግዴታቸውን እንዲወጡ ድጋፍ እና ክትትል ያደርጋል፤

22/ Supports and monitors that industries to meet environmental and safety requirements and fulfill their social obligations;

23/ የተቀናጁ የአግሮ ኢንዱስትሪ ፓርኮች፣ ሁለገብ የኢንዱስትሪ ፓርኮች፣ የገጠር ትራንስፎርሜሽን ማዕከላት፣ የመካከለኛ ክላስተር ሸዶች፣ ሕንፃዎች እና የምርት ማሰባሰቢያ ማዕከላት እንዲገነቡ ያደርጋል፣ ያስተዳድራል፣ ይቆጣራል፤ የግል ባለ ሀብቱን የሚስቡ ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥራል፤

23/ Causes for the construction of integrated agro-industrial parks, multi-purpose industrial parks, rural transformation centers, intermediate cluster shades, buildings, and product collection centers; manages and controls; creates favorable conditions attracting private investors;

24/ ከፓርኮች እና ከልዩ የኢኮኖሚ ዞኖች አስተዳደር እና አሠራር ጋር በተያያዘ ለሚነሡ አለመግባባቶች አግባብነት ባላቸዉ ሕጎች መሠረት ከሚመለከታቸዉ አካላት ጋር በመቀናጀት መፍትሔዎችን ያፈላልጋል፤

24/ Finds solutions for resolving disputes arising in connection with the administration and operation of parks and special economic zones in accordance with relevant laws in coordination with concerned bodies;

25/ ለረጅም ጊዜ የኬሚካል፣ የከፍተኛ ብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ልማት፣ ለማሽኖች፣ ለልዕለ ማሽኖች፣ የግብዓት እና ኬሚካል ቴክኖሎጂዎች መሠረት ለመጣል በፋብሪኬሽን ኢንጂነሪንግ የሽግግር ዝግጅት ያደርጋል፣ ሥርዓት ይዘረጋል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

25/ Makes transition preparations in fabrication engineering to lay foundation for the long-term chemical and high-level metallic development, machinery, supermachinery, input and chemical technologies; establishes a system, and monitors its implementation;

26/ የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፉ በሜካናይዜሽን፣ በኃይል፣ በግብዓት እና በኦቶሜሽን የቴክኖሎጂ ተወዳዳሪነት ለሚተገበር ኢንዱስትሪያላይዜሽን ቁልፍ ሚና እንዲጫወት ያደርጋል፤

27/ የክልሉን የኢንቨስትመንት ስምሪቶች በበላይነት ይመራል፣ ይከታተላል፣ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን ተገቢውን ሁሉ ያደርጋል፤

28/ በክልሉ ውስጥ ምቹ እና ተወዳዳሪ የኢንቨስትመንት አከባቢ እንዲፈጠር የሚያበረታቱ የፖሊሲ ሐሳቦችን ያመነጫል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤

29/ የኢንቨስትመንት ስምሪት ዘፈቀዳዊ እንዳይሆን ከክልሉ ስትራቴጂያዊ ጉዳዮች በመነሣት የአልሚዎችን መረጣ በጥናት ላይ ተመሥርቶ እንዲፈፀም ያደርጋል፤

30/ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን ለእውነተኛ አልሚዎች በተቀላጠፈ ቢሮክራሲ ላይ የተመሠረተ ድጋፍ ይሰጣል፤ በአንፃሩ መሬት ወስደው በወቅቱ በማያለሙ እና ኪራይ ጠባቂዎች ላይ አስፈላጊውን እርምጃ ይወስዳል፣ ያስወስዳል፤

31/ የኢንቨስትመንት ስምሪቶች በታቀደ ዘርፍ እና ቦታ፣ ከመሠረተ ልማት፣ ከሰው ኃይል እና ከግብዓት አቅርቦት ጋር ተቀናጅተው እንዲፈፀሙ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፤

32/ አልሚዎች በማልማት ብቃታቸው ተወዳድረው እና ተመርጠው በተመረጡ ዘርፎች በተለዩ የኢኮኖሚ ቀጠናዎች በተቆረጠ የማስጀመሪያ እና የማጠናቀቂያ ጊዜ፣ በታቀደ የምርት ግብ ውል መሠረት እንዲሠማሩ ያደርጋል፣ ውጤታማነቱን ይከታተላል፤

33/ ውጤታማ እና ቀልጣፋ የሆነ የክትትል፣ የግምገማ እና የተጠያቂነት ሥርዓት ይዘረጋል፤

34/ በክህሎት፣ በሥነ ምግባር እና በሕዝብ አገልጋይነታቸው የተመሰከረላቸው ሙያተኞች በማፍራት የኢንቨስትመንት አሳላጭ ቢሮክራሲ ይፈጥራል፤

26/ Makes the manufacturing industry sector to play a key role in industrialization through mechanization, energy, input and automation technology competitiveness;

27/ Supervises and monitors investment projects of the region, and does everything appropriate in collaboration with relevant body;

28/ Generates policy ideas that encourage to create favorable and competitive investment environment in the region, and implements them when approved;

29/ Ensures that the selection of developers is carried out based on the strategic issues of the region so that investment projects do not become haphazardly,

30/ Provides support to genuine developers based on a streamlined bureaucracy in collaboration with the relevant body; takes and causes to be taken necessary action against those who do not develop land in time and rent-seekers;

31/ Provides the necessary support to ensure investment operations to be implemented in a planned sector and location integrated with infrastructure, human resources and input provision;

32/ Ensures that developers compete and are selected based on their development capabilities and are engaged in selected sectors and economic zones within a set starting and completion period based on a planned production target contract, and monitors its effectiveness;

33/ Establishes an effective and efficient monitoring, evaluation and accountability system;

34/ Creates an investment-friendly bureaucracy by producing professionals who are proven in their skills, ethics, and public servitude;

35/ የመንግሥት እና የግሉ ዘርፍ የኢንቨስትመንት ትብብር ሥርዓት እንዲኖር ይሠራል፣ ቋሚ የምክክር ጉባኤ ያቋቁማል፣ በበላይነት ያስተባብራል፤

36/ በክልሉ ውስጥ የሚገኙትን የኢንቨስትመንት አቅም መረጃዎችን ያሰባስባል፣ ያጠናቅራል፤ በመረጃው መሠረት ክልላዊ የኢንቨስትመንት መሪ ዕቅድ ያዘጋጃል፣ መረጃዎችን ለባለሀብቶች ያሰራጫል፤

37/ በሚመለከተው አካል ተለይተው በተዘጋጁ የኢንቨስትመንት ዘርፎች ባለሀብቶች ወደ ሥራ እንዲገቡ ይሠራል፤ የቀጠናዎቹ ወሰን እና የአጠቃቀም ለውጥ በመሬት ቢሮ እንዲመዘገብ ያደርጋል፤

38/ በጥናት በሚለዩ እና የተሻለ የኢንቨስትመንት ፍሰት ባለባቸው የክልሉ የኢኮኖሚ ቀጠናዎች ለባለሀብቱ የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫዎችን ያቋቁማል፤

39/ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን ኢንቨስትመንትን ከማስፋፋት እና ከማበረታታት ጎን ለጎን የክልሉን መልካም ገፅታ ለመገንባት የሚረዱ ሥራዎችን ይሠራል፤

40/ ስለ ኢንቨስትመንት የወጡ ሀገር አቀፍ ፖሊሲዎች እና ሕጎች በክልሉ ውስጥ በትክክል ሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፣ ይቆጣጠራል፤

41/ በባለሀብቶች የሚቀርቡለትን የኢንቨስትመንት ጥያቄዎች መርምሮ ፈቃድ ይሰጣል፣ ያድሳል፣ ይሰርዛል፣ የአገልግሎት ክፍያ ይሰበስባል፤

42/ የኢንቨስትመንት ፈቃድ የተሰጠውን ፕሮጀክት አፈፃፀም በቅርብ በመከታተል በፈቃዱ መሠረት መተግበሩን፣ የተሰጠው ማበረታቻ ለታለመለት ዓላማ መዋሉን ያረጋግጣል፤ ከታለመለት ዓላማ ውጭ ሆኖ ሲያገኘው እርምጃ እንዲወሰድ ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፤

35/ Works towards a system of investment cooperation between government and private sector, establishes permanent consultative council, and coordinate ontop of its supervision.

36/ Collects and compiles information of the investment potential in the region, prepares regional investment master plan based on the information, disseminates the information to investors;

37/ Works towards the engagement of investors in investment sectors identified by the relevant body, ensures boundaries of the zones and changes in their use to be registered by the Bureau of Land;

38/ Establishes one-stop service centers for investors in economic zones of the region identified through research and with better investment flows;

39/ Works with relevant body to carry out works helping to build good image of the region besides promoting and encouraging investment;

40/ Ensures and monitors the proper implementation of national policies and laws enacted on investment in the region;

41/ Examines investment requests submitted to it by investors and grants, renews and cancels license, and collects service fees;

42/ Closely monitors implementation of the investment project to ensure that it is implemented in accordance with the license and the incentive provided is used for the intended purpose; submits it to the relevant body for action to be taken when it is found to be outside the intended purpose;

43/ ለኢንቨስትመንት መስፋፋት የሚረዱ ልዩ ልዩ ማትጊያዎችን በማጥናት ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

44/ ለኢንቨስትመንት መስፋፋት እንቅፋት የሚሆኑ ማነቆዎችን ይለያል፣ በወቅቱ እንዲፈቱም ያደርጋል፤

45/ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት የድኅረ ኢንቨስትመንት የድጋፍ እና ክትትል ሥራዎችን ያከናውናል፤

46/ ከፋይናንስ ተቋማት ጋር በመተባበር የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ወደ ሥራ የሚያስገባቸው የብድር አገልግሎት እንዲመቻችላቸው ያደርጋል፤

47/ ዘመናዊ የኢንቨስትመንት መረጃ ሥርዓት ይዘረጋል፣ ኢንቨስትመንት ነክ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ያጠናቅራል፣ ይተነትናል፣ ወቅታዊ ያደርጋል፣ ለተጠቃሚዎች ያሰራጫል፤

48/ በኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች በሚፈጠሩ የሥራ ዕድሎች የክልሉ ኅብረተሰብ ቅድሚያ ተጠቃሚ መሆኑን ይከታተላል፤ ጉድለት በተገኘበት ቦታ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፣ እንዲወሰድ ያደርጋል፤

49/ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች በአካባቢ እና በሰዎች ጤና ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የማያደርሱ ስለመሆናቸው በማረጋገጥ ተቀባይነት ላገኙት ፈቃድ ይሰጣል፤

50/ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክት የሚገመገምበትን መስፈርት ያዘጋጃል፣ ፕሮጀክቶችን በመቀበል ይገመግማል፤ ከፍተኛ ጥቅም ያላቸውን እና ተቀባይነት ያገኙትን ለክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ያቀርባል፤ ሲወሰን የሚመለከተውን አካል ያሳውቃል፣ ሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፣ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤ ጉድለት በተገኘበት ቦታ ከሚመለከተው አካል ጋር እርምጃ ይወስዳል፣ እንዲወሰድ ያደርጋል፤

43/ Studies various incentives to promote investment and submits same to the Regional Government Council implements them when approved, and monitors their implementation;

44/ Identifies obstacles to investment promotion and makes same to be solved in time;

45/ Carries out post-investment support and monitoring activities in coordination with relevant parties;

46/ Collaborates with financial institutions to facilitate startup credit services for investment projects;

47/ Establishes a modern investment information system, collects, compiles, analyzes, updates, and disseminates investment-related information to users,

48/ Monitors that the regional society is the primary beneficiary of job opportunities created by investment projects; takes and causes to be taken corrective action being with relevant body where deficiencies are found;

49/ Issues license for accepted investment projects, being with concerned body, ensuring as they have no negative impact on the environment and human health;

50/ Prepares criteria for evaluating investment projects, receives and evaluates projects; presents those are of high benefit and accepted ones to the Regional Head of Government; notifies same to relevant body when decision is made, makes to be implemented, monitors and controls; takes and causes to be taken action being with relevant body where deficiencies are found;

51/ በክልሉ የሚካሄዱ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ለሁለንተናዊ ዕድገት የሚያስፈልገውን የእውቀት፣ የክህሎት እና የቴክኖሎጂ ሽግግር እንዲያመጡ ይሠራል፤

52/ ለኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የሚቀርብ የዓይነት ለውጥ ጥያቄን ከሚመለከተው አካል ጋር አጣርቶ በአሠራሩ መሠረት ይፈፅማል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

53/ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን በአርሶ አደሮች፣ የደረጃ ሽግግር ባደረጉ አነስተኛ እና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች፣ በኅብረት ሥራ ማኅበራት እና በሴቶች የሚካሄዱ ኢንቨስትመንቶችን በልዩ ሁኔታ ለማስተናገድ የሚያስችል አሠራር ያዘጋጃል፣ በሚመለከተው አካል ሲፀድቅ ሥራ ላይ ያውላል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

54/ በክልሉ ውስጥ እየሠሩ ያሉ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የሚጠበቅባቸውን ማኅበራዊ ኃላፊነት እንዲወጡ ያደርጋል፣ ያበረታታል፤

55/ ዝርዝሩ በመመሪያ የሚወሰን ሆኖ አስፈላጊ በሆኑ አካባቢዎች የኢንቨስትመንት ማስተባበሪያ ጽሕፈት ቤት ሊያቋቁም ይችላል።

## 26. <u>የመሬት ቢሮ</u>

በሌሎች ሕጎች አስቀድሞ የተደነገገው ወይም ወደ ፊት የሚደነገገው እንደ ተጠበቀ ሆኖ የክልሉ መሬት ቢሮ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ዝርዝር ሥልጣን እና ተግባራት ይኖሩታል፦

1/ የሀገሪቱን ፖሊሲ እና ሕግ መሠረት በማድረግ የክልሉን የመሬት አስተዳደር፣ አጠቃቀም ፖሊሲ፣ ስትራቴጂ እና ሕግ ያመነጫል፤ ለአፈፃፀሙ ከክልላዊ የልማት አቅጣጫ ጋር የተጣጣመ ዝርዝር መርሃ ግብር ያዘጋጃል፣ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

51/ Makes investment projects carried out in the region bring about transfer of knowledge, skills and technology required for comprehensive development;

52/ Examines the request for type change of investment projects with the relevant body and implements it in accordance with the procedure; monitors and supervises its implementation;

53/ Prepares a procedure with the relevant body to enabling to treat investments made by farmers, small and micro enterprises that have undergone level transition, cooperatives and women in a special way; and implements it upon approval by the relevant body and monitors its implementation;

54/ Ensures and encourages investment projects being carried out in the region to fulfill their expected social responsibilities;

55/ May establish Investment Coordination Offices in necessary areas, being the details to be determined by directive.

## 26. <u>Bureau of Land</u>

Without prejudice to the existing or subsequent provisions to be issued, the Regional Bureau of Land shall, pursuant to this proclamation, have the following specific powers and duties:

1/ Initiates the regional land administration, use policy, strategy and law based on the national policy and law; prepares detailed program for its implementation in line with the regional development direction, and implements it upon approval;

2/ በክልሉ ውስጥ የሚገኘውን የከተማ እና የገጠር መሬት አጥንቶ በዓይነት እና በመጠን መዝግቦ ይይዛል፤ የመሬት ይዞታዎችን አስተዳደር እና አጠቃቀም ይወስናል፤ ይቆጣጠራል፤ ለባለ ይዞታዎችም የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር እና ካርታ ይሰጣል፤

2/ Studies and maintains recording urban and rural land found in the region by type and size; determines and controls the administration and use of land holdings, and provides land holding certificates and maps to landholders;

3/ በክልሉ ውስጥ የሚገኘን የገጠር መሬት አጠቃቀም ያጠናል፤ ይወስናል፤ የመሬት ተጠቃሚዎች ለይዞታቸው እንክብካቤ ማድረጋቸውን ይከታተላል፤ የማትጊያ ዘዴዎችን ይቀይሳል፤ ግዴታቸውን ባልተወጡት ላይ ተገቢውን እርምጃ ይወስዳል፤

3/ Studies and determines the land use found in the region; follows up that land users take care of their holdings; devises incentive methods; and takes an appropriate measure on those who do not discharge their own duties;

4/ እንደ ሁኔታው ባሕላዊ እና ዘመናዊ የቅየሳ ዘዴዎችን በመጠቀም እያንዳንዱን የገጠር መሬት ይዞታ እና ማሳ ይለካል፤ ይመዘግባል፤ በምዝገባው መሠረት የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር እና ካርታ ይሰጣል፤

4/ Measures and registers each rural land-holding and farm using traditional and modern surveying instruments having regard to circumstances, and thereby issues certificate of holding with map as per such registration;

5/ የመሬት ይዞታ እና የመጠቀም መብት የተሰጣቸው ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች የይዞታ መብታቸውን እንደ አግባብነቱ በውርስ፣ በኪራይ፣ በስጦታ፣ በለውጥ ወይም በብድር ዋስትና የሚያስተላልፉበትን ሥርዓት ያስፈፅማል፤ በመሬት ይዞታ ላይ የሚካሄዱ ለውጦችን እየመዘገበ መረጃውን ወቅታዊ ያደርጋል፤

5/ Executes the system whereby individuals or organizations granted land holding and use rights may transfer their holding rights, as appropriate, by inheritance, lease, donation, exchange or loan security; and keeps the information up to date by recording changes taken place in land holding;

6/ በባለ ይዞታዎች ለሚቀርቡ የስመ ንብረት ዝውውር ጥያቄዎች ተገቢውን ምላሽ ይሰጣል፤ በመሬት ይዞታ ላይ የሚካሄዱ ለውጦችን እየመዘገበ መረጃውን ወቅታዊ ያደርጋል፤

6/ Responds appropriately to requests for transfer of title submitted by landholders; records changes taken place in land holding and keeps the information up to date;

7/ ማናቸውንም የመሬት ሊዝ አሠራሩን እና ተመኑን እያጠና በመስተዳደር ምክር ቤት ያስወስናል፣ ሲፈቀድም ሥራ ላይ ያውላል፤

7/ Studies and gets determined the procedure and rate of any land lease by the Government Council, and implements when approved;

8/ የከተማ መሬት የሊዝ ሕግ እና ሌሎች ሕጎች፣ የመሬት አጠቃቀም እና አስተዳደር ሕግ ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፣ አተገባበራቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

8/ Forces the implementation of the Urban Land Lease Laws and other laws, the Land Use and Administration Law; monitosrs and supervises their implementation;

CS CamScanner

9/ ለገጠር ቀበሌ ማዕከላት እና አዳዲስ ለሚፈጠሩ መንደሮች የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ ያዘጋጃል፣ የግንባታ ፈቃድ ይሰጣል፣ ግንባታቸውን ላጠናቀቁ አካላት በካርታ የተደገፈ ሰርቲፊኬት ይሰጣል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤

10/ ለሕዝብ ጥቅም ሲባል የመሬት ይዞታ በሚለቀቅበት ወቅት ከመሬታቸው የሚነሡ የልማት ተነሺ ባለይዞታዎችን ይለያል፣ ግንዛቤ ይፈጥራል፣ የሀብት እና ንብረት ቆጠራ ያካሂዳል፣ ካሣ ይገምታል፣ በሕጉ መሠረት ካሣ እንዲከፈላቸው ያደርጋል፤

11/ አግባብ ባለው ሕግ መሠረት በልማት ምክንያት ከይዞታቸው የሚነሡ ባለይዞታዎችን በጉዳት መጠናቸው በደረጃ ይለያል፤ አማራጭ የፕሮጀክት ሐሳብ ያዘጋጃል፣ ከተነሺዎች ጋር ይወያያል፣ ከአጋር አካላት ጋር በመተባበር የልማት ፋይናንስ፣ የመሥሪያ እና የመኖሪያ ቦታ እንዲያገኙ ያደርጋል፤በዘላቂነት የማቋቋም ሥራ በማከናወን በሂደቱ የሚነሡ አቤቱታዎች እና ቅሬታዎች የሚፈቱበትን ሥርዓት ይዘረጋል፤

12/ በዘመናዊ ሁኔታ በሚለሙ ትላልቅ የመስኖ ፕሮጀክቶች ውስጥ ለሚኖሩ ባለይዞታዎች በሕግ አግባብ የመሬት ሽግሽግ ያካሂዳል፤ የሁለተኛ ደረጃ ደብተር እና ካርታ እንዲያገኙ ያደርጋል፤

13/ በክልሉ ውስጥ ለሚገኙ የመሬት ይዞታዎች እና ማሳዎች ልዩ ኮድ ይሰጣል፣ የተሰጠውን መለያ ኮድ ሌሎች መሥሪያ ቤቶች እና የልማት ተቋማት እንዲገለገሉበት ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

14/ ለተለያዩ የልማት አገልግሎቶች የሚውሉ መሬቶችን በጥናት ይለያል፤ ወደ መሬት ባንክ ያስገባል፣ በበቂ ሁኔታ እንዲዘጋጅ ያደርጋል፤

9/ Prepares land use plans for rural kebele centers and newly emerged villages, issues construction permission, issues certificate supported by map to entities that have completed their construction, and monitors its implementation.

10/ Identifies landholders who are subject to leave their plot of land during public expropriation, creates awareness, conducts census of their assets and property, valuates compensation and ensures compensation to be paid to them in accordance with the law;

11/ In accordance with the relevant law, classfies landholders who are displaced due to development according to the extent of their damage; prepares alternative project ideas, discusses with the displaceds, makes for the provision of development finance, work and housing plot in cooperation with partner organizations; establishes a system for resolving complaints and grievances arising during the process of implementing sustainable development work;

12/ Conducts legal land transfers for landholders living in large irrigation projects being developed in modern way, and provides them with secondary level holding book and map;

13/ Provides a unique code for land holdings and farms in the region, and facilitates conditions in which other offices and development institutions use the given code;

14/ Identifies lands to be used for different purposes through research; enters them into the land bank, and ensures to be prepared sufficiently;

15/ ለመሬት አስተዳደር ሥርዓት ግንባታ አገልግሎት የሚውሉ የጂኦ ስፓሻል እና ተያያዥ መረጃዎችን ይሰበስባል፤ ያደራጃል፤ ይተነትናል፤ መስፈርቱን አሟልተው ለሚቀርቡ አካላት መረጃ ይሰጣል፤

16/ በገጠር እና በከተማ ለካዳስተር ሥራ የሚያገለግል የአየር ፎቶ ግራፍ ያስነሣል፤ መረጃ ይሰበስባል፤ ያደራጃል፤ ጥቅም ላይ ያውላል፤

17/ ለካዳስተር ሥራ የሚውሉ የቅየሳ መቆጣጠሪያ ነጥቦችን ይመሠርታል፤ መለያ ምልክት ወይም ሞኑመንት ይተክላል፤ መረጃ ያደራጃል፤ የቅየሳ ነጥቦቹ በዘላቂነት እንዲያገለግሉ አስፈላጊውን ጥበቃ ያደርጋል፤ ይቆጣጠራል፤

18/ አነስተኛ እና የተበታተነ የገጠር መሬት ይዞታን ባለ ይዞታዎችን በማሳተፍ እና ፍላጎት እንዲፈጥሩ በማድረግ ይዞታን ለማጠጋጋት የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፤ በክልሉ መንግሥት ሲፈቀድለትም ተግባራዊ ያደርጋል፤

19/ መሬት ነክ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን በመለየት ወጥነት እና ግልፅነት ባለው አሠራር ይፈታል፤ የመሬት ዘመናዊ መረጃ አስተዳደር ሥርዓት በመገንባት የአገልግሎት እና የመረጃ ተደራሽነትን ያሰፋል፤

20/ የመሬት አስተዳደር ሥርዓቱን የሚያዘምኑ እና ቀጣይነቱን የሚያረጋግጡ ዓለም-አቀፍ ልምዶችን ይቀምራል፤ ጥናት እና ምርምር ያካሂዳል፤ ተግባራዊ ያደርጋል፤

21/ በመሬት አስተዳደር ሥርዓቱ ላይ የሚታዩ ብልሹ አሠራሮችን ለመከላከል የሚያስችሉ የአሠራር ስልቶችን ይነድፋል፤ ኦዲት ያከናውናል፤ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን የማስተካከያ እርምጃዎችን ይወስዳል፤

22/ ለማዕድን ልማት ሥራ የሚውል መሬት በሌላ አካል አለመያዙን ወይም ለሌላ አገልግሎት እየዋለ አለመሆኑን በማጣራት እና በመከለል ለሚመለከተው አካል መረጃ ያስተላልፋል፤

15/ Collects, organizes and analyzes geospatial [illegible] related data used for the land administration [illegible] building; provides information to entities that [illegible] the requirements;

16/ Takes aerial photographs for rural and urban cadastral work, collects, organizes data and uses same

17/ Establishes survey control points used for cadastral work, installs markers or monuments, organizes data, provides necessary protection and supervision to ensure the continual use of the surveying points.

18/ Establishes a system in which enabling to consolidate small and scattered rural land holdings by engaging landholders and creating demand, and implements same when approved by the regional government.

19/ Solves by identifying land-related good governance issues through a consistent and transparent process, expands service and information accessibility through building modern land information management;

20/ Formulates international experiences modernizing the land management system and ensuring its sustainability, conducts research and study, implements same;

21/ Designs operational strategies to prevent irregularities in the land administration system, conduct audits, and takes corrective measures in collaboration with relevant parties;

22/ Transfers information to the relevant body by verifying land that could be used for mining development is not occupied by another party or is not being used for other purposes;

የማዕድን ልማት ሥራ ፈቃድ ላለው አካል ጊዜያዊ የመጠቀም መብት የምስክር ወረቀት ይሰጣል፣ እየተንከባከበ መሆኑን ይከታተላል፣ የማዕድን ልማቱ ሲጠናቀቅ መሬቱ ለሌላ የልማት ሥራ መዋል በሚችልበት ሁኔታ መስተካከሉን በማረጋገጥ ወደ መሬት ባንክ እንዲገባ ያደርጋል፤

23/ የልማት ተነሽ ካሳ ክፍያ አፈጻጸም መመሪያ በሕጉ መሠረት በማዘጋጀት ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ያቀርባል፣ ሲፀድቅ ሥራ ላይ ያውላል፤

24/ በከተሞች ውስጥ እና በከተሞች ወሰን ላይ ሕገ-ወጥ ግንባታ እንዳይፈፀም ከሚመለከተው አካል ጋር ይሠራል፣ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

25/ ለልማት እና ለልዩ ልዩ አገልግሎት የሚውል የከተማ እና የገጠር መሬት መጠን ያጠናል፣ ለመንግሥት ያቀርባል፣ ሲፀድቅ ሥራ ላይ ያውላል፤

26/ የካዳስተር ሕግ እና የመሠረተ ልማት ኔትወርክ ቴክኖሎጂ ሥርዓት ያለማል፣ እንዲለማ ያደርጋል፣ ያዘምናል፣ ያስተዳድራል፤ የካዳስተር ሕግ መረጃዎች ሕጉ በሚፈቅደው መሠረት ለሕዝብ ክፍት እንዲሆን ያደርጋል፤

27/ ለኢንቨስትመንት ፕሮጀክት የሚውል መሬት አጥንቶ ያዘጋጃል፣ ወደ መሬት ባንክ ያስገባል፣ መረጃውን ለኢንዱስትሪ እና ኢንቨስትመንት ቢሮ ይሰጣል፣ በሕግ አግባብ ለተፈቀደለት አካል ያስተላልፋል፣ መሬቱ ለተፈለገው ዓላማ መዋሉን ይከታተላል፣ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፣ እንዲወሰድ ያደርጋል፤

28/ የይዞታ ልዩ ቁጥር ወይም ኮድ ስታንዳርድ ላይ በመመሥረት በካዳስተር ሕግ ለተመዘገበ እና ወሰኑ በግልጽ ለታወቀ ቦታ የባለቤትነት ማረጋገጫ ይሰጣል፤

issues a temporary use right certificate to the entity that has a mining development license, monitors its maintenance, and upon completion of the mining development, makes for transferring to land bank after ensuring the land is adjusted to a condition that can be used for other development activities upon completion of the mining development;

23/ Prepares directive for the implementation of expropriation compensation payments in accordance with law and submits to the Regional Government Council, and implements same upon approval;

24/ Works with the relevant body to prevent; monitor and control illegal construction in cities and on the boundaries of cities;

25/ Studies the amount of urban and rural land to be used for development and various services, submits to the government, and implements it upon approval;

26/ Develops and causes for the development, modernization and management of cadaster law and infrastructure network technology system; makes the cadastral law information available to the public as permitted by law;

27/ Studies and prepares land for investment projects, enters it into the land bank, provides the information to the Industry and Investment Bureau, transfers it to the authorized body according to law, monitors the use of the land for the intended purpose, takes and causes to be taken corrective action in cooperation with the relevant body;

28/ Provides proof of ownership for an area registered under the cadaster law and clearly defined based on a holding unique number or code standard;

29/ የመሬት ይዞታ ባለቤትነት እና የመሬት መረጃ ምዝገባ ሕጎች እና ስታንዳርዶች በክልሉ ውስጥ በተመሳሳይ መልኩ ሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፤

30/ የከተማ እና የገጠር መሬት የባለይዞታነት እና የአገልግሎት ለውጥ ጥያቄ በሕጉ መሠረት ይፈፅማል፣ ለሚመለከተው አካል ያሳውቃል፣ በሥራ ላይ መዋሉን ያረጋግጣል።

## 27. የከተማ እና መሠረተ ልማት ቢሮ

በሌሎች ሕጎች አስቀድሞ የተደነገገው ወይም ወደ ፊት የሚደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ የከተማ እና መሠረተ ልማት ቢሮ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ዝርዝር ሥልጣን እና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1/ የከተማ እና መሠረተ ልማት ተወዳዳሪነትን በቀጣይነት የሚያረጋግጡ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች እና ሕጎችን ያመነጫል፤ ለአፈፃፀሙ ከክልላዊ የልማት አቅጣጫ ጋር የተጣጣመ ዝርዝር መርሃ ግብር ያዘጋጃል፣ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

2/ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን የተቀናጀ የከተማ መሠረተ ልማት መዋቅራዊ እና ማስተር ፕላን ያዘጋጃል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

3/ ከገጠር ወደ ከተማ ለሚሸጋገሩ አካባቢዎች ስታንዳርድ ያወጣል፣ የከተማነት መስፈርት የሚያሟሉ የቀበሌ ማዕከላትን መረጃ ከሚመለከተው አካል ይወስዳል፣ መስፈርት የሚያሟሉትን የከተማነት እውቅና ይሰጣል፣ የልማት ፕሮግራም ይቀርፃል፣ ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፣ ይቆጣጠራል፤

4/ የአከታተም ሥርዓትን በተመለከተ ጥናት ያካሂዳል፤ ዘመናዊ የከተማ ልማት ሥርዓትን እውን ለማድረግ በሚመለከተው አካል የሚዘጋጀውን ፕላን ተግባራዊ ያደርጋል፤

5/ የከተማ ልማት ከገጠር ልማት ጋር በተቀናጀ መንገድ የሚከናወንበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣ የተቀናጀ ድጋፍ ይሰጣል፤



29/ Ensures that landholding ownership and land information registration laws and standards are applied uniformly throughout the region;

30/ Executes requests for changes of holding and use of urban and rural land based on the law; notifies to the relevant body, ensures whether they are implemented.

## 27. Bureau of Urbans and Infrastructure

Without prejudice to the existing or subsequent provision of other laws, the Regional Bureau of Urbans and Infrastructure shall, pursuant to this proclamation, have the following specific powers and duties:

1/ Initiates policies, strategies and laws that sustainably ensuring competitiveness of urban and infrastructure, prepares detailed program for its implementation in line with the regional development direction, and implements it upon approval;

2/ Prepares, in collaboration with the relevant body, a structural and master plan for integrated urban infrastructure, monitors and controls its implementation;

3/ Sets standards for areas transitioning from rural to urban areas, obtains information from the relevant body about kebele centers that meet the criteria for urbanization, recognizes those meet the criteria as urban, designs development programs, implements and monitors them;

4/ Conducts research on the urbanization system; implements the plan to be prepared by concerned body to realize modern urban development system;

5/ Facilitates conditions in which the integration of urban development with rural development, and provides coordinated support;

6/ የተመጣጠነ የከተሞች እድገት እና የሕዝብ አሰፋፈር እንዲኖር ለማድረግ የሚያስችሉ ስልቶችን ይነድፋል፣ ይተገብራል፤

7/ የከተሞችን ፈርጅ ለመወሰን መመዘኛ ያዘጋጃል፤ የከተሞችን ፅዳት፣ ውበት እና አረንጓዴ ልማት ስታንዳርድ ያወጣል፤ የክልሉ ከተሞች ውብ፣ ፅዱ እና አረንጓዴ እንዲሁም ለኑሮ እና ለሥራ ተስማሚ እንዲሆኑ አስፈላጊውን ድጋፍ እና እገዛ ያደርጋል፣ ይቆጣጠራል፤

8/ የመሠረተ ልማት አቅርቦት እና አገልግሎት አሰጣጥ የተቀናጀ እንዲሆን በማድረግ የከተሞችን አገልግሎት አሰጣጥ በማሻሻል መልካም አስተዳደር እንዲያሰፍኑ ያደርጋል፤

9/ ለከተሞች የልማት ፋይናንስ ማጠናከሪያ ሥርዓት ይዘረጋል፣ በሚመለከተው አካል ያስፀድቃል፣ በአፈፃፀሙ ላይ ድጋፍ እና ክትትል ያደርጋል፤

10/ የሪል ስቴት እና ልዩ ልዩ የቤት ልማት አማራጮች ተግባራዊ የሚሆኑበትን ፖሊሲ፣ ስትራቴጂ እና ሕግ ያመነጫል፣ ሲፀድቅም ተግባራዊ መደረጉን ይከታተላል፤

11/ ከተሞች የፖለቲካ፣ የማኅበራዊ እና የኢኮኖሚ ልማት ማዕከልነታቸውን በብቃት እንዲወጡ ለማስቻል ሁለገብ ድጋፍ ይሰጣል፤ የከተማ አሰፋፈር እና የዕድገት አቅጣጫውን ያጠናል፣ ይከታተላል፤

12/ የከተሞችን ፕላን በጠበቀ መልኩ የመሠረተ ልማት አውታሮች የሚስፋፉበትን ዘዴ ይቀይሳል፣ የቅርብ ክትትል እና ድጋፍ ያደርጋል፤ በልማቱም ኅብረተሰቡን ተሳታፊ እንዲሆን የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፤

13/ ከተሞች ከአንድ ደረጃ ወደ ሌላ ደረጃ እንዲሸጋገሩ ለማድረግ የሚያስችል ጥናት ያጠናል፣ መስፈርቱን የሚያሟሉ ከተሞች ሽግግር እንዲፈቀድላቸው ለመስተዳድር ምክር ቤት አቅርቦ ያስወስናል፤

6/ Designs and implements strategies to ensure balanced urban growth and population settlement;

7/ Prepares criteria for determining the classification of urbans, issues standards for the cleanliness, beauty and green development of urbans; provides the necessary support and assistance to ensure that urbans of the region to be beautiful, clean and green, and suitable for living and working;

8/ Makes the prevalence of good governance through improving service delivery of urbans by making provision of infrastructure development and service delivery to be integrated;

9/ Establishes a system for strengthening development finance for urbans, gets approved by relevant body, provides support and followup for its implementation;

10/ Initiates policy, strategy and law for the implementation of real estate and various housing development options, monitors their implementation once approved;

11/ Provides comprehensive support to urbans so as to effectively serve as centers of political, social and economic development, studies and monitors urban settlement and development trends;

12/ Designs, closely monitors and supports the development of infrastructure networks in accordance with urban plans; establishes a system of procedure allowing the community to participate in the development;

13/ Conducts research to enable cities to transform from one level to another, submits it to the Government Council for approval so that urbans that meet the criteria to get transitional permission;

CamScanner

14/ የከተሞችን ልማት ለማፋጠን፣ የአገልግሎት አሰጣጥን ለማሻሻል እና መልካም አስተዳደርን ለማስፈን የሚያግዙ የተለያዩ ጥናቶችን ያካሂዳል፣ እንዲካሄዱ ያደርጋል፣ የአሠራር ስልቶችን ይቀይሳል፤

15/ ከከተሞች ፕላን ጋር የሚጣጣም እና የነዋሪዎችን የገቢ አቅም ያገናዘበ የቤት ልማት አማራጮችን ይለያል፤ የነዋሪዎችን የመኖሪያ ቤት ችግር የሚቀርፍ የቤት ልማት ተግባራዊ እንዲደረግ ለመስተዳድር ምክር ቤት የውሳኔ ሐሳብ ያቀርባል፣ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

16/ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን የግል ሴክተሩን እና የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን አቅም በማሳደግ በከተማ ልማት፣ በሆቴል፣ በመኖሪያ ቤት እና በሪል ስቴት ልማት በንቃት የሚሳተፉበትን ስልት ይቀይሳል፤

17/ በክልሉ መንግሥት እና በከተሞች ባለቤትነት ሥር የሚገኙ ቤቶችን በአግባቡ ለመምራት አግባብ ላላቸው አካላት ተፈላጊውን ቴክኒካዊ እና አስተዳደራዊ ድጋፍ ያደርጋል፤

18/ በክልሉ የሚገኙ ከተሞችን በበላይነት ይመራል፣ ይቆጣጠራል፤

19/ የከተሞችን የምግብ ዋስትና፣ የኑሮ ማሻሻያ እና የድጋፍ ማዕቀፎችን ያስተባብራል፣ ዕቅድ ያዘጋጃል፣ የምግብ ዋስትና እና የሥራ እድል ፈጠራ የማስፈፀም አቅም ይገነባል፣ ተፈፃሚ ያደርጋል፤

20/ በከተሞች የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ እና የሥራ ዕድል ለመፍጠር አስፈላጊ የሆኑ ሥራ የሌላቸውን፣ መሥራት የሚችሉ እና የማይችሉትን ለችግር ተጋላጭ የሆኑ ዜጎችን በጥናት በመለየት መረጃ ይይዛል፣ ያደራጃል፣ ይተነትናል፤

21/ ከተሞች የአገልግሎት እና መሠረተ ልማት የመዘርጋት አቅማቸውን ለማዳበር የሚያስችላቸውን ድጋፍ ያገኙ ዘንድ መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች እና ከሌሎች ድጋፍ ሰጭ አካላት ጋር የሥራ ግንኙነት ያደርጋል፣ ይከታተላል፤

14/ Conducts, causes to be conducted, and designs operational strategies to accelerate urban development, improve service delivery, and promote good governance;

15/ Identifies housing development options consistent with the urban plan and considering income potential of residents; submits recommendation to the Government Council for the implementation of housing development that solves housing problems of residents, implements it upon approval;

16/ In collaboration with the relevant body, develops a strategy to actively participate in urban development, hotel, housing and real estate development by increasing the capacity of the private sector and government development organizations;

17/ Provides the necessary technical and administrative support to the appropriate bodies to properly manage houses owned by the regional government and urbans;

18/ Leads, on top, urbans found in the region, and supervises same;

19/ Coordinates food security of urbans, livelihood improvement and support frameworks; and implements urban food security, livelihood improvement, and support frameworks;

20/ Holds, compiles and analyzes necessary information on the identification of jobless, able and unable to work vulnerable people enabling to ensure food security and job creation in urbans;

21/ Makes work relationships with non-governmental organizations and other supportive bodies to ensure that urbans receive support enabling them to develop their capacity to provide services and infrastructure;

CamScanner

22/ ከተሞች ከሌሎች ሀገሮች ከተሞች ጋር እህትማማችነት እንዲፈጥሩ እና የልማት አቅም እንዲገነቡ ጉዳዩ ከሚመለከተው አካል ጋር ይሠራል፤

23/ ከተሞችን በደረጃ ለመለየት የምዘና እና የውድድር መስፈርቶችን ያዘጋጃል፣ ሥራ ላይ ያውላል።

24/ ዝርዝሩ በመመሪያ የሚወሰን ሆኖ የከተማ ማዘጋጃ ቤቶችን ገቢ ይወስናል፣ ይሰበስባል፣ የሙያ ድጋፍ ይሰጣል፤

## 28. የውኃ እና ኢነርጂ ቢሮ

በሌሎች ሕጎች አስቀድሞ የተደነገገው ወይም ወደ ፊት የሚደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ ውኃ እና ኢነርጂ ቢሮ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ዝርዝር ሥልጣን እና ተግባራት ይኖሩታል፦

1/ ውኃ እና ኢነርጂን የሚመለከት ፖሊሲ፣ ስትራቴጂ እና ሕግ ያመነጫል፤ ለአፈፃፀሙ ከክልላዊ የልማት አቅጣጫዎች ጋር የተጣጣመ ዝርዝር መርሃ ግብር ያዘጋጃል፣ በሚመለከተው አካል ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

2/ የተቀናጀ የውኃ ሀብት አስተዳደርን በተፋሰሶች ውስጥ ተግባራዊ ለማድረግ የሚረዱ የፖሊሲ ጥናቶችን፣ ቅኝቶችን እና ምርምሮችን ያደርጋል፣ ሲፀድቅም ይተገብራል፤

3/ የውኃ አስተዳደር ተግባራትን ለመምራት እና ለመደገፍ የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፤ በተፋሰሶች ውስጥ የሚተገበሩ ከውኃ ጋር የተገናኙ ፕሮጀክቶች ከተቀናጀ የውኃ ኃብት አስተዳደር ጋር የተጣጣሙ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤

4/ የክልሉን የገፀ ምድር እና የከርሰ ምድር የውኃ ሀብት ክምችት እና ስርጭት በማጥናት መረጃዎችን ያደራጃል፤ ይህንኑ ሀብት ዘላቂ እና አስተማማኝ በሆነ መንገድ ጥቅም ላይ ለማዋል የተፋሰሶችን የውኃ ሀብት ስትራቴጂያዊ ዕቅድ ያዘጋጃል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፤



22/ Works with concerning body of the issue to make urbans create sisterhood with urbans of other countries, and build developmental capacity;

23/ Prepares and implements evaluation and competition criteria for classifying urbans in level.

24/ Being the details determined by a directive, it determines and collects urban municipality revenue and provides professional support therefor;

## 28. Bureau of Water and Energy

Without prejudice to the existing or subsequent provisions of other laws, the Regional Bureau of Water and Energy shall, pursuant to this proclamation, have the following specific powers and duties:

1/ Initiates policy, strategy and law related to water and energy, prepares detailed program for its implementation in line with the regional development directions, and implements it upon approval by the relevant body;

2/ Conducts policy studies, surveys and research helping to implement integrated water resources management in river basins, and implements them when approved;

3/ Establishes a system to guide and support water management activities, ensures that water-related projects implemented in basins are consistent with integrated water resources management;

4/ Studies and organizes data on the storage and distribution of surface and groundwater resources in the region; prepares and implements a strategic plan for water resources in the basins to utilize these resources in a sustainable and reliable manner;

5/ የክልሉን ውኃ ሀብት ለማልማት እና ጥቅም ላይ እንዲውል ለማድረግ የፈቃድ አገልግሎት ይሰጣል፣ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፤

6/ በክልሉ በሁሉም አካባቢዎች ፍትሐዊ የውኃ ተቋማት ስርጭት እና አጠቃቀምን ለማስፈን የሚያግዝ ዘላቂ እና የተቀናጀ የውኃ ሀብት አስተዳደር ሥርዓት ይዘረጋል፣ ይተገብራል፤

7/ ለልዩ ልዩ አገልግሎቶች የሚውል ውኃ ሊኖረው የሚገባውን የጥራት ደረጃ ይወስናል፤ የውኃ ብክለት እንዳይኖር ይቆጣጠራል፣ በየጊዜው ክትትል ያደርጋል፤

8/ በክልሉ ውስጥ የሚገኙ የውኃ አካላት እና ተቋማት ከብክለት እና ከአደጋ እንዲጠበቁ ያደርጋል፣ ይቆጣጠራል፤

9/ የንፁህ መጠጥ ውኃ አቅርቦት እና የሳኒቴሽን መሠረተ ልማቶችን ሽፋን ለማሳደግ የግል ዘርፉ ተሳትፎ እና ሚና እንዲጎለብት የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፤ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

10/ በመጠጥ ውኃ እና ሳኒቴሽን ዘርፍ በአገልግሎት ሰጭነት፣ በአማካሪነት፣ በሥራ ተቋራጭነት፣ በምርት እና ዕቃ አቅርቦት የተሠማሩ የግል፣ መንግሥታዊ እና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማትን አቅም ለመገንባት የሚያስችል ድጋፍ ይሰጣል፤

11/ ክልላዊ የመጠጥ ውኃ እና ሳኒቴሽን የጥናት እና ዲዛይን፣ የግንባታ እና የተቋማት አስተዳደር መስፈርቶች፣ ስታንዳርዶች እና ማኑዋሎችን ያዘጋጃል፣ ያሰራጫል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

12/ በፌደራል፣ በክልሉ መንግሥት እና ከውጭ እርዳታ እና ብድር በሚገኝ በጀት የሚሠሩ የመጠጥ ውኃ እና ሳኒቴሽን መሠረተ ልማቶች ግንባታ የጥራት ደረጃቸውን ጠብቀው እንዲከናወኑ ያደርጋል፣ ይከታተላል፤

5/ Provides licensing services making for the development and utilization of the region's water resources, and monitors their implementation;

6/ Establishes and implements sustainable and integrated water resources management system for the prevalence of equitable distribution and utilization of water facilities in all areas of the region;

7/ Determines the quality standards of water used for various services, controls and regularly monitors for the absence of water pollution;

8/ Makes water bodies and institutions found in the region to be protected from pollution and hazards;

9/ Establishes, monitors and controls a system to enhance the participation and role of the private sector to increase the coverage of clean drinking water supply and sanitation infrastructure;

10/ Provides support to build the capacity of private, governmental and non-governmental institutions engaged in drinking water and sanitation sector as service providers, consultants, contractors, and suppliers of products and materials;

11/ Prepares, disseminates, monitors and controls the implementation of regional drinking water and sanitation maintenance and design, construction and institutional management requirements, standards and manuals;

12/ Ensures and monitors the quality of construction of drinking water and sanitation infrastructures funded by the federal government, regional government, and foreign aid and loans;

CamScanner

13/ በፌደራሉ መንግሥት ባለቤትነት በክልሉ ውስጥ የሚካሄዱ የውኃ ልማት ፕሮጀክቶች ውጤታማ እንዲሆኑ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፤

14/ በከተማ እና በገጠር የንፁህ መጠጥ ውኃ አቅርቦት ሽፋንን ለማሳደግ የማሻሻያ እና ማስፋፊያ ጥናት እና ዲዛይን ሥራዎች ያካሂዳል፤ ዲዛይኑ በሚመለከተው ሲፀድቅ ይገነባል፣ ያስገነባል፣ ክትትል እና ቁጥጥር ያደርጋል፤

15/ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን በከተሞች ዘመናዊ የፍሳሽ ቆሻሻ አወጋገድ ስርዓት በመዘርጋት ግንባታዎች እንዲገነቡ ያደርጋል፣ ይከታተላል፤

16/ በክልሉ ለንፁህ መጠጥ ውኃ አቅርቦት የተገነቡ ተቋማት ዘላቂ እና አስተማማኝ አገልግሎት የመስጠት አቅም እንዲኖራቸው ድጋፍ ይሰጣል፤

17/ በክልሉ ፍትሐዊ የውኃ ታሪፍ፣ የሮያልቲ እና የወጭ አመላለስ እና አወሳሰን ሥርዓት ቀርፆ ለመስተዳድር ምክር ቤት ያቀርባል፤ ሲፀድቅ በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤

18/ የክልሉ የውኃ ሀብት እና የተገነቡ የውኃ ተቋማት ዘላቂ እና ተፈላጊውን አገልግሎት እንዲሰጡ የመለስተኛ እና ከፍተኛ ጥገና ያካሂዳል፣ እንዲካሄዱ ያደርጋል፤ የኅብረተሰቡን የባለቤትነት ስሜት ለማሳደግ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠና ይሰጣል፤

19/ ከውኃ ሥራዎች ጋር የተያያዙ ቴክኖሎጅዎች ጥራታቸውን የጠበቁ እና ስታንዳርድ ያሟሉ ስለመሆናቸው ያረጋግጣል፤ አዳዲስ ቴክኖሎጅዎችን በመፈተሽ ወደ ስርጭት እንዲገቡ ፈቃድ ይሰጣል፣ ያበረታታል፤

20/ በክልሉ ወይም በፌደራሉ መንግሥት አካላት የወጡ የውኃ ሀብት አስተዳደር ሕጎች፣ ደንቦች እና መመሪያዎች በክልሉ ውስጥ ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፤



13/ Provides the necessary support to ensure that water development projects as ownership of the federal government undergo in the region to be effective;

14/ Conducts improvement and expansion studies and design works to increase the coverage of clean drinking water supply in urban and rural areas; constructs and causes for the construction the design when is approved by relevant body, and monitors and controls;

15/ In collaboration with relevant body, establishes and monitors the construction of modern sewerage disposal systems in urbans;

16/ Provides support to institutions built for provision of clean drinking water in the region to have the capacity to provide sustainable and reliable services;

17/ Formulates fair water tariff, royalty and expenditure turnover and determination system in the region and submit it to the Government Council; implements same upon approval;

18/ Conducts and causes for the conduction of medium and high maintenance so that water resources of the region and water institutions built provide sustainable and the required services; provides awareness-raising training to increase the sense of ownership of the community;

19/ Ensures that technologies related to water works meet their quality and standard; tests, issues license so that new technologies enter to distribution, encourages;

20/ Ensures that water resources management laws, regulations and directives issued by the regional or federal government bodies to be implemented in the region;

CamScanner

21/ በክልሉ ውስጥ አማራጭ የኢነርጂ ልማት እንዲስፋፋ ጥናት ያካሂዳል፤ እንዲጠና ያደርጋል፤ የግል ባለሀብቶች በስፋት እንዲሳተፉ ያበረታታል፤

22/ የታዳሽ ኢነርጂ ልማት እንዲስፋፋ ለማድረግ ከአነስተኛ እስከ መካከለኛ ያሉ የፀሐይ፣ የነፋስ፣ የጅኦ ተርማል፣ የውኃ እና የባዮ ጋዝ ልማቶችን ያከናውናል፤

23/ አግባብ ካላቸው የፌደራሉ መንግሥት አካላት ጋር በመሆን በክልሉ የኤሌክትሪክ ኃይል ለማመንጨት ይሠራል፤

24/ በገጠር የኢነርጂ አማራጭ ቴክኖሎጅዎች በሠርቶ ማሳያ ሙከራ ተደግፈው እንዲስፋፉ ያደርጋል፤ የኢነርጂ ተጠቃሚዎች እና የቴክኖሎጂ አምራቾች ተደራጅተው የብድር አገልግሎት የሚያገኙበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

25/ የአካባቢ ጥበቃ ሕግ በሚፈቅደው መሠረት በዋጋቸው ተመጣጣኝ የሆኑ የኢነርጂ ምንጮችን እና ቴክኖሎጂዎችን ልማት፣ ስርጭት እና አጠቃቀም ያሳድጋል፤

26/ ዘመናዊ ቴክኖሎጅን በመጠቀም የክልሉን ውኃ እና ኢነርጂ በሚመለከት የመረጃ አደረጃጀትን እና አጠቃቀምን የሚያቀላጥፍ ሥርዓት ይዘረጋል፤ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ያጠናቅራል፣ ይተነትናል፣ ያሰራጫል፤

27/ ውኃ አጠር እና ለድርቅ ተጋላጭ በሆኑ አካባቢዎች የአስቸኳይ ጊዜ ውኃ አቅርቦት እንዲኖር ለማድረግ ይሠራል፤

28/ የገፀ ምድር እና የከርሰ ምድር ውኃ መገኛ ቦታዎችን በጥናት ይለያል፤ በሚመለከተው አካል የባለቤትነት ካርታ እንዲዘጋጅላቸው እና ከሦስተኛ ወገን ነፃ እንዲሆኑ ያደርጋል፤ ጉዳት እንዳይደርስባቸው ጥበቃ እንዲደረግላቸው ያደርጋል፤



21/ Conducts and causes for conduction of studies to promote alternative energy development in the region; encourages private investors to participate widely;

22/ Implements small to medium-sized solar, wind, geothermal, hydro and biogas projects to promote renewable energy development;

23/ Works with appropriate federal government bodies to generate electricity in the region;

24/ Causes for the expansion of alternative energy technologies in rural areas being supported through demonstration experiments; facilitates conditions in which energy users and technology producers being organized get credit facilities;

25/ Promotes the development, distribution and use of affordable energy sources and technologies in accordance with the Environmental Protection Law;

26/ Establishes a system that streamlines the organization and use of information related to water and energy of the region using modern technology; collects, compiles, analyzes and disseminates information;

27/ Works to ensure for the provision of emergency water supply in water scarce and drought-prone areas;

28/ Conducts research to identify surface and groundwater sources; ensures that ownership maps to be prepared by relevant body and to be free from third parties; makes to be protected from damage;

CamScanner

29/ ማንኛውም አካል ሕጋዊ ፈቃድ ሳይኖረው በውኃ እና ኢነርጅ ልማት ሥራ ላይ እንዳይሠማራ፣ ውኃ እንዳይሸጥ እና የውኃ ቆጣሪ እንዳያስገባ ይቆጣጠራል፣ አስፈላጊውን እርምጃ ይወስዳል፣ እንዲወሰድ ያደርጋል፤

30/ የሕዝብን ተጠቃሚነት የሚያረጋግጥ ሆኖ ሲገኝ በማንኛውም ሰው መሬት ወይም ንብረት ላይ የውኃ መስመር ሊዘረጋ፣ የውኃ ጉድጓድ ሊቆፍር ወይም የውኃ ግንባታ ሊያካሂድ ይችላል፤ በዚህ ምክንያት በመሬት ወይም ንብረታቸው ላይ ጉዳት ለደረሰባቸው ባለ ይዞታዎች በሕጉ መሠረት ካሣ ይከፍላል፤

31/ በውኃ ፕሮጀክቶች ላይ ከጥናት ጀምሮ ሕዝብ እንዲሳተፍ ያደርጋል፤ ግንባታቸው የተጠናቀቁ የውኃ መሠረተ ልማቶችን ለተጠቃሚዎች ያስረክባል፣ እንዲያስተዳድሩት ያደርጋል፣ ከተጠቃሚዎች አቅም በላይ ሲሆን የጥገና እና ዕድሳት ሥራ ያከናውናል፤

32/ ተገንብተው አገልግሎት እየሰጡ ያሉ የውኃ፣ የሳኒቴሽን እና የኢነርጂ መሠረተ ልማቶች ጉዳት እንዳይደርስባቸው ክትትል እና ቁጥጥር ያደርጋል፣ ያስደርጋል፤ በሌሎች የልማት ሥራዎች ምክንያት ጉዳት ቢደርስባቸው እና አገልግሎታቸው ቢቋረጥ እንዲጠገኑ፣ እንዲተኩ ያደርጋል፣ ያስደርጋል፤

33/ የንፁሕ መጠጥ ውኃ አቅርቦት እና የሳኒቴሽን አገልግሎትን ለኅብረተሰቡ ተደራሽ ለማድረግ ለውኃ አገልግሎት ተቋማት የብድር አገልግሎት የሚያገኙበትን እና ፈንድ የሚያሰባስቡበትን ሁኔታ ያመቻቻል።

## 29. <u>የማዕድን ቢሮ</u>

በሌሎች ሕጎች አስቀድሞ የተደነገገው ወይም ወደ ፊት የሚደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ የማዕድን ቢሮ የሚከተሉት ዝርዝር ሥልጣን እና ተግባራት ይኖሩታል፦

1/ የሀገሪቱን የማዕድን ሀብት ልማት ፖሊሲዎች፣ ሕጎች እና ስትራቴጂዎች ከክልሉ ተጨባጭ ሁኔታዎች ጋር በማጣጣም ያመነጫል፤ በሚመለከተው አካል ሲፀድቅ ተግባራዊ ያደርጋል፤

29/ Controls, takes and causes to be taken necessar measures to prevent any body from engaging in water and energy development, selling water, or installing water meters without a legal license;

30/ May lay a water line, dig water well, or carry out water construction on the land or property of any person when it is deemed to be public interest, pays compensation to owners of the land or property who have suffered damage as a result of this, in accordance with the law;

31/ Makes for the involvement of the public in water projects from the start of the study; hands over the completed water infrastructures to the users, causes them to manage it, carries out maintenance and renovation work when it is beyond the users' capacity;

32/ Monitors, controls and cuases to be same the water, sanitation and energy infrastructures that are being constructed and providing services not to be damaged; makes to be repaired, replaced or causes same if they are damaged or their services are interrupted due to other development activities;

33/ Facilitates conditions for water service institutions to obtain credit services and raise funds to make clean drinking water supply and sanitation services accessible to the community.

## 29. <u>Bureau of Mines</u>

Without prejudice to what has been previously or may be provided for in other laws, the Regional Mining Bureau shall have the following detailed powers and duties:

1/Initiates the regional mining resource development based on country's policies, laws and strategies in accordance with the actual conditions of the region, implements them upon approval by the relevant body;

CamScanner

2/ በክልሉ ውስጥ የማዕድን ሀብት ልማት እንዲስፋፋ የሥነ ምድር ጥናት እና ምርምር ያካሂዳል፤ በሌሎች እንዲካሄድ ያደርጋል፤ በነዚሁ ጥናቶች አማካኝነት የክልሉን ዕምቅ የማዕድን ሀብቶች በዓይነት፣ በመጠን እና በጥራት ይለያል፤

3/ የኮንስትራክሽን ዘርፍ ልማትን የግብዓት እና የማጠናተቂያ ቁሶች ፍላጎትን በአገር ውስጥ የማዕድን ሀብት እንዲሟሉ ይሠራል፤

4/ ለዘመናዊ ግብርና፣ ለአምራች ኢንዱስትሪ፣ ለዲጅታል ቴክኖሎጅ፣ ለኬሚካል ኢንዱስትሪ ልማት በግብዓትነት የሚያገለግሉ ማዕድናትን ይፈልጋል፣ ያስፈልጋል፤

5/ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን በማዕድን ዘርፉ ዘላቂ ማኅበረሰባዊ፣ ክልላዊ እና ሀገራዊ ተጠቃሚነት እንዲረጋገጥ ይሠራል፤

6/ በሰለጠነ የሰው ኃይል፣ በጥናት እና ምርምር፣ በዘመናዊ የማዕድን ፍለጋ ላቦራቶሪ እና ቴክኖሎጂ የተጠናከረ የማዕድን ተቋማዊ አቅም እንዲሁም አገር በቀል የማዕድን ኢንዱስትሪ እንዲገነባ ይሠራል፤

7/ ስትራቴጂያዊ ጠቀሜታ ላላቸው ማዕድናት ቅድሚያ በመስጠት የማዕድን ዘርፍ ልማት ለክልሉ ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት መነሻ የሚሆን መሠረታዊ የሥነ ምድር ካርታ በማዘጋጀት ማዕድናትን በዓይነት፣ በጥራት፣ በሽፋን እና በክምችት መጠን ይለያል፣ ያስለያል፤ ጥራት ያለው የማዕድን አለኝታ መረጃ ይሰበስባል፣ እንዲጠናከር ይሠራል፤

8/ በዘርፉ ልማት ተስተካካይነትን ለማረጋገጥ የክልሉን የመልከዓ ምድር ሁኔታ፣ የመሠረተ ልማት እና የማዕድናት ዓይነትን መሠረት ያደረገ ዘመናዊ የማዕድን ፍለጋ ቴክኖሎጂ ጥቅም ላይ እንዲውል ይሠራል፣

2/ Conducts geological study and research to promote the development of mineral resources in the region, causes to be conducted by others; identifies the potential mineral resources of the region in terms of type, quantity and quality based on these studies;

3/ Works for the fulfillment of demand of inputs and finishing materials of the construction sector development with domestic mining resource;

4/ Explores and causes to be explored minerals used as inputs for modern agriculture, manufacturing industry, digital technology and chemical industry development;

5/ Works with relevant parties to ensure sustainable social, regional, and national benefits in the mining sector;

6/ Works to build a strong mining institutional capacity and indigenous mining industry through skilled manpower, study and research, and modern mining search laboratories and technology;

7/ Identifies and causes for the identification of minerals by type, quality, coverage and deposit amount by preparing basic geological map serving as mining sector development to be basis for social and economic growth of the region through prioritizing minings of strategic importance; collects and works for strengthening quality mineral resource data;

8/ Works for modern mining exploration technology to be utilized based on the regional geographical conditions, infrastructure and mineral types to ensure competitiveness of the sector development;

CamScanner

9/ የማዕድን ፍለጋ ሥራዎችን ለማከናወን የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፤ በግሉ ዘርፍ፣ በመንግሥት እና በምርምር ተቋማት መካከል ጥምረት በመፍጠር በጋራ ለመሥራት የሚያስችሉ ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥራል፤

10/ ለዘመናዊ የማዕድን ሀብት ልማት የሚመጥን የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፣ ውጤታማነቱን ይከታተላል፤

11/ የዘርፉን ውጤታማነት የሚያሳድግ ተፈፃሚ እና ችግርን በወቅቱ መፍታት የሚያስችል የክትትል እና ግምገማ ሥርዓት ይዘረጋል፤

12/ ቴክኖሎጂን በመጠቀም የሥነ ምድር ጥናት እና የማዕድን ልማት ሥራዎችን የሚመለከቱ መረጃዎችን ይሰበስባል፤ የጂኦ ስፓሻ ካርታ ያዘጋጃል፣ ይተነትናል፣ ያደራጃል፣ ለተጠቃሚዎች ያሰራጫል፤

13/ የማዕድን ጥናት እና ፍለጋ ለማፋጠን የሚያግዙ የቤተ ሙከራ እና የማዕድን ጥራት ማረጋገጫ ማዕከላትን ያደራጃል፣ እንደ አስፈላጊነቱ በዘርፉ የሚሠማሩ አካላት እንዲደራጁ ድጋፍ ያደርጋል፤

14/ በባሕላዊ፣ በአነስተኛ፣ በልዩ አነስተኛ እና በከፍተኛ ደረጃ የሚካሄድን የማዕድን ሀብት ፍለጋ ፈቃድ ይሰጣል፣ ያግዳል፣ ያድሣል፣ ይሰርዛል፤

15/ በባሕላዊ እና በአነስተኛ ደረጃ የሚመረቱ ማዕድናት ምርት እና ግብይት ሕጋዊ መስመር እንዲይዝ ሥርዓት ይዘረጋል፤

16/ ባሕላዊ የማዕድን ማምረት ሥራዎችን በማጠናከር በክልሉ ውስጥ ዜጐች ተደራጅተው ማምረት የሚችሉበትን የሥራ ዕድል ይለያል፤ ለተደራጁ እንዲያመርቱ ፈቃድ ይሰጣል፣ ይቆጣጠራል፤

17/ ዝርዝሩ በመስተዳድር ምክር ቤቱ በሚወጣ መመሪያ የሚወሰን ሆኖ ከማዕድን ሥራዎች የሚገኝን የሮያሊቲ እና የመሬት ኪራይ ክፍያዎች ይሰበስባል፣ ገቢውን ለሚመለከተው አካል ያስተላልፋል፤



9/ Establishes a system enabling to conduct mineral exploration activities; creates favorable environment enabling to work collaborately among the private sector, government, and research institutions;

10/ Establishes a system of operations suitable for modern mineral resource development, implements, and monitors for its effectiveness;

11/ Establishes a monitoring and evaluation system that enhances the efficiency of the sector and enables timely resolution of problems;

12/ Collects data related to geological research and mineral development activities using technology; prepares, analyzes and organizes geo-spatial map, and distribute to users;

13/ Organizes laboratories and mineral quality assurance centers helping to accelerate mineral study and exploration, and provides support to the organization of entities engaged in the sector as necessary;

14/ Grants, suspends, renews, and cancels licenses for traditional, small-scale, ultra-small-scale, and large-scale mineral resource exploration;

15/ Establishes a system to ensure that the production and trade of traditional and small-scale minerals to be legal;

16/ Identifies job opportunities for citizens to organize and produce in the region by strengthening traditional mining operations; grants licenses to those who are organized and controls them;

17/ Details being determined by a directive to be issued by the Government Council, collects royalties and land rents from mining operations, and transfers the income to the relevant body;

18/ የሥነ ምድር የቅድመ አደጋ ስልቶችን እና የማዕድን የልማት ቀጠና ያጠናል፣ ይተነትናል፣ መረጃ ይሰጣል፤

19/ በሕገ ወጥ መንገድ የሚከናወን ማናቸውም የማዕድናት ፍለጋ እንዳይካሄድ አስፈላጊውን ሥርዓት ይዘረጋል፣ ይቆጣጠራል፤

20/ የማዕድን ፍለጋ ሥራ በሚከናወንበት አካባቢ የአካባቢውን ኅብረተሰብ ተጠቃሚነት የሚያረጋግጥ ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፣ የሕግ ማዕቀፍ ያመነጫል፣ በሚመለከተው አካል ሲፀድቅም በአግባቡ መፈፀማቸውን ይከታተላል፤ በአካባቢ ጥበቃ የተቀመጡ መስፈርቶች መሟላታቸውን ያረጋግጣል፤

21/ በማዕድን ሀብት ጥበቃ እና አጠቃቀም ዙሪያ ለማዕድን ሥራ ባለፈቃዶች፣ ለማዕድን ግብይት ተዋናዮች እና የተፈጥሮ ሀብቱ ባለቤት ለሆኑ የኅብረተሰብ ክፍሎች ሥልጠና እና ሙያዊ የምክር አገልግሎቶችን ይሰጣል፤

22/ በክልሉ የሚካሄዱ የማዕድን ፍለጋ እና ጥናት ፕሮጀክቶች ለማዕድን ዘርፉ ዕድገት የሚያስፈልገውን የእውቀት፣ የክህሎት እና የቴክኖሎጂ ሽግግር እንዲያመጡ ይሠራል፤

23/ የክልሉን የማዕድን ሥራዎች አማካሪ ምክር ቤት እንዲቋቋም ያደርጋል፤

24/ የፌዴራል መንግሥት ሥልጣን የሆኑ የማዕድን ልማት ሥራዎችን በተመለከተ ከሚመለከተው የሚኒስቴር መሥሪያ ቤት ውክልና ሲሰጠው ተግባራዊ ያደርጋል፤

25/ የማሽን፣ የግብዓት፣ የኃይል ምንጭ እና የኦቶሜሽን ሥርዓትን ከጫፍ እስከ ጫፍ ለማስተሳሰር የኢንዱስትሪ እና ቴክኖሎጂ ስትራቴጂን በማዕድን ሀብት ልማት ለመደገፍ ይሠራል።



18/ Study, analyze, and provide information on geological hazard prevention strategies and mineral development zones;

19/ Establish and controls the necessary system to prevent any illegal mineral exploration;

20/ Create a conducive environment in the area where mining activities are carried out to ensure the benefit of the local community, develops a legal framework, monitors its proper implementation after approval by the relevant body, and ensure that environmental protection requirements are met;

21/ Provide training and professional advisory services to mining licensees, mining market players and natural resource owners in the field of mineral resource protection and utilization;

22/ Work to ensure that mineral exploration and research projects conducted in the region bring about the transfer of knowledge, skills and technology needed for the development of the mining sector;

23/ Establish a regional advisory council for mining operations;

24/ Implement the delegation of the relevant ministry regarding mining development activities that are the responsibility of the federal government;

25/ Work to support the industrial and technological strategy for the development of mineral resources by integrating machinery, resources, energy sources and automation systems from end to end.

## 30. የመንገድ፣ ትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ ቢሮ

## 30. Bureau of Roads, Transport and Logistics

በሌሎች ሕጎች አስቀድሞ የተደነገገው ወይም ወደ ፊት የሚደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ የመንገድ፣ ትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ ቢሮ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ዝርዝር ሥልጣን እና ተግባራት ይኖሩታል፦

Without prejudice to what has been previously or may be provided for in other laws, the Regional Roads, Transport and Logistics Bureau shall have the following detailed powers and duties under this Proclamation:

1/ የመንገድ ዘርፉን ውጤታማነት እና ተወዳዳሪነትን በቀጣይነት የሚያረጋግጥ ቴክኖሎጂ ጥቅም ላይ ያውላል፤ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችን፣ ፕሮግራሞችን እና ሕጎችን ያመነጫል፤ ለአፈፃፀሙ ከክልሉ የልማት አቅጣጫዎች ጋር የተጣጣመ ዝርዝር መርሃ ግብር ያዘጋጃል፤ በሚመለከተው አካል ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

1/ Implements technology to continuously ensure the efficiency and competitiveness of the road sector; initiates policies, strategies, programs and laws; prepares detailed program for its implementation in line with the development directions of the region, and implements it when approved by the relevant body;

2/ ቴክኖሎጂን በመጠቀም ቅልጥፍና እና ምርታማነትን ባማከለ መልኩ በክልሉ የሚገኙ መንገዶችን ያለማል፣ ይጠግናል፣ እንዲጠገን ያደርጋል፣ ያስተዳድራል፤

2/ Builds, maintains and manages roads found in the region in a manner that focuses on efficiency and productivity using thechnolgy;

3/ የመንገድ ልማት እና ጥገናን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ከሚመለከታቸው የፌዴራል እና የክልል ተቋማት ጋር በመተባበር በጋራ ይሠራል፤

3/ Work in collaboration with relevant federal and regional institutions on issues related to road development and maintenance;

4/ የተቀናጀ ክልላዊ የመንገድ አውታር ዕቅድ ያዘጋጃል፤ በቴክኖሎጂ የተደገፈ ክልላዊ የመንገድ ሀብት አስተዳደር መረጃ ሥርዓት እንዲኖር ይሠራል፤ የክልሉን የመንገድ አውታር እና የመንገድ ሁኔታ መረጃ አደራጅቶ ይይዛል፣ መረጃውን ለሚመለከተው አካል ያስተላልፋል፤

4/ Prepares an integrated regional road network plan; works to establish a technology-supported regional road resource management information system; organizes and maintains information on the regional road network and road conditions; and transmit the information to the relevant body;

5/ በክልሉ ውስጥ መንገዶችን ለማስፋፋት፣ ለመንከባከብ እና ደረጃ ለማሻሻል የመንገድ ልማት ዕቅዶችን እና ፕሮግራሞችን ያዘጋጃል፤

5/ Prepares road development plans and programs to expand, treat and improve the quality of roads in the region;

6/ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን ለመንገድ ሥራ እና ለአማካሪ አገልግሎቶች ውል ያዘጋጃል፣ ይዋዋላል፤ ሥራው በውሉ መሠረት መፈፀሙን ይከታተላል ወይም ክትትል እንዲደረግ ያደርጋል፤

6/ Prepares and enters into contracts for road works and consultancy services in collaboration with relevant body; monitors the execution of the work in accordance with the contract or cause it to be monitored;

CS CamScanner

7/ ለመንገድ ሥራዎች የሚያስፈልጉ የዲዛይን ዝግጅት፣ የአዋጭነት ጥናት፣ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ እና ሌሎች ተዛማጅ ጥናቶች ያዘጋጃል፣ እንዲዘጋጁ ያደርጋል፤

8/ አግባብነት ያላቸውን የክልሉ መንግሥት የግዥ እና ንብረት አስተዳደር መመሪያዎችን መሠረት በማድረግ የመንገድ ዲዛይኖችን ከሚሠሩ ወይም የቁጥጥር እና ተዛማጅ አገልግሎቶችን ከሚሰጡ አማካሪ ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች ጋር ስምምነቶችን ያደርጋል፤

9/ የመንገድ ግንባታ እና ጥገና ጥራትን ለመቆጣጠር የሚያስችል ቴክኖሎጂ ጥቅም ላይ ያውላል፣ ይቆጣጠራል፣ ተገቢውን ክትትል ያደርጋል፤

10/ በክልሉ ውስጥ ያሉ የፌደራል የመንገድ ፕሮጀክቶች የዕቅድ ዝግጅት እና ትግበራ ላይ ከፌዴራል መንግሥት ሀብት አስተዳደር ጋር በጋራ ይሠራል፤

11/ በክልሉ ውስጥ በፌዴራል መንግሥት የገንዘብ ድጋፍ የሚገነቡ የመንገድ ፕሮጀክቶችን አፈፃፀም ውጤታማ እንዲሆን ትብብር ያደርጋል፤ ወቅታዊ ሪፖርት እና መረጃዎችን ለፌደራል መንገዶች አስተዳደር ያቀርባል፤

12/ በማኅበረሰብ ተሳትፎ እና በወረዳ በጀት ለሚገነቡ እና ለሚጠገኑ መንገዶች የቴክኒካል እና ሌሎች የማቴሪያል ድጋፍ ያደርጋል፤

13/ የመንገድ ጥናት እና ምርምር ያካሂዳል ወይም እንዲካሄድ ያደርጋል፤ እንዲሁም ለመንገድ ዘርፍ የሚፈለገውን የሰው ኃይል አቅም ይገነባል፤

14/ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን የክልሉ መንገዶችን ወሰን እና የግንባታ ማቴሪያል መገኛ ቦታዎችን ይለያል፤

15/ መንገዶችን ከአደጋ እና ተገቢ ካልሆኑ አገልግሎቶች ይከላከላል፤ በመንገድ ላይ የሚገኙ ለትራፊክ እንቅስቃሴ አስቸጋሪ የሆኑ ነገሮችን ያስወግዳል ወይም እንዲወገዱ ያደርጋል፤

7/ Prepares and cause to be prepared the design preparation, feasibility study, environmental impact assessment and other related studies required for road works;

8/ Enters into agreements with individuals or organizations that design roads or provide inspection and related services in accordance with relevant procurement and property management directives of the regional government;

9/ Implements technology enabling to monitor quality of road construction and maintenance, controls, and conducts the appropriate monitoring;

10/ Works with the federal government property management on the planning and implementation of federal road projects found in the region;

11/ Cooperates in the effective implementation of road projects in the region; and submits timely reports and information to the Federal Roads Management;

12/ Provides technical and other material support for roads constructed and maintained by community participation and wereda budget;

13/ Conducts or causes to be conducted road studies and research; and builds capacity of human resource required for the road sector;

14/ In collaboration with the relevant body, identifies boundaries of the regional roads and locations of construction materials;

15/ Protects roads from damages and inappropriate services; removes or causes to be removed objects on the road that hinder traffic movement;

16/ በክልል እና በፌደራል መንግሥት ለሚገነቡ የመንገድ ሥራዎች አገልግሎት የሚውል እንደ ካምፕ፣ ቢሮ፣ መጋዘን እና ሌሎች ተዛማጅ አገልግሎቶች የሚውሉ ከክፍያ ነፃ የሆነ ቦታ እና የግንባታ ማቴሪያል መገኛ ቦታ ያመቻቻል፤ የግለሰብ ይዞታ ከሆነ ለመሬቱ እና በመሬቱ ላይ ለሚገኙ ንብረቶች በካሣ ሕጉ መሠረት ክፍያ ይፈፅማል፤

17/ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በሕጉ መሠረት ተገቢውን ካሣ በወቅቱ እንዲከፈል በማድረግ ለመንገድ ሥራ የሚፈለግን መሬት ከሦስተኛ ወገን ነፃ ያደርጋል፤

18/ በመንገድ ላይ ጉዳት የሚያደርሱ እንቅፋቶችን ወይም እንደ ነዳጅ፣ ዘይት ነክ ፈሳሾችን በመንገዶች ላይ በሚደፉ ግለሰቦች እና ድርጅቶች ላይ ሕጋዊ እርምጃ ይወስዳል፣ ያስወስዳል፤

19/ የመንገድ ሥራዎች በሚከናወኑበት ጊዜ አካባቢን ከብክለት እና ጉዳት ለመጠበቅ በአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን የተቀመጡ መስፈርቶች እንዲሟሉ ያደርጋል፤ አስፈላጊ የሆኑ የማሻሻያ ተግባራትን ይተገብራል፤

20/ በክልሉ ውስጥ የሚገኙ መንገዶች ላይ የትራፊክ መቆጣጠሪያ ምልክቶችን ወይም መሣሪያዎችን ንድፍ በማዘጋጀት አስፈላጊ በሆኑ የገጠር መንገዶች ላይ ያኖራል ወይም እንዲተከሉ ያደርጋል፤

21/ በጋራ አገልግሎት እንዲውል በየትኛውም አካል ኃላፊነት የተገነባ እና የተጠገነ ማናቸውም መንገድ ደረጃውን ጠብቆ መሠራቱን ሲያረጋግጥ መንገዱን ተረክቦ ያስተዳድራል፤

22/ ለመንገድ ግንባታ እና ጥገና አገልግሎት የሚውሉ ማሽኖች እና መሣሪያዎች ከብክነት እና ጉዳት ጠብቆ ውጤታማ በሆነ አግባብ ለመጠቀም የሚያስችል የአጠቃቀም እና አስተዳደር ሥርዓት መመሪያዎችን ያዘጋጃል፣ በተግባር ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፤



16/ Facilitates free space for construction materials and construction sites such as camps, offices, warehouses and other related services for road works constructed by the regional and federal governments; makes compensation for the land and assets on the land in accordance with the compensation law if it is privately owned;

17/ In cooperation with the relevant parties, expropriates land required for road works from third parties by ensuring appropriate compensation to be timely paid in accordance with the law;

18/ Takes and causes to be taken legal actions against individuals and organizations that cause obstacle to roads or spill liquids such as fuel and oil on roads;

19/ Makes the requirements set by the Environmental Protection Authority to be met to protect an environment from pollution and damage during road works; implements necessary improvement measures;

20/ Prepares designs for traffic control signs or devices on roads within the region and installs or causes them to be installed on necessary rural roads;

21/ Takes over and manages any road constructed and maintained by any body to be commonly used, after ensuring it is constructed meeting the required standard;

22/ Prepares and implements directives for the use and management of machinery and equipment used for road construction and maintenance enabling to use effectively and efficiently, avoiding waste and damage;

CamScanner

23/ ከፌደራል፣ ከክልል እና ሌሎች አጋር አካላት የሚገኙ ሀብቶችን በአግባቡ በመጠቀም የመንገድ ልማት ደኅንነቱ የተረጋገጠ፣ ቀልጣፋ፣ አስተማማኝ፣ ፍትሐዊ እና ተደራሽ እንዲሆን ለማድረግ የሚያስችሉ ተግባራትን ያከናውናል፣ እንዲከናወኑ ያደርጋል፣ ያስተባብራል፣ ይቆጣጠራል፤

23/ Carries out, causes to be carried out, coordinates and supervises activities to ensure that road development is safe, efficient, reliable, equitable and accessible by properly utilizing resources from federal, regional and other partner bodies;

24/ በሕጉ መሠረት ለአካል ጉዳተኞች፣ ለአረጋውያን እና አቅመ ደካሞች ምቹ የሆኑ መንገዶች እንዲስፋፉ ያደርጋል፣ አተገባበሩ ላይ ክትትል እና ቁጥጥር ያደርጋል፣

24/ Makes for the expansion of roads suitable for the disabled, elderly and infirmity in accordance with the law, and monitors and supervises on the implementation;

25/ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን ለመንገድ አገልግሎት የሚውሉ የተለያዩ የግንባታ ማቴሪያሎችን ለግንባታ ከመዋላቸው በፊት ጥራታቸውን በተመለከተ በቴክኖሎጂ የተደገፈ የብቃት እና የጥራት ፍተሻ ያደርጋል፣ ያስደርጋል፤

25/ In collaboration with the relevant body, conducts and causes to be conduct technology-based quality and competency testing of various construction materials used for road construction before they are used for construction;

26/ የራስን ኃይል በመጠቀም የመንገድ ግንባታ እና ጥገና ሥራዎች በማከናወን ቅልጥፍና እና ምርታማነት እንዲያድግ ይሠራል፤

26/ Works to increase efficiency and productivity by using own energy in carrying out road construction and maintenance works;

27/ የትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ ዘርፍ ልማትን እና ተወዳዳሪነትን በቀጣይነት የሚያረጋግጥ ፖሊሲ፣ ሕግ፣ ስትራቴጂ፣ እና ፕሮግራም ያመነጫል፣ ሲፀድቅለትም ተግባራዊ ያደርጋል፤

27/ Initiates policy, law, strategy, and program ensuring the continuous development and competitiveness of the transport and logistics sector, and implements same upon approval;

28/ የትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ አገልግሎቶችን ለመምራት እና ለመቆጣጠር በክልል እና በፌደራሉ መንግሥት የወጡ አዋጆች፣ ደንቦች እና መመሪያዎች በክልሉ ውስጥ መከበራቸውን ያረጋግጣል፤

28/ Ensures that the proclamations, regulations and directives issued by the regional and federal governments to guide and regulate transport and logistics services are implemented in the region;

29/ የክልሉን የልማት ስትራቴጂዎች ተግባራዊ ለማድረግ የልማት ማዕከላትን እና የዕድገት ኮሪደሮችን የትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ ፍላጎት ለማሟላት የየብስ እና የባሕር ትራንስፖርት አገልግሎቶች የተቀናጁ፣ ቀልጣፋ እና ተደራሽ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤

29/ Ensures that land and sea transport services are coordinated, efficient and accessible to meet the transport and logistics needs of development centers and growth corridors for the implementation of the regional development strategies;

30/ የትራንስፖርት መገልገያ ቴክኖሎጅዎችን ያጠናል፤ ስታንዳርድ ያዘጋጃል፤ ይመዝናል፤ ጥያቄ ሲቀርብለትም የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤

31/ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን ሀገራዊ እና ክልላዊ የትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ ውሕደት እና መናበብ እንዲፈጠር ሥርዓት ይዘረጋል፤ ለአፈፃፀሙ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፤

32/ በትራንስፖርት እና ሎጅስቲክስ ልማት ዘርፍ የግል ዘርፉን ተሳትፎ እና ሚና በማሳደግ በክልሉ ውስጥ የብዙኃን የትራንስፖርት አገልግሎት እንዲስፋፋ ይሠራል፣ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፤

33/ የክልሉን የተቀናጀ የትራንስፖርት እና ሎጅስቲክስ መሠረተ ልማቶች ማስተር ፕላን ያዘጋጃል፣ ተግባራዊ መደረጋቸውን ይከታተላል፤

34/ የትራንስፖርት መገልገያዎችን በተመለከተ የግዥ ሰነዶችን ያዘጋጃል፤ ስለ አያያዝ፣ አጠቃቀም እና አወጋገዳቸው የቴክኒክ ድጋፎችን ይሰጣል፤

35/ ባለሞተር ተሽከርካሪዎች እና ጀልባዎችን ይመዘግባል፤ ብቃት እና ደኅንነታቸውን ያረጋግጣል፣ ደረጃ ያወጣል፤ ለተለያዩ አሽከርካሪዎች፣ ኦፕሬተሮች እና ካፒቴኖች የመንጃ ፈቃድ ይሰጣል፣ ያድሳል፣ ያግዳል፣ ይሰርዛል፤

36/ የትራንስፖርት እና ሎጅስቲክስ አገልግሎት አሰጣጥ የደኅንነት ደረጃዎችን ያዘጋጃል፣ ተግባራዊ እንዲደረጉ ያደርጋል፤

37/ ያገለገሉ ተሽከርካሪዎችን የዋጋ ግምት ይሠራል፤ የተሽከርካሪዎችን ስመ ንብረት ዝውውር እና ምዝገባ ያከናውናል፤ ቦሎ ይሰጣል፣ እንደ አስፈላጊነቱ በውክልና ያሠራል፣ ያድሳል፤

38/ በትራንስፖርት እና ሎጅስቲክስ ዘርፍ ላይ በክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች መካከል ትብብር እንዲጎለብት ያደርጋል፤ የትብብር ስምምነት ያደርጋል፣ ተግባራዊ እንዲሆን ይሠራል፤



30/ Studies transport service technologies, prepares standards, evaluates, and issues certificates of competency upon request;

31/ Establishes a system for integration and coordination of national and regional transportation and logistics being collaborated with relevant body; creates conducive environment for its implementation;

32/ Works to expand mass transportation services in the region by increasing the participation and role of the private sector in the development of transportation and logistics, and provides the necessary support;

33/ Prepares the regional integrated transport and logistics infrastructure master plan, and monitors their implementation;

34/ Prepares procurement documents related to transport facilities; provides technical support for their management, use and disposal;

35/ Registers motor vehicles and boats; ensures their suitability and safety, sets standards; issues, renews, suspends and cancels driving licenses for various drivers, operators and captains;

36/ Prepares and ensures the implementation of safety standards for the provision of transport and logistics services;

37/ Appraises used vehicles; carries out title transferring and registeration of vehicles; issues bolo and, as necessary, makes the work through delegation;

38/ Makes for the enhancement of cooperation between regions and city administrations in the transport and logistics sector; concludes cooperation agreements, and implement them;

CamScanner

39/ የክልሉን የመንገድ ደኅንነት ፈንድ ያቋቁማል፣ ጥቅም ላይ እንዲውል ያደርጋል፤

40/ ለክልሉ ጠቀሜታ ያላቸውን አማራጭ የደረቅ ወደብ አገልግሎቶች አያጠና ለክልሉ መንግሥት ያቀርባል፤ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

41/ በከተሞች ውስጥ ዘመናዊ እና ደኅንነቱ የተጠበቀ የፓርኪንግ አገልግሎት እንዲስፋፋ ይሠራል፤ በጥናት ላይ ተመሥርቶ የአገልግሎት ገቢ ይወስናል፣ ይሰበስባል፤

42/ በክልሉ በሁሉም አካባቢዎች በቂ የትራንስፖርት አገልግሎት ሽፋን እና የስምሪት ተደራሽነት እንዲኖር ያደርጋል፤

43/ የትራንስፖርት እና ሎጅስቲክስ መሠረተ ልማቶች አስተማማኝ እና ደኅንነታቸው የተረጋገጠ እንዲሆኑ የቁጥጥር ሥርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፤

44/ በትራንስፖርት እና ሎጅስቲክስ ዘርፉ ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎች እና የአሠራር ሥርዓቶች ይዘረጋል፤ መረጃዎችን ያደራጃል፣ ጥቅም ላይ ያውላል፣ ያሰራጫል፤

45/ ለከተማ እና ለሕዝብ ትራንስፖርት ማኅበራት የሥራ ፈቃድ ይሰጣል፣ ያድሳል፣ ይሰርዛል፤

46/ የትራንስፖርት አገልግሎት ታሪፍ፣ ጣሪያ እና ወለል በጥናት ላይ ተመሥርቶ ይወስናል፤ በሂደት በገበያ ውድድር እንዲመራ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

47/ የትራንስፖርት እና ሎጅስቲክስ መሠረተ ልማቶች እና አገልግሎቶች በአካባቢ እና በአየር ንብረት የሚኖራቸውን አሉታዊ ተፅዕኖ ለመቀነስ የሚያስችሉ ስልቶችን ይነድፋል፣ ሥራ ላይ ያውላል፤

48/ የትራንስፖርት አስተዳደር ሥርዓትን ለማሻሻል የሚያስችል ጥናት ያደርጋል፤ መረጃዎችን በማጠናቀር ይይዛል፣ ጥቅም ላይ ያውላል፤

39/ Establishes and ensures the utilization of the Regional Road Safety Fund;

40/ Studies alternative dry port services of beneficial to the region and presents same to the regional government; implements them when approved, and monitors its implementation;

41/ Works for the expansion of modern and safe parking services in urbans; determines and collects service revenue based on studies;

42/ Ensures adequate transportation service coverage and accessibility in all areas of the region;

43/ Establishes and implements a regulatory system to ensure transport and logistics infrastructures to be reliable and safe;

44/ Establishes modern technologies and operating systems in the transport and logistics sector; organizes, utilizes, and disseminates information;

45/ Grants, renews, and revokes operating licenses for urban and public transport associations;

46/ Determines the transportation service tariff, ceiling and baseline based on research; facilitates conditions for it to be gradually led by market competition, and monitors its implementation;

47/ Designs and implements strategies to reduce negative impact of transportation and logistics infrastructure and services on an environment and climate;

48/ Conducts a research enabling to improve the transport management system; maintains by compiling data, and utilizes them;

CS CamScanner

49/ ከአጎራባች ክልሎች ጋር መልካም የሆነ የሥራ ግንኙነት በመፍጠር የሕዝብ እና የጭነት ትራንስፖርት ተሽከርካሪዎችን ያሠማራል፤ ይቆጣጠራል፤

49/ Operates and controls public and freight transport vehicles by creating good working relations with neighboring regions;

50/ በክልሉ ውስጥ ለሚቋቋሙ የትራንስፖርት መገልገያ አምራቾች፣ የተሽከርካሪ ልዩ ልዩ ቴክኖሎጂ አስመጭዎች፣ የአካል ለውጥ ለሚያከናውኑ የተሽከርካሪ ጋራዦች የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፣ ያድሳል፣ ይሰርዛል፤

50/ Issues, renews, and revokes professional qualification assurance certificates for transport equipment manufacturers, various vehicle technology importers, and vehicle modification garages to be established in the region;

51/ የትራንስፖርት እና የሎጂስቲክስ መሠረተ ልማቶችን በግል፣ በመንግሥት ወይም በጋራ እንዲቋቋሙ እና እንዲለሙ ያደርጋል፤ ስታንዳርዶችን ያወጣል፣ የአገልግሎት አሰጣጡን ይመራል፣ ይቆጣጠራል፤

51/ Causes for the development of transport and logistics infrastructures whether privately, in public, or jointly; sets standards, directs and controls the service provision;

52/ በክልሉ ውስጥ በመደበኛው የትራንስፖርት አገልግሎት የማይሸፈን እና አስገዳጅ ሁኔታ ሲከሰት ችግሩ እስከሚፈታ የመንግሥትን፣ የድርጅቶችንም ሆነ የግለሰብ ተሽከርካሪዎችን በጊዜያዊነት ያሠማራል፣ ለዝርዝር አፈፃፀሙ መመሪያ ያወጣል፤

52/ In the event of an emergency situation that is not covered by the regular transport service in the region, temporarily deploys government, organization and private vehicles until the problem is resolved; and issues a directive for its detailed implementation;

53/ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን የምርት ግብዓቶች በተቀናጀ መንገድ ለአርሶ አደሩ እንዲደርሱ እና ምርቶችም በወቅቱ ለገበያ እንዲቀርቡ ይሠራል፣ የቀዝቃዛ ጭነት ትራንስፖርት እና የማቆያ መጋዘኖች እንዲስፋፉ ያደርጋል፤

53/ In collaboration with the relevant body, works to ensure that production inputs reach to farmers in a coordinated manner and products are marketed on time, and makes cold-cargo transport and storage facilities to be expanded;

54/ የሞተር አልባ እንቅስቃሴን ለማስፋፋት የእግረኛ፣ የሳይክል እና የእንስሳት የትራንስፖርት ዘዴዎች የሚስፋፉበትን የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፣ ያበረታታል፣ ክትትል እና ድጋፍ ያደርጋል፤

54/ Establish, encourages, monitors and supports a system for the expansion of pedestrian, bicycle and animal transport methods in order to promote non-motorized movement;

55/ ለአሽከርካሪ፣ ለልዩ ማሽነሪዎች እና ለትራንስፖርት ቴክኒሽያን ማሠልጠኛ ተቋማት እና ለተሽከርካሪ ምርመራ ማዕከላት የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፣ ያድሳል፣ ይሰርዛል፤

55/ Issues, renews, and revokes professional qualification assurance certificates for drivers, special machinery and transport technician training institutions and vehicle inspection centers;

CamScanner

56/ የተሽከርካሪ ሰሌዳዎችን ያትማል፣ ያሰራጫል፣ ያስተዳድራል፤ የጠፋ ሰሌዳ ይተካል፣ የሰሌዳ ለውጥ ያደርጋል፣ ሰሌዳ ለሌላቸው ተሽከርካሪዎች ለአንድ ጉዞ ብቻ የሚያገለግል የመሸኛ ወረቀት ይሰጣል፤

57/ በሕግ ከተሰጡት ተግባራት እና ኃላፊነቶች የሚመነጭ የአገልግሎት ክፍያዎችን ይሰበስባል፤

58/ የተሽከርካሪ ባለንብረቶች የሦስተኛ ወገን መድኅን ሽፋን እንዲገቡ ያደርጋል፣ ፈቃዳቸውን እንዲያድሱ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል።

## 31. የሥራ እና ክህሎት ቢሮ

በሌሎች ሕጎች አስቀድሞ የተደነገገው ወይም ወደ ፊት የሚደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ የሥራ እና ክህሎት ቢሮ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ዝርዝር ሥልጣን እና ተግባራት ይኖሩታል፦

1/ የሥራ፣ የሥራ ስምሪት እና የሰው ሀብት ልማት ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች እና ሕጎችን ያመነጫል፤ ለአፈፃፀሙ ከክልላዊ የልማት አቅጣጫ ጋር የተጣጣመ ዝርዝር መርሃ ግብር ያዘጋጃል፣ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

2/ የቴክኒክ እና ሙያ ሥልጠና ከክልሉ እና ከሀገራዊ የልማት ፖሊሲ እና ከሥራ፣ ከሥራ ስምሪት እና የሰው ሀብት ልማት ፍላጎት ጋር በተጣጣመ መልኩ ለማከናወን የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

3/ የቴክኒክ እና ሙያ ሥልጠና ደረጃዎችን እና የሥርዓተ ሥልጠና ማዕቀፍ ይቀርፃል፤ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

4/ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን በቴክኒክ እና ሙያ ሥልጠና ተቋማት እና በዘርፎቹ መካከል ለሥራ ገበያ፣ ለስምሪት እና ለሰው ሀብት ልማቱ የሚያግዝ ምቹ ትስስር እንዲፈጠር ያደርጋል፤



56/ Prints, distributes and manages vehicle plates; replaces lost plates, changes plates, issues a single-trip ticket to vehicles without plates;

57/ Collects service fees arising from the duties and responsibilities assigned to it by law;

58/ Ensures that vehicle an owner has third-party insurance coverage, monitors and controls the renewal of their licenses.

## 31. Bureau of Labour and Skills

Without prejudice to what has been previously or may be provided for in other laws, the Regional Bureau of Labour and Skills shall have the following detailed powers and duties under this Proclamation:

1/ Initiates policy, strategy and laws for work, labour employment and human resource development; prepares a detailed program for its implementation in line with the regional development direction, and implements it upon approval;

2/ Establishes a system enabling to implement technical and vocational training in line with the regional and national development policy and needs of labour, labour employment and human resource development, and monitors its implementation;

3/ Formulates technical and vocational training standards and training frameworks; implements them when approved, and monitors their implementation;

4/ In collaboration with the relevant body, creates favorable linkages between technical and vocational training institutions and their sectors that contribute to the labor market, employment, and human resource development;

CamScanner

5/ ብቁ እና ተወዳዳሪ የሆነ የሰው ሀብት ለማልማት እና የዘመናዊ ቴክኖሎጂ አጠቃቀም ውጤታማነትን ለማሻሻል የሚረዱ የማሰልጠኛ ማዕከላትን ያቋቁማል፤ ያስተዳድራል፤

6/ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን ቀልጣፋ እና ፍትሐዊ የሥራ ዕድል እና ስምሪት አገልግሎት እንዲኖር ሥርዓት ይዘረጋል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

7/ ክልላዊ፣ ሀገራዊና አለም አቀፍ የሥራ ገበያ መረጃ ሥርዓት በመዘርጋት የሥራ ፈላጊዎችን መረጃ ይይዛል፣ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤ የሥራ ቀጣሪ ድርጅቶች እንዲሁም ሌሎች የቁልፍ የሥራ ገበያ መረጃ አመላካቾችን መረጃ ይመዘግባል፤ ያደራጃል፤ ይተነትናል ለተጠቃሚ አካላት ያሰራጫል፤

8/ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን መደበኛ ያልሆነውን የኢኮኖሚ ዘርፍ ወደ መደበኛ ኢኮኖሚ ለማሸጋገር የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

9/ የሥራ ዕድል ፈጠራ ሥራዎችን በበላይነት ያስተባብራል፣ ይከታተላል፤ ከሚመለከተው አካል ሪፖርት እንዲቀርብለት ያደርጋል፤

10/ በሥራ ገበያ ላይ የሚታዩ የክህሎት ክፍተቶችን በጥናት ይለያል፣ በግኝቱ መሠረት የአቅም ግንባታ ሥልጠና ይሰጣል፤

11/ የሙያ ዘርፎች ከሥራ ገበያ ፍላጎቶች ጋር እንዲጣጣሙ ይሠራል፤ ለሥራ ፈጣሪዎች እና ፈላጊዎች የሥራ ፈጣሪነት ክህሎት ሥልጠና እና ድጋፍ ይሰጣል፤

12/ የቅድመ ብድር እና የአዲስና የነባር ኢንተርፕራይዞችን ቁጠባ ያስተባብራል፤ ለነባርና አዲስ የጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በማሽነሪ ሊዝ እና በጥሬ ገንዘብ ብድር ከሚያቀርቡ የፋይናንስ ተቋማት በኩል የብድር አገልግሎት እንዲመቻች ያደርጋል፤ የብድር ውጤታማነትና አመላለሱን ይከታታላል፣ በቅንጅት ይሠራል፤

5/ Establishes and manages training centers that help to develop qualified and competitive human resource and improve the effectiveness of the use of modern technology;

6/ Develops a system for the existence of efficient and equitable job opportunity and employment services in collaboration with the relevant body, monitors its implementation;

7/ Maintains information of job seekers by establishing a regional, national and international labor market information system; provides certificate for such; records, organizes and analyzes information on employment agencies and other key labor market indicators; disseminates same to user entities;

8/ Develops a system of operations to transform the informal economy into formal economy in collaboration with the relevant body, and monitors its implementation;

9/ Coordinates and monitors ontop of job creation activities; and requests reports from relevant body;

10/ Identifies skill gaps in the labor market through research and provides capacity building training based on the findings;

11/ Works to align vocational sectors with labor market needs; provides training and support for entrepreneurs and job seekers in entrepreneurial skills;

12/ Coordinates pre-financing and savings for new and existing enterprises; facilitates credit services for existing and new micro and small enterprises through financial institutions that provide machinery lease and cash loans; monitors the effectiveness and turnover of credit, and works in coordination;

CS CamScanner

13/ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን ሴቶች ወይም አካል ጉዳተኞች የተለየ የክህሎት ሥልጠና እንዲያገኙ ያመቻቻል፤

14/ ክልላዊ የሥራ ዕድል ፈጠራ ሥራዎች እንዲበረታቱ የሚያደርግ የማበረታቻ ሥርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤

15/ በክልሉ በቅጥር ላይ የተመሠረተ ፍትሐዊ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ የሀገር ውስጥ እና የውጭ ሀገር የሥራ ሥምሪት አገልግሎቶች እንዲሰጡ ለሀገር ውስጥ እና ለውጭ ሀገር የግል ሥራ እና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎች ፈቃድ ይሰጣል፣ ይሰርዛል፤ በሕጉ መሠረት እንዲሠሩ ይቆጣጠራል፤

16/ ለሴቶች፣ ለስደት ተመላሾች፣ ለጎዳና ተዳዳሪዎች እና አካል ጉዳተኞች የሥራ እድል እንዲፈጠር ያደርጋል፣ ይከታተላል፣ ያስተባብራል፣ ይደግፋል፤

17/ በሥራ ዕድል ፈጠራ እና በጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት እና ተወዳዳሪነት ላይ እንቅፋት የሆኑ ጉዳዮችን በመለየት በወቅቱ መፍትሔ እንዲያገኙ ያደርጋል፤

18/ በዘርፉ የተሠማሩ ኢንተርፕራይዞች በቂ የማምረቻ እና የመሸጫ ቦታዎች እንዲያገኙ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ተቀናጅቶ ይሠራል፣ የተገነቡ ሸዶችን ያስተዳድራል፣ ለተጠቃሚዎችም ያስተላልፋል፤

19/ የጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በየዘርፎቻቸው በማኅበር እንዲደራጁ ይደግፋል፤ የገበያ ክፍተት በማጥናት የዉጭና የሀገር ዉስጥ ገበያ ትስስር እንዲፈጠርላቸዉ ያደርጋል፤ ምርትና አገልግሎቶቻቸዉ ወደ ዲጂታል ግብይት እንዲገባ የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፣ ይተገበራል፣ ተወዳዳሪነታዉን ያጠናክራል፤

13/ In collaboration with the relevant body, facilitates access to specialized skills training for women or persons with disabilities;

14/ Establishes an incentive system to encourage regional job creation activities, and monitors its implementation;

15/ Provides and revokes licenses for local and foreign private employment and labor liaison agencies so that fair, efficient and effective employment-based domestic and foreign employment services to be given in the region, and supervises their operation in accordance with the law;

16/ Causes for job creation to women, migration returnees, street dwellers and people with disabilities; monitors, coordinates, and supports;

17/ Identiies and addresses issues that hinder job creation and development and competitiveness of micro and small enterprises;

18/ Works being coordinated with relevant stakeholders to ensure that enterprises engaged in the sector have adequate production and sale space; manages the developed shades, and transfer it to users;

19/ Supports the organization of micro and small enterprises in their respective sectors through associations; studies market gaps and creates connections between foreign and domestic markets; develops and implement a system for their products and service in order to enter to digital commerce, and strengthens their competitiveness;

CamScanner

20/ የጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን የዕድገት ደረጃን መሠረት ያደረገ የሥልጠና እና የተሟላ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን የድጋፍ አገልግሎቶችን እንዲያገኙ በማድረግ ከደረጃ ደረጃ እንዲሸጋገሩ ያደርጋል፤ ለሚሸጋገሩትም የእዉቅና የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤ ወደ ታዳጊ መካከለኛ የሚሸጋገሩትን ለሚመለከተዉ ተቋም ያስረክባል፡፡

21/ የጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የሒሳብ አያያዝ እና የኦዲት አገልግሎት በራሱም ሆነ በሌሎች አማራጮች እንዲያገኙ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፤

22/ የጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ምርትና አገልግሎት ለገበያ እና ለተጠቃሚዎች ተደራሽ ለማድረግ፣ እርስ በርስ እንዲደጋገፉ ሀገራዊ እና ዓለም አቀፋዊ ተወዳዳሪነታቸውን የሚያሳድጉ ከባቢያዊና ክልላዊ የንግድ ትርዒትና ኤግዚቢሽኖችን፣ ባዛሮችን እና ፌስቲቫሎችን እንዲዘጋጁ ያስተባብራል፣ ያዘጋጃል፡፡

23/ የተለያዩ መገናኛ ዘዴዎችን በመጠቀም የቴክኒክ እና ሙያም ሆነ የጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ስትራቴጅን ለኅብረተሰቡ በስፋት የማስተዋወቅ እና የግንዛቤ ፈጠራ ሥራዎችን ያከናውናል፤

24/ የሞዴል ቴክኒክ እና ሙያ ኮሌጆችን እንዲሁም የጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን ምርጥ ተሞክሮዎች ያጠናል፣ ይቀምራል፣ ያስፋፋል፤

25/ በቴክኒክ እና ሙያ፣ በጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ስትራቴጂ መሠረት ኢንተርፕራይዞችን ይደግፋል፤ የደረጃ ሽግግር የሚያካሂዱ ኢንተርፕራይዞችን ለይቶ እንዲሸጋገሩ ያደርጋል፣ የእውቅና የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤

26/ በክልሉ ውስጥ ለሚንቀሳቀሱ የመንግሥት፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና የግል ፖሊ ቴክኒክም ሆነ የቴክኒክ እና ሙያ ማሠልጠኛ ኮሌጆች እንዲሁም የአጫጭር ሥልጠና መስጫ እና የክህሎት ማሳደጊያ ማዕከላት እውቅና ፈቃድ ይሰጣል፤ ከደረጃ በታች ሆነው ሲገኙ እውቅና ፈቃዳቸውን ይሰርዛል፤



20/ Transfers micro and small enterprises from level to level based on their development level by providing training and comprehensive industrial extension support services; provides recognition and certificates to those which are transferred; handsover those which transferred to emereging-medium enterprises to the relevant institution.

21/ Provides the necessary support to micro and small enterprises to obtain accounting and audit services, either on its own or through other options;

22/ Coordinates and organizes local and regional trade fairs and exhibitions, bazaars and festivals to make products and services of micro and small enterprises accessible to the market and consumers, to support each other, and to enhance their national and international competitiveness.

23/ Conducts activities to widely promote and create awareness of technical and vocational as well as micro and small enterprises development strategies to the public using various means of communication;

24/ Studies, formulates and expands best practices of model technical and vocational colleges as well as micro and small enterprises;

25/ Supports enterprises in accordance with the technical and vocational, micro and small enterprises development strategy; identifies and transfer enterprises undergoing level transferring, and issues recognition and certificates;

26/ Provides recognition license to government, non-governmental organizations and private polytechnics as well as technical and vocational training colleges, as well as short-term training and skill development centers operating in the region; revokes their license when they are found to be below standard;

CamScanner

27/ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን የመንግሥት ቴክኒክ እና ሙያ ኮሌጆች ውጤታማ የቴክኒክ እና ሙያ ትምህርት እና ሥልጠና ለመስጠት ያስችላቸው ዘንድ የውስጥ ገቢ አሰባሰብ እና አጠቃቀም ሥርዓት ይዘረጋል፤ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤

28/ የቴክኖሎጂ ምርምር፣ የፍተሻ ቤት ሙከራ፣ የኢንዱስትሪ አሠራሮች እና ተሞክሮዎች ማስተዋወቂያ እና የምክር አገልግሎት መስጫ ማዕከላትን ያቋቁማል፤

29/ ለጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን የማስተዋወቅ፣ የኬሚካል ትንተና፣ የልኬታ፣ የመካኒካል ሙከራ፣ የብረታ ብረት እና መሰል ሙያዊ የምክር አገልግሎት ይሰጣል፤

30/ የክልሉ ቴክኒክ እና ሙያ፣ የሥራ እድል ፈጠራ እና ጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ምክር ቤት እንዲቋቋም ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣ የምክር ቤቱ ሴክሬታሪያት ሆኖ ያገለግላል፤

31/ የሥራ ባሕል እና የምርታማነት ግንባታን በማጎልበት የቤተሰብና የማኅበረሰብ ቢዝነስን ያደራጃል፤ የንግድ ፈጠራ ሐሳብ ያበረታታል፣ ይደግፋል፤

32/ በከተማና በገጠር የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን ዉጤታማነት የሚያሻሽሉ የአንድ ማዕከላት አገልግሎት መስጫ ማዕላትን ያቋቁማል፣ ያጠናክራል፤ ዘመናዊ አሠራር ይዘረጋል፣ ያስተዳድራል፤

33/ በግብርና፣ በኢንዱስትሪ እና በአገልግሎት ዘርፎች ውስጥ በሥራ ሊሠማራ የሚችለውን የሰው ሀብት በጥራት ይለያል፤ ኢኮኖሚው በሚፈልገው መንገድ ብቁ እና በቴክኖሎጂ ተወዳዳሪ እንዲሆን የክህሎት ማሳደጊያ ሥልጠና ይሰጣል፣ ውጤታማነቱን ይከታተላል፤

27/ Being with the relevant body, establishes a system for collecting and utilizing internal revenue for the government technical and vocational colleges enabling them provide effective technical and vocational education and training, and monitors its implementation;

28/ Establishes centers for technological research, testing laboratories, industrial practices and experiences promotion and advisory service provision;

29/ Provides advisory services for the promotion of new technologies, chemical analysis, measurement, mechanical testing, metallurgy and similar professional services to micro and small enterprises;

30/ Facilitates conditions for the establishment of the Regional Council for Technical and Vocational Training, Job Creation and Micro and Small Enterprise Development, and serves as the Council's secretariat.

31/ Organizes family and community businesses through enhancing work culture and productivity building; encourages and supports business innovation ideas;

32/ Establishes and strengthens one-stop service centers that improve the efficiency of micro and small enterprises in urban and rural areas; develops and manages modern procedures;

33/ Clearly identifies human resources that can be engaged in agriculture, industry and service sectors; provides skills development training to make the economy competent and technologically competitive in the way it needs, and monitors its effectiveness;

CamScanner

34/ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ሕጎች በትክክል ሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

35/ ሠራተኛ በሥራ ላይ እያለ የሚከሠትበትን አደጋ እና በሥራ ምክንያት የሚመጣ በሽታን ለመከላከል የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፤ የሙያ ጤንነት እና ደኅንነት እንዲጠበቅ ያደርጋል፣ ይቆጣጠራል፤

36/ የኢንዱስትሪ ሰላም ለማስጠበቅ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊነቱንም ያረጋግጣል፤

37/ አሠሪዎች እና ሠራተኞች በማኅበር የመደራጀት እና የኅብረት ድርድር የማድረግ መብቶቻቸውን እንዲጠቀሙ ያበረታታል፣ ይደግፋል፤ በክልሉ የሚደራጁ የሠራተኛ እና የአሠሪ ማኅበራትን ይመዘግባል፤

38/ በአሠሪዎች እና በሠራተኞች መካከል የሁለትዮሽ እና የመንግሥት ወገንን ጨምሮ የሦስትዮሽ ውይይት እንዲደረግ ያደርጋል፤ የሥራ ክርክሮችን ክስተት ለመቀነስ ስልቶችን ይቀይሳል፤ ለሥራ ክርክሮችም የተቀላጠፈ የውሳኔ መስጫ ሥርዓት ይዘረጋል፣ ያስፈፅማል፤

39/ ዘመናዊ የአሠሪ እና ሠራተኛ፣ ክልላዊ፣ ሀገራዊ እና ዓለም አቀፋዊ የሥራ ገበያ የመረጃ ሥርዓት በመዘርጋት የሥራ ፈላጊዎችን መረጃ ይይዛል፤ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፣ ክፍት የሥራ መደቦችን መረጃ ይመዘግባል።

## 32. የገንዘብ ቢሮ

በሌሎች ሕጎች አስቀድሞ የተደነገገው ወይም ወደ ፊት የሚደነገገው እንደ ተጠበቀ ሆኖ የክልሉ ገንዘብ ቢሮ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ዝርዝር ሥልጣን እና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1/ የክልሉ የኢኮኖሚ ዕድገት እና ልማት ዘላቂ እና የተረጋጋ እንዲሆን የሚያስችሉ የፊሲካል ፖሊሲ እና ስልት ያመነጫል፣ ሥራ ላይ ያውላል፣ አፈፃፀማቸውን ይከታተላል፤



34/ Monitors and supervises the proper implementation of labour and employment laws;

35/ Establishes a system of procedures to prevent accidents and occupational diseases that may occur to workers while at work; ensures and supervises occupational health and safety;

36/ Establishes a system to maintain industrial peace and ensures its implementation;

37/ Encourages and supports employers and employees to exercise their rights of getting organized in association and collectively bargaining; registers labor and employers' associations organized in the region;

38/ Makes bilateral dialogue between employers and employees and tripartite dialogue including the government; devises strategies to reduce the incidence of labor disputes, and establishes and causes implementation of expeditious decision-making system for labor disputes;

39/ Maintains information of job seekers by establishing a modern employer-employee, regional, national and international labor market information system; issues certificate, and records information on vacant positions.

## 32. Bureau of Finance

Without prejudice to what has been previously or may be provided for in other laws, the Regional Finance Bureau shall have the following detailed powers and duties under this Proclamation:

1/ Initiates, implements and monitors fiscal policy and strategy enabling to the sustainability and stability of the regional economic growth and development;

CamScanner

2/ የግብር እና ታክስ ሕጎችን፣ ደንቦችን እና መመሪያዎችን ማውጣት ወይም በሥራ ላይ ያሉትን ማሻሻል ሲያስፈልግ ጥናቶችን ያካሂዳል፤ ረቂቅ እንዲዘጋጅ ያደርጋል፣ ይህንኑ ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት አቅርቦ ያስፀድቃል፤

3/ የክልሉ መንግሥት በየጊዜው ለሚያወጣቸው የታክስ እና የግብር ሕጎች መሠረት የሚሆኑ የፖሊሲ ማዕቀፎችን ይቀርፃል፤ ሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣ እንደ አስፈላጊነቱም የማሻሻያ ሐሳቦችን ያመነጫል፤

4/ የክልሉ ፋይናንስ፣ ግዥ እና ንብረት አስተዳደር የሚመራበትን ሥርዓት ይዘረጋል፤ በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

5/ በክልሉ እና በፌደራሉ መንግሥት መካከል የሚደረገውን የፋይናንስ እና የፊሲካል ግንኙነት ሥራዎችን ይመራል፣ ያስተባብራል፤ በሁለቱ መካከል የተጣጣመ አሠራር መዘርጋቱን ያረጋግጣል፤

6/ የክልሉ ዓመታዊ የበጀት ዝግጅት የሚመራበትን ፊሲካል ማዕቀፍ ያዘጋጃል፣ በተግባር ያውላል፣ ይከታተላል፤

7/ በክልሉ መንግሥት ተቋማት እየተዘጋጀ የሚቀርብለትን የመደበኛ እና የካፒታል በጀት ጥያቄ ተቀብሎ የመንግሥት ተቋማትን ዓመታዊ በጀት ያዘጋጃል፤ በመስተዳድር ምክር ቤት ያስፀድቃል፣ የተፈቀደውን ያስተዳድራል፤

8/ በክልሉ ምክር ቤት እና በመስተዳድር ምክር ቤት አማካኝነት በፀደቀው የበጀት መደልደያ ቀመር መሠረት ለወረዳዎች፣ ለከተማ አስተዳደሮች እና ለብሔረሰብ አስተዳደር ዞኖች በጀት ይደለድላል፤

9/ የክልሉን የተጠቃለለ ፈንድ ይይዛል፣ ያስተዳድራል፤ የክልሉን የፋይናንስ ክንውን እና የገንዘብ ይዞታ የሚያሳይ ጠቅላላ መግለጫ በየወቅቱ እያዘጋጀ ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ያቀርባል፤ የክልሉን ዓመታዊ የገቢ እና የወጭ ሒሳብ ሪፖርት በወቅቱ በማዘጋጀት ለኦዲት ተግባር ምቹ ያደርጋል፤

2/ Conducts studies, prepares drafts, and submits them to the Regional Government Council for approval when necessary to enact tax laws, regulations, and directives or to amend the existing ones;

3/ Formulates policy frameworks which would be foundation of tax and custom laws to be issued periodically by the regional government; monitors their implementation, and proposes amendments as deemed as necessary;

4/ Devises a system to adminster financial, procurement and property management of the region; causes its implementation, and monitors the implementation;

5/ Directs and coordinates the financial and fiscal relations between the Region and the Federal Government; and ensures the establishment of harmonization procedure of the two;

6/ Prepares, implements, and monitors the fiscal framework that preparation of the annual budget of the region to be administered;

7/ Prepares the annual budget of government institutions by receiving the regular and capital budget requests submitted by the regional government institutions; gets approved same by the Government Council, and administers the approved budget;

8/ Allocats budget to weredas, city administrations and nationality administration zones in accordance with the budget allocation formula approved by the Region Council and the Government Council;

9/ Holds and administers consolidated funds of the region; submits general report showing the region's finance performance and holding by periodically preparing same to the regional government council; makes favorable to auditing by preparing the region's annual revenue and expenditure report on time;

CamScanner

10/ ከሀገር ውስጥ እና ከውጭ የሚገኙ ዕርዳታዎችን፣ ብድሮችን እና ፕሮጀክቶችን አስመልክቶ የሚደረጉ ስምምነቶችን በክልሉ መንግሥት ስም ይፈራረማል፤ አፈፃፀማቸውን ይከታተላል፣ ኦዲት ያደርጋል፣ በሌላ አካል ኦዲት እንዲደረግ ያደርጋል፤ የፕሮግራሙ ጊዜ ቆይታ ሲጠናቀቅ የሥራ እና የንብረት ርክክብ እና ማስተላለፍ ሥራ ያከናውናል፤

11/ ከሌሎች የፌዴራል መንግሥት አካላት እና መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች የሚገኝ ሀብት እና ንብረትን ይከታተላል፤ አጠቃላይ ወደ ክልሉ የሚገቡ ሀብቶችን በበላይነት ይመራል፣ ያስተዳድራል፣ ይቆጣጠራል፤

12/ ዘመናዊ የመንግሥት ግዥ፣ የንብረት ማስወገድ አገልግሎቶች፣ የሀብት አስተዳደር እና አጠቃቀም ሥርዓት ይዘረጋል፤ ከሚመለከተው አካል ተለይተው የሚሰጡትን የግዥ እና ንብረት ማስወገድ የአገልግሎት ጥያቄዎች ላይ ተገቢውን ምላሽ ይሰጣል፤ አፈፃፀሙን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

13/ በማንኛውም አግባብ የክልሉ መንግሥት ንብረት የሆነ እና ማንኛውም በክልሉ ውስጥ የሚገኝ ባለቤት አልባ የሆነ ንብረትን በመንግሥት ንብረትነት ይይዛል፣ ያስተዳድራል፤

14/ በክልሉ ባሉ የመንግሥት ተቋማት የውስጥ ኦዲት ቁጥጥር ሥርዓት ይዘረጋል፤ አፈፃፀሙን ይከታተላል፣ የውስጥ ኦዲት ሥርዓቱን በበላይነት ይመራል፤ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን ተጠያቂነትን ያረጋግጣል፤

15/ የክልሉን ልማት ለመደገፍ እና ለማጠናከር ከተለያዩ የእርዳታ እና ድጋፍ ሰጭ አካላት ጋር በመሆን የተለያዩ ሀብቶች ወደ ክልሉ እንዲፈሱ ያደርጋል፤ ፍትሐዊ ስርጭቱን እና ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣ ይቆጣጠራል፤

10/ Signs agreements on behalf of the regional government regarding domestic and foreign grants, loans and projects; monitors their implementation, conducts audits, and have them to be audited by another body; carries out handover and transfer of work and assets upon completion of the program period;

11/ Monitors resources and assets obtained from other federal government entities and non-governmental organizations; leads, manages, and controls on top of all resources entering to the region;

12/ Establishes a modern government procurement, asset disposal services, and asset management and utilization system; responds appropriately to requests for procurement and asset disposal services provided separately from relevant entity; monitors and controls their implementation;

13/ Hold and administer any property owned by the regional state in any case and ownerless property found in the region as state property;

14/ Establishes an internal auditing control system in government institutions in the region; monitors its implementation, and oversees the internal audit system; ensures accountability in collaboration with the relevant body;

15/ In collaboration with various aid and supporting bodies, ensures that various resources flow into the region in order to support and strengthen the development of the region; facilitates and monitors their equitable distribution and conditions;

CamScanner

16/ የክልሉ ሕዝብ በጥሬ ገንዘብ፣ በቁሳቁስ፣ በእውቀቱ እና በጉልበቱ አስተዋፅኦ እንዲያበረክት እና የልማት ሥራዎችን በፋይናንስ መደገፍ የሚችልበትን ሥርዓት ይዘረጋል፤ በበላይነት ያስተባብራል፣ ውጤታማነቱን ይከታተላል፤

17/ የመንግሥት ተቋማትን ፍላጎት መሠረት በማድረግ ገቢ የሚሰበሰብበትን ደረሰኝ ያሳትማል፤ ለሚመለከተው አካል ያሰራጫል፣ ከአገልግሎት ውጭ የሆኑትን ይሰበስባል፣ ይቆጣጠራል፤

18/ የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን ፕራይቬታይዝ ለማድረግ የሚስፈልጉ ሰነዶችን ያዘጋጃል፤ ከሚመለከታቸው የመንግሥት ተቋማት ጋር በመቀናጀት የፕራይቬታይዜሽን ሒደቱን ያስተባብራል።

## 33. የገቢዎች ቢሮ

በሌሎች ሕጎች አስቀድሞ የተደነገገው ወይም ወደ ፊት የሚደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ ገቢዎች ቢሮ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ዝርዝር ሥልጣን እና ተግባራት ይኖሩታል፦

1/ በክልሉ ውስጥ የታክስ ሕጎችን፣ ደንቦችን እና መመሪያዎችን ያስከብራል፣ ያስፈፅማል፤

2/ በሕግ ተለይተው እንዲሰበሰቡ የተመደቡትን እና የፌደራሉ መንግሥት በሚሰጠው ውክልና መሠረት በክልሉ መንግሥት እውቅና የፌደራሉን እና የጋራ ገቢዎችን ይወስናል፣ ይሰበስባል፤

3/ በክልሉ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ላይ ተመሥርቶ ጥናቶችን በማካሄድ ክልሉ ያለውን የገቢ መሠረት ለማስፋት እና ገቢ የመሰብሰብ አቅሙን ለማሳደግ ይሠራል፤

4/ በግብር አስተዳደሩ ውስጥ የሚከሰቱ ችግሮችን በማጥናት እንዲፈቱ ያደርጋል፤

16/ Establishes a system whereby people of the region can contribute in cash, materials, knowledge and force and financially support development projects; coordinates ontop and monitors its effectiveness;

17/ Publishes receipts for revenue collection based on needs of government institutions; distributes them to the relevant parties, collects and controls those that are not in service;

18/ Prepares documents required for the privatization of government development enterprises; coordinates the privatization process in coordination with the relevant government institutions.

## 33. Bureau of Revenues

Without prejudice to the existing or subsequent provision of other laws, the Regional Bureau of Revenues shall, pursuant to this proclamation, have the following specific powers and duties:

1/ Causes the enforcement and implementation of tax laws, regulations and directives in the region;

2/ Determines and collects the federal and common revenues based on deligation of the federal government assigned to be collected identified by law with the recognition of the regional government;

3/ Works to expand the region's revenue base and increase its revenue collection capacity by conducting research based on the economic activities of the region;

4/ Makes problems araised from the tax administration to be solved through study;

CamScanner

5/ በክልሉ ውስጥ የሚካሄዱ የታክስ ሥርዓት ማሻሻያ ፕሮግራሞችን አፈፃፀም በባለቤትነት ይመራል፣ ያስተባብራል፤

6/ የታክስ ሕጎችን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ በማናቸውም ግለሰብ ወይም ድርጅት እጅ የሚገኙ ሰነዶችን ይመረምራል፣ ይይዛል፤

7/ ግብር ከፋዩ ኅብረተሰብ መብት እና ግዴታውን በመረዳት የሚፈለገበትን ታክስ በወቅቱ የመክፈል ባሕል እንዲያዳብር የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎችን ይሠራል፣ ውጤታማነቱን ይከታተላል፤

8/ ለታክስ አስተዳደሩ ብቃት ያላቸውን ባለሙያዎች ለማፍራት የሚያስችለውን የሥልጠና እና የሙያ ማሻሻያ ስልት ይቀይሳል፣ በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤

9/ በክልሉ ውስጥ ዘመናዊ የታክስ እና የግብር አወሳሰን እና አሰባሰብ ሥርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ያደርጋል፤ በመስኩ የግልፅነት እና የተጠያቂነት መርሆችን መሠረት በማድረግ ፍትሐዊ፣ ቀልጣፋ እና ጥራት ያለው አገልግሎት ይሰጣል፤ ግብር ወይም ታክስ-ነክ መብቶች እንዲከበሩ ያደርጋል፣ ያስደርጋል፤

10/ በከተማ አስተዳደሮች ሥልጣን ሥር የሚሸፈኑ የአገልግሎት ገቢዎችን ይወስናል፣ ይሰበስባል፣ የሙያ ድጋፍ ይሰጣል፤

11/ ለግብር እና ታክስ አወሳሰን የሚያስፈልጉትን መረጃዎች ያሰባስባል፣ ያጠናቅራል፤ እነዚህኑ በመጠቀም ግብር እና ታክሶችን ይወስናል፣ ይሰበስባል፤



5/ Leads in the sense of ownership and coordinates implementation of the ongoing tax system reform program in the region;

6/ Examines and retains documents in the possession of any individual or organization required for the enforcement of tax laws;

7/ Conducts awareness-raising activities and monitors their effectiveness so that the taxpayer society can develop a culture of paying the required taxes on time, understanding their rights and obligations;

8/ Devise and implement training and professional improvement strategies enabling to produce qualified professionals administration;

9/ Establishes and implements a modern tax and custom determination and collection system in the region; provides fair, efficient and quality services based on the principles of transparency and accountability in the field; ensures that custom or tax-related rights to be respected;

10/ Determines and collects service revenues under the jurisdiction of city administrations and provides technical support therefor;

11/ Collects and compiles information required for the determination of custom and tax; determines custom and tax using same;

CamScanner

12/ የታክስ ሕጎችን በመጣስ የሚፈፀሙ ወንጀሎችን ይመረምራል፤ ይከሳል፤ ይከራከራል፤ ይህንኑ ለማከናወን የራሱን የታክስ ወንጀል መርማሪዎች እና ዐቃቢያነ ሕግ ያደራጃል፤ አፈፃፀማቸውን ይቆጣጠራል፤

13/ ለግብር ከፋዩ ኅብረተሰብ አማራጭ የታክስ መክፈያ ተቋማትን ያመቻቻል፤

14/ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን የታክስ ወይም የግብር ግዴታቸውን ያልተወጡ የግብር ወይም የታክስ ከፋዮችን ንብረት በሕግ መሠረት ያስከብራል፤ ያስይዛል፤ በሀራጅ እንዲሸጥ ያደርጋል፤

15/ የክልሉን ገቢ የመሰብሰብ አቅም በቀጣይነት የሚያሳድጉ አሠራሮችን ይቀርፃል፤ ይተገብራል፤ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

16/ ኢንቨስትመንትን ለማበረታታት ለባለሀብቶች የተሰጡ የታክስ እፎይታ መብቶች በአግባቡ እንዲፈፀሙ ያደርጋል፤ ይከታተላል፣ እርምጃ ይወስዳል፤

17/ ታክስ ከፋዮች በፍቃደኝነት ታክስ የመክፈል ባሕልን እንዲያዳብሩ የሚያግዝ ሥርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ያደርጋል፤

18/ የክልሉ መንግሥት ተቋማት ከሥራ ባሕሪያቸው ምክንያት የሚመነጭ የውስጥ ገቢ ወደ ክልሉ መንግሥት ትሬዠሪ እንዲገባ እና እንዲመዘገብ ክትትል ያደርጋል፤ ዝርዝር አፈፃፀሙ በሕግ ይወሰናል፤

19/ የተቋሙን የሰው ኃይል ያስተዳድራል፣ የአደረጃት እና የጥቅማጥቅም ማሻሻያ ጥናት በማካሄድ ለመስተዳድር ምክር ቤቱ ያቀርባል፣ ሲፀድቅለትም ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

12/ Investigates, sues, and litigates on crimes committed in violation of tax laws; organizes its own tax crime investigators and prosecutors to execute same and supervises their implementation;

13) Facilitates tax paying alternative institutions for the taxpayer society;

14/ In cooperation with the relevant body, cuases the observation, seizing and auctioning of assets of taxpayers, in accordance with the law, who have not fulfilled their custom or tax obligations;

15/ Formulates procedures that will continuously increase revenue collection capacity of the region; implements and monitors its implementation;

16/ Ensures that tax relief rights granted to investors are properly implemented to encourage investment; monitors and takes action;

17/ Establishes and implements a system that helps taxpayers develop a culture of voluntarily tax payment;

18/ Monitors the internal revenue generated by regional government institutions due to their work characteristics to be deposited in the regional government treasury and recorded; detailed implementations shall be determined by law;

19/ Manages the human resources of its institution; conducts a study on organizational and benefit reform and submits same to the Government Council, and implements it upon approval.

CamScanner

## 34. የትምህርት ቢሮ

በሌሎች ሕጎች አስቀድሞ የተደነገገው ወይም ወደ ፊት የሚደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ ትምህርት ቢሮ በዚህ አዋጁ መሠረት የሚከተሉት ዝርዝር ሥልጣን እና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1/ የሀገሪቱን የትምህርት እና ሥልጠና ፖሊሲ መሠረት በማድረግ የክልሉን የአጭር፣ የመካከለኛ እና የረዥም ጊዜ ስትራቴጂያዊ እቅዶች እና ፕሮግራሞች ያዘጋጃል፤ በሚመለከተው አካል ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፣ ውጤታማነቱን ይከታተላል፤

2/ ሀገራዊ የትምህርት ስታንዳርዶችን መሠረት በማድረግ በየደረጃው ለሚገኙ የትምህርት ተቋማት ክልል አቀፍ ስታንዳርድ ያዘጋጃል፤ በስታንዳርዱ መሠረት መሟላቱን በኢንስፔክሽን ምርመራ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የማስተካከያ እርምጃዎችን ይወስዳል፤

3/ ሀገራዊ ስታንዳርዶችን መሠረት በማድረግ ተግባራዊ የጎልማሶች መሠረታዊ ትምህርት፣ የቅድመ አንደኛ፣ የልዩ ፍላጎት፣ የአንደኛ እና የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት እንዲሁም የመምህራን ትምህርት ኮሌጆች ሥርዓተ ትምህርቶችን ያዘጋጃል፤ ተግባራዊ መሆናቸውን ይከታተላል፣ ይገመግማል፣ ያሻሽላል፤

4/ የሥርዓተ ትምህርት ማቴሪያሎች በነፃ ገበያው በማወዳደር በጥራት እንዲታተሙ እና እንዲሠራጩ ያደርጋል፤ በገበያ ላይ በበቂ ሁኔታ መገኘታቸውን ያረጋግጣል፤

5/ የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማረጋገጫ ፓኬጅን ተግባራዊ በማድረግ ለክልሉ ብሎም ለሀገሪቱ አጠቃላይ ልማት እውን መሆን ምክንያት የሚሆን ብቁ ዜጋ ለማፍራት ስልት ይቀይሳል፤ ተግባራዊ ያደርጋል፣ ሂደቱንም በየጊዜው እየገመገመ ያሻሽላል፤

## 34. Bureau of Education

Without prejudice to the existing or subsequent provision of other laws, the Regional Bureau of Education shall, pursuant to this proclamation, have the following specific powers and duties;

1/ Prepares short, medium and long-term strategic plans and programs of the region based on the country's education and training policy; implements them when approved by the relevant body, and monitors their effectiveness;

2/ Prepares regionalwide standards for educational institutions found at all levels based on the national education standards; followsup and monitors the compliance of the standard through its inspectional investigation; takes corrective measure when it finds necessary;

3/ Prepares curricula for pragmatic adult basic education, pre-primary, special needs, primary and secondary education as well as teacher education colleges based on national standards; monitors, and evaluates their applicability, and improves thereof;

4/ Makes curriculum materials to be published and distributed in a quality manner through free market competition; ensures that they are adequately available in the market;

5/ Devises a system in which qualified citizens to be produced causing for the realization of general development of the region as well as the country by implementing the General Education Quality Assurance Package; implements and improves by periodically reviewing the process;

6/ የትምህርት አቅርቦቱን ሚዛናዊ እና ፍትሐዊ በሆነ መንገድ ለማስፋፋት የሚረዱ ልዩ ልዩ ስልቶችን እና አማራጮችን በመንደፍ ጥራት ያለው ትምህርት ለሁሉም እንዲዳረስ ያደርጋል፤

7/ በክልሉ ውስጥ የሚሰጠው ትምህርት የአካባቢውን ተጨባጭ ሁኔታ እና ፍላጎት ያገናዘበ፣ የፆታ፣ የቦታ እና ማኅበራዊ ሚዛናዊነትን የጠበቀ እና ለተግባራዊ እንቅስቃሴ የሚያግዝ ሆኖ ዴሞክራሲያዊ እና ሳይንሳዊ አስተሳሰቦችን እና አሠራሮችን ለማጎልበት የሚረዳ ስለ መሆኑ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

8/ በክልሉ ውስጥ ከቅድመ አንደኛ ትምህርት እስከ አንደኛ እና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት የሚደርሱ ተቋማትን ያደራጃል፣ አዳዲስ ይከፍታል፤ አስፈላጊ የሆኑ ማናቸውም የትምህርት ግብዓቶችን ለማሟላት የተለያዩ ስልቶችን ይቀይሳል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፤

9/ የክልሉ የትምህርት ፕሮግራሞች ከሀገራዊ የትምህርት ፕሮግራም ጋር ተናበው ወጥ እና ሴኩላር ሆነው እንዲተገበሩ ያደርጋል፤ ለተማሪዎች እና መምህራን የሬዲዮ ትምህርት ፕሮግራምን በቴክኖሎጅ እና በፕላዝማ የተደገፈ አዳጊ፣ ዘመናዊ፣ የተደራጀ እና ተደራሽ እንዲሆን ያደርጋል፣ ያስተዳድራል፤

10/ የመምህራንን፣ የርዕሳነ-መምህራንን እና የሱፐርቫይዘሮችን ብቃት ለማሳደግ የፍላጎት ዳሰሳ ጥናት ያካሂዳል፤ በጥናቱ ውጤት መሠረትም የቅድመ ሥራ እና ተከታታይ የሙያ ማሻሻያ ሥልጠናዎች እንዲሰጡ ያደርጋል፣ ይከታተላል፣ የማስተካከያ እርምጃዎችን ይወስዳል፤

11/ የትምህርት ግብዓቶች እና የክዘና ማዕከላትን ያደራጃል፤ ተገቢውን አገልግሎት እንዲሰጡ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፣ ይቆጣጠራል፣ ያስተዳድራል፤

6/ Causes the accessibility of quality education for all by designing various strategies and options helping to promote the provision of education in a balanced and equitable manner;

7/ Follows up and supervises the education provided in the region takes into account the realities and needs of the environment, maintains gender, place and social balance and helps to develop democratic and scientific thoughts being to assist for the practical activity;

8/ Organize institutions ranging from pre-primary education to primary and secondary education in the region, opens new ones; devises and implements various strategies to meet any necessary educational resources;

9/ Ensure that the regional education programs are implemented in consistent and secular manner in line with the national education program; makes radio education programs to be accessible for students and teachers being supported by technology and plasma, modern and organized, and manages same;

10/ Conducts need assessment study to enhance the competency of teachers, principals and supervisors; causes for the provision of pre-employment and continuous professional development training based on results of the study; monitors and takes corrective measures;

11/ Organizes educational resources and warehouse centers; establishes a system to enable them to provide the appropriate services, supervises and manage same;

12/ የግል ትምህርት ተቋማት ከፍተው በቢሮው ሕግ፣ ደንብ እና ውሳኔ መሠረት የትምህርት አገልግሎት ሥራ ለመሥራት ጥያቄ ላቀረቡ ግለሰቦች፣ ድርጅቶች፣ ማኅበራት እና ግብረ ሰናይ ድርጅቶች አጠቃላይ ስታንዳርድ ማሟላታቸው ተረጋግጦ አስፈላጊነቱ በቢሮው ሲታመንበት የትምህርት አገልግሎት ሥራ እውቅና ፈቃድ ይሰጣል፣ ያድሳል፣ ይቆጣጠራል፣ ይሰርዛል፤

13/ በክልሉ የግል ትምህርት ቤቶችን እንዲስፋፉ ያመቻቻል፣ ይደግፋል፤ የትምህርት አገልግሎት ክፍያን፣ የመማር ማስተማር አጠቃላይ ወጭን እና ወቅታዊ የዋጋ ሁኔታን በማጥናት ታሪፍን በመመሪያ ይወስናል፣ ያሻሽላል፣ ያስፈፅማል፣ ይቆጣጠራል፤

14/ የግል ትምህርት ቤቶች በራሳቸው በጀት በቂ የመማሪያ እና የትምህርት ማጣቀሻ መጽሐፍት እንዲሁም ሌሎች የትምህርት ግብዓቶች በወቅቱ እንዲያገኙ ያደርጋል፤

15/ የአንደኛ እና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ ፈተናዎችን ያዘጋጃል፣ ይሰጣል፤ የማለፊያ ውጤቱን ይወስናል፣ በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚዘጋጁ ፈተናዎችን በክልሉ ውስጥ ያስፈፅማል፤

16/ ሁሉም ዕድሜያቸው ለትምህርት የደረሱ ሕፃናትን እና ወጣቶች የመማር ዕድል እንዲያገኙ ያደርጋል፤ የትምህርት ቤቶችን የቅበላ አቅም የማሳደግ ሥራ ይሠራል፤ ተግባራዊ ያደርጋል፤

17/ በሰው ሠራሽ ወይም በተፈጥሮ አደጋ ምክንያቶች የሚፈጠር ክልላዊ የተማሪ ማቋረጥ ምጣኔ እንዲቀንስ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ይሠራል፤ ችግሮቹን በጥናት ይለያል፣ ተመጣጣኝ የመፍትሔ እርምጃዎችን ይወስዳል፤

18/ ዘመናዊ የመረጃ ሥርዓት በመዘርጋት የትምህርት ስታትስቲካዊ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ይተነትናል፣ ያጠናቅራል፤ ጥቅም ላይ እንዲውል ያደርጋል፣ ያሰራጫል፤

12/ Grants, renews, monitors, and revokes educational service licenses to individuals, organizations, associations, and charitable organizations that have opened private educational institutions and have applied to provide educational services in accordance with the laws, regulations, and decisions of the Bureau, provided that they have met the general standards and that the Bureau deems it necessary;

13/ Facilitates and supports for the expansion of private schools in the region; determines by a directive, improves, implements and controls the educational service fee, the total cost of teaching and learning through studying the current price situation;

14/ Ensures that private schools, within their own budget, have access to sufficient textbooks and reference books as well as other educational resources in time;

15/ Prepares and administers primary and secondary school leaving examinations; determines the passing score, and executes national examinations prepared at national level in the region;

16/ Ensures that all children and youth of school age have access to education; works to increase the capacity of schools admission, and implements;

17/ Works with relevant bodies to reduce the regional student dropout rate caused by man-made or natural disasters; identifies problems through research, and takes balanced remedial measures;

18/ Collects, analyzes and compiles educational statistical data by establishing modern information system; makes available for use, distributes;

CamScanner

19/ ኅብረተሰቡ እና የየደረጃው አስተዳደር አካላት ትምህርት ቤቶችን በባለቤትነት ስሜት ይዘው በትምህርት አመራር፣ በበጀት አመዳደብ እና አፈፃፀም ላይ ሙሉ ተሳትፎ እና ቁጥጥር እንዲያደርጉ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፤

20/ በክልሉ ውስጥ ትምህርትን ከማስፋፋት እና ጥራቱን ከመጠበቅ አንፃር ልዩ ልዩ ሥልቶችን በመንደፍ በኅብረተሰቡ፣ በግለሰቦች እና በድርጅቶች አማካኝነት የትምህርት ማስፋፊያ ሀብት ያሰባስባል፣ ይህንኑ ለትምህርት ሥራ ያውላል፤

21/ ለትምህርት የሚመደበውን የመንግሥት እና የዕርዳታ በጀት እና ንብረት ያስተዳድራል፤ አጠቃቀሙም ወጭ ቆጣቢ እና ውጤታማ መሆኑን ያረጋግጣል፤

22/ በሥራ ላይ ያሉ እና ትምህርት ነክ የሆኑ ፖሊሲዎች፣ ሕጎች፣ ደንቦች እና መመሪያዎች ከወጡበት ዓላማ እና ተግባር አንፃር በሥራ መተርጎማቸውን ያረጋግጣል፤

23/ የተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎችን በመጠቀም ትምህርት ነክ ፖሊሲዎችን፣ ፕሮግራሞችን፣ ውሳኔዎችን፣ ዕቅዶችን፣ ሪፖርቶችን እና ሌሎች መረጃዎችን ለኅብረተሰቡ እና ለሚመለከተው አካል ያደርሳል፤

24/ በክልሉ ውስጥ የመንግሥት ትምህርት ቤቶችን ይገነባል፣ ያስፋፋል እንዲሁም ከፌደራል መንግሥት፣ ወረዳዎች፣ ከተማ አስተዳደሮች እና የብሔረሰብ ዞኖች በቀጥታ በሚመደብ በጀት እና በልማት ድርጅቶች፣ በግል ባለሀብቶች፣ በኅብረተሰብ ተሳትፎ እና የዕርዳታ ድርጅቶች ድጋፍ ትምህርት ቤቶች እንዲገነቡ ያስተባብራል፤ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን የግንባታ ዲዛይን እንዲፀድቅ ያደርጋል፤ሕጉን ጠብቆ በጥራት ስለመገንባቱ ክትትል እና ቁጥጥር ያደርጋል፤

19/ Establishes and implements a system enabling the society and administrative bodies at all levels to have a sense of ownership of schools and to fully participate and control on educational management, budget allocation and implementation;

20/ Collects educational expansion resource from the society, individuals and organizations by devising various methods to expand and maintain the quality of education in the region; utilizes same for educational purposes;

21/ Manages the government and aid budget and assets allocated to education; ensures that the utilization is cost-effective and successful;

22/ Ensures that existing and educational-related policies, laws, regulations and directives are implemented in accordance with the intended objectives and duties for which they were issued;

23/ Disseminates educational-related policies, programs, decisions, plans, reports and other information to the public and relevant parties using various means of communication;

24/ Constructs and expands government schools in the region, as well coordinates the construction of schools with the direct budget allocated from the federal government, weredas, city administrations and nationality zones, and with the support of development organizations, private investors, society participation and aid organizations; causes for the approval of construction design in collaboration with the relevant body; monitors and controls the quality of construction in compliance with the law;

CamScanner

25/ ከትምህርት ግብዓት ጋር የተያያዙ የሀገር ውስጥ እና ዓለም አቀፍ ግዥን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ይፈጽማል፤ ውል ይይዛል፤ በቂ የትምህርት ግብዓቶች እንዲሟሉ ይሠራል፤

26/ የዞን፣ ከተማ አስተዳደር እና ወረዳ ተጠሪ የትምህርት ተቋማት ከቢሮው የወረደላቸውን የሥራ ዕቅድ በሕግ እና ደንብ መሠረት የመማር ማስተማር አጠቃላይ አገልግሎት ስለ መስጠታቸው ክትትል እና ቁጥጥር ያደርጋል፤

27/ በክልሉ የመንግሥት መምህራን ትምህርት ኮሌጆችን እና ልዩ አዳሪ ትምህርት ቤቶችን የግንባታ ዲዛይን ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን እንዲፀድቅ ያደርጋል፤ በቂ በጀት ይዞ ይገነባል፣ ያደራጃል፣ ያስፋፋል እንዲሁም በልማት ድርጅቶች፣ በግል ባለሀብቶች እና እርዳታ ድርጅቶች ድጋፍ የሚስፋፉበትን ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፣ ያስተዳድራል፤

28/ የተሰጡትን ተግባራት እና ኃላፊነቶች በብቃት መወጣት የሚያስችሉ የሥርዓተ ትምህርት፣ የፈተና፣ የተማሪ እና መምህራን አስተዳደር፣ የትምህርት ግብዓት አቅርቦት፣ የመምህራን ኮሌጆች እና ትምህርት ቤቶች አስተዳደር፣ የትምህርት አመራር እና ዲኖች አስተዳደር እንዲሁም የበታች ተቋማት ቁጥጥር ሥርዓት እና ሌሎች ተያያዥ ዝርዝር መመሪያዎችን በማውጣት በሥራ ላይ ያውላል፤

29/ በግል እና በመንግሥት ትምህርት ቤቶች እና መምህራን ኮሌጆች የሚካሄደውን የትምህርት አሰጣጥ አስመልክቶ የትምህርት ጥራት ኢንስፔክሽን እና ኦዲት በማካሄድ የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፣ እንዲወሰዱ ያደርጋል፤

25/ Conducts domestic and international procurement related to educational resources in collaboration with relevant parties, enters into contracts; works for the fulfillment of sufficient educational resources;

26/ Monitors and supervises the provision of teaching learning comprehensive services work plan downwarded from the bureau of the zone, city administration and wereda accountable educational institutions in accordance with law and regulations;

27/ Makes construction designs of government teacher training colleges and special boarding schools in the region to be approved being with the relevant body; constructs, organizes and expands having sufficient budget; as well as creates and manages favorable environment for their expansion with the support of development organizations, private investors and aid organizations;

28/ Issues and implements detailed directives on curriculum, examination, student and teacher management, provision of educational inputs, administration of teachers' colleges and schools, school leadership and deans management as well as lower institutions supervision system and other related issues enabling to effectively carryout the assigned duties and responsibilities;

29/ Takes and causes to be taken corrective measures regarding the provision of education by private and government schools and teachers colleges through conducting educational quality inspection and auditing;

CamScanner

30/ የመንግሥት ትምህርት ቤቶችን እና መምህራን ኮሌጆችን ደረጃ፣ ስታንዳርድ እና የቦታ ስፋት በማጥናት ይወስናል፤ የራሳቸው ካርታ እንዲሠራላቸው በማድረግ በባለቤትነት ያስተዳድራል፣ ይቆጣጠራል፤

31/ በየደረጃው ለሚገኙ መምህራን፣ ርዕሰ መምህራን እና ሱፐርቫይዘሮች የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፣ ያድሳል፣ ይሰርዛል፤

32/ የመማር ማስተማሩን ውጤታማ ለማድረግ የትምህርት ቤቶች የምገባ መርሃ ግብር ሥርዓት ይዘረጋል፤ ተገቢውን ትኩረት እንዲያገኝ ያደርጋል፣ ለዚሁ የሚውል የተለያዩ የፋይናንስ አማራጮችን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ያመቻቻል፣ ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል።

## 35. <u>የጤና ቢሮ</u>

በሌሎች ሕጎች አስቀድሞ የተደነገገው ወይም ወደ ፊት የሚደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ ጤና ቢሮ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ዝርዝር ሥልጣን እና ተግባራት ይኖሩታል፦

1/ የሀገሪቱን የጤና ፖሊሲ እና ስትራቴጂ መሠረት በማድረግ የክልሉ ሕዝብ ጤና የሚጠበቅበትን ዕቅድ እና ፕሮግራም ያዘጋጃል፤ በክልሉ ውስጥ የጤና አገልግሎት እንዲስፋፋ ያደርጋል፤

2/ የሕዝብ ጤና አጠባበቅን በተመለከተ የወጡ ሕጎች በክልሉ ውስጥ መከበራቸውን ያረጋግጣል፤

3/ በየደረጃው የሚገኙትን የጤና አገልግሎትም ሆነ የማሠልጠኛ ተቋማት እና የጥናት እና ምርምር ማዕከላት አስፈላጊነት በማጥናት እንዲፈቀድ ያደርጋል፣ ያደራጃል፣ ያስተዳድራል፤



30/ Determines the level, standard and area of government schools and teachers' colleges through studying same; manages and supervises them by having their own maps to be prepared;

31/ Issues, renews and cancels professional qualification certificates for teachers, principals and supervisors found at all levels;

32/ Establish schools feeding program to make the teaching and learning effective; makes it to get the appropriate attention, facilitates and causes for the implementation of various financial options in collaboration with relevant parties.

## 35. <u>Bureau of Health</u>

Without prejudice to the existing or subsequent provisions of other laws, the Regional Bureau of Health shall, pursuant to this proclamation, have the following particular powers and duties:

1/ Prepares plans and programs whereby heal of people of the region might be protected in line with the country's health policy and strategy; causes for expansion of health services in the region;

2/ Ensurees that laws issued regarding public health protection are enforced in the region;

3/ Studies the necessity of health services as well as training institutions and research centers at all levels and makes same to be allowed; organizes and manages them;

CamScanner

4/ በክልሉ ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውሉ መድኃኒቶች እና የሕክምና መገልገያ መሣሪያዎች የጥራት ደረጃቸውን የጠበቁ መሆናቸውን ይቆጣጠራል፤ ጥራታቸውን ባልጠበቁት ላይ እርምጃ ይወስዳል፣ ያስወስዳል፤

5/ በክልሉ ውስጥ በግል ወይም በድርጅቶች ለሚቋቋሙ ሆስፒታሎች፣ ስፔሻሊቲ ማዕከላት፣ ጤና ጣቢያዎች፣ ክሊኒኮች፣ የዲያግኖስቲክ ማዕከላት እና መድኃኒት ቤቶች የሙያ ፈቃድ ይሰጣል፤ በሀገር ዓቀፍ ደረጃ የወጡትን መስፈርቶች ጠብቀው መሥራታቸውን ይቆጣጠራል፤

6/ አዲስ የሚቋቋሙ የመንግሥት የጤና ተቋማት አስፈላጊውን ደረጃ ማሟላታቸውን በማረጋገጥ ሥራ እንዲጀምሩ ያደርጋል፤

7/ የመንግሥት እና የግል ጤና ተቋማትን የአገልግሎት አሰጣጣቸውን በበላይነት ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ እርምጃ ይወስዳል፤

8/ በክልሉ ውስጥ በሕዝብ ጤና አገልግሎት ሥራ ላይ የተሠማሩ ባለሙያዎች ለዚሁ የተወሰነውን ደረጃ ማሟላታቸውን ያረጋግጣል፣ ይቆጣጠራል፤

9/ ፈዋሽነታቸው ለተረጋገጡ ሀገር በቀል የባሕል መድኃኒቶች እና የሕክምና ዓይነቶች በመስፈርቱ መሠረት ፈቃድ ይሰጣል፣ ያድሳል፣ ይሰርዛል፤ ከዘመናዊው ሕክምና ጋር ተዋሕደው በሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፤ ባለሙያዎችን ያደራጃል፣ ለዘርፉ የወጣውን ሕግ እና ደንብ ጠብቀው ስለ መሥራታቸው ይቆጣጠራል፤

10/ የሀገሪቱን የጤና ፖሊሲ ለማስፈፀም የተዘረጉ እና የሚዘረጉ ፕሮግራሞችን እና ስትራቴጅዎችን በክልሉ ውስጥ ይፈፅማል፣ ያስፈፅማል፤

11/ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን የጤና ተቋማት የግንባታ ዲዛይን እንዲፀድቅ ያደርጋል፤ የጤና ተቋማትን መሠረተ ልማት ያስፋፋል፣ አስፈላጊ ግብዓቶች መሟላታቸውንም ያረጋግጣል፤

4/ Supervises whether medicines and medical devices to be used in the region meet their quality standards; takes and causes to be taken action against those who do not meet their quality standards;

5/ Issues professional licenses to hospitals, specialty centers, health centers, clinics, diagnostic centers, and pharmacies to be established privately or by organizations in the region; supervises whether they operate in accordance with the requirements set forth at the national level;

6/ Makes newly to be established government health institutions begin work after ensuring whether they meet the required standards;

7/ Monitors, supervises and takes action on the provision of services by government and private health institutions;

8/ Ensures that professionals engaged in public health services in the region meet the standards set for this purpose, and supervises thereof;

9/ Grants, renews and cancels licenses for indigenous traditional medicines and types of medical treatments proven to be effective; makes to be implemented being integrated with modern treatment; organizes professionals, and monitors their operation in accordance with laws and regulations issued for the sector;

10/ Executes and causes for the execution of programs and strategies developed and will be developed in the region to implement the country's health policy;

11/ In collaboration with the relevant body, gets construction designs of health institutions to be approved; expands infrastructure of health institutions, ensures fulfillment of necessary resources;

CamScanner

12/ የሕዝቡ ጤና እንዲጠበቅ ለማድረግ የኳራንቲን ቁጥጥር ያካሂዳል፤

13/ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በክልሉ ውስጥ ከሚገኙት የመንግሥትም ሆነ የግል የጤና ኮሌጆች ለሚመረቁ የጤና ባለሙያዎች የብቃት ማረጋገጫ ፈተና እና የምስክር ወረቀት ይሰጣል፣ የሙያ ምዝገባ ያካሂዳል፣ ፈቃድ ይሰጣል፣ ያድሳል፣ ይሰርዛል፣ ይቆጣራል፤

14/ በመከላከል እና አክሞ ማዳን ላይ አተኩረው የሚፈፀሙ የጤና ልማት ሥራዎችን ያስተባብራል፣ ይመራል፣ ያስፈፅማል፤

15/ በክልሉ ውስጥ የሚካሄዱ ጤና እና ጤና ነክ የምርምር ተግባራትን ያስተባብራል፣ ይመራል፣ ያስፈፅማል፤

16/ ለጤና ዘርፉ ዕድገት የሚያግዝ የገንዘብ ማግኛ ሥርዓት ይዘረጋል፣ አፈፃፀሙን በበላይነት ይመራል፣ ይቆጣጠራል፤

17/ ሁሉን አቀፍ የጤና መድኅን ሥርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

18/ የሀይጅን እና የአካባቢ ጤና አጠባበቅ ሥራዎችን በበላይነት ይመራል፣ ይቆጣጠራል፤ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በትብብር ይሠራል፤

19/ በጤናው ዘርፍ የዘላቂ ልማት ግቦችን ለማሳካት፣ ለእናቶች እና ሕፃናት ጤና አጠባበቅ፣ ኤች አይ ቪን፣ የወባ፣ የሳንባ ነቀርሳ በሽታዎችን እንዲሁም ሌሎች ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር ልዩ ትኩረት ሰጥቶ ይሠራል፤

20/ ዘመናዊ የዲጂታል ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም የክልሉን የጤና መረጃ ያደራጃል፣ ይተነትናል፣ ጥቅም ላይ እንዲውል ያደርጋል፤

12/ Undertakes quarantine control with the view to taking care of the public health;

13/ In cooperation with the relevant bodies, issues competence assurance examination and certificate for health professionals graduating from both public and private health colleges in the region; conducts professional registration, issues, renews and cancels licenses, and controls therefrom;

14/ Coordinates, directs and implements health development activities focused on prevention and treatment;

15/ Coordinates, directs and implements health and health-related research activities conducted in the region;

16/ Establishes a financial system that will support the development of the health sector, leads and controls its implementation;

17/ Establishes a universal health insurance system, ensures its implementation and monitors its implementation;

18/ Leads and monitors hygiene and environmental health care activities; works in collaboration with relevant bodies;

19/ In order to achieve the Sustainable Development Goals in the health sector, works paying special attention to maternal and child health care including HIV, malaria, tuberculosis as well as other non-communicable diseases to prevent and control them;

20/ Organizes, analyzes and utilizes the region's health information using modern digital technologies;

CamScanner

21/ በክልሉ ውስጥ የምግብ እና የመጠጥ አገልግሎት ሰጭ ተቋማት የሕዝብ ጤና አጠባበቅ ደንቦችን እና መመሪያዎችን ተከትለው መሥራታቸውን በቅርብ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤ ጥፋተኞች ሆነው ሲገኙም አስተዳደራዊ እርምጃዎችን ይወስዳል፣ ያስወስዳል፤

22/ የግል ክሊኒኮች፣ ላቦራቶሪዎች፣ ፋርማሲዎች፣ ስፔሻሊቲ ማዕከላት፣ ዲያግኖስቲክ ማዕከላት፣ ሆስፒታሎች እና የመድኃኒት ንግድ መደብሮች የመንግሥትን ደንብ እና መመሪያ አክብረው መሥራታቸውን ይቆጣጠራል፤ ጥፋተኞች ሆነው ሲገኙም እርምጃዎችን ይወስዳል፣ ያስወስዳል፤

23/ የጤና ተቋማት ልዩ ልዩ የጤና አገልግሎቶች እንዲጀምሩ ጥያቄ ሲቀርብለት አስፈላጊነቱን በመመዘን ይፈቅዳል፣ ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፣ ደረጃቸውን ጠብቀው መሥራታቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

24/ የሀገሪቱ የኤች አይ ቪ/ኤድስ ፖሊሲ በክልሉ ውስጥ በተቀናጀ መንገድ እንዲተገበር ሁለንተናዊ ድጋፍ ይሰጣል፤ በዚሁ ዙርያ የሚሠሩ ድርጅቶች እና ግለሰቦች ተገቢውን ሥልጠና እና ድጋፍ የሚያገኙበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣ የተሟላ ድጋፍ በማሰባሰብ እንዲንቀሳቀሱ ያበረታታል፤

25/ በክልሉ ውስጥ ለኤች አይ ቪ/ኤድስ በሽታ እና ለወረርሽኞች የማያጋልጥ የተሟላ ግንዛቤ እና ጤናማ ባሕሪ ይጐለብት ዘንድ ለክልሉ ኅብረተሰብ የተለያዩ ዘዴዎች በመጠቀም ግንዛቤ ያስጨብጣል፣ ይቀሰቅሳል፤

26/ ዝርዝሩ ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣ ደንብ የሚወሰን ሆኖ በሥራ ላይ ያሉትን የአካል ጉዳተኞች ድጋፍ፣ ተሐድሶ እና እንክብካቤ ማዕከላትን ያስተዳድራል፤ በክልሉ ውስጥ በተለያዩ አካባቢዎች እንደየተገቢነታቸው መሰል ማዕከላት እንዲቋቋሙ ያደርጋል፤ ከሚመለከተው ጋር በመሆን በኢኮኖሚ ራሳቸውን እንዲችሉ ተገቢውን ድጋፍ ይሰጣል፤

21/ Closely follows up and supervises that food and beverage service delivery institutions in the region operate in compliance with public health regulations and directives; takes and causes to be taken administrative measures against found to be at fault;

22/ Monitors the compliance of private clinics, laboratories, pharmacies, specialty centers, diagnostic centers, hospitals, and drug stores with government regulations and directives; takes and cuases to be taken action measures when found guilty;

23/ Allows evaluating its necessity when a request is made of health institutions to start various health services, creates a favorable environment, monitors and supervises their operation maintaining their standards;

24/ Provides comprehensive support for the implementation of the country's HIV/AIDS policy in a coordinated manner in the region; facilitates conditions for provision of appropriate training and support to organizations and individuals working in this area, and encourages them mobilizing full support;

25/ Raises awareness and mobilizes the regional society through various methods to develop a complete understanding and healthy behavior that does not expose them to HIV/AIDS and other infectious diseases in the region;

26/ Being the details determined by a regulation to be issued to implement this proclamation, manages the existing rehabilitation and care centers for the disabled; causes for establishment of similar centers in various areas of the region, as appropriate; in being with concerned, provides the appropriate support to make them economically self-sufficient;

CS CamScanner

27/ የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራሙን አተገባበር ስኬታማ ለማድረግ የሰው ኃይል እና ግብዓት ያሟላል፣ ውጤታማነቱን ይከታተላል፣ ይደግፋል፤

28/ የኅብረተሰብ ጤና አደጋዎችን እና ወረርሽኞችን ከስተት ይተነብያል፣ ይቃኛል፤ የዳሰሳ ጥናቶችን እና ዝግጅቶችን ያካሂዳል፣ እንደ አስፈላጊነቱ ፈጣን ምላሽ ይሰጣል፤

29/ በመንግሥት ጤና ተቋማት ደረጃውን የጠበቀ የላቦራቶሪ፣ የዲያግኖሲስ አገልግሎት እስዲሰጥ ለማድረግ የሚያስችል ግብዓት ያሟላል፣ ይከታተላል፣ ይደግፋል፤

30/ በመንግሥትም ሆነ በግል ጤና ተቋማት ከመደበኛ የሕክምና አገልግሎት ሥርዓት ባሻገር የሜዲካል ቱሪዝምን የሚተገብሩ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታሎች ያደራጃል፣ ይከታተላል፣ ይደግፋል፡፡

## 36. የፍትሕ ቢሮ

በሌሎች ሕጎች አስቀድሞ የተደነገገው ወይም ወደ ፊት የሚደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ፍትሕ ቢሮ የሚከተሉት ዝርዝር ሥልጣን እና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1/ በሕግ ጉዳዮች ረገድ የክልሉ መንግሥት ዋና አማካሪ ሆኖ ይሠራል፣ የክልሉን መንግሥት መብት እና ጥቅም ያስከብራል፣ በሀገር አቀፍ ደረጃ ተፈፃሚነት በሚኖራቸው ወይም በክልሉ በወጡ ሕግጋት ዙርያ ማኅበረሰቡ ተገቢውን መረዳት እንዲኖረው ያደርጋል፤

2/ የሀገሪቱ የወንጀል ፍትሕ ፖሊሲ በክልሉ ውስጥ ተግባራዊ እንዲሆን ይሠራል፣ ያስተባብራል፣ ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፤

3/ በክልሉ ውስጥ የወንጀል ነክ መረጃዎችን ለመሰብሰብ፣ ለማደራጀት፣ ለመተንተን እና ለማሰራጨት የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፤ ለፍትሕ ሥርዓቱ ውጤታማነት ጥቅም ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፤

27/ Fulfills the human resources and inputs to ensure successful implementation of the health extension program, monitors its effectiveness, and supports it;

28/ Predicts and surveys public health emergencies and epidemics; conduct surveys and preparations for, and provides rapid response as necessary;

29/ Ensures the availability of inputs to provide quality laboratory and diagnostic services in government health institutions;

30/ Organizes, monitors and supports specialized hospitals that implement medical tourism beyond the regular medical service system in both government and private health institutions.

## 36. Bureau of Justice

Without prejudice to the existing or subsequent provisions of other laws, the Regional Bureau of Justice shall, pursuant to this proclamation, have the following particular powers and duties:

1/ Act as the chief advisor to the regional government on legal matters, protects the rights and interests of the regional government, and ensure that the society has proper understanding of laws that are applicable nationwide or enacted in the region;

2/ Works for the implementation of the national criminal justice policy in the region, coordinates, followsup and ensures thereof;

3/ Establishes a system for collecting, organizing, analyzing and disseminating criminal information in the region, makes them to be utilized for the effectiveness of the justice system;

CamScanner

4/ የዐቃቤ ሕግ የውሳኔ አሰጣጥ እና የፍቅደ ሥልጣን አጠቃቀም ወጥነትን ለማረጋገጥ ይሠራል፤ ከዚሁ ጋር በተያያዘ በፍትሕ ሚኒስቴር የፀደቀን መመሪያ እንደ አግባብነቱ በክልሉ ውስጥ ተግባራዊ መደረጉን ያረጋግጣል፤

5/ ዐቃብያን ሕግ የሚያሳልፏቸው ውሳኔዎች በሕግ መሠረት መስጠታቸውን እና መፈፀማቸውን ያረጋግጣል፤ ክትትል እና ቁጥጥር ያደርጋል፤ ጉድለቶችን በጥናት ላይ ተመሥርቶ ይለያል፤ በግኝቱ መሠረትም የእርምት እርምጃዎችን ይወስዳል፤

6/ በትርፍ ላይ ያልተመሠረተ ዓላማ ይዘው የተቋቋሙ እና በክልሉ ውስጥ የሚንቀሳቀሱ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶችን ሕጋዊነት በማረጋገጥ ይመዘግባል፤ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ጋር በመተባበር ይቆጣጠራል፤ ይሰርዛል፤

7/ የማኅበራዊ ፍርድ ቤት ዳኞችን አቅም በማሳደግ በሕግ ተለይቶ የተሰጣቸውን ሥልጣን እና ኃላፊነት እንዲወጡ ድጋፍ እና ክትትል ያደርጋል፤

8/ ከማናቸውም የክልሉ አስፈፃሚ ተቋማት የሚመነጩ የሕግ ረቂቅ ዝግጅቶች ሕጋዊነት ሳይመረመር እና የማረም ሥራ ሳይሠራ ወደ መስተዳድር ምክር ቤት አለመላካቸውን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤ ማስተካከያ ይወስዳል፤ እንዲወሰድ ያደርጋል፤

9/ የሕግ ታራሚዎች ይቅርታ የሚያገኙበትን ሥርዓት ይዘረጋል፤

10/ በክልሉ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ውስጥ ተመድበው ወይም ተቀጥረው የሚሠሩ የሕግ ባለሙያዎች ሥራቸውን በማከናወን ሂደት ውስጥ የሕዝብ እና የመንግሥትን መብት እና ጥቅም በማስከበር ሂደት ስለሚኖራቸው ሚና፣ ተጠያቂነት እና የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፤ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፤

4/ Works to ensure consistency of decision-making and exercise of discretionary power of the prosecutor, ensures that the relevant directives approved by the Ministry of Justice related to such are implemented in the region as appropriate;

5/ Ensures that decisions made by the prosecutor are made and implemented in accordance with the law, undertakes monitoring and supervision, identifies deficiencies based on research, and takes corrective measures based on the findings;

6/ Registers verifying the legality of civil society organizations established with non-profit objectives and operating in the region; supervises and cancels them in cooperation with those concerned;

7/ Supports and monitors through enhancing capacity of judges of the Social Court to carry out the powers and responsibilities assigned to them by law;

8/ Monitors and supervises that draft laws originating from any executive institutions of the region are not sent to the Government Council without being examined and corrections are made; takes corrections and causes to be taken;

9/ Establishes a system for granting pardons to prisoners of law;

10/ Establishes a system of role, accountability and procedure of legal professionals assigned or employed in government offices of the region in the process of carrying out their work in protecting the rights and interests of the public and government; details of which shall be determined by a directive;

11/ የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ፣ የፍትሐ ብሔር እና ሕግ ጉዳዮች፣ የአስተዳደር እና ሪፎርም ሥራዎች ዘርፎችን እና አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች የሥራ ክፍሎችን ያደራጃል፤

12/ የተቋማት የውል አስተዳደርን በተመለከተ አቤቱታ ይቀበላል፣ አቅጣጫ ያስቀምጣል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

13/ የሙስና ወንጀል ሊፈፀም ስለመሆኑ ጥቆማ ሲደርሰው ጉዳዩ የቀረበበት ወይም የሚገኝበት መሥሪያ ቤት የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስድ እና ውጤቱን እንዲያሳውቅ ያደርጋል፤

14/ የክልሉን የዓቃቤ ሕግ አስተዳደር ጉባኤ ያቋቁማል፤ ዝርዝር አፈፃፀሙ በደንብ የሚወሰን ይሆናል፤

15/ የወንጀል ጉዳይን በተመለከተ:-

ሀ) በክልሉ ፍርድ ቤቶች ሥልጣን ስር በሚወድቁ ወይም በፍትሕ ሚኒስቴር በተሰጠው ውክልና መሠረት የሚታዩ የወንጀል ጉዳዮች ላይ ምርመራ እንዲጀመር ወይም የተጀመረ ምርመራ እንዲቋረጥ ወይም የምርመራ ቡድን በማደራጀት ምርመራው እንዲጣራ ያደርጋል፤ ምርመራን በበላይነት ይመራል፣ ሪፖርት እንዲደርሰው ያደርጋል፤

ለ) በሕግ ያለመከሰስ መብት የተሰጠው ሰው ላይ የወንጀል ክስ ለማቅረብ በቂ ማስረጃ በቀረበ ጊዜ ያለመከሰስ መብቱ እንዲነሣ ጥያቄውን ለክልሉ ምክር ቤት ወይም ለሌላ አግባብ ላለው አካል ያቀርባል፤ ሲፈቀድለት ተጠርጣሪው እንዲያዝ እና ክስ እንዲቀርብበት ያደርጋል፤

ሐ) በወንጀል ተካፋይ የሆነ ሰው ስለ ተፈፀመው ድርጊት እና ስለ ተባባሪዎች ሚና ጠቃሚ ማስረጃ ከሰጠ በሕግ በተቀመጠው አግባብ መሠረት ከክሱ ነፃ እንዲሆን ያደርጋል፤

11/ Organizes the attorney general, civil and legal affairs, administrative and reform works sector and other necessary work units;

12/ Receives complaints regarding administration of contracts of institutions, sets directions; monitors its implementation;

13/ Makes the office where the case was filed or is located take corrective action and notify the result when a tip-off is received that corruption crime is about to be committed;

14/ Establishes the Regional Prosecutor's Administrative Council; detailed implementation of which shall be determined by a directive;

**15/ Concerning Criminal Matters:**

A) Initiates investigation to be instituted or terminates an investigation that has already been initiated, or organizes an investigation team to conduct the investigation on criminal cases falling under jurisdiction of the regional courts or under delegation power given by Ministry of Justice; supervise investigation, makes report to be submitted to it;

B) Submits a request to the Region Council or other appropriate body to lift the immunity when sufficient evidence is presented to file a criminal case against a person who has been granted immunity by law; causes the suspect to be arrested and charged upon permission;

C) Exemptes from charges in accordance with procedures by law if a person who is participant in a crime provides relevant evidence about the committed act and the role of accomplices;

CamScanner

መ) በወንጀል ምርመራ ሂደት በተያዙ ኤግዚቢቶች ላይ ውሳኔ ይሰጣል፤ እንደአግባብነቱ ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲሰጥበት ይጠይቃል፤ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

ሠ) በሕግ አግባብ መሠረት የክስ አይቀርብም ውሳኔ ይሰጣል፤ በስር ዐቃብያነ ሕግ የተሰጡ ትእዛዝ እና ውሳኔዎችን ይመረምራል፣ ግድፈት ካለበት እንዲታረም ያደርጋል፤ በየደረጃው የሚገኝ ዐቃቤ ሕግ በትይዩ ባሉት ፍርድ ቤቶች የወንጀል ክስ አቅርቦ ተከራክሮ ያስወስናል፤

ረ) ሕገ-መንግሥታዊ ትርጉም የሚያስፈልጋቸው የመጨረሻ ውሳኔ ያገኙ ጉዳዮችን ለሕገ-መንግሥት አጣሪ ጉባኤ አቤቱታ አቅርቦ ያስወስናል፤

ሰ) የእጅ ከፍንጅ ወንጀሎች ተፈፅመው ሲገኙ በተፋጠነ ሥነ-ሥርዓት ውሳኔ የሚያገኙበትን መንገድ ያመቻቻል፤ ከፖሊስ እና ከሌሎች ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ተባብሮ ይሠራል፤

ሸ) ወንጀል መፈፀማቸው አጠራጣሪ የሆነ ሰዎችን ፖሊስ በሕግ መሠረት እንዲለቅ መመሪያ ይሰጣል፤ አፈፃፀሙን ይከታተላል፣ ሕጋዊ እርምጃ ይወስዳል፤

ቀ) ዝርዝሩ ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ የሚወሰን ሆኖ አግባብ ባለው ሕግ መሠረት የጥፋተኝነት ድርድር ያደርጋል፣ አማራጭ የመፍትሄ እርምጃ እንዲወሰድ ይወስናል፤

በ) የወንጀል ፍርድን ወይም የወንጀል ፍርድ ሳይኖር ሀብት የማስመለስ ሥርዓቶችን ተጠቅሞ በሕገ ወጥ መንገድ የተገኙ ንብረቶችን ለማስመለስ የሚያስችል ክስ ከወንጀል ክስ ጋር በተጓዳኝ ወይም በተናጠል በፍትሐብሔር በማቅረብ እና በመከራከር የሕዝብ እና የመንግሥት ሀብት የማስመለስ ሥራ ያከናውናል፤ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፣ ከአገር ውጭ ሀብት ለማስመለስ ከፍትሕ ሚኒስቴር ጋር በትብብር ይሠራል፤

D) Makes decisions on exhibits seized during criminal investigation process, requests the court to make a decision as appropriate, monitors its implementation.

E) Makes no-proceeding decisions in accordance with the law; examines orders and decisions issued by lower prosecutors, makes errors to be corrected; prosecutors at each level files criminal charges in the parallel courts, argues and gets decided;

F) Submits petition to the Constitutional Inquiry Council for final decisions on matters requiring constitutional interpretation and gets them to be decided;

G) Facilitates ways in which red-handed crimes get decision in expeditious procedure; works in collaboration with the police and other relevant parties;

H) Directs the police to release persons hesitating of committing crimes in accordance with the law; monitors its implementation, takes legal action;

I) Being details determined by a directive to be issued by the Bureau, makes plea bargaining based on relevant law, and determines adoption of alternative remedies;

J) Conducts works of recovery of public and government assets by filing and arguing charges, either in conjunction with criminal cases or separately to recover assets obtained illegally using criminal or non-criminal asset recovery systems; monitors its implementation and works in collaboration with the Ministry of Justice to recover assets from abroad;

CamScanner

ተ) በሕግ የታገዱ ንብረቶችን የሚያስተዳድር አካል ያሾማል፤ የንብረቶቹ አስተዳደር ከብክነት በፀዳ መልኩ በሕግ እና በተዘረጋው አሠራር መሠረት መከናወኑን ይከታተላል፤ የተጓደለ ነገር ሲኖር የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፤ እንዲወሰዱ ያደርጋል፤

ቸ) ጥቆማዎችን እና ጠቋሚዎችን ይመዘግባል፤ በሚስጥር ይይዛል፤ አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ምስክሮች ወይም ጠቋሚዎች እና የወንጀል ተጎጅዎች ተገቢውን ጥበቃ እና ከለላ እንዲያገኙ ያደርጋል፤ ለጠቋሚዎች ተገቢውን ጥበቃ መደረጉን ያረጋግጣል፤

ኀ) ለወንጀል ምስክሮች መጥሪያ እንዲደርስ እና ምስክሮችን ወደ ፍርድ ቤት እንዲያቀርብ ለፖሊስ ትዕዛዝ ይሰጣል፤

ነ) ለጠቋሚዎች ሽልማት ስለ ሚከፈልበት አግባብ መመሪያ ያዘጋጃል፤ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

ኘ) በወንጀሉ የተገኘውን ጥቅም በማስመለስ የሙስና ወንጀል ክስ የተመሠረተባቸው ወይም በምርመራ ላይ ያሉ የሙስና ወንጀሎች ከክስ በመለስ እንዲቋጩ ያደርጋል፤ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፤

አ) የሞት ቅጣት ውሳኔዎችን ለኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፓብሊክ ፕሬዚደንት ያቀርባል፤ አፈፃፀማቸውን ይከታተላል፤

ከ) በፍርድ ቤት የሚወሰኑ የወንጀል ቅጣቶች በአግባቡ እንዲፈፀሙ ይከታተላል፤ የአሠራር ሥርዓቶችን ይዘረጋል ወይም መደራጀታቸውን ያረጋግጣል፡፡

**16/ የፍትሐብሔር ጉዳዮችን በተመለከተ፡-**

ሀ) የክልሉ ሕዝብ እና መንግሥት መብቶች እና ጥቅሞች ሕጋዊ ወኪል በመሆን ይደራደራል፤ ይከራከራል፤ ያስከብራል፤ እንዲከበሩ ያደርጋል፤

ለ) ለክልሉ መንግሥት መሥሪያ ቤቶች ሕጋዊ ምክር ይሰጣል፤ በተሰጠው ምክር መሠረት ጉዳዩ ስለመፈፀሙ እና የመንግሥት ተቋማት ሀብት እና ንብረት ያለ አግባብ እንዳይባክን እና እንዳይመዘበር ተገቢውን ክትትል እና ቁጥጥር ያደርጋል፤

K) Gets a body to be appointed to manage assets seized by law, monitors management of assets in a manner free from waste in accordance with the law and the established procedures, takes corrective measures in case of any irregularities, causes to be taken;

L) Records and keeps confidential tip-offs and whistle blowers, ensures witnesses or whistle blowers and victims of crime receive appropriate protection and security in accordance with relevant law, ensures appropriate protection is provided to whistle blowers;

M) Issues orders to the police to serve summons to witnesses of crimes and to produce witnesses in court;

N) Prepares directive in which rewards are paid to whistle blowers and monitors its implementation;

O) Makes corruption crimes charges have been filed or under investigation to be resolved by recovering benefit of crime except charging; details shall be determined by a directive;

P) Submits death penalty decisions to the President of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and monitors their implementation;

Q) Monitors the proper execution of criminal penalties imposed by the court, establishes procedures or ensures their organization.

**16/ Concerning Civil Matters**

A) Negotiates being as legal representative of rights and interests of the people and government of the region; litigates, enforces and cuases for their enforcement;

B) Provides legal advice to regional government offices, carries out appropriate monitoring and supervision to ensure the advice is implemented and in order not resources and property of government institutions are wasted or misused;

ሐ) ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በክልሉ መንግሥት ፕሮጀክቶች እና በሌሎች ጉዳዮች የውል ሰነዶችን ያዘጋጃል፣ ረቂቅ ውሎችን ይመረምራል፣ ሕጋዊነቱን ያረጋግጣል

መ) ከስር ዐቃብያነ ሕግ በሚላኩለት የፍትሐብሔር መዛግብት ላይ የክስ አይቀርብም ውሳኔዎችን ይሰጣል፣ የስር ዐቃቤ ሕግ በሰጠው ትዕዛዝ እና ውሳኔ ላይ ቅሬታ ሲቀርብለት ወይም በራሱ አነሣሽነት ውሳኔውን መርምሮ ያፀናል፣ ይሽራል ወይም ተለዋጭ ትዕዛዝ ይሰጣል፤

ሠ) የክልሉ መንግሥት መሥሪያ ቤቶች አንዱ ከሌላው ጋር ያልተግባቡባቸው የፍትሐብሔር ጉዳዮች ያጋጠሙ እንደሆነ እርስ በርስ በማደራደር ውሳኔ ላይ እንዲደርሱ ጥረት ያደርጋል፤ መስማማት ያልቻሉ ከሆነ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ይሰጣል፣ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፤

ረ) የክልሉ መንግሥት መሥሪያ ቤቶችን በመወከል በየደረጃው ያለ ዐቃቤ ሕግ በትይዩ ባሉ ፍርድ ቤቶች ክስ ይመሠርታል፣ ሲከሰሱም መልስ ይሰጣል፣ የይግባኝ እና የሰበር አቤቱታዎችን ያቀርባል፣ በይግባኝ እና በሰበር ተጠሪነት መልስ በማቅረብ ይከራከራል፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም ደረጃውን ሳይጠብቅ ጉዳዩን ተረክቦ እንዲከራከር ያደርጋል፤

ሰ) በልዩ ሁኔታ የራሳቸው የሕግ ባለሙያ ያላቸው የኅብረት ሥራ ማኅበራት ተከራካሪ በሚሆኑባቸው የፍትሐብሔር ክሶች እና የመብት ጥያቄዎች ዙሪያ የክትትል እና ቁጥጥር ሥራዎችን ያከናውናል፤ የሕግ ድጋፍ ሲጠየቅ ድጋፍ ያደርጋል፣ መብት እና ጥቅም እንደሚጎዳ ባመነ ጊዜ በራሱ ተነሳሽነት ጉዳዩን ይዞ ይከራከራል፤

C) In collaboration with relevant parties, prepares contract documents for regional government projects and other matters, reviews draft contracts, and ensures their legality;

D) Issues no-proceeding decisions on civil cases sent to it by subordinate prosecutors; examines decisions and confirms, reverses or issues alternative orders when complaint is filed against orders and decisions of subordinate prosecutors or on its own initiative;

E) Makes them try to arrive at decision through negotiation if regional government offices have civil matters that they disagree with each other; and issues a decision on the matter if they are unable to agree, details shall be be determined by a directive;

F) Makes prosecutors at each level institute suit in parallel courts and give response when they are sued representing the regional government institutions; submit petions of appeals and cassasion, litigate through presenting responses in appeals and cassasions, take over and argue the case without waiting for the level when necessary;

G) Carries out monitoring and control activities regarding civil lawsuits and rights issues in which cooperatives with their own legal experts under special circumstances are litigants; provides legal assistance when requested; takes up the matter on its own initiative and argues the matter when it believes that rights and interests will be affected;

ኸ) ከወረዳ ፍርድ ቤት የስረ ነገር ሥልጣን ተመን በላይ በሆኑ ጉዳዮች የክልሉን ኅብረት ሥራ ማኅበራትን በመወከል ሲከሱም ሆነ ሲከሰሱ ይከራከራል፣ ይደራደራል፤ እንደ አስፈላጊነቱ ሌሎች የሕግ ድጋፎችን ይሰጣል፤

H) Litigates and negotiates on behalf of regional cooperatives in cases beyond the material jurisdiction of the wereda court; provides other legal support as necessary;

ቀ) በወንጀል ድርጊት ከባድ ጉዳት የደረሰባቸውን እና ገንዘብ ከፍለው መከራከር የማይችሉ አቅም የሌላቸው ሰለባዎች፣ የአደጋ ተጋላጭ የሆኑ ሕፃናት፣ ሴቶች፣ አካል ጉዳተኞች፣ አረጋውያን፣ የኤች አይ ቪ ኤድስ ሕሙማንን ወክሎ በድርድር ወይም በክልሉ ፍርድ ቤቶች እና በሌሎች የዳኝነት አካላት ዘንድ ክስ በመመሥረት እና በመከራከር እነዚሁ ወገኖች ካሣ እንዲያገኙ እና ፍትሐብሔር-ነክ ጥቅሞቻቸው እንዲከበሩ ያደርጋል፤

I) Represents victims of crime who have suffered serious harm and are unable to pay for legal aid, vulnerable children, women, the disableds, the elderly, and HIV/AIDS patients, and ensures that these parties receive compensation and their civil-related rights are respected through mediation or instituting suit and litigate in regional courts and other judicial bodies;

በ) በክልሉ መንግሥት መሥሪያ ቤቶች እና ድጋፍ በሚያስፈልጋቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች መካከል በሚነሡ የፍትሐብሔር ክርክሮች ጉዳዩን በድርድር ለመፍታት ጥረት ያደርጋል፤ በድርድር መፍታት ያልተቻለ እንደሆነ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችን ወክሎ ይከራከራል፤

J) Endeavors to resolve civil disputes between regional government offices and segments of the society in need of support through negotiation, and litigates on behalf of government offices if resolution through negotiation is not possible;

ተ) አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከፍትሐብሔር ጉዳይ ጋር የተያያዙ ሥልጣን እና ተግባራቱን ለሌሎች የክልሉ መንግሥት አካላት በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል፤

K) May delegate its powers and duties related to civil matters to other organs of the regional government when found necessary;

ቸ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ተ) የተደነገገው ቢኖርም በክልሉ መንግሥት መሥሪያ ቤት የተመደቡ የሕግ ባለሙያዎች ወይም ሌሎች አካላት እንደ አስፈላጊነቱ ቢሮው በግልጽ የጽሑፍ ውክልና ለሚመለከተው ተቋም እስካልሰጠ ድረስ በማንኛውም መደበኛ ፍርድ ቤት የመንግሥት መሥሪያ ቤትን ወክለው የፍርድ ቤት ክርክር አለማድረጋቸውን ይከታተላል፤

L) Notwithstanding the provision of Alphabetical Order (K) of this Sub-article, ensures that legal experts or other entities assigned to the regional government offices do not conduct legal proceedings on behalf of the government office in any regular court unless the Bureau has expressly authorized the relevant institution to do so in writing;

CamScanner

ነ) የክልሉ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሥራ ኃላፊዎች እንዲሁም በየመሥሪያ ቤቶቹ ውስጥ የሚገኙ የሕግ ባለሞያዎች ተቋማት በሚከሰሱበትም ሆነ በሚከሱበት ጊዜ ለክርክር የሚያስፈልጉ ጠቃሚ ማስረጃዎችን አሟልተው ወዲያውኑ ሥልጣን ላለው የክፍሉ ዐቃቤ ሕግ እንዲልኩ ያደርጋል፣ ያገዛል፤

M) Makes heads of the regional government offices as well as institutions having their legal professionals immediately prepare and send all the necessary evidence required for litigation to the competent prosecutor department whenever they sue or to be sued.

**17/ የሕግ ማርቀቅ እና ማጠቃለልን በተመለከተ:-**

**17/ Concerning Legislative Drafting and Consolidation of Laws**

ሀ) ከሚመለከታቸው መሥሪያ ቤቶች ጋር የመነሻ ጥናት በማድረግ ረቂቅ አዋጆችን፣ ደንቦችን እና መመሪያዎችን ያዘጋጃል፤ በሌሎች አካላት ተዘጋጅተው ሲቀርቡለት ጥራታቸውን ጠብቆ ያበለፅጋል፤

ለ) የሚዘጋጁ የሕግ ረቂቆች ከሕገ መንግሥቱም ሆነ ከክልሉ እና ከፌደራል መንግሥቱ ሕግጋት ጋር የተጣጣሙ ስለ መሆናቸው ይከታተላል፤

ሐ) የተዘጋጁ ረቂቅ ሕግጋት በሕዝብ ውይይት እንዲዳብሩ ያደርጋል፤

መ) የፀደቁ መመሪያዎችን ይመዘግባል፣ ተገቢውን ቁጥር በመስጠት ለአሠራር ምቹ ያደርጋል፣ መመሪያዎች ለሕዝብ ተደራሽ እንዲሆኑ ይሠራል፤

ሠ) የክልሉ መንግሥት ሕጎች ተግባራዊ መደረጋቸውን እና አተገባበራቸውም ወጥነት ያለው መሆኑን ያረጋግጣል፤ እንዲሁም የክልሉ መንግሥት አስፈፃሚ መሥሪያ ቤቶች ሥራቸውን በሕግ መሠረት ማከናወናቸውን በቅርብ ይከታተላል፤

ረ) በሥራ ላይ ያሉትን የክልሉን ሕጎች በየጊዜው እያጠና ወይም በሌሎች እያስጠና የሚሻሻሉበትን የውሳኔ ሐሳብ በማዘጋጀት ለክልሉ መንግሥት ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ለማሻሻያዎቹ የሚያስፈልጉትን ረቂቆችን በማዘጋጀት ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አካላት አቅርቦ ያስፀድቃል፤

ሰ) የሕግ ጉዳዮችን በተመለከተ የክልሉን መንግሥት ተቋማት ያማክራል፤

A) Prepares draft proclamations, regulations and directives by conducting initial research with relevant offices; enriches maintaining their quality when prepared and submitted to it by other bodies;

B) Monitors whether draft laws are prepared in compliance with the Constitution as well as laws of the regional and federal governments;

C) Ensures draft laws to be developed through public discussion;

D) Registers approved directives, provides same the appropriate number and makes ready for use, works for the accessibility of them to the public;

E) Ensures that laws of the regional government are implemented and uniformly implemented, as well closely monitors implementation of executive offices of the regional government is in accordance with the law;

F) Periodically reviews or make others review the existing regional laws and prepares proposals for their amendment and submits them to the regional government; when approved, prepares the drafts required for the amendments and submits them to the relevant bodies for approval;

G) Counsels the regional government institutions on legal matters;

CamScanner

ሸ) ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ዐቃብያነ ሕግ ስለ ሥራቸው ያላቸውን አመለካከት፣ እውቀት እና ክህሎት በተከታታይ እና በየደረጃው ለማሳደግ ይቻላቸው ዘንድ ተገቢውን የአቅም ግንባታ ድጋፍ እንዲያገኙ ያደርጋል፤

ቀ) የሕግ የበላይነትን ለማረጋገጥ ለክልሉ መንግሥት ባለሥልጣናት፣ ሌሎች ተሿሚዎች፣ የሕዝብ ተመራጮች፣ ሠራተኞች እንዲሁም የግሉ ዘርፍ ተሳታፊዎች እንዳስፈላጊነቱ የንቃተ ሕግ መርሃ- ግብሮችን ያዘጋጃል፣ ይሰጣል ወይም እንዲሰጥ ያደርጋል፤

በ) የክልሉን እና በክልሉ ውስጥ ተፈጻሚነት ያላቸውን የፌደራል መንግሥት ሕግጋት ያሰባስባል፣ ያደራጃል፣ ያጠቃልላል::

18/ ሰብዓዊ መብቶችን በተመለከተ:-

ሀ) የሰብዓዊ መብት ጥሰትን በተመለከተ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን እና ቅሬታዎችን ይመረምራል፣ እንዲመረመሩ ያደርጋል፤

ለ) የክልሉ መንግሥት መሥሪያ ቤቶች ዕቅድ የሰብዓዊ መብት ጉዳዮችን ያካተተ ስለ መሆኑ በቅርብ ይከታተላል፣ ይደግፋል፤

ሐ) ነፃ የሕግ ድጋፍ አሰጣጥ ስትራቴጂዎችን ይቀርፃል፣ አፈፃፀማቸውን ይከታተላል፣ በመስኩ ስትራቴጂዎችን በመቅረጽ የሚሠማሩ አካላትን ያስተባብራል፤

መ) ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በፌደራል ደረጃ የወጣው የብሔራዊ ሰብዓዊ መብት የድርጊት መርሃ ግብር በክልሉ ውስጥ ያለውን ተፈፃሚነት ይከታተላል፤ በክልል አቀፍ ደረጃ ተሳታፊ የሚሆኑትን ወገኖች እንቅስቃሴዎች ያስተባብራል፣ አግባብ ላላቸው አካላት ሪፖርት ያቀርባል፤



H) In collaboration with relevant bodies, ensures that prosecutors receive appropriate capacity building support to enable them to continuously and at all levels improve their perspectives, knowledge and skills regarding their work;

I) Prepares, provides or causes to be provided, as necessary, legal awareness programs for regional government officials, other appointees, public officials, employees and private sector participants to ensure the rule of law;

J) Compiles, organizes and summarizes laws of the region and the federal government applicable within the region.

**18. Concerning Human Rights:**

A) Investigates and causes the investigation of appeals and complaints submitted concerning human rights violations;

B) Closely Follows up and supports about the inclusion of human rights issues in plans of the regional government offices;

C) Develops free legal aid delivery strategies, monitors their implementations, and coordinates parties to be engaged in the field;

D) Monitors implementation of the National Human Rights Action Plan issued by federal level in the region in collaboration with concerned bodies of the issue; coordinates activities of participants at the regional level, and reports same to appropriate bodies;

CamScanner

ሠ) በፖሊስ ጣቢያ እና በማረሚያ ቤት ጥበቃ እና ቁጥጥር ሥር ያሉ ሰዎችን ይጎበኛል፣ አያያዛቸው እና ቆይታቸው በሕግ መሠረት መከናወኑን ያረጋግጣል፣ እንዲሁም ሕግን ተላልፈዋል በተባሉ ሰዎች ላይ በሕግ መሠረት እርምጃዎች እንዲወሰዱ ያደርጋል፤

ረ) የክልሉ ኅብረተሰብ ሰብአዊ መብቶቹን እና ግዴታዎቹን በውል ተገንዝቦ ሕግ አክባሪ እና አስከባሪ እንዲሆን በተለያዩ ዘዴዎች የሰብአዊ መብት እና የንቃተ ሕግ ትምህርት ይሰጣል፤ በዘርፉ የተሠማሩ አካላትን እንቅስቃሴዎች ያስተባብራል፤

ሰ) ኢትዮጵያ ያፀደቀቻቸው ወይም የተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ እና አህጉራዊ የሰብዓዊ መብት ስምምነቶች በክልሉ ውስጥ ያላቸውን ተፈፃሚነት ይከታተላል፤

ሸ) እንደ ሥርዓተ ፆታ እና የኤድስ ሕሙማን ያሉ ዘርፈ ብዙ እና ለአደጋ ተጋላጭ የሆኑ የኅብረተሰብ ክፍሎችን ያካተቱ የሰብዓዊ መብት ተግባራትን ያከናውናል፤

ቀ) ሰብዓዊ መብትን የሚመለከቱ ፕሮጀክቶችን ያስተባብራል፣ ይደግፋል፣ ይከታተላል፤

በ) ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት በኩል ጥያቄ ሲቀርብለት ሀገሪቱ የተቀበለቻቸውን የሰብዓዊ መብት ስምምነቶች ብሔራዊ የአፈፃፀም ሪፖርት በማዘጋጀት ረገድ ይተባበራል፣ ያግዛል፤

ተ) የክልሉ መንግሥት መሥሪያ ቤቶች ሰብዓዊ መብቶችን የማክበር እና የማስከበር ኃላፊነታቸውን በአግባቡ ስለመወጣታቸው የክትትል እና የቁጥጥር ሥራ ይሠራል፤

**19/ የጠበቆች አስተዳደርን በተመለከተ፡-**

ሀ) በክልሉ ፍርድ ቤቶች ደረጃ የጥብቅና አገልግሎት ለሚሰጡ ጠበቆች ወይም የጥብቅና ድርጅቶች ፈቃድ ይሰጣል፣ ያድሳል፣ ያግዳል፣ ይሰርዛል፤

E) Visits people under custody and control in police station and correction center, ensures their treatment and detention is carried out in accordance with law, and causes measures to be taken legal measures against those who transpassed law;

F) Provides human rights and legal-awareness education in various ways so that the regional society become obedient to law and become enforcer of same cause recognizing their human rights and obligations; coordinates activities of those involved in the sector;

G) Monitors implementation of international and continental human rights treaties ratified or adopted by the Ethiopia;

H) Performs human right activities of corss cutting issues such as gender and AIDS patients including vulnerable groups;

I) Coordinates, supports and monitors projects concerning human rights;

J) Collaborates and assists in the preparation of national implementation report on human rights treaties the country has adopted upon request from concerned bodies;

K) Monitors and supervises whether the regional government offices properly discharge their responsibilities of respecting and enforcing human rights;

**19) Concerning the Administration of Advocates:**

A) Renders, renews, suspends and revokes licenses to advocates or law firms providing advocacy services in courts at the regional level;

CS CamScanner

ለ) የጠበቆችን አገልግሎት አሰጣጥ ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤

ሐ) ለአደጋ ተጋላጭ የሆኑ ድሀ የኅብረተሰብ ክፍሎችን ፍትሕ የማግኘት መብት ለማስከበር የግል ጠበቆችን፣ የጥብቅና ድርጅቶችን ወይም ልዩ የጥብቅና ፈቃድ ያላቸውን የሲቪል ማኅበራት በማስተባበር ነፃ የሕግ ድጋፍ እንዲያገኙ ያደርጋል፤ በአገልግሎቱ ላይ ቅሬታ ሲቀርብ አጣርቶ ተገቢው የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፤

መ) ጠበቆች በሕጉ በተወሰነው ጉዳይ ልክ የነፃ የሕግ ድጋፍ አገልግሎት ስለመስጠታቸው ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፤

ሠ) ጠበቆች ለፍትሕ አጋዥ መሆን የሚያስችላቸውን ሥልጠና ይሰጣል፣ በሌሎች መሰጠቱን ይከታተላል፤

ረ) የዲሲፒሊን ጥፋት በፈፀሙ በየደረጃው በሚገኙ ጠበቆች ላይ በጠበቆች የዲሲፒሊን ጉባኤ እና በመደበኛ ፍርድ ቤቶች ፊት እየቀረበ የዲሲፒሊን ጉዳዮችን ይዞ ይከራከራል፣ ክስ ይመሠርታል።

**20/ የሰነዶች ምዝገባ እና ማረጋገጥን በተመለከተ:-**

ሀ) የማይንቀሳቀሱ ወይም ልዩ ተንቀሳቃሽ ንብረቶች የሽያጭ ውል ሕጋዊነትን በማረጋገጥ ይመዘግባል፤

ለ) ግልጽ የኑዛዜ ውሎችን ሕጋዊነት በማረጋገጥ ይመዘግባል፤

ሐ) የንግድ ማኅበራት መመሥረቻ ጽሑፎች፣ መተዳደሪያ ደንቦች እና ማሻሻያዎቻቸውን ይመዘግባል፤

መ) በክልሉ ውስጥ የሰነዶችን ሕጋዊነት ያረጋግጣል፣ ይመዘግባል፤

ሠ) በተጭበረበረ ሰነድ ወይም ያለአግባብ የተረጋገጠ እና የተመዘገበ ሰነድ በሚገኝበት ጊዜ ይህንኑ ያግዳል፣ ያጣራል፤ ያለ አግባብ ተሰጥቶ ሲገኝም ይሠርዛል፤

B) Follows up and monitors the provision of services of advocates;

C) Causes on the provision of free legal aid to poor sections of the society by coordinating private advocates, law firms or civic associations having special advocacy license in order to enforce justice aquiring rights; investigates and ensures that appropriate corrective action is taken when a complaint is made about the service;

D) Makes the proper monitoring and supervision whether advocates provide free legal aid services in accordance with the provisions of the law;

E) Provides training to advocates enabling to be advocators for justice, monitors its provision by others;

F) Litigates and institutes sue on disciplinary cases against advocates at all levels who have committed disciplinary offenses, appearing before the Lawyers' Disciplinary Council and regular courts.

**20/ Concerning Registration and Verification of Documents:**

A) Registers verifying legality of the sale contract of immovable or special movable properties;

B) Records verifying legality of public wills;

C) Records memorandum of association, article of association and their amendments of trade associations;

D) Verifies and records the legality of documents in the region;

E) Blocks and filters when forged document or improperly verified and registered document is found; deletes when it is improperly provided;

CamScanner

21/ የአገልግሎት አሰጣጥ እና ሥነ-ምግባር ክትትልን በተመለከተ፡-

ሀ) ትድሚያ የሚሰጣቸውን የደንበኞች ፍላጎቶች በጥናት በመለየት የአገልግሎት አሰጣጥ ስልት ይቀይሳል፤

ለ) በግልም ሆነ በወል የሚቀርቡ ቅሬታዎችን እና ጥቆማዎችን ተቀብሎ ያጣራል፣ ፍትሐዊ ውሳኔዎችን ይሰጣል፤

ሐ) በሥራ ላይ ያሉ ሕጎችን በመተላለፍ የዲሲፕሊን ጥፋት በፈፀሙ በየደረጃው በሚገኙ ዐቃብያነ ሕግ በዐቃብያነ ሕግ አስተዳደር ጉባኤ ፊት የዲሲፕሊን ጉዳዮችን ይዞ ይከራከራል፤ ክስ ይመሠርታል፣

መ) ከዲሲፕሊን ውሳኔዎች ጋር በተያያዘ ዐቃብያነ ሕግን አስመልክቶ ቢሮው በሰጣቸው ውሳኔዎች ላይ ለመደበኛ ፍርድ ቤቶች በሚቀርቡ የይግባኝ ጉዳዮች ላይ መልስ ይሰጣል፣ ፍርድ ቤት ቀርቦ ይከራከራል፤

ሠ) የቢሮው አገልግሎት አሰጣጥ፣ የቅሬታ አቀባበል እና የሥነ-ምግባር ደንቦች እና መመሪያዎች በሁሉም ባለሙያዎች እና አስተዳደር ሠራተኞች ዘንድ ተገቢውን ግንዛቤ አግኝተው በአግባቡ እንዲተገበሩ ለማስቻል ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት ይሠራል፤

ረ) የክልሉን የፍትሕ ሥርዓት ውጤታማ ሊያደርግ የሚችል የለውጥ ፕሮግራሞችን ይተገብራል፤ ውጤታማነቱን ይከታተላል።

22/ በሌሎች ሕጎች የተሰጡ ተግባራት እና ኃላፊነቶች እንደተጠበቁ ሆነው የፍትሕ ቢሮ ኃላፊው፡-

ሀ) የክልሉ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ሆኖ ያገለግላል፤

ለ) ረቂቅ የዐቃብያነ ሕግ መተዳደሪያ ደንብ አዘጋጅቶ ለመስተዳድር ምክር ቤት ያቀርባል፣ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

ሐ) የየደረጃውን ዐቃብያነ ሕግ በሚወጣው ደንብ መሠረት ይሾማል፣ ያስተዳድራል፣ ያሰናብታል፤



21/ Concerning the Followup of Service Delivery and Ethics

A) Designs service delivery strategies by identifying the prioritize customer needs through study;

B) Verifies complaints and suggestions given by private as well as in common by receiving them, and gives fair decisions therefor;

D) Handles disciplinary matters before the Prosecutors' Administrative Council against prosecutors at all levels who have committed disciplinary offenses in violation of applicable laws; files charges against them;

E) Responds to and litigates in court on appeals to regular courts against decisions made by the Bureau regarding prosecutors in relation to disciplinary decisions;

F) Works in coordination with relevant parties to ensure that service delivery, complaint handling, and ethical regulations and directives of the Bureau are properly understood and implemented by all professionals and administrative staff of the Bureau;

G) Implements reform programs that can make the regional justice system effective; monitors its effectiveness.

**22/ Without prejudice to the duties and responsibilities assigned by other laws, the Head of the Justice Bureau shall:**

A) Serves as being Attorney General of the region;

B) Prepares draft bylaw of prosecutors and submits it to the Government Council, and implements same upon approval;

C) Appoints, administers and dismisses prosecutors of each level in accordance with the bylaw to be issued;

መ) የሕዝብ ጥቅም መኖሩ በግልፅ ሲታወቅ የወንጀል ምርመራ እንዲቋረጥ ወይም የተቋረጠ የወንጀል ምርመራ እንዲቀጥል፣ የተጀመረ ክስ እንዲነሣ፣ የተነሣ ክስ እንዲቀጥል ያደርጋል፤

ሠ) ከሙስና እና ከሌሎች ወንጀሎች ጋር በተያያዘ በፍርድ ቤት የዕግድ ትዕዛዝ እስኪወጣ ድረስ ንብረቱ እንደሚባክን ሲያምንበት ወይም አስቸኳይ ሁኔታ ሲያጋጥም አግባብ ባለው ሕግ መሠረት እንዲያዝ ወይም እንዲታገድ ጊዜያዊ ትዕዛዝ ይሰጣል፤

ረ) በንብረት ማስመለስ ሂደት በተፋጠነ ሁኔታ ሊሸሽ ወይም ኢኮኖሚያዊ ጥቅምን ሊያሳጣ የሚችል ድርጊት መኖሩ ሲታመንበት አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ንብረቱ እንዲታገድ፣ የተጠርጣሪ ንብረት፣ የባንክ ሒሳብ፣ ሰነዶች እና ሌሎች ተመሳሳይ ጉዳዮች እንዲያዙ፣ እንዲታገዱ ትዕዛዝ ይሰጣል፤ በሕጉ በተመለከተው አግባብ ለፍርድ ቤት ያሳውቃል፤

ሰ) በምክትል ቢሮ ኃላፊ ወይም በሌሎች ዐቃብያነ ሕግ የተሰጡ ውሳኔዎችን ይሽራል፣ ያሻሽላል፣ ያፀናል ወይም ጉዳዩ እንዲጣራ ወይም ውሳኔውን በሰጠው አካል እንደገና እንዲታይ ያደርጋል፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘውም መዛግብትን አስቀርቦ የተፈፀመ ስህተት ቢኖር ጉዳዩ እንደገና እንዲንቀሳቀስ እና ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት እንዲቀርብ ያደርጋል፤

ሸ) በግብር እና ታክስ ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎችን በተመለከተ በክልሉ ገቢዎች ቢሮ የሚተዳደረው ዐቃቤ ሕግ አጣርቶ የክስ አይቀርብም ውሳኔ የሰጠባቸውን ውሳኔዎች ይከልሳል፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘውም ክርክሩ በተዋረድ የተካሄደባቸውን መዛግብት አስቀርቦ የተፈፀመ ስህተት ቢኖር ጉዳዩ እንደገና እንዲንቀሳቀስ እና ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት እንዲቀርብ አግባብ ላለው አካል ትዕዛዝ ይሰጣል::

D) Where it is clearly in the public interest, causes a criminal investigation to be discontinued or a discontinued criminal investigation to be continued, an initiated case to be dismissed, or an initiated case to be continued;

E) Where it is believed that the property will be wasted until a restraining order is issued by the court in relation to corruption and other crimes or in cases of emergency, issues a temporary order to seize or freeze it in accordance with the relevant law;

F) When it is believed that there is an act that could lead to the expeditious escape or economic loss in the asset recovery process, orders the freezing of the assets, the seizure of the suspect's assets, bank accounts, documents and other similar matters in accordance with the relevant law; notifies same to the court as provided for by the law;

G) Annuls, amends and upholds decisions made by Deputy Head of the Bureau or other prosecutors, or causes the case to be investigated or reviewed by the body that issued the decision; when he finds it necessary, causes the case to be re-opened and submitted to the competent court with the necessary documents, if there is any error made;

H) Investigates and reviews decisions made by a prosecutor administered by the regional bureau of revenues regarding crimes committed against tribute and taxes; if he finds it necessary, he orders the appropriate body to re-open the case and present it to the competent court, after reviewing the records of the proceedings undertaken in lower hierarchies.

## 37. የሰላም እና ፀጥታ ቢሮ

በሌሎች ሕጎች አስቀድሞ የተደነገገው ወይም ወደ ፊት የሚደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ ሰላም እና ፀጥታ ቢሮ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ዝርዝር ሥልጣን እና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1/ ከሰላም ጋር የተያያዙ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችን እና ሕጎችን ያመነጫል፣ በሚመለከተው አካል ሲፀድቁም በሥራ ላይ ያውላል፤

2/ አግባብ ካላቸው የፌደራል እና የክልል መንግሥታት አካላት ጋር በመተባበር በክልሉ የሕግ የበላይነትን ለማስከበር እና ሰላም ለማስጠበቅ ይሠራል፤ የሕዝብ ሰላም እንዲከበር የሚያስችል ስልት ይነድፋል፣ የግንዛቤ እና የንቅናቄ ሥራዎችን ያከናውናል፤

3/ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ክልላዊ እና ሀገራዊ አንድነት እና መግባባትን የሚያጎለብት የባሕል ልውውጥ የሚካሄድበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

4/ በተለያዩ ሃይማኖቶች እና እምነቶች ተከታዮች እንዲሁም በተለያዩ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች መካከል ሰላም እና መከባበር እንዲሰፍን ለማድረግ አግባብ ካላቸው የመንግሥት አካላት፣ የባሕል እና የሃይማኖት ተቋማት ጋር በመተባበር ይሠራል፤

5/ በወሳኝ ሀገራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ብሔራዊ መግባባት እንዲፈጠር አግባብነት ያላቸውን አካላት ያስተባብራል፤ የመፍትሔ ሐሳቦችን ለመንግሥት ያቀርባል፣ ሲወሰንም አፈጻፀሙን ይከታተላል፤

6/ የክልሉን ሰላም ሊያናጉ በሚችሉ የተለያዩ ሕገ ወጥ ተግባራት ላይ ተሠማርተው የፍርድ ውሳኔ ያልተሰጠባቸውን አካላት የክልሉ መንግሥት ሲያምንበት ተቀብሎ አጫጭር የተሐድሶ ሥልጠና ይሰጣል፣ ከኅብረተሰቡ ጋር ተቀላቅለው በሰላም የሚኖሩበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣ እንዲቋቋሙ ያደርጋል፤

## 37. Bureau of Peace and Security

Without prejudice to existing or subsequent provisions of other laws, the regional Bureau of Peace and Security shall, pursuant to this proclamation, have the following particular powers and duties:

1/ Initiates policies, strategic and laws related to peace, and implements them once approved by the relevant body;

2/ In collaboration with appropriate federal and regional government bodies, works to enforce the rule of law and maintain peace in the region; devises a strategy to ensure public peace, and carries out awareness and mobilization activities;

3/ In cooperation with relevant bodies, facilitates the development of cultural exchanges that enhance regional and national unity and understanding;

4/ works in cooperation with relevant government bodies, cultural and religious institutions to promote peace and respect among followers of different religions and beliefs as well as among different nations, nationalities and peoples;

5/ Coordinates relevant bodies to create national consensus on important national issues; submits recommendations to the government, and monitors their implementation when decided;

6/ Accepts individuals, when the regional government believes, who have not been convicted of various illegal activities that may disrupt the peace of the region and provides them short-term rehabilitation training; facilitates their integration into the society and enable them to live peacefully, and ensures their rehabilitation;

7/ በሃይማኖት፣ በብሔር እና ሌሎች ምክንያቶች ሽፋን የሚደረግ የአክራሪነት እና የፅንፈኝነትን አስተሳሰብ ለመከላከል የሚያስችሉ ስልቶችን ይቀይሳል፣ ያስፈፅማል፤

7/ Designs and executes strategies to prevent begotry and extremism ideology under the guise of religion, ethnicity and other reasons;

8/ በኅብረተሰቡ መካከል የሰላም፣ የመከባበር እና የመቻቻል ባሕል እንዲዳብር የግንዛቤ ማሳደጊያ ንቅናቄዎችን ያካሂዳል፣ ስልቶችን ይቀይሳል፣ አተገባበሩን ይከታተላል፤

8/ Undertakes awareness-raising campaigns to develop a culture of peace, respect and tolerance among the society, designs strategies and monitors their implementation;

9/ ለአካባቢያዊ ግጭቶች መንስኤ የሆኑ ጉዳዮችን በጥናት ይለያል፤ ኅብረተሰቡ ወደ ግጭት እና አለመረጋጋት እንዳያመራ የመፍትሔ አቅጣጫዎችን የሚያመላክት ጥናት ያቀርባል፤ ሲወሰንም ተግባራዊ ያደርጋል፤

9/ Identifies issues that cause local conflicts through research; presents research indicating solutions to prevent the society from leading to conflict and instability, and implements same when decided;

10/ የሃይማኖት ተቋማት በተናጠል እና በጉባኤያቸው በኩል ለክልሉ ሰላም እና አብሮነት ለሚያደርጉት አስተዋፅዖ ድጋፍ ያደርጋል፣ እውቅናም ይሰጣል፤

10/ Supports and recognizes contributions of religious institutions, individually and through their congregations, to peace and solidarity in the region;

11/ በፌደራል መንግሥት እና በክልሎች መካከል በመግባባት እና በአጋርነት ላይ የተመሠረተ መልካም ግንኙነት እና ትብብር እንዲኖር በማድረግ የፌደራል ሥርዓቱ እንዲጠናከር የግንኙነቱ ማዕከል ሆኖ ያገለግላል፤

11/ Serves as center of the relationship to strengthen the federal system through causing the existence of good relations and cooperation based on understanding and partnership between the federal government and the regions;

12/ አግባብ ካላቸው የክልል እና የፌደራል መንግሥቱ አካላት ጋር በመተባበር በየትኛውም የክልሉ አካባቢዎች ዜጎች በሰላማዊ ሁኔታ የሚኖሩበት እና የሚንቀሳቀሱበትን ሥርዓት ይዘረጋል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

12/ Establishes a system in which citizens can live and move peacefully in any part of the region, in cooperation with the appropriate regional and federal government bodies, monitors its implementation;

13/ የክልሉ ሕዝብ ሰላም፣ ደኅንነት እና ነፃነት እንዲከበር የሚያስችሉ ስልቶችን ይነድፋል፤ የተቋሙን አጠቃላይ የመፈፀም አቅም ያሳድጋል፣ አዳዲስ አቅም የሚፈጥሩ የማሻሻል ስልቶችን ይነድፋል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፤

13/ Devises strategies that will ensure the peace, security and freedom of the people of the region; enhances the overall performance capacity of the institution, devises and implements improvement strategies that will create new capabilities;

CS CamScanner

14/ የሰላም እሴቶችን በመገንባት እና በማስፋፋት ረገድ የክልላዊ ወጎችን፣ እሴቶችን እና ባሕሎችን ባማከለ መልኩ በኅብረተሰቡ ውስጥ ተከታታይነት ያላቸው የግንዛቤ ትምህርቶችን በማሳደግ የንቅናቄ ተግባራትን ያከናውናል፣ እንዲከናወኑ ያደርጋል፤

15/ በሕዝቦች መካከል አስተሳሳሪ እና አሻጋሪ የሆኑ ሐሳቦችን በማስረጽ ዘላቂ ሰላም እንዲፈጠር ይሠራል፣

16/ በክልሉ ውስጥ ባሉ የአስተዳደር መዋቅሮችም ሆነ ከአጎራባች ክልሎች ጋር የሚነሡ አለመግባባቶች እና ግጭቶች በሰላማዊ መንገድ እንዲፈቱ ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፤ የክልሉን ሰላም እና ደኅንነት ለማረጋገጥ የሚያስችል የምክክር፣ የትብብር፣ የትንጅት ሥራዎችን ይሠራል፤

17/ የክልሉን ሕዝብ አደጋ ላይ የሚጥሉ ስጋቶችን በመለየት መረጃ ይሰበስባል፣ ያደራጃል፣ ይተነትናል፤ ለሚመለከተው የበላይ አካል ለውሳኔ ያቀርባል፤

18/ የክልሉ ሚሊሻ እና ሰላም አስከባሪ ኃይል የሚጠቀምባቸውን የጦር መሳሪያዎች ይመዘግባል፣ ያስታጥቃል፣ ያወርዳል፣ ያስተዳድራል፣ ይቆጣጠራል፤

19/ በጥናት ላይ ተደግፎ የግጭት መንስኤዎችን ይለያል፤ ግጭት ሲከሰት ባሕላዊ እና ዘመናዊ የግጭት አፈታት ዘዴዎችን በመጠቀም እንዲፈታ ይሠራል፤ በግጭቱ ውስጥ የተካፈሉ ተዋናዮችን እንዲረጋጉ የሚያስችሉ ተግባራትን ያከናውናል፤

20/ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን በክልሉ ውስጥ የሚገኙ የሚሊሻ እና የሰላም አስከባሪ አባላት እና አመራሮች በሰብዓዊ እና ዴሞክራሲያዊ መብቶች አያያዝ፣ አጠባበቅ እና የሰብዓዊ መብቶች ማክበር እና ማስከበር ዙሪያ አቅማቸውን እንዲገነባ ይሠራል፤



14/ Carries out and causes for the implementation of mobilization through enhancing continuous awareness lessons in the society based on regional customs, values and cultures regarding building and promoting peace cultures;

15/ Works to create lasting peace by instilling harmonious and transformative ideas among the people;

16/ Creates a favorable environment for the peaceful resolution of disputes and conflicts arising within the administrative structures of the region and with neighboring regions; carries out consultation, cooperation and coordination activities to ensure the peace and security of the region;

17/ Collects, organizes, analyzes and presents information to relevant superior body for decision by identifying threats to the people of the region;

18/ Registers, equips, disposes, manages and controls weapons used by the regional militia and peacekeeping force;

19/ Based on research, identifies causes of conflict; works for resolution of conflicts using traditional and modern conflict resolution methods; carries out activities that will help stabilize the actors involved in the conflict;

20/ Works with relevant parties to build the capacity of militia and peacekeeping members and leaders in the region in human and democratic rights management, protection, and respect and enforcement of human rights;

CamScanner

21/ የሚሊሻ እና የሰላም አስከባሪ ኃይል የሚመሩባቸውን ፖሊሲዎች፣ ሕጎች፣ ስትራቴጅዎች እና የአሠራር ሥርዓቶች ያመነጫል፤ ተልዕኳቸውን ለመፈፀም የሚያስፈልጋቸውን የሰው ኃይል፣ የትጥቅ እና የሌሎች አጋዥ ቁሳቁሶች ፍላጎት ያጠናል፤ በጥናቱ መሠረትም ግብዓቶቹ በወቅቱ እንዲሟሉ ያደርጋል፤

22/ በግጭት መከላከል፣ አያያዝም ሆነ አፈታት እና በሕዝብ ደኅንነት አጠባበቅ ረገድ አግባብ ካላቸው የፌደራሉ መንግሥት እና ሌሎች አካላት ጋር የሥራ ግንኙነቶችን ያደርጋል፣ ችግሮችን በጋራ መድረኮች ይፈታል፤

23/ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ እና በክልሉ መንግሥት ሲታመንበት የሀገር ሰላም እና ደኅንነትን ለማስከበር ከአገር መከላከያ ሠራዊት ጋር በቅንጅት ይሠራል።

## 38. የባሕል፣ ቱሪዝም እና ስፖርት ቢሮ

በሌሎች ሕጎች አስቀድሞ የተደነገገው ወይም ወደ ፊት የሚደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ የባሕል፣ ቱሪዝም እና ስፖርት ቢሮ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ዝርዝር ሥልጣን እና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1/ ቱሪዝምን፣ ባሕልን እና ስፖርትን የሚመለከቱ የፖሊሲ ሐሳቦችን ያመነጫል፤ ስትራቴጂዎችን፣ ሕጎችን ይቀርጻል፣ ለአፈፃፀሙ ከሀገራዊ እና ክልላዊ የልማት አቅጣጫ ጋር የተጣጣመ ዝርዝር መርሃ ግብር ያዘጋጃል፣ በሚመለከተው አካል ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፣ ሥራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፤

2/ የክልሉን ሕዝብ የመልካም ባሕል እሴቶች እና ሀገር በቀል እውቀቶች ያጠናል፤ ተጠብቀው ለተተኪው ትውልድ እንዲሸጋገሩ ያደርጋል፣ መልካም የባሕል ገፅታውን ያለማል፣ ይከታተላል፤

21/ Develops policies, laws, strategies and systems of procedure for the militia and peacekeeping forces; studies needs of manpower, weapons and other supporting materials needed to carry out their missions; and makes the inputs to be fulfilled timely based on the study;

22/ Establishes working relationships with the relevant federal government and other entities regarding conflict prevention, management and resolution, and public safety; solves problems through joint forums;

23/ When found necessary and believed by the regional government, works in coordination with the National Defense Forces to maintain national peace and security.

## 38. Bureau of Culture, Tourism and Sports

Without prejudice to what has been previously or may be provided for in other laws, the Regional Culture, Tourism and Sports Bureau shall have the following detailed powers and duties under this Proclamation:

1/ Generates policy ideas related to tourism, culture and sports; formulates strategies and laws; prepares a detailed program for its implementation in line with the national and regional development directions; implements same upon approval by the relevant body; and monitors its implementation;

2/ Studies the values of good culture and indigenous knowledge the people of the region; makes them to be passed to the next generation being preserved; develops and monitors the good cultural images;

3/ በክልሉ ውስጥ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች እና መጤ ባሕሎች እንዲወገዱ እና ጠቃሚ የባሕል እሴቶች እንዲስፋፉ ኅብረተሰቡን በማሳተፍ ከተለያዩ መንግሥታዊ እና መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር በትንጅት ይሠራል፤

4/ ማኅበራዊ ዕድገትን የሚያንቀፉ አመለካከቶችን፣ አጉል እምነቶችን እና ልማዳዊ ድርጊቶች እንዳይስፋፉ ይሠራል፣ ግንዛቤ ይፈጥራል፤ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በትንጅት ይሠራል፤

5/ የክልሉን ሕዝብ መልካም ባሕል እና እሴቶች ለማልማት በክልሉ ውስጥ የባሕል ቡድኖች እና የኪነ ጥበብም ሆነ የዕደ ጥበብ ክበባት እንዲደራጁ ያደርጋል፤ በባሕል፣ በቱሪዝም እና በስፖርት ኢንዱስትሪው ልማት ገብተው በንቃት እንዲሳተፉ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣ ያበረታታል፤

6/ በባሕል ዘርፉ ለሚሠማሩ አካላት የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ይሰጣል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

7/ የክልሉን መልካም ባሕል እና እሴቶች ለመንከባበከብ፣ ለማጥናት፣ ለኤግዚቢሽን ለማቅረብ እንዲሁም ሳይንሳዊ፣ ታሪካዊ እና ሥነ-ጥበባዊ ትንታኔ የሚሰጡባቸውን ሙዚየሞች ያለማል፣ ያስፋፋል፣ ያስተዳድራል፤

8/ በክልሉ ውስጥ የሚኖሩት ብሔር ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ታሪክ እና ባሕል በሚገባ ተመዝግቦ እንዲያዝ እና እንዲጠና፣ ቋንቋዎቻቸውም እንዲዳብሩ እና እንዲስፋፉ ያደርጋል፤ የባሕል ፌስቲባሎችን ያዘጋጃል፤

9/ በክልሉ ውስጥ ባሕል-ነክ የሆኑ መረጃዎችን ያሰባስባል፣ ያጠናቅራል፣ ይተነትናል፣ ያሰራጫል፣

3/ Works in coordination with various governmental and non-governmental organizations to eliminate harmful traditional practices and newcoming cultures in the region and to promote valuable cultural values through involving the community;

4/ Works to prevent the spread of attitudes, superstitions and traditional practices that hinder social development and creates awareness; works in coordination with relevant parties;

5/ Makes cultural groups and art as well as craft clubs get organized in the region to develop the good culture and values of the people of the region; facilitates conditions and encourages them to actively participate in the development of culture, tourism and sports industries;

6/ Issues professional qualification assurance certificates to entities engaged in the cultural sector, monitors and supervises its performance;

7/ Establishes, expands and manages museums to preserve and study the good culture and values of the region, present same to exhibition, as well as to provide scientific, historical and artistic analysis;

8/ Ensure that the history and culture of the nations, nationalities and peoples living in the region are properly recorded and studied, and their languages are developed and promoted; organizes cultural festivals;

9/ Collects, compiles, analyzes and disseminates cultural information in the region;

CamScanner

10/ መንግሥታዊ እና ሕዝባዊ የባሕል አገልግሎት ተቋማት፣ ሙዚየሞች፣ የባሕል ማዕከል፣ የባሕል አዳራሾች፣ ቤተ መጽሐፍት እና መዝገብ ቤት፣ የትያትር እና ፊልም ቤቶች በክልሉ ውስጥ እንዲስፋፉ ይሠራል፣ የሙያ ፈቃድ ይሰጣል፣ ይመዘግባል፤

11/ በክልሉ መልካም ባሕል እና እሴት ግንባታ ዕድገት ውስጥ የላቀ ውጤት ያስመዘገቡ አካላትን ያበረታታል፣ ዕውቅና እንዲያገኙ ያደርጋል፣ ይሸልማል፤

12/ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን ሕዝቡን በስፖርት ለሁሉም እና ባሕላዊ ስፖርት ተሳታፊ እና ተጠቃሚ እንዲሆን ያደርጋል፤

13/ የክልሉን ሕዝብ ቋንቋዎች፣ ታሪክ እና ጥበብ እንዲስፋፋ በበላይነት ይሠራል፤ የክልሉን ሕዝብ ቋንቋዎች፣ ታሪክ እና ጥበብ ያጠናል፣ ለሚያጠና አካል ድጋፍ ይሰጣል፤ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን በመደበኛ የትምህርት ሥርዓት ውስጥ እንዲካተቱ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

14/ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን በክልሉ ውስጥ የሚለጠፉ የንግድ ስሞች፣ ማስታወቂያዎች እና የመሳሰሉት ጽሑፎች የኅብረተሰቡን ባሕል እና እሴቶች የጠበቁ እንዲሆኑ ያደርጋል፤ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

15/ የቱሪዝም እና ቅርስ ልማት ተግባራትን በቀጣይነት የሚያረጋግጡ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችን እና የሕግ ማዕቀፎችን ያመነጫል፣ ለአፈፃፀሙ ዝርዝር መርሃ ግብር ያዘጋጃል፣ ሲፀድቅለትም ተግባራዊ ያደርጋል፤

16/ የክልሉን የቱሪዝም ሀብቶች እና ቅርሶች በሀገር ውስጥ እና በውጭ ሀገር የማስተዋወቅ ሥራ ይሠራል፣ ቱሪዝምን ያስፋፋል፤

17/ የክልሉን የቱሪዝም፣ የማኅበረሰብ አቀፍ እና የኢኮቱሪዝም መስህቦች በመለየት ለቱሪዝም ገበያ አመቺ ሆነው እንዲደራጁ እና እንዲለሙ ያደርጋል፤

10/ Works to promote the expansion of governmental and public cultural service institutions, museums, cultural centers, cultural halls, libraries and archives, theaters and cinemas in the region; issues and registers professional licenses;

11/ Encourages, recognizes and rewards entities that have achieved outstanding results in development of good culture and value building of the region;

12/ Makes the people to participate and benefit from sports for all and traditional sports in collaboration with the relevant bodies,

13/ Works ontop of promoting languages, history and arts of the people of the region; studies languages, history and arts of the people of the region, and provides support to studying entities; facilitates conditions for their inclusion in the regular education system being with the relevant bodies;

14/ Makes trade names, advertisements and similar articles posted in the region respect the culture and values of the society being with the relevant body; monitors its implementation;

15/ formulates policies, strategies and legal frameworks that ensure the continuity of tourism and heritage development activities; prepares detailed program for its implementation, and implements it upon approval;

16/ Promotes the region's tourism resources and heritages both domestically and abroad, and promotes tourism;

17/ Identifies the region's tourism, community-based and ecotourism attractions and makes them to be organized and developed in a manner suitable for the tourism market;

CamScanner

18/ የክልሉን የቱሪዝም ገበያ ጥናት በማካሄድ ባለ ድርሻ አካላት የሚያከናውኗቸውን ተግባራት በመለየት፣ የገበያ ትስስር እንዲፈጠር በማድረግ ዘርፉ ለኢኮኖሚ የሚያበረክተውን ድርሻ ያሳድጋል፤

19/ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን አዳዲስ የቱሪዝም መስህቦች እንዲለሙ፣ የቱሪዝም መዳረሻዎች በመሠረተ ልማት እንዲጎለብቱ እና የቱሪዝም ምርት እና አገልግሎት በዓይነት እና በመጠን እንዲያድጉ እና ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ያደርጋል፤

20/ የክልሉን ቅርሶች እና የቱሪዝም መስህቦች መሟላት ያለባቸውን ስታንዳርዶች እንዲያሟሉ በማድረግ በዓለም አቀፍ ቅርስነት እንዲመዘገቡ ያደርጋል፣ ድጋፍ ይሰጣል፤ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት ይሠራል፤

21/ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት በመሥራት የቅርስ ጥገና እና እንክብካቤ ያደርጋል፣ ያስደርጋል፣ የሙያ ድጋፍ ይሰጣል፤

22/ በክልሉ ውስጥ የስፖርት፣ የኤግዚቢሽን፣ የስብሰባ፣ አግሮ ቱሪዝም እና የመሳሰሉት ቱሪዝሞች እንዲስፋፉ ያደርጋል፤

23/ የክልሉን የተፈጥሮ እና ሰው ሠራሽ መስህብ ሀብቶች እንዲጠኑ፣ እንዲጠበቁ እና ለቱሪዝም አመቺ ሆነው ጥቅም ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፤

24/ የቱሪዝም ዘርፉ በቴክኖሎጂ፣ በጥናት እና ምርምር እንዲደገፍ እና ለክልሉ ኢኮኖሚ ሁለንተናዊ አስተዋፅዖ እንዲያበረክት አፈጻፀሙን ይከታተላል፤

25/ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን በክልሉ ውስጥ የሚገኙ ብሔራዊ ፓርኮች፣ ፓርኮች፣ ጥብቅ ስፍራዎች እና የማኅበረሰብ አቀፍ ጥብቅ ስፍራዎች እንዲሁም የዱር እንስሳት ጥብቅ ቦታዎች የመስህብ ሀብት በመሆን ለኅብረተሰቡ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም እንዲያመነጩ ያደርጋል፤

18/ Increases the sector's contribution to the economy through conducting tourism market study of the region, identifying activities of stakeholders and creating market linkages;

19/ Works with concerned bodies to develop new tourism attractions, develop tourism destinations through infrastructure, and increase the variety and scale of tourism products and services and make them competitive;

20/ Ensures that the region's heritages and tourism attractions meet the required standards and are registered as world heritage sites; provides support, and works with concerned bodies;

21/ Makes and causes to be made heritage maintenance and care through working in coordination with concerned bodies; provides professional support;

22/ Causes sports, exhibition, conference, agro-tourism and other tourism activities to be promoted in the region;

23/ Ensures that the natural and man-made attractions of the region to be studied, protected and utilized in a manner suitable for tourism;

24/ Monitors the implementation of the tourism sector so that it is supported by technology and research, and contribute to the overall economy of the region;

25/ Being with relevant bodies, ensures that national parks, parks, protected areas and community-based protected areas as well as wildlife sanctuaries in the region become resource of attraction and generate economic benefits for the society;

26/ በቱሪዝም ዘርፍ ልማት የግል ዘርፉን ተሳትፎ እና ሚና ለማሳደግ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፣ ለአፈፃፀም ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፤

27/ የቱሪስት አገልግሎት ሰጭ ተቋማትን ደረጃ ይወስናል፤ በሆቴል እና ቱሪዝም ዘርፍ ለሚሠማሩ አካላት የአገልግሎት ብቃት ማረጋገጫ ይሰጣል፤

28/ በክልሉ ውስጥ በቱሪዝም ዘርፍ ለሚሠማሩ የባለ ኮከብ ሆቴሎች ደረጃ እና ተገቢውን ሙያዊ ድጋፍ ይሰጣል፤ ለሥራ ምቹ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

29/ ከመንግሥት፣ ከማኅበረሰብ፣ ከማኅበር እና ከግል የቱሪዝም ተዋናዮች ጋር በመሆን ጥራት ያለው የቱሪዝም ምርት እና አገልግሎት ማቅረብ ይችሉ ዘንድ ከአጋር አካላት ጋር ትብብር በመፍጠር ይሠራል፤

30/ የክልል የቱሪዝም ምክር ቤት የሚጠበቅበትን ሚና እንዲያበረክት ምቹ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

31/ የሚዳሰሱ እና የማይዳሰሱ ቅርሶችን ይለያል፣ ይመዘግባል፤ የሕገ ወጥ ቅርሶችን ዝውውር ለመከላከል እና የተዘረፉትን ለማስመለስ ከተለያዩ ባለ ድርሻ እና አጋር አካላት ጋር በትብብር ይሠራል፤

32/ የቅርሶች ይዞታ ሕጋዊ ወሰን፣ የይዞታ ማረጋገጫ እና የአስተዳደር እቅድ እንዲኖራቸው ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በትብብር ይሠራል፤

33/ በክልሉ በሚገኙ የቱሪዝም መዳረሻዎች እና የመስህብ ስፍራዎች የጎብኝዎችን የመግቢያ እና የሌሎች አገልግሎት ክፍያዎችን የክፍያ ተመን በጥናት ይወስናል፤

34/ በክልሉ ውስጥ ቱሪዝም-ነክ እና የቅርስ ልማት መረጃዎችን ያሰባስባል፣ ያጠናቅራል፣ ይተነትናል፣ ያሰራጫል፤

35/ የሀገር ውስጥ እና የውጭ ሀገር ጎብኝዎች ቁጥር እንዲጨምር ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት ይሠራል፣ ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፤

26/ Establishes a system to increase the participation and role of the private sector in the development of the tourism sector, and creates a conducive environment for its implementation;

27/ Determines level of tourist service provider institutions; provides service qualification assurance to entities engaged in hotel and tourism sector;

28/ Provides the level and appropriate professional support to star hotels to be engaged in the tourism sector in the region; facilitates favorable conditions for work;

29/ Works creating collaboration with stakeholders being with government, community, association and private tourism actors to provide quality tourism products and services;

30/ Facilitates favorable conditions so that the Regional Tourism Council to play its expected role;

31/ Identifies and registers tangible and intangible heritages; works in collaboration with various stakeholders and partners to prevent the illegal transfer of heritage and recover looted heritages;

32/ Works in collaboration with relevant parties so that heritage holdings to have legal boundaries, holding verification and management plans;

33/ Studies and determines the rates of admission and other service fees for visitors to tourism destinations and attraction sites in the region;

34/ Collects, compiles, analyzes and disseminates tourism-related and heritage development information in the region;

35/ Works in coordination with relevant bodies to increase the number of domestic and foreign visitors; and creates favorable conditions;

CamScanner

36/ በክልሉ ውስጥ በማንኛውም ሰው፣ ማኅበር፣ የሃይማኖት ድርጅት ወይም ተቋም እጅ የሚገኙ ቅርሶች በሚገባ እንዲያዙ እና እንዲጠበቁ ድጋፍ ይሰጣል፤ ይመዘግባል፣ ይቆጣጠራል፤ በኤግዚቢትነት የተያዙ ቅርሶችን፣ የዱር እንስሳት ውጤቶችን ተቀብሎ አግባብነት ባለው መንገድ ያስተዳድራል፤

36/ Provides support for the proper management and protection of heritages in the hands of any person, association, religious organization or institution in the region; registers, controls; receives and manages exhibits and wildlife products and in an appropriate way;

37/ በተለያዩ ምክንያቶች በሕገ ወጥ መንገድ ከክልሉ የወጡ የክልሉ ባሕል እና እሴቶች መገለጫ የሆኑ ጥንታዊ እና ባሕላዊ ቅርሶች እንዲመለሱ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በትብብር ይሠራል፤

37/ Works in coordination with relevant bodies to return ancient and cultural heritages being manifestation of the culture and values of the region which have been illegally removed from the region in various reasons;

38/ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን የቱሪዝም መስህብነት ያላቸው የቅሪት አካላት፣ የእምነት እና የተፈጥሮ ሀብት ሥፍራዎች በሕግ እንዲከለሉ እና እንዲጠበቁ ያደርጋል፣ ያለማል፤

38/ Makes fossils having attractions, religious and natural resource sites to be demarcated and protected by law, being with the concerned body; develops same;

39/ ቅርሶች እና የመስህብ ሀብቶች ለዘላቂ እና ሁሉንተናዊ እድገት አስተዋፅዖ እንዲያደርጉ እና ለተተኪው ትውልድ እንዲተላለፉ የክልሉን ነዋሪ ሕዝብ፣ የመንግሥት አካላት እና የሌሎች ደጋፊ አካላትን እውቀት፣ ሀብት እና ጉልበት በማስተባበር በዘላቂነት እንዲጠበቁ እና እንዲጠገኑ ይሠራል፤

39/ Work to sustainably protect and maintained heritages and tourist attractions so that they contribute to sustainable and inclusive development and are passed to future generations through coordinating the knowledge, resources and force of the regional population, government bodies and other supporting bodies;

40/ ከቱሪዝም ሚኒስቴር እና ከክልሉ ፕላንና ልማት ቢሮ ጋር በመተባበር የቱሪዝም ሳተላይት አካውንት በክልላዊ እና አገራዊ የኢኮኖሚ አካውንት ሥርዓት ውስጥ ለማዋሐድ ሥርዓት ይዘረጋል፤

40/ In cooperation with the Ministry of Tourism and the Regional Planning and Development Bureau, establishes a system to integrate the Tourism Satellite Account into the regional and national economic account system;

41/ የክልሉን ስፖርት-ነክ መሠረታዊ መረጃዎች ያሰባስባል፣ ያደራጃል፣ ይተነትናል፣ ለሚመለከታቸው አካላት ያሠራጫል፤ የጥናት እና ምርምር ሥራዎችን ያካሂዳል፣ የሥልጠና ስታንዳርዶችን እና የአቅም ግንባታ ፓኬጆችን እያዘጋጀ ከትምህርት ተቋማት ጋር በመተባበር ለስፖርት ልማት ሥልጠና እንዲሰጥ ያደርጋል፣ አፈፃፀሙንም ይከታተላል፤

41/ Collects, organizes and analyzes basic information related to sports in the region and disseminates to relevant bodies; undertakes research works, prepares training standards and capacity building packages and makes training to be provided for sports development in collaboration with educational institutions, and monitors its implementation;

CamScanner

42/ ስፖርትን በተመለከተ በሀገር አቀፍ ደረጃ የወጡ ፖሊሲዎች እና ስትራቴጂዎች በክልሉ ነዋሪ ኅብረተሰብ ዘንድ በሚገባ ሠርፀው በክልሉ ውስጥ እንዲተገበሩ ይሠራል፣ ይከታተላል፣ ያስተባብራል፣ ይቆጣጠራል፤

43/ በክልሉ ውስጥ የተለያዩ ስፖርቶች ሊስፋፉ የሚችሉባቸውን አካባቢዎች እና ለስፖርቱ ዕድገት አስተዋፅዖ ያላቸውን ፀጋዎች ለይቶ ጥቅም ላይ ለማዋል የስፖርት ፕሮጀክቶችን እና ተቋማትን ያቋቁማል፤ ተገቢውን ድጋፍ እና ክትትል በማድረግ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሆኑ ስፖርተኞችን ለማፍራት ይሠራል፤

44/ ኅብረተሰብ አቀፍ የስፖርት ተሳትፎ ፕሮግራም ወይም ፓኬጅ በማዘጋጀት ማኅበረሰቡ በሚኖርበት፣ በሚሠራበትም ሆነ በሚማርበት አካባቢ በሚከናወኑ ስፖርታዊ እንቅስቃሴዎች ተሳታፊ እና ተጠቃሚ እንዲሆን ያደርጋል፤

45/ የተለያዩ የገቢ ማሰባሰቢያ ስልቶችን በመጠቀም የስፖርት ገቢዎችን ያሰባስባል፤ የስፖርት ማኅበራት የሚሰበስቡት ገቢ ለዓላማቸው ማስፈፀሚያ ብቻ መዋሉን ለማረጋገጥ ሒሳባቸውን ይመረምራል፣ ይቆጣጠራል፤

46/ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን በክልሉ ውስጥ በስፖርት ኢንቨስትመንት ለሚሠማሩ ባለሀብቶች ስታንዳርድ ያዘጋጃል፤ በስታንዳርዱ መሠረት የሙያ ፈቃድ እንዲያገኙ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣ ይቆጣጠራል፤

47/ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን በወጣት ስብዕና ማዕከላት፣ በታላላቅ ሆቴሎች፣ ሪልስቴቶች፣ ሆስፒታሎች፣ ትምህርት ቤቶች፣ በጋራ መኖሪያ ቤቶች፣ በፋብሪካዎች እና የኢንዱስትሪ መንደሮች እና በመሳሰሉት ሌሎች አካባቢዎች የአካል ብቃት እንቅስቃሴ መሥሪያ ቦታዎች ተካተው መሠራታቸውን ወይም መገንባታቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ ድጋፍ ይሰጣል፤

42/ Works to ensure that the policies and strategies issued at the national level regarding sports to be well-indoctrinated by residents of the region and implemented in the region; followsup, coordinates and supervises same;

43/ Establishes sports projects and institutions to identify and utilize areas and resources having contribution for the sport's development in the region where various sports can be promoted; works to produce internationally competitive athletes by providing the appropriate support and supervision;

44/ Develops community-wide sports participation program or package enabling the society to participate and benefit from sports activities in their living, working, or educational environments;

45/ Collects sports revenues using various revenue-raising strategies; investigates and monitors accounts of sports associations to ensure revenues they collect are used only for implementation of their objectives;

46/ In collaboration with the relevant body, prepares standards for investors to be engaged in sports investment in the region; facilitates and supervises conditions for obtaining professional licenses in accordance with the standards;

47/ In collaboration with relevant body, monitors, controls and supports for the construction or installation of physical exercise facilities in youths' personality development centers, large hotels, real estates, hospitals, schools, condominiums, factories and industrial villages and other such areas;

CamScanner

48/ በክለቦች የታቀፉ ስፖርተኞች በየትኛውም ሁኔታ የጉልበት ብዝበዛ እንዳይደርስባቸው ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

49/ የስፖርት ሥልጠና ማዕከላት እና የስብዕና ልማት ማዕከላት ከፍተው የማሠልጠን ሥራ ለሚያከናውኑ አካላት በስታንዳርዱ መሠረት ሙያዊ ፈቃድ ይሰጣል፣ ተገቢውን ድጋፍ ያደርጋል፣ ይቆጣጠራል፤

50/ በክልሉ ውስጥ በየደረጃው ለሚቋቋሙ የስፖርት ማኅበራት ስታንዳርድ ያወጣል፣ በስታንዳርዱ መሠረት ያቋቁማል፣ ፈቃድ ይሰጣል፣ የሥራ ውል ይይዛል፣ ፕሮግራሞቻቸውን ያስተባብራል፣ ይቆጣጠራል፤

51/ በክልሉ ውስጥ በየደረጃው የስፖርት ምክር ቤቶች እንዲቋቋሙ እና እንዲጠናከሩ ያደርጋል፤

52/ የክልሉን ስፖርታዊ ውድድሮች ስታንዳርድ ያዘጋጃል፣ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ውድድሮችን ያዘጋጃል፣ ያካሂዳል፣ ውድድር ለሚያዘጋጁ ሌሎች አካላትም ፈቃድ ይሰጣል፤

53/ በክልሉ ውስጥ ስፖርታዊ ጨዋነት እንዲዳብር ይሠራል፣ የጨዋታ ሥነ ምግባር ጉድለት ፈፅመው በተገኙ ስፖርተኞችም ሆነ ደጋፊዎች ላይ ሕጋዊ እርምጃ ይወስዳል ወይም እንዲወሰድ ያደርጋል፤

54/ ክልላዊ የስፖርት ውድድሮችን በሚመለከት በስፖርት ማኅበራት እና በሌሎች አካላት መካከል የሚነሡ አለመግባባቶችን መርምሮ አስተዳደራዊ ውሳኔ ይሰጣል፤

55/ የክልሉን ባሕላዊ ስፖርቶች ያጎለብታል፣ እንዲታወቁ ይሠራል፣ እንዲሻሻሉ እና እንዲያድጉ ያበረታታል፣ የየራሳቸው ሕግና ደንብ እንዲወጣላቸው ያደርጋል፣ ይከታተላል፤

56/ በቂ የስፖርት ትጥቆች እና መሣሪያዎች እንዲኖሩ ይሠራል፣ ከሀገር ውስጥም ሆነ ከውጭ ሀገር በድጋፍ መልክ የሚገኙበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

48/ Monitors and supervises that athletes affiliated with clubs are not subjected to any form of labor exploitation;

49/ Issuees professional licenses, in accordance with the standards, to those undertaking training works opening sports training centers and personality development centers; provides the appropriate support and controls same;

50/ Issues standards for sports associations to be established at all levels in the region, establishes them based on the standard, issues licenses, takes work contracts, coordinates and supervises their programs;

51/ Makes sport councils to be established and strengthened at all levels in the region;

52/ Prepares standards of regional sports competitions, organizes and conducts competitions in cooperation with relevant bodies, and grants licenses to other bodies organizing competitions;

53/ Works to promote sportsmanship in the region, and take or cause to be taken legal actions against athletes and fans found to have committed misconduct in the game;

54/ Investigates and makes administrative decisions on disputes between sports associations and other bodies regarding regional sports competitions;

55/ Promotes the regional cultural sports, works for them to be known, encourages them to be improved and developed, causes for issuance of their own laws and regulations, and monitors same;

56/ Works for the availability of sufficient sports equipment and facilities, facilitates conditions in which thet are obtained from locally or abroad;

57/ ለኅብረተሰቡ ጠቃሚ የሆኑ የአካል ብቃት እንቅስቃሴዎች፣ የስፖርት የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርቶችን ከሚዲያ ተቋማት ጋር በመተባበር በተለያዩ መገናኛ ዘዴዎች እንዲተላለፉ ይሠራል፤

58/ ስፖርትን በማስፋፋት እና በማጎልበት ረገድ ከፍተኛ አስተዋፅዖ ላደረጉ የስፖርት ግለሰቦች፣ ማኅበረሰቦች፣ ሲቪክ ማኅበራት፣ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችም ግልፅ መመሪያ በማዘጋጀት የማበረታቻ ሽልማቶችን ይሰጣል፤

59/ ከክልሉ ጤና ቢሮ ጋር በመተባበር ከስፖርቱ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ጤናነክ ተግባራት በዕቅድ አካቶ ያከናውናል።

## 39. <u>የሴቶች፣ ወጣቶች እና ማኅበራዊ ጉዳይ ቢሮ</u>

በሌሎች ሕጎች አስቀድሞ የተደነገገው ወይም ወደ ፊት የሚደነገገው እንደ ተጠበቀ ሆኖ የክልሉ ሴቶች፣ ወጣቶች እና ማኅበራዊ ጉዳይ ቢሮ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ዝርዝር ሥልጣን እና ተግባራት ይኖሩታል፡ -

1/ በክልሉ ውስጥ የሴቶች፣ ወጣቶች፣ ሕፃናት፣ አረጋዊያን እና አካል ጉዳተኞች መብቶችን እና ጥቅሞችን ለማስከበር የሚረዱ የፖሊሲ ሐሳቦችን ያመነጫል፤ የማስፈፀሚያ ስልቶችን በመቀየስ ለተግባራዊነታቸው አስፈላጊውን ክትትል ያደርጋል፤

2/ በሴቶች፣ በወጣቶች፣ በሕፃናት፣ በአካል ጉዳተኞች እና አረጋዊያን መብቶች ዙሪያ የተደነገጉ ዓለም አቀፋዊ እና አህጉራዊ ስምምነቶች በክልሉ ተፈፃሚ ስለመሆናቸው ክትትል ያደርጋል፤ የሀገሪቱ ማኅበራዊ ጉዳይ ፖሊሲዎች እና ሕጎች በክልሉ ውስጥ ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፤



57/ Works to disseminate physical activities and sports awareness-raising lessons that are beneficial to the society through various means of communication in collaboration with media institutions;

58/ Provides rewards to sports individuals, communities, civic associations, governmental and non-governmental organizations that have made significant contributions to the promotion and development of sports by preparing clear directives;

59/ Carries out health-related activities related to sports in collaboration with the Regional Health Bureau.

## 39. <u>Bureau of Women, Youth and Social Affairs</u>

Without prejudice to what has been previously or may be provided for in other laws, the Regional Women, Youth and Social Affairs Bureau shall have the following detailed powers and duties under this Proclamation:

1/ Initiates policy ideas with the view to enforcing the rights and interests of women, youth, children, elders and disables in the region; makes the necessary follow up by devising implementation strategies;

2/ Monitors the implementation of international and continental conventions regarding the rights of women, youth, children, persons with disabilities and the elderly in the region; makes the country's social policies and laws to be implemented in the region;

CamScanner

3/ የሴቶችን፣ የሕፃናት እና ወጣቶችን እንዲሁም የማኅበራዊ ጥበቃን በተመለከተ የወጡ ሀገር አቀፍ ፖሊሲዎች፣ ፓኬጆች እና ስትራቴጂዎች በክልሉ ውስጥ እንዲፈፀሙ አግባብ ያለው የስርፀት ሥራ ይሠራል፣ ይከታተላል፣ ያስተባብራል፤

4/ በክልሉ መንግሥት አካላት የሚዘጋጁ ፖሊሲዎች፣ ሕጎች፣ የልማት ፕሮግራሞች፣ ፕሮጀክቶች እና ሪፖርቶች የሥርዓተ ፆታን፣ የሕፃናትን፣ የወጣቶችን፣ አረጋዊያንን እና የአካል ጉዳተኞችን ጉዳዮች ለማካተት የሚያስችላቸውን ስልት በመንደፍ አስፈላጊውን ክትትል እና ድጋፍ ያደርጋል፤ በሂደቱም የሴቶችን፣ ሕፃናትን፣ አረጋዊያንን፣ የወጣቶችን እና የአካል ጉዳተኞችን ተሳትፎ እና ተጠቃሚነት ያረጋግጣል፤

5/ በሴቶች፣ በሕፃናት፣ በአረጋዊያን እና አካል ጉዳተኞች ላይ የሚቃጡ መድልኦዎችን እና የሚፈፀሙ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን በጥናት በመለየት የሚወገዱበትን የመፍትሔ ሐሳብ ያመነጫል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

6/ አካል ጉዳተኞችን በተመለከተ በማኅበረሰቡ ዘንድ ያለውን የተዛባ አመለካከት ለመቀየር የሚያስችሉ ቀጣይነት ያላቸው የግንዛቤ ማሳደጊያ እና የንቅናቄ ሥራዎችን ያከናውናል፤

7/ ከሚመለከታቸው የፌደራል እና የክልል መንግሥታዊ እና መንግሥታዊ ያልሆኑ አካላት ጋር በመቀናጀት በሕፃናት ላይ የሚፈፀሙ የጉልበት ብዝበዛ፣ ሰውን በሕገ ወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር እና በሕገ-ወጥ መንገድ ሰውን ለሥራ ወደ ውጭ አገር መላክ ወንጀልን እና ሌሎች የመብት ጥሰቶችን በተመለከተ መረጃ ያጠናቅራል፤ የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም ስለ ወንጀሉ አስከፊነት የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ ይሠራል፣ ይከላከላል፤



3/ Works, monitors and coordinates the necessary indoctrination work in the implementation of national policies, packages and strategies regarding women, children and youth as well as social protection in the region;

4/ Provides the necessary monitoring and support by designing a strategy that will enable the policies, laws, development programs, projects and reports prepared by the regional government bodies to include the issues of gender, children, youth, the elders and the disabled; ensures the participation and benefit of women, children, the elders, youth and the disabled in the process;

5/ Identifies discrimination and harmful traditional practices committed on women, children, elders and disables through study, and initiates recommendations onhow to avoid same, and monitors the implementation;

6/ Conducts ongoing awareness-raising and mobilization activities to change the stereotypes of people with disabilities in society;

7/ In coordination with relevant federal and regional governmental and non-governmental organizations, compiles information on child labor exploitation, illegal border crossing, and illegal labour immigration and other human rights violations; and uses various methods to raise awareness about the seriousness of the crime and prevents it;

8/ ሴቶች በኢኮኖሚ፣ በማኅበራዊ እና በፖለቲካዊ ጉዳዮች ረገድ ተሳትፏቸውን ለማሳደግ ልዩ ትኩረት እና ድጋፍ መስጠት ስለሚቻልበት ሁኔታ ለክልሉ መንግሥት ሐሳብ ያቀርባል፣ አተገባበሩን ይከታተላል፤

8/ Submits proposals to the regional government on how to provide special attention and support to women in increasing their participation in economic, social and political matters, and monitors its implementation;

9/ ሴቶች ወይም አካል ጉዳተኞች በክልሉ ውስጥ በሚሰጡ የሥራ ቅጥር፣ የሥልጠና እና የደረጃ ዕድገት ዕድሎችም ሆነ እነዚህኑ ለማስፈፀም በሚደራጁ የተለያዩ ኮሚቴዎች ውስጥ በሚገባ ስለ መወከላቸው ይከታተላል፤

9/ Monitors the representations of women or disables in employment, training and promotion opportunities in the region as well as in various committees organized to implement same;

10/ የተለያዩ የክልሉ መንግሥት አካላት ሴቶችን የውሳኔ ሰጭነት ሚና በማሳደግ ረገድ በቂ ትኩረት ስለ መስጠታቸው ይከታተላል፣ ብቃት ያላቸውን ሴቶች እየለየ በየደረጃው ለሚገኙ ወሳኝ አካላት ያቀርባል፤

10/ Monitors whether various regional government bodies are paying sufficient attention to enhancing the role of women in decision-making; identifies qualified women and presents them to decision-making bodies at all levels;

11/ ሴቶችን፣ ወጣቶችን፣ ሕፃናትን፣ አረጋዊያንን እና አካል ጉዳተኞችን እንደየ ችግሮቻቸው ዓይነት በነፃ ፍላጎታቸው ተደራጅተው ለመብቶቻቸው እና ለጥቅሞቻቸው መከበር እንዲታገሉ እና በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ፣ በመልካም አስተዳደር እና በልማት እንቅስቃሴዎች ውስጥ በሙሉ አቅማቸው በመሳተፍ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ሁለንተናዊ ድጋፍ ያደርጋል፣ በየተቋቋሙበት አግባብ ተግባራቸውን እየተወጡ ስለመሆኑም በቅርበት ይከታተላል፤

11/ Provides an overall support to women, youth, children, elders and disables to fight for their rights and interests being organized in their free will accordingly the type of their respective problems and to fully participate and become benficial in building democratic system, good governance and development activities; closely monitors wether they carryout their duties according to their perspective establishment;

12/ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙትን ሴቶች፣ ሕፃናት፣ አረጋዊያን፣ አካል ጉዳተኞች እና ሌሎች የማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ተጋላጭ የኅብረተሰብ ክፍሎችን የኑሮ ሁኔታ ለማሻሻል የሚረዱ ጥናቶችን ያካሂዳል፣ እንዲጠኑ ያደርጋል፤ ፕሮግራሞችን እና ፕሮጀክቶችን በመቅረጽ ተግባራዊ ያደርጋል፤ በዚሁ ዓላማ ላይ ተመሥርተው ለሚንቀሳቀሱ ድርጅቶች አስፈላጊውን እገዛ ያደርጋል፤

12/ Conducts and causes to be conducted studies to improve the living conditions of women, children, elders, disables living at lower living standard and other vulnerable groups to socio-economic problems; implements programs and projects by formulating same; and provides the necessary support to organizations operating for this purpose;

CamScanner

13/ ሥርዓተ ፆታን በሚመለከቱ ጉዳዮች ዙሪያ መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች፣ ከተለያዩ የማኅበረሰብ ተቋማት እና ከራሳቸው ከሴቶች ማኅበራት ጋር ተባብሮ ይሠራል፤

14/ የሥርዓተ ፆታ እኩልነትን ለማስፈን፣ በተለያዩ እንቅስቃሴዎች ውስጥ የሴቶችን ተሳትፎ ለማጎልበት እና ኅብረተሰቡ በሴቶች ላይ ያለውን የተሳሳተ ግንዛቤ ለመቀየር የሚረዱ የግንዛቤ ማሳደጊያ ሥልጠናዎችን እና አውደ ጥናቶችን ያካሂዳል፣ ውጤቱን ይገመግማል፤

15/ አረጋዊያንን፣ አካል ጉዳተኞችን እና ሌሎች የማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ችግር ተጋላጭ የኅብረተሰብ ክፍሎችን ፍትሐዊ፣ ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ የሚረዱ ሥልጠናዎችን እና አውደ ጥናቶችን ያካሂዳል፣ ውጤቱን ይገመግማል፤

16/ ሴቶችን፣ ወጣቶችን፣ ሕፃናትን፣ አረጋዊያንን እና አካል ጉዳተኞችን ለሚያግዙ እና ለክልሉ ዘላቂ ልማት አስተዋፅዖ ለሚያደርጉ ፕሮግራሞች እና ፕሮጀክቶች ማስፈፀሚያ የሚውል ሀብት ያፈላልጋል፣ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆንም ድጋፉ የእነዚህን የኅብረተሰብ ክፍሎች ሕይወት ለማሻሻል ስለመዋሉ እና ውጤታማ ስለመሆኑ ይከታተላል፤

17/ አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የቤተሰብ እና የሕፃናት ደኅንነት እንዲጠበቅ ለማድረግ እና የጋብቻ ሥርዓትን ለመንከባከብ የወጡ ፖሊሲዎችን ተግባራዊ ያደርጋል፤

18/ ሴቶችን፣ ወጣቶችን፣ ሕፃናትን፣ አረጋዊያንን፣ አካል ጉዳተኞችን እና ሌሎች ተጋላጭ የኅብረተሰብ ክፍሎችን ማዕከል አድርገው የሚሠሩ የተለያዩ አካላትን ዕቅድ እና የተግባር አፈፃፀም ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤ ቅንጅታዊ አሠራር እንዲኖራቸው ያስተባብራል፣ ተጠያቂነትን ያሰፍናል፤



13/ Works in collaboration with non governmental organizations, various community institutions and their own women's assocations regarding to gender issues;

14/ Conducts trainings and seminars helping to secure gender equality, strengthen women's participations in various activities and change society's misconceptions about women; evaluates its results;

15/ Conduct trainings and seminars helping to secure the fair, social and economic benefits for elders, disables and other socio-economic vulnerable groups; evaluates its results;

16/ Findsout resources helping for the implementation of programs and projects that support women, youth, children, elders and disables and contribute to the sustainable development of the region; followsup wether the support is utilized to improve the lives of these sections of the society being with concerned bodies;

17/ Implements policies issued to protect safety of family and children and to care marriage system in collaboration with pertinent bodies;

18/ Followsup and controls plan and actual implementation of different bodies working centering at of women, youth, children, elders, disables and other vulnerable groups; coordinates them to have integrated procedure, and maintains accountablity;

19/ ዝርዝሩ ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣ ደንብ የሚወሰን ሆኖ በሥራ ላይ ያሉትን የአረጋዊያን ማዕከላት ያስተዳድራል፤ በክልሉ ውስጥ በተለያዩ አካባቢዎች ማዕከላት እንዲቋቋሙ ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፤

20/ የማኅበራዊ ኑሮ ጠንቆች ይወገዱ ዘንድ የክልሉን ሕዝብ ሁለንተናዊ ጥረት ያስተባብራል፤ እንደ ሴተኛ አዳሪነት እና ጎዳና ተዳዳሪነት ያሉ አስከፊ ችግሮች የደረሰባቸው ወገኖችን ያደራጃል፣ ያቋቁማል፤

21/ አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር በተፈጥሮ እና ሰው ሠራሽ አደጋዎች ምክንያት ለከፋ የማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች የሚጋለጡ የኅብረተሰብ ክፍሎች ተገቢውን የድጋፍ አገልግሎት እንዲያገኙ አማራጭ የድጋፍ ስልቶችን ይቀይሳል፣ ተጋላጮችን ይለያል፣ ድጋፉን ያስተባብራል፤

22/ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን በገጠርም ሆነ በከተማ የሴፍትኔት ፕሮግራም ውስጥ ተጠቃሚ የሆኑ ሴቶች፣ ወጣቶች፣ ሕፃናት፣ አረጋዊያን እና አካል ጉዳተኛ የኅብረተሰብ ክፍሎችን መረጃ ይለያል፣ ያደራጃል፣ ተጠቃሚነታቸውን ያረጋግጣል፤

23/ ዘመናዊ የመረጃ አስተዳደር ሥርዓት በመዘርጋት የሴቶች፣ ሕፃናት እና ሌሎች የማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ችግር ተጋላጭ ኅብረተሰብ ክፍሎችን መረጃ ያሰባስባል፣ ያደራጃል፣ ጥቅም ላይ ያውላል፤

24/ የማኅበራዊ ጥበቃ ተቋማት እንዲቋቋሙ ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ያቋቁማል፣ ውጤታማ እንዲሆኑ ድጋፍ እና ክትትል ያደርጋል፤

25/ ከሚመለከው አካል ጋር በመሆን የዜግነት በጎ ፈቃድ አገልግሎት ሥርዓት እንዲዘረጋ እና የማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ተጋላጭ የኅብረተሰብ ክፍሎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይሠራል፤



19/ Being the details determined to implement this proclamation, manages the existing elderly centers; creates favorable conditions for the establishment of centers in various areas of the region;

20/ Coordinates the overall efforts of the region to eliminate harms of social life; organizes and establishes victims of serious problems such as prostitution and street living;

21/ In collaboration with pertinent bodies, formulates alternative support strategies to the provision of necessary support for groups of the society to be exposed for serious social and economic problems due to natural and manmade disasters; identifies vulnerables and coordinates the support;

22/ In collaboration with the relevant body, identifies, organizes and ensures the beneficiary of women, youth, children, the elders and disabled people who benefit from the safety net program in both rural and urban areas;

23/ Collects, organizes and utilizes information of women, children and other socially and economically vulnerable segments of the society through establishing modern information management system;

24/ Proposes to the relevant body for the establishment of social protection institutions, establishes same when approved, provides support and monitoring to make them effectiveness;

25/ Works with relevant body for the establishment of civic volunteer service system and to benefit vulnerable segments of the society facing social and economic problems;

26/ የሚመለከታቸውን አካላት በማስተባበር የሕፃናት መልካም አስተዳደግ እና ስብዕና ግንባታ፣ ድጋፍ፣ እንክብካቤ እና ተሐድሶ ዙሪያ ለወላጆች እና አሳዳጊዎች ተገቢውን ግንዛቤ በመስጠት ላይ ትኩረት ሰጥቶ ይሠራል፤

27/ በተለያዩ ምክንያቶች ለችግር የተጋለጡ እና ወላጆቻቸውን ያጡ ሕፃናት ጉዲፈቻን ጨምሮ በሀገር ውስጥ ባሉ አማራጭ የድጋፍ እና እንክብካቤ ዘዴዎች ተጠቃሚ የሚሆኑበትን ስልት ይቀይሳል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፤

28/ ወጣቶች በክልሉ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ በንቃት ለመሳተፍ የሚያስችሏቸው ዕድሎች የተመቻቹላቸው ስለመሆኑ በትርብ ይከታተላል፤

29/ የክልሉ ወጣቶች በክልሉም ሆነ በሀገሪቱ የሚገኙትን ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ባሕል እና ታሪክ ለማወቅ የሚያስችሏቸውን የማኅበረሰብ ንቅናቄ እና የተሳትፎ መድረኮችን ያዘጋጃል፣ ሥራውን ያስተባብራል፤

30/ የወጣቶች የበጎ ፈቃድ አገልግሎት በክልሉ እንዲስፋፋ እና ባሕል እንዲሆን ለማድረግ ያስተባብራል፣ የበጎ ፈቃድ ማኅበራትን ያደራጃል፣ ይደግፋል፣ ያስተባብራል፣ ይቆጣጠራል፤

31/ በወጣቶች ሁለንተናዊ ተሳትፎ እና ተጠቃሚነት ዙሪያ የላቀ አበርክቶ ላደረጉ እና ልዩ የፈጠራ እና ክህሎት ላላቸው ወጣቶች፣ ግለሰቦች፣ በጎ ፈቃደኞች፣ አደረጃጀቶች፣ እንዲሁም ከፍተኛ አስተዋፅዖ ላደረጉ ሲቪክ ማኅበራት፣ መንግሥታዊ እና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ግልጽ መመሪያ በማዘጋጀት የማበረታቻ ሽልማቶችን ይሰጣል፣ ለበለጠ ሥራ ያነሣሣል፤

26/ Works focusing on giving the appropriate awareness to parents and guardians on children's well-behave and personality building, support, care and rehabilitation by coordinating concerned bodies;

27/ Devises and implements local alternative support and care systems including adoption to benefit vulnerables due to various reasons and orphaned children;

28/ Closely monitors opportunities available to youth to actively participate in the political, economic and social activities of the region;

29/ Organizes and coordinates community mobilization and participation platforms enabling the youth of the region to learn about the culture and history of the nations, nationalities and peoples in the region as well as the country;

30/ Coordinates the expansion and culture of the youth volunteer service in the region, organizes, supports, coordinates and supervises volunteer associations;

31/ Provides encouragement awards to youth, individuals, volunteers, organizations as well as civic associations, governmental and non-governmental organizations that have made outstanding contributions to the comprehensive participation and benefit of youth and have special creativity and skills after preparing clear directive, and initiates them for better work;

32/ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን ወጣቶችን ከማኅበራዊ ጠንቆች፣ ከአደንዛዥ እፆች እና አሉታዊ መጤ ባሕሎች እንዲሁም ሌሎች ጤንነታቸውን ከሚጎዱ ነገሮች ለመከላከል ይሠራል፤ በሥነ ምግባር የታነፁ፣ ንቁ እና ሀገር ወዳድ ዜጎች እንዲሆኑ እና ብሔራዊ አገልግሎት እንዲሰጡ ለማድረግ ይሠራል፣ ውጤታማነቱን ይከታተላል፤

33/ የክልሉን ሕዝብ የመልካም ባሕል እሴቶች ማዕከል ያደረገ የወጣቶችን ስብዕና መገንቢያ ተቋማት ስታንዳርድችን ያዘጋጃል፤ በየደረጃው በሚገኙ የአስተዳደር እርከኖች የወጣቶች ስብዕና መገንቢያ ማዕከላት እንዲገነቡ ያደርጋል፣

34/ የወጣቶችን ሁለንተናዊ ተሳትፎ እና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የሚያስችል የወጣቶች ልማት ፈንድ ያቋቁማል፣ ያስተባብራል፣ ይመራል፤

35/ የክልሉን ወጣት ነክ መሠረታዊ መረጃዎች ያሰባስባል፣ ያደራጃል፣ ይተነትናል፣ ለሚመለከታቸው አካላት ያሰራጫል፤

36/ ወጣት ተኮር የጥናት እና ምርምር ሥራዎችን ያካሂዳል፣ የሥልጠና ስታንዳርዶችን እና የአቅም ግንባታ ፓኬጆችን እያዘጋጀ ከትምህርት ተቋማት ጋር በመተባበር ለወጣቶች ልማት ሥልጠና እንዲሰጥ ያደርጋል፣ አፈፃፀሙንም ይከታተላል፤

37/ ሴቶች፣ ወጣቶች እና ሌሎች ለኤች አይ ቪ በሽታ ተጋላጭ የኅብረተሰብ ክፍሎች ራሳቸውን ከበሽታው ለመከላከል ይቻላቸው ዘንድ አስፈላጊውን መረጃ በወቅቱ እንዲያገኙ ያደርጋል፤

38/ ከኤች አይ ቪ ቫይረስ ጋር ለሚኖሩ ወገኖች፣ ለሕሙማን እና በኤድስ ምክንያት ወላጆቻቸውን ላጡ ሕፃናት፣ ለታዳጊ ወጣቶች እና ለቤተሰቦቻቸው ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን መብታቸው እንዲከበር ይሠራል፣ መከበሩን ያረጋግጣል።



32/ In collaboration with the relevant body, works to protect the youth from social dangers, drugs and negative foreign cultures as well as other things that harm their health; works to make them morally upright, active and patriotic citizens and provide national service, and monitors its effectiveness;

33/ Prepares standards for youth personality development institutions focusing on the values of good culture of people of the region; makes youth personality development centers to be established at all levels of administration.

34/ Establishes, coordinates and manages a Youth Development Fund to ensure the full participation and benefit of youth;

35/ Collects and organizes youth-related basic information in the region and disseminates same to relevant bodies;

36/ Conducts youth-oriented research and studies, causes training for youth development to be provided by preparing training standards and capacity-building packages in collaboration with educational institutions, and monitors its implementation;

37/ Ensures that women, youth and other HIV disease vulnerable segments of the society have timely access to the necessary information to protect themselves from the disease;

38/ Works with concerned bodies for the observance of the rights of people living with HIV, patients, and orphans of children due to the disease, adolescents and their families; ensures its observance.

CamScanner

## 40. የፕላን እና ልማት ቢሮ

በሌሎች ሕጎች አስተድሞ የተደነገገው ወይም ወደ ፊት የሚደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ የፕላን እና ልማት ቢሮ የሚከተሉት ዝርዝር ሥልጣን እና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1/ የልማት፤ የክልላዊ ስታቲስቲክስ እና የሥነ ሕዝብ ጉዳዮችን የሚመለከቱ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችን እና ሕጎችን ያመነጫል፤ ለአፈፃፀሙ ከክልሉ የልማት አቅጣጫዎች ጋር የተጣጣመ ዝርዝር መርሃ ግብር ያዘጋጃል፣ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

2/ በክልሉ ተቋማት የሚመነጩ የልማት ፖሊሲዎች እና ስትራቴጂዎች ከክልሉ የልማት አቅጣጫዎች ጋር የተጣጣሙ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤

3/ የኢኮኖሚ እና ማኅበራዊ ልማት ፖሊሲ ጥናት እና ትንተና ያካሂዳል፤ በሚገኙ ውጤቶች መሠረት ስትራቴጂያዊ የሶሾ ኢኮኖሚ ጉዳዮችን ይለያል፣ የፖሊሲ ምክረ ሐሳብ ያቀርባል፤

4/ የክልሉን የአጭር፣ የመካከለኛ እና የረዥም ጊዜ የልማት ዕቅዶች ለማዘጋጀት የሚረዱ የኢኮኖሚ ጥናት እና ምርምሮችን ያካሂዳል፤ የኢኮኖሚያዊ እና የማኅበራዊ ሁኔታዎች መለኪያዎችን እና መመዘኛዎችን ያዘጋጃል፤

5/ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የልማት ፕላን አካል የሆነውን ክልላዊ የኢኮኖሚ ዕድገት ትንበያ እና የማክሮ ኢኮኖሚ ማዕቀፍ ያዘጋጃል፤ ከማክሮ ኢኮኖሚ ማዕቀፉ የተጣጣሙ የቁጠባ፣ የኢንቨስትመንት የማክሮ ኢኮኖሚ ግቦችን ያዘጋጃል፤

6/ የልማት ዕቅድን ለማሳካት እንዲሁም የመንግሥትን የማስፈፀም አቅም ለማጠናከር እና ቀጣይነት ያለው ተቋማዊ አቅም እንዲፈጠር ለማድረግ የሥርዓት ማሻሻያ ጥናት ያካሂዳል፤ በጥናቱ ላይ ተመሥርቶ ተቋማትን ይፈጥራል፣ ያሻሽላል፣ ያጥፋል እንዲሁም ተግባር እና ኃላፊነታቸውን ይደነግጋል፤ የውሳኔ ሐሳብ አደራጅቶ ለክልሉ መንግሥት ያቀርባል፤



## 40. Bureau of Planning and Development

Without prejudice to existing or subsequent provisions of other laws, the Regional Bureau of Planning and Development shall, pursuant to this proclamation, have the following specific powers and duties:

1/ Initiates policies, strategies and laws concerning development, regional statistics and demographic issues; prepares detailed program for its implementation in line with development directions of the region, and implements it upon approval;

2/ Ensures that development policies and strategies generated by regional institutions to be consistent with the regional development directions;

3/ Conducts research and analysis of economic and social development policies; identifies strategic socio-economic issues based on the results obtained, and provides policy recommendations;

4/ Conducts economic research helping to prepare the short, medium and long term development plans of the region; prepares standards and measurements of economic and social conditions;

5/ In collaboration with relevant bodies, prepares the regional economic growth forecast and macroeconomic framework which is part of the development plan; prepares macroeconomic goals for savings and investment consistent with the macroeconomic framework;

6/ Conducts a study of system reform to achieve the development plan, strengthen the government's execution capacity and create sustainable institutional capacity; based on the study, creates, improves and abolishes institutions; and determines their duties and responsibilities; organizes and submits recommendation to the regional government;

7/ ለክልሉ ዘላቂ ልማት እና ዕድገት ፋይዳ ያላቸው የቅየሳ፣ የካርታ እና የጂኦግራፊ ጥናት ሥራዎችን ያከናውናል፣ እንዲከናወኑ ያስተባብራል፣ ይከታተላል፤

8/ ክልላዊ የሥነ-ሕዝብ ጉዳዮችን አስመልክቶ ጥናት እና ምርምር ያካሂዳል፣ መረጃዎችን ያደራጃል፣ ለተጠቃሚዎችም ያሰራጫል፤

9/ በክልሉ የኢኮኖሚ እና የማኅበራዊ ልማት ፖሊሲዎች እና ስትራቴጅዎች ዙሪያ ጥናት እና ምርምር ያካሂዳል፤ ሳይንሳዊ እና ተተግባሪ የሆኑ ምክረ ሐሳቦችን ያመነጫል፣ ተግባራዊ እንዲሆኑ ድጋፍ እና ክትትል ያደርጋል፤

10/ የፖሊሲ ጥናት እና ምርምር ሥራዎችን በበላይነት ያስተባብራል፤

11/ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን በአጭር፣ በመካከለኛ እና በረዥም ጊዜ የልማት ዕቅዶች ውስጥ ሊንፀባረቁ የሚገባቸው እና በክልሉ መንግሥት የሚከናወኑ ፕሮጀክቶች እንዲጠኑ እና እንዲዘጋጁ ያደርጋል፣ ይገመግማል፤

12/ በሀገሪቱ የልማት ስትራቴጂዎች ላይ የተመሠረተ እና በክልሉ መንግሥት የሚፈፀም የአጭር፣ የመካከለኛ እና የረዥም ጊዜ የልማት ዕቅዶችን ያዘጋጃል፤ ሲፀድቅ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፣ ይገመግማል፤

13/ በሁሉም የክልሉ አካባቢዎች ውጤታማ እና ፍትሐዊ የመልማት እና የልማት ተጠቃሚነትን የሚያረጋግጡ ስፓሻል ፕላኖችን ያዘጋጃል፤ በክልሉ መንግሥት ሲፀድቅ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፣ ይቆጣራል፤

14/ የክልሉ መንግሥት የአጭር፣ የመካከለኛ እና የረዥም ጊዜ የልማት እና የመልካም አስተዳደር ዕቅዶች ዝግጅት፣ አተገባበር፣ ክትትል እና ግምገማ ማዕከል ሆኖ ይሠራል፤

7/ Conducts, coordinates and monitors surveying, mapping and geographic research activities beneficial to the sustainable development and growth of the region;

8/ Conducts studies and research concerning on regional demographic issues, organizes information, and disseminates it to users;

9/ Undertakes studies and research on the region's economic and social development policies and strategies; generates scientific and practical recommendations, provides support and monitoring for their implementation;

10/ Coordinates on top of policy study and research works;

11/ Being with the relevant body, causes for the studying and preparation of projects which should be reflected in short, medium and long-term development plans and implemented by the regional government; evaluates same;

12/ Prepares short, medium and long-term development plans based on the country's development strategies and implemented by the regional government; monitors and evaluates their implementation upon approval;

13/ Prepares spatial plans that ensure effective and equitable development and development benefits in all areas of the region; monitors and controls their implementation when approved by the regional government;

14/ Works being as center of preparation, implementation, monitoring and evaluation of short, medium and long-term development and good governance plans of the regional government;

CamScanner

15/ የክልሉን ተቋማት የአጭር፣ የመካከለኛ እና የረዥም ጊዜ ዕቅድ አተገባበር ውጤታማነት በኃላፊነት ይከታተላል፣ ይገመግማል፤ የተግባር አፈፃፀምን መሠረት አድርጎ ተቋማትን ይመዝናል፣ ለዚህም ያመቸው ዘንድ በስትራቴጂያዊ የትኩረት መስኮች ከፋፍሎ የየዘርፉን ዕቅዶች እና ሪፖርቶች ይቀበላል፣ የተጠቃለለ ሪፖርት ለክልሉ መንግሥት ያቀርባል፤

16/ በመንግሥት በጀት፣ በመንግሥት ዋስትና ብድር እንዲሁም በሌሎች ተመሳሳይ የበጀት ምንጮች እንዲከናወኑ የታቀዱ የክልሉ መንግሥት የልማት ፕሮጀክቶች ላይ የአዋጭነት እና አስፈላጊነት ግምገማ ያካሄዳል፤ የልማት ፕሮጀክቶችን ቅደም ተከተል ያስይዛል፣ የልማት ፕሮጀክቶችን የሱፐርቪዥን ሥራ ይመራል፣ አፈፃፀማቸውንም ይከታተላል፣ ይገመግማል፤

17/ የልማት እና የመልካም አስተዳደር ዕቅዶችን አተገባበር ይከታተላል፤ የሚገኙ ውጤቶችን በመተንተን ከተገማች አንድምታዎች ጋር አግባብ ላላቸው ፈፃሚ አካላት በወቅቱ ያስተላልፋል፣ መፈፀማቸውን ይከታተላል፤

18/ የክትትል እና ግምገማ ሥርዓቱን ለተቋማት ለማስተዋወቅ እና ለማስረጽ የግንዛቤ ፈጠራ ሥራዎችን ያከናውናል፤ የፈፃሚ አካላት የክትትል እና ግምገማ ክህሎት የሚጎለብትበትን ስልት ይቀይሳል፤

19/ የመንግሥት እና የግል ተቋማት የክልሉን ልማት ለማፋጠን በንቃት የሚሳተፉበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣ ተጠያቂነት የሰፈነበት የክትትል እና ግምገማ ሥርዓት ይዘረጋል፣ ይከታተላል፤

20/ የልማት ዕቅድ ፕሮግራም እና ፕሮጀክቶች አዘገጃጀት ሥርዓት በመዘርጋት በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፣ የሙያ ምክር እና የአቅም ግንባታ ድጋፍ ይሰጣል፤



15/ Followsup and evaluates responsibly for the effectiveness of the implementation of short, medium and long-term plans of the regional institutions; evaluates institutions based on performance, and for this purpose, receives sector plans and reports by dividing them into strategic focus areas, and submits consolidated report to the regional government;

16/ Undertakes feasibility and importance assessments on regional government development projects planned to be implemented through the government budget, government-guaranteed loans and other similar budget sources; prioritizes development projects, leads the supervision work of development projects, and monitors and evaluates their implementation;

17/ Followsup the implementation of development and good governance plans; analyzes the results obtained and transfers them to the appropriate executive bodies timely with the expected implications, and monitors their implementation;

18/ Undertakes awareness-raising activities to introduce and indoctrinate the monitoring and evaluation system to institutions; designs strategy to strengthen the monitoring and evaluation skills of executive bodies;

19/ Facilitates conditions to the active participation of public and private institutions in accelerating development of the region; establishes and monitors an accountable monitoring and evaluation system;

20/ Establishes and implements a system for preparing development plan programs and projects; provides professional advice and capacity building support;

21/ ዓለም አቀፍ እና ሀገራዊ የስታትስቲክስ እና የጅኦስፓሻል መረጃ ስታንዳርዶችን መሠረት በማድረግ መረጃዎች በክልሉ እንዲሰበሰቡ ሥርዓት ይዘረጋል፣ ይከታተላል፣ ያስፈፅማል፤

22/ ዓለም አቀፍ እና ሀገራዊ የመረጃ ስታንዳርዶችን መሠረት ያደረገ ዘመናዊ የመረጃ አስተዳደር ሥርዓት ይዘረጋል፤ የክልሉ የሶሾ ኢኮኖሚ፣ የስታትስቲክስ እና የጅኦስፓሻል መረጃ ማዕከል በመሆን ያገለግላል፤ ማስፈፀሚያ መመሪያ ያዘጋጃል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

23/ የክልሉን ተቋማት የመረጃ አሰባሰብ ሂደት ይቆጣጠራል፤ የአሠራር ስታንዳርድ እና የናሙና ዘዴዎችን ያፀድቃል፣ አተገባበሩን ይከታተላል፤

24/ የክልሉን የተፈጥሮ ሀብት፣ የጂኦ-ስፓሻል፣ የግብርና፣ የአገልግሎት እና የኢንዱስትሪ መረጃዎች ያሰባስባል፣ ያጠናቅራል፤ ለሚመለከታቸው ያስተላልፋል፤

25/ የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊ እና የሥነ-ሕዝብ ስታትስቲክስ የመረጃ ጥራት ክትትል ያደርጋል፣ ይገመግማል፤

26/ በክልሉ ውስጥ በወሰን ተለይተው ለሚቋቋሙ የከተማ እና የገጠር አስተዳደራዊ እርከኖች የአስተዳደር ወሰን ይለያል፤ መለያ ኮዶችን በመስጠት ካርታ ይሠራል፣ የሥነ ሕዝብ መረጃዎችን ያደራጃል፣ ለተጠቃሚዎችም ያሰራጫል፤

27/ ክልላዊ የኢኮኖሚ አካውንት እና ስታትስቲክስ በማዘጋጀት ጠቅላላ የክልል ውስጥ ምርት ግመታ ያካሂዳል፤ ከፌደራል መንግሥቱ የኢኮኖሚ አካውንት ጋር የተጣጣመ እና ደረጃውን የጠበቀ ክልላዊ የኢኮኖሚ አካውንት ሥርዓት ይዘረጋል፣ ለተዋረድ ተቋማት የሙያ ድጋፍ ይሰጣል፤



21/ Establishes, monitors and implements a system for collecting data in the region based on international and national statistical and geospatial data standards;

22/ Establishes modern information management system based on international and national data standards; serves being as the regional socio-economic, statistical and geospatial data center; prepares implementation directive, and monitors its implementation;

23/ Controls the data collection process of the regional institutions; approves operating standards and sampling methods, monitors its implementation;

24/ Collects and compiles the regional natural resources, geo-spatial, agricultural, service and industrial data, and transfers same to those concerned;

25/ Monitors and evaluates data quality of economic, social and demographic statistics;

26/ Delimits administrative boundaries of urban and rural administrative levels to be established within the region; maps them by providing identification codes, organizes demographic data, and disseminates them to users;

27/ Conducts regional gross domestic product estimation by preparing regional economic accounts and statistics; establishes a regional economic account system consistent with the federal government's economic accounts and meets standards, and provides professional support to subordinate institutions;

CamScanner

28/ መንግሥታዊም ሆነ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በብሔራዊው የሥነ-ሕዝብ ፖሊሲ አፈፃፀም የሚያደርጓቸውን እንቅስቃሴዎች ያስተባብራል፣ ይመራል፣ በቅንጅት ይሠራል፤

29/ በክልሉ የሚከናወኑ የካፒታል ፕሮጀክቶች ከክልሉ የልማት ዕቅድ ጋር ተገናዝበው እንዲፈፀሙ፣ ውጤታማ እና ፍትሐዊ የሆነ ስርጭት እንዲኖር ለማድረግ የካፒታል በጀት መደልደያ ቀመር እና መስፈርቶችን ያዘጋጃል፤ በመስተዳድር ምክር ቤት ያስፀድቃል፣ አተገባበሩን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

30/ የክልሉን የማኅበራዊ፣ የኢኮኖሚያዊ እና የመልካም አስተዳደር ዕቅዶች ለማዘጋጀት እንዲሁም ለፖሊሲ እና ስታራቴጂ ቀረፃ በሚያገለግል መልኩ የሲቪል እና የቤተሰብ ምዝገባ አገልግሎት ያከናውናል፤ የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፣ ይገመግማል።

## 41. የሲቪል ሰርቪስ እና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ

በሌሎች ሕጎች አስቀድሞ የተደነገገው ወይም ወደ ፊት የሚደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ ሲቪል ሰርቪስ እና የሰው ኃብት ልማት ቢሮ የሚከተሉት ዝርዝር ሥልጣን እና ተግባራት ይኖሩታል፦

1/ የክልሉን ሲቪል ሰርቪስ እና የሰው ሀብት ልማት የሚመለከቱ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጅዎችን እና ሕጎችን ያመነጫል፤ ለአፈፃፀሙ ከክልሉ የልማት አቅጣጫዎች ጋር የተጣጣመ ዝርዝር መርሃ ግብር ያዘጋጃል፣ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

2/ የመንግሥት አገልግሎት እና አስተዳደር ፖሊሲን ለማስፈፀም የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፤ ከፌደራል ተቋማት ጋር ተናባቢ በሆነ አግባብ እንዲፈፀም ያደርጋል፣ ውጤታማነቱን ይከታተላል፤



28/ Coordinates and leads activities of governmental as well as non-governmental organizations in the implementation of the national population policy; works in coordination;

29/ Prepares the capital budget allocation formula and criteria so that capital projects to be implemented in the region to be implemented in line with the regional development plan and the exisistence of effective and equitable distribution; gets approved it by government council, monitors its implementation, and evaluates it;

30/ Carries out civil and family registration services in a way used to prepare the region's social, economic and good governance plans as well as for policy and strategy formulation; establishes operating systems, monitors and evaluates its implementation.

## 41. Bureau of Civil Service and Human Resource Development

Without prejudice to the existing or subsequent provision of other laws, the Regional Bureau of Civil Service and Human Resource Development shall, pursuant to this proclamation, have the following specific powers and duties:

1/ Initiates policies, strategies and laws concerning the civil service and human resource development of the region; prepares detailed program for its implementation based on the development directions of the region, and implements it upon approval;

2/ Establishes system of procedures to implement the government service and administration policy; ensures that it is implemented in a manner consistent with federal institutions, monitors its effectiveness;

3/ የክልሉን ሲቪል ሰርቪስ የደመወዝ ስኬል፣ ልዩ ልዩ አበል እና ጥቅማ ጥቅም አጥንቶ ለመስተዳድር ምክር ቤት ያቀርባል፣ ሲፀድቅለት ተግባራዊ ያደርጋል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

4/ የመንግሥት አገልግሎት አሰጣጥን አስመልክቶ ፖሊሲዎችን እና ሕጎችን ያመነጫል፣ ከክልል ጀምሮ እስከ ታችኛው የመንግሥት መዋቅር በሚገኙ ተቋማት የአገልግሎት አሰጣጥ ድጋፍ እና ክትትል ያደርጋል፣ አፈፃፀምን የሚያሻሽል የማበረታቻ ሥርዓት ይዘረጋል፣ ጉድለቶች ላይ የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፣ እንዲወሰድ ያደርጋል፤

5/ ለክልሉ ዘላቂ ዕድገት አስተዋፅዖ ሊያደርጉ የሚችሉ የተቋማት ሪፎርም ሥራዎችን በማጥናት ለመስተዳድር ምክር ቤት የውሳኔ ሐሳብ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፣ ይከታተላል፤

6/ ተቋማት በአሠራር እንዲጠነከሩ እና በተገቢ መንገድ ሥራዎችን እንዲያከናውኑ ያግዛል፣ ከተቋማት በተናጠል የሚቀርቡ አስፈላጊ የሥራ መደቦችን ይፈቅዳል፤

7/ የተቋማትን ዓላማ ስኬታማ ለማድረግ የሚያስፈልገውን አደረጃጀት እና የሰው ኃይል ፍላጎት ያጠናል፣ ይወስናል፤ ከተቋማት በተናጠል የሚቀርቡ የሥራ መደቦች ላይ በሕጉ መሠረት ውሳኔ ይሰጣል፤

8/ የሥራ ምዘና እና ደረጃ አወሳሰን ጥናት ያካሂዳል፣ የሥራ መደቦችን ሥራ ዝርዝር ያዘጋጃል፣ ይመዝናል፣ ተግባራዊ ስለመሆኑ ክትትል እና ድጋፍ ያደርጋል፤

9/ በክልሉ ሲቪል ሰርቪስ ተቋማት ላይ የለውጥ ፕሮግራሞችን ውጤታማ ለማድረግ የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፣ ክትትል፣ ግምገማ እና ድጋፍ ያካሂዳል፤

3/ Studies the salary scale, various allowances and benefits of the regional civil service and submit them to the government council, implements them upon approval, and monitors their implementation;

4/ Generates policies and laws regarding government service delivery, supports and monitors the service delivery in institutions ranging from the regional to the lower levels of the government structure, establishes an incentive system improving performance, takes and causes to be taken corrective actions on deficiencies;

5/ Studies for institutional reform projects that can contribute to sustainable development of the region and submits recommendation to the government council, implements and monitors upon approval;

6/ Assists institutions to strengthen their operations and carry out their tasks appropriately, allows necessary positions offered by individual institutions;

7/ Studies and determines the organization and human resource needs required to achieve objectives of institutions; makes decisions on positions offered by individual institutions in accordance with the law;

8/ Conducts job evaluation and grading determination study, prepares and evaluates job descriptions, monitors and supports the implementation;

9/ Establishes a system of operations to make reform programs effective in the civil service institutions of the region; monitors, evaluates and supports them;

CamScanner

10/ በክልሉ ሲቪል ሰርቪስ ተቋማት የመንግሥት ሠራተኞች የሥራ አፈፃፀም ምዘና ሥርዓት ይዘረጋል፤ የመንግሥት ሠራተኞችን ብቃት እና ውጤታማነት በየጊዜው ይገመግማል፤ ይመዝናል፤ እንዲመዘኑ ያደርጋል፤ የመንግሥት ሠራተኞች ብቃት እና ውጤታማነት የሚገነባበትን ሥልት ይነድፋል፣ ሥራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፤

10/ Establishes performance appraisal system for civil servants in the regional civil service institutions; periodically assess, evaluates and have them to be evaluated; designs a system to build the competence and effectiveness of civil servants, and monitors its implementation;

11/ ለክልሉ ሲቪል ሰርቪስ ተቋማት የመንግሥት ሠራተኞች የቅጥር፣ የምደባ፣ የዝውውር፣ የደረጃ ዕድገት አሠራር ፍትሐዊ፣ ግልፅ እና ብቃትን መሠረት ያደረገ እንዲሆን ያደርጋል፣ ያረጋግጣል፤ ሕግን እና መርህን ተከትሎ እንዲፈፀም ድጋፍ እና ክትትል ያደርጋል፤ የስምሪት ጉድለት ሲፈፀም የእርምት እርምጃ ይወስዳል፣ ያስወስዳል፤

11/ Makes and ensures the recruitment, assignment, transfer and promotion procedures for civil servants in the regional civil service institutions to be fair, transparent and based on merit; provides support and monitoring so that they are carried out in accordance with the law and principles; takes and causes to be taken corrective measures when there is operational deficiency;

12/ የሲቪል ሰርቪስ አስተዳደር ፍርድ ቤቶችን የአገልግሎት አሰጣጥ የሚያሻሽል የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፣ ድጋፍ ያደርጋል፤

12/ Establishes a system enabling the Civil Service Administration Courts improve their service delivery; and supports same;

13/ በክልሉ ሲቪል ሰርቪስ ተቋማት ውስጥ በመንግሥት ሠራተኞች የሚቀርቡ ይግባኞች በአስተዳደር ፍርድ ቤት አማካኝነት መርምሮ እና አጣርቶ በፍሬ ነገር ደረጃ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል፤

13/ Provides final decision on essencial level by investigating and verifying appeals filed by government employees in the regional civil service institutions through the Administrative Court;

14/ ዲጅታል ሲቪል ሰርቪስ በመገንባት ለዜጎች ቀልጣፋ፣ ጥራት እና ቅቡልነት ያለው አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፣ ውጤታማነቱን ይቆጣጠራል፤

14/ Establishes a system of procedures enabling to provide efficient, quality and acceptable services to citizens by developing a digital civil service; implements and controls its effectiveness;

15/ በሁሉም ተቋማት ዘመናዊ የመረጃ ሥርዓት እንዲዘረጋ በማድረግ የክልሉን የመንግሥት ሠራተኞች ዝርዝር መረጃ መዝግቦ ይይዛል፤ ስታቲስቲካዊ መረጃዎችን ያጠናቅራል፣ ያሰራጫል፤

15/ Maintains detailed information of civil servants of the region by causing an establishment of modern information system in all institutions; compiles and disseminates statistical information;

16/ በክልሉ ሲቪል ሰርቪስ ዘመናዊ የተሟላ ሰብአዊ ሀብት አመራር እንዲኖር በሠራተኞች ላይ የሚታዩ የአቅም ክፍተቶችን በጥናት ይለያል፤ በትምህርት እና ሥልጠና ያበቃል፤ የሰው ሀብት ልማቱን በተማከለ መልኩ ለመምራት የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊ እንዲሆን ድጋፍ እና ክትትል ያደርጋል፤

17/ የሲቪል ሰርቫንቱን የሀገር ውስጥ እና የውጭ ሀገር ሥልጠና የሚፈፀምበትን የአሠራር መመሪያ በማዘጋጀት ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ሥራ ላይ ያውላል፣ ይከታተላል፤

18/ የሲቪል ሰርቪሱን አቅም ለመገንባት አስፈላጊ የሆኑ የትምህርት፣ ሥልጠናና የብቃት ምዘና ተቋማት እንዲቋቋሙ ለክልሉ መንግሥት ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ሥራ ላይ ያውላል፣ ይደግፋል፣ ያስተዳድራል፤

19/ የመንግሥት አገልግሎት አሰጣጥን በተመለከተ ጥናት ያደርጋል፣ ሕዝባዊ መድረኮችን እና ወርክ ሾፖችን ያዘጋጃል፣ ውጤታማነቱን ያረጋግጣል፤

20/ የክልሉን መንግሥት ሠራተኞች ሥነ-ምግባር ለማሻሻል የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

21/ ተቋማት የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርድ እና የቅሬታ ማስተናገጃ ሥርዓት መዘርጋታቸውን እና ሥራ ላይ ማዋላቸውን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፣ ኦዲት ያደርጋል፤ ጉድለት ሲያጋጥም የእርምት እርምጃ ይወስዳል፣ እንዲወሰድ ያደርጋል፤

22/ የመንግሥት ሠራተኛ የጡረታ ዕድሜው ሞልቶ ነገር ግን በሚሠራበት ተቋም ለተጨማሪ ጊዜ እንዲያገለግል የተቋሙ ኃላፊ ጥያቄ ሲያቀርብ በሕጉ መሠረት ውሳኔ ይሰጣል፤



16/ Identifies the capacity gaps among employees through research to ensure modern and comprehensive human resource management in the regional civil service; qualifies through education and training; establishes system of procedure to centrally manage human resource development; provides support and monitoring for its implementation,

17/ Prepares a procedural directive for the implementation of domestic and foreign training of civil servants and submits same to the concerned body; implements and monitors it when approved;

18/ Submits to the regional government so that educational, training and competency assessment institutions necessary to build capacity of the civil service to be established; implements, supports and manages upon approval;

19/ Conducts research regarding government service delivery, organizes public forums and workshops, and ensures the effectiveness;

20/ Establishes a system enabling to improve ethics of the regional civil servants, and monitors its implementation;

21/ Monitors, ensures and audits the establishment and implementation of service delivery standards and complaint handling systems in institutions; take and causes to be taken corrective measures when deficiencies encountered;

22/ Make a decision in accordance with the law when head of an institution requests for a civil servant who has reached retirement age to serve for an additional period of time in the institution in which he works;

23/ ልዩ የሥራ ባሕሪ ወይም የሥራ ክብደት ያላቸው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ላይ ተመሥርቶ ልዩ ቅጥር እና ጥቅማጥቅም እንዲፈቀድ ጥያቄ ሲቀርብለት ጉዳዩን በጥልቀት መርምሮ ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት የውሳኔ ሐሳብ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤

23/ Submits recommendation to the Regional Government Council by thoroughly investigating the matter when a request is made to allow special employment and benefits based on the nature of the work or the workload of government offices, and implements same upon approval;

24/ ውድድርን መሠረት ያደረገ ነፃ፣ ገለልተኛ፣ አካታችነትን ያረጋገጠ እና የክልሉን ብዝኃነት የሚያስተናግድ የሲቪል ሰርቪስ ሥርዓት እንዲዘረጋ ያደርጋል፤

24/ Causes for the establishment of civil service system free, independent, inclusive and competitive, and that accommodates the diversity of the region;

25/ ቀልጣፋ እና ውጤታማ የመንግሥት አገልግሎት እንዲኖር ለማድረግ ለሲቪል ሰርቫንቱ የሥልጠና መርሃ-ግብሮችን በመንደፍ ክህሎታቸውን፣ እውቀታቸውን እና ብቃታቸውን እንዲያሳድጉ ያደርጋል፤ ሙያዊ ዕድገት እና ውጤታማ የመንግሥት አስተዳደርን እንዲረጋገጥ ይሠራል፤

25/ Makes civil servants enhance their skills, knowledge and competence by designing training programs in order to ensure efficient and effective government service; works to ensure professional development and effective government administration;

26/ የክልሉን ዕቅድ ለማሳካት የሰው ኃይል ፍላጎትን በመተንተን እና የመጭውን ፍላጎት በመተንበይ በሲቪል ሰርቪሱ በቂ እና የሰለጠነ የሰው ኃይል መሟላቱን ያረጋግጣል፣ ለተግባራዊነቱም ይሠራል፤

26/ Ensures the fulfillment of suffient and trained human power by analyzing demand of human power and forcasting demand of the future inorder to achieve the regional plan; works for its implementation;

27/ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን የሲቪል ሰርቪስ አገልጋይነትን ለማጠናከር፣ ተነሳሽነቶችን ለማሳደግ፣ ምርጥ ተሞክሮዎችን ለመለዋወጥ እና የመንግሥት ስትራቴጂዎችን ተግባራዊ ለማድረግ በትኩረት ይሠራል፤

27/ Being with the relevant body, works to strengthen civil service servitude, enhance initiations, exchange best practices and implement government strategies;

28/ ቴክኖሎጅን በመጠቀም ከተገልጋይ እና ከሠራተኛ እርካታ ጋር የተያያዙ መረጃዎችን በመሰብሰብ እና በመተንተን ፖሊሲ ለመቅረፅ እና አሠራሮችን ለማሻሻል የሚያስችል ጥናት ያደርጋል፤ የማሻሻያ ሐሳቦች በመቅረፅ ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፤

28/ Conducts research using technology enabling to collect and analyze data related to customer and employee satisfaction to formulate policy and improve practices; formulates improvement ideas and causes to be implemented;

29/ የሲቪል ሰርቪሱን ባሕሪያት ከተቋማት ፖሊሲ፣ ርእይ፣ ዕሴቶች እና ግቦች ጋር እንዲጣጣም፣ ሠራተኞች ምቾት ተሰምቷቸው ሥራን በብቃት እንዲሠሩ እና ሕዝብን በቅንነት እንዲያገለግሉ የሚያደርግ ምቹ የሥራ ቦታ እና የሥራ አውድ እንዲፈጠር ይሠራል።

29/ Works for the creation of comfortable workplace and work context to align characteristics of the civil service with the institution's policy, vision, values and goals, employees work effectively feeling comfort, and serve the public with integrity.

## 42. የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን

በሌሎች ሕጎች አስቀድሞ የተደነገገው ወይም ወደ ፊት የሚደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ አካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ዝርዝር ሥልጣን እና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1/ የአካባቢ ጤንነት እና ደኅንነትን የሚያሳድጉ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችን እና ሕጎችን ያመነጫል፤ ለአፈፃፀሙ ከክልሉ የልማት አቅጣጫዎች ጋር የተጣጣመ ዝርዝር መርሃ ግብር ያዘጋጃል፣ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

2/ ዘርፉን በሚመለከት በሀገር አቀፍ እና በክልል ደረጃ የወጡ ፖሊሲዎች እና ሕጎችን እንዲሁም ኢትዮጵያ ተቀብላ ያፀደቀቻቸውን ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፤

3/ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት እና ከነዋሪው ሕዝብ ጋር በመመካከር የአካባቢ ፖሊሲ ማስፈፀሚያ ሕጎችን፣ መርሃ ግብሮችን እና ስልቶችን ያዘጋጃል፣ ይገመግማል፣ ይቆጣጠራል፤

4/ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ያስተባብራል፣ ለአየር ንብረት ለውጥ ተጋላጭ በሆኑ ተቋማት ላይ የተፅዕኖዎች ማቃለያ እና መቋቋሚያ ስልቶችን በዕቅዳቸው ውስጥ አካተው እንዲተገብሩ ክትትል እና ድጋፍ ያደርጋል፣ የሚቀንሱትን የሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀት መጠን ያረጋግጣል፤

5/ የአካባቢን ደኅንነት ለመጠበቅ እና በማናቸውም ሁኔታ የተጎዳ አካባቢን መልሶ እንዲያገግም ለማድረግ አግባብ ካላቸው መሥሪያ ቤቶች ጋር ይሠራል፣ የአቅም ግንባታ ድጋፎችን ይሰጣል፤

6/ የአካባቢ ብክለት እና ብክነትን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር ደረጃውን የጠበቀ ቤተ-ሙከራ በማቋቋም የወጡ የአካባቢ ደረጃዎችን ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፤

## 42. Authority of Environment and Protection

Without prejudice to the existing or subsequent provisions of other laws, the Regional Authority of Environment shall, pursuant to this proclamation, have the following specific powers and duties:

1/ Initiates policies, strategies and laws that promote environmental health and safety; prepares detailed program for its implementation in line with the regional development directions, and implements it upon approval;

2/ Implements policies and laws issued at the national and regional levels regarding the sector as well as international conventions that Ethiopia has accepted and adopted;

3/ Prepares, evaluates, and monitors environmental policy implementation laws, programs and strategies in consultation with stakeholders and the public;

4/ Coordinates a climate-resilient green economy, monitors and supports institutions vulnerable to climate change to include and implement mitigation and adaptation strategies in their plans, and ensures the reduction of greenhouse gas emissions;

5/ Works with relevant offices to protect an environment and to restore any damaged environment in anyway, and provides capacity building support;

6/ Establishes standardized laboratory to prevent and control environmental pollution and wastage and causes environmental standards issued to be implemented;

CamScanner

7/ በመንግሥትም ሆነ በግል ፕሮጀክቶች፣ በማኅበራዊ እና በኢኮኖሚያዊ የልማት ፖሊሲዎች፣ ስልቶች፣ ሕጎች እና መርሃ ግብሮች ላይ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ለማካሄድ የሚያስችል ክልል አቀፍ ሥርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፤

8/ በአካባቢ እና ደን ጥበቃ ላይ የተሠማሩ ግሪን ኢንተርፕራይዞች፣ ክበባት እና የአካባቢ ተቆርቋሪ ማኅበራት ስለ አካባቢ ደኅንነት ጉዳይ እና በአየር ንብረት ለውጥ ተፅዕኖዎች ላይ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ሥልጠና ይሰጣል፣ ይከታተላል፣ ተሞክሮ ቀምሮ ያስፋል፤ እውቅና ይሰጣል፣ ያበረታታል፤

9/ በደን እና የደን ውጤቶች ላይ የሚጣል የሮያሊቲ ክፍያን በመስተዳድር ምክር ቤት አቅርቦ ያስወስናል፣ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፣ ውጤታማነቱን ይከታተላል፤

10/ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን በክልሉ ውስጥ በረሀማነትን ለመከላከል እና የድርቅን አሉታዊ ተፅዕኖ ለመቀነስ የሚያስችሉ ጥናቶችን ያካሂዳል፣ የመፍትሔ ሐሳቦችን ያመነጫል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፤

11/ ጉዳዩ የሚመለከታቸውን አካላት እና ማኅበረሰቡን በማስተባበር የተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ እና አወጋገድ ሥርዓትን በከተሞች ተግባራዊ እንዲደረግ ክትትል እና ድጋፍ ያደርጋል፣ ቆሻሻን መልሶ መጠቀም የሚችሉ አረንጓዴ ቴክኖሎጅዎችን እንዲተገበሩ ያደርጋል፣ ያበረታታል፣ የቁጥጥር ሥርዓት ይዘረጋል፤

12/ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን በልማት ዕቅዶች እና በኢንቨስትመንት መርሃ ግብሮች ውስጥ የሚካተቱ የአካባቢ የአዋጭነት ጥናት ቀመር እና ስሌት ያዘጋጃል፣ እንዲዘጋጁ ያደርጋል፣ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፣ ውጤታማነቱን ይከታተላል፤

7/ Devises a regional-wide system enabling to conduct environmental impact assessment on on public as well as private projects, social and economoic development policies, strategies, laws and programs; Implements same;

8/ Provides training to green enterprises, clubs, and environmental organizations engaged in environmental and forest conservation in order to raise awareness about environmental safety issues and impacts of climate change; monitors, promotes by formulating best practices, gives recognition, encourages same;

9/ Makes royalty payment on forests and forest products determined by submitting same to the Government Council, implements upon approval, and monitors its effectiveness;

10/ Being with the relevant body, conducts studies to prevent desertification and reduce the negative impact of drought in the region, generates recommendations, and implements them;

11/ In coordination with relevant parties and the community, monitors and supports the implementation of an integrated solid waste management and disposal system in urbans, makes green technologies that can reuse waste to be implemented, encourages and establishes a regulatory system;

12/ Being with the relevant party, prepares and causes for the preparation of formulas of environmental feasibility studies and calculations to be included in development plans and investment programs; cuases them to be utilized, and monitors its effectiveness;

CamScanner

13/ ዘላቂነት የጎደለው የተፈጥሮ ሀብቶች አጠቃቀም ልምድን በመከላል የአካባቢ መራቆት እና እና ብክለትን ለመከላከል የሚያስችል የመግቻ እና የማበረታቻ ዘዴዎችን ይቀይሳል፣ ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፤

14/ የአካባቢ እና ደን ጥበቃ መረጃዎችን ያሰባስባል፣ ያደራጃል፣ በሥራ ላይ ያውላል፣ ለሕዝብ ተደራሽ እንዲሆኑ ያደርጋል፤

15/ የአካባቢ እና የደን ጥበቃ ተግባራት አፈፃፀም ውጤታማነትን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ጥናት እና ምርምሮች እንዲካሄዱ ያደርጋል፣ እንደ አስፈላጊነቱም ራሱ ያካሂዳል፤

16/ አግባብ ባላቸው የሕግ ድንጋጌዎች መሠረት የአካባቢ ጥበቃ ግዴታዎች መከበራቸውን ለማረጋገጥ በማናቸውም መሬት፣ ቅጥር ግቢ ወይም ሌላ ቦታ ይገባል፣ ይፈትሻል፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ናሙናዎችን ይወስዳል፤

17/ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን የአካባቢ እና ደን ጥበቃ ሥራዎች በሥርዓተ ትምህርት ውስጥ እንዲካተቱ ያደርጋል፣ መደበኛ ያልሆኑ የአካባቢ እና ደን ጥበቃ ትምህርት መርሃ ግብሮችን ያስፋፋል፣ ትምህርት ይሰጣል፤

18/ የአካባቢ እና ደን ጥበቃ የድርጊት እቅዶችን እና ፕሮጀክቶችን ዝግጅት ያበረታታል ወይም ያግዛል፤ ለድርጊት ዕቅዶቹ እና ፕሮጀክቶቹ ማስፈፀሚያ የሚውሉ ድጋፎችን ያፈላልጋል፤

19/ ሀገር አቀፍ የአካባቢ ደኅንነት፣ የደንና የዱር እንስሳት ጥበቃ እና አጠቃቀም ሕጎችን በክልሉ ውስጥ ተፈፃሚ ለማድረግ የሚያስችል መመሪያ ያወጣል፣ በሥራ ላይ ያውላል፤

20/ በክልሉ የአካባቢ እና ደን ጥበቃ ምክር ቤት ያቋቁማል፣ እንደ አስፈላጊነቱ በተዋረድ የአስተዳደር እርከኖች እንዲቋቋሙ እና እንዲጠናከሩ ያደርጋል፣ ይከታተላል፣ ይደግፋል፤

13/ Designs and implements prevention and encouragement systems enabling to prevent environmental degradation and pollution through preventing unsustainable use of natural resources;

14/ Collects and organizes information of environmental and forest protection, implements and makes available to the public;

15/ Causes for undertaking of studies and research to ensure the effectiveness of environmental and forest protection activities, and conducts by its own as necessary;

16/ Enters into any land, compound or other place, and inspects to ensure the compliance of environmental protection obligations in accordance with relevant legal provisions; and takes samples when found necessary;

17/ Being with the relevant body, makes environmental and forest protection activities to be included in the curriculum, promotes non-formal environmental and forest protection education programs, and provides education;

18/ Encourages or assists preparation of environmental and forest protection action plans and projects; seeks support for the implementation of the action plans and projects;

19/ Issues and implements a directive enabling to implement national environmental safety, forest and wildlife protection and utilization laws in the region;

20/ Establishes a Regional Environment and Forest Conservation Council and, as necessary, makes same to be established and strengthened in lower administrative levels; monitors and supports;

21/ የአካባቢ አያያዝን እና ጥበቃን ተቀዳሚ ዓላማቸው በማድረግ ለሚሠሩ ለማናቸውም ድርጅቶች ወይም ግለሰቦች ሙያዊ የምክር አገልግሎት ይሰጣል፤ የአካባቢ እና ደን ጥበቃ ምክር ቤቱ ሲወስን የፋይናንስ ድጋፍ ይሰጣል፤

22/ አግባብ ያላቸው መ/ሥሪያ ቤቶች በአካባቢ እና ደን ጥበቃ ሕጎች የተጣለባቸውን ግዴታዎች በትክክል እንዲወጡ ተገቢውን ድጋፍ እና የምክር አገልግሎት ይሰጣል፤ የእርምት እርምጃ ሊወሰድባቸው በሚገቡ ጉዳዮች ላይ እርምጃ ይወስዳል፣ በሌሎች አካላት እንዲወሰድ ያደርጋል፤

23/ በሳይንሳዊ እና በአካባቢያዊ መርሆች ላይ የተመሠረቱ እና ተግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉ የአካባቢ ደረጃዎችን ያዘጋጃል፣ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አካላት መረጃ ይሰጣል፤

24/ በአካባቢ ላይ የሚደርሱ ድንገተኛ የተፈጥሮ እና ሰው ሠራሽ አደጋዎችን ለመቋቋም ስለሚወሰዱ የጥንቃቄ እርምጃዎች የክልሉን መንግሥት ያማክራል፤

25/ የአካባቢ እና ደን ጥበቃ ጉዳዮችን ለሚያማክሩ እና ለሚያጠኑ ድርጅቶች እና ባለሙያዎች ሙያዊ ድጋፍ እና የብቃት ማረጋገጫ ሰነድ ይሰጣል፣ ያድሳል፣ ይሰርዛል፤

26/ በክልሉ ውስጥ የሚካሄደውን የደን ሀብት ውጤቶች ዝውውር ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

27/ የክልሉ ኅብረተሰብ ስለ ዱር እንስሳት አያያዝ፣ ጥበቃ እና አጠቃቀም በቂ ግንዛቤ እንዲኖረው ያደርጋል፣ ብርቅየ የዱር እንስሳት ዝርያዎች ልዩ ጥበቃ እና እንክብካቤ እንዲደረግላቸው ይሠራል፤

21/ Provides professional advisory services to any organizations or individuals working in environmental management and protection as their primary objective, and provides financial support when the Environment and Forest Protection Council determines;

22/ Provides the appropriate support and advisory services to relevant offices to make them properly fulfill their obligations under the Environment and Forest Protection Laws, takes measure on issues requiring to be corrective actions, and have them to be taken by other bodies;

23/ Prepares environmental standards that are based on scientific and environmental principles and that can be applicable, and provides information to relevant bodies;

24/ Advises the regional government on precautionary measures to be taken to deal with natural and man-made disasters that may occur in an environment;

25/ Provides professional support and quality assurance certificate to organizations and professionals who consult and study on issues of environment and forest protection, renews, and cancels;

26/ Monitors and controls the movement of forest resources products within the region;

27/ Makes the regional society have sufficient awareness about the management, protection and use of wild animals, and works to ensure that rare wild animal species are given special protection and care;

CamScanner

28/ በክልሉ ውስጥ የሚገኙ ወንዞችን እና ሐይቆችን የሚያዋስኑ አካባቢዎችን እንዲሁም እርጥበት አዘል መሬቶችን የሚመለከት መረጃ ያሰባስባል፤ ደኅንነታውን አደጋ ላይ የሚጥሉ እንቅስቃሴዎችን በቅርብ ይከታተላል፣ ይቆጣራል፤

29/ የብዝኃ ሕይወት፣ የሥርዓተ ምሕዳሮችን እና የሌሎች የአካባቢ ሀብቶችን አያያዝ እና አጠቃቀም ለማሻሻል የሚያግዙ ጥናቶችን ያካሂዳል፣ የመፍትሔ አማራጮችን ይተገብራል፤

30/ የአካባቢ ሀብቶችን አስመልክቶ የዋጋ ትመና ጥናቶችን ያካሂዳል፣ በትመናው ውጤት መሠረትም ፕሮግራሞች እና ፕሮጀክቶች ሲነደፉ በአዋጭነት ስሌታቸው ውስጥ የአካባቢ ሀብቶች ዋጋ እንዲካተት ያደርጋል፣ በትግበራ ወቅት ለሚደርሰው ማናቸውም የአካባቢ ሀብት ጥፋት በሀብት ትመናው መሠረት ተመጣጣኝ ካሣ እንዲከፈል ያደርጋል፤

31/ የአካባቢ ደኅንነትን ለማስከበር መንግሥታዊ እና መንግሥታዊ ባልሆኑ ተቋማት ተግባር ላይ የምርመራ እና የክትትል ሥራዎችን ያከናውናል፤ ኃላፊነታቸውን በአግባቡ ባልተወጡት ላይ ተገቢውን እርምጃ ይወስዳል፣ ያስወስዳል፤

32/ ማንኛውም የልማት ፕሮጀክት በሚታቀድበት ጊዜ አስቀድሞ የአካባቢ ተፅዕኖ ዳሰሳ ጥናት እንዲካሄድ ያደርጋል፣ መስፈርት ያዘጋጃል፣ ለሚመለከተው አካል ይሰጣል፣ ልማቱ በአካባቢ ላይ ተፅዕኖ እንዳያደርስ ይቆጣጠራል፤

33/ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በክልሉ ውስጥ የሚገኙትን የተለያዩ የደን አይነቶችን፣ ፓርኮች እና ሌሎች ጥብቅ ስፍራዎች ያጠናል፣ ይመዘግባል፣ ይጠብቃል፣ ያስተዳድራል፤

28/ Collects information on the areas bordering rivers and lakes in the region as well as wetlands; closely monitors and controls activities that threaten their safety;

29/ Conducts studies helping to improve management and use of biodiversity, ecosystems and other environmental resources, and implements alternative solutions;

30/ Conducts valuation studies regarding environmental resources, makes the value of environmental resources in formulating feasibility study of programs and projects to be included based on the results of the valuation, and makes appropriate compensation to be paid for any damage to environmental resources during implementation based on the valuation;

31/ Carries out investigation and monitoring activities on the activities of governmental and non-governmental institutions to protect environmental safety; takes and causes to be taken appropriate action against those who do not properly fulfill their responsibilities;

32/ Makes an environmental impact assessment to be conducted when any development project is planed, prepares criteria, provides them to the relevant body, and monitors the development not cause impact on an environment;

33/ Studies, registers, protects and manages various types of forests, parks and other protected areas in the region in cooperation with the relevant bodies;

34/ የክልሉ የደን ሀብት ትርጉም ያለው ኢኮኖሚያዊ እና ሥነ ምሕዳራዊ ጥቅም እንዲሰጥ ለማስቻል የደን ሀብት ጥበቃ እና አጠቃቀም ዕቅድ ያዘጋጃል፣ ይተገብራል፣ ውጤታማነቱን ይከታተላል፤

35/ የክልሉን የደን ሀብት መረጃ በዘመናዊ መንገድ ይሰበስባል፣ ያደራጃል፣ ይተነትናል፤

36/ በክልሉ ውስጥ የሚካሄዱ የደን ጥበቃ፣ አጠቃቀም እና አስተዳደር ሥራዎችን በበላይነት ያስተባብራል፤

37/ የክልሉ የደን ሀብት ለአየር ንብረት ለውጥ ተጋላጭነትን እና አደጋን ለመቀነስ የሚያበረክተውን አስተዋፅዖ በተመለከተ ጥናቶችን ያካሂዳል፣ የጥናት ውጤቶች ተግባራዊ እንዲደረጉ ያስተባብራል፤

38/ ከፍተኛ የካርበን ልቀት ያላቸው ሴክተሮች ልቀት እንዲቀንስ ይሠራል፣ ካርበን ትሬዲንግ ወይም ኢሚሽን ትሬዲንግን በመጠቀም የብክለት መጠናቸውን የሚቀንሱ ኩባንያዎችን ያበረታታል፣ ብክለትን መቆጣጠር የሚያስችል የገበያ ሥርዓት ይዘረጋል፣ ለአፈጻፀሙ መመሪያ ያዘጋጃል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፤

39/ የግሉ ዘርፍ በደን ጥበቃ፣ አጠቃቀም እና ግብይት ሥራዎች ላይ ጉልህ አስተዋፅዖ እንዲኖረው ድጋፍ እና ክትትል ያደርጋል፤

40/ በሐይቆች እና አካባቢያቸው የተከሰቱ ወይም ወደ ፊት ሊከሰቱ የሚችሉ አደገኛ፣ መጤ እና ወራሪ አረሞችን በጥናት ይለያል፣ ሊወገዱ የሚችሉበትን ስልት ነድፎ ተግባራዊ ያደርጋል፣ ውጤታማ መሆኑን ይከታተላል፤

41/ ሐይቆችን እና አካባቢያቸውን የሚጎዱ የብክለት ምንጮችን ይለያል፣ የመፍትሔ እርምጃዎችን ይወስዳል፣ ብክለት የሚያመጡ ነገሮች ወደ ውኃ አካላቱ እንዳይገቡ የሚያስችሉ ቴክኖሎጅዎችን በመለየት በሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፤



34/ Prepares, implements, and monitors effectiveness of forest resource conservation and utilization plan to ensure that the region's forest resources provide meaningful economic and ecological benefits;

35/ Collects, organizes, and analyzes information on the region's forest resources in a modern manner;

36/ Coordinates ontop of forest conservation, utilization, and management activities taken place in the region;

37/ Conducts studies on the contribution of the region's forest resources to reducing vulnerability and risk to climate change, and coordinates the implementation of research results;

38/ Works to the reduction of emissions in sectors with high carbon emissions, encourages companies with less pollution levels through carbon trading or emission trading, establishes a market system to control pollution, prepares and implements directive for its implementation;

39/ Supports and monitors the private sector to make a significant contribution to forest protection, use and marketing activities;

40/ Identifies through research the dangerous, new-coming and invasive weeds that have occurred or may occur in lakes and their surroundings, designs and implements strategies for their elimination, and monitors its effectiveness;

41/ Identifies sources of pollution that affect lakes and their surroundings, takes remedial measures, and identifies and implements technologies that prevent pollutants from entering to water bodies;

CamScanner

42/ ከሐይቆች ጋር ተያያዥነት ያላቸው ውኃ አዘል መሬቶች እና ወንዞች በዘላቂነት እንዲጠበቁ፣ እንዲያገግሙ እና ጥቅም ላይ እንዲውሉ የሚያስችል ጥናት እና ምርምር እንዲካሄዳል፣ የአያያዝ ዕቅድ እንዲዘጋጅ እና ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፤

43/ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን የሐይቆችን ህልውና ለማረጋገጥ የሚያስችል የተቀናጀ የተፋሰስ ልማት እና ጥበቃ ሥራ እንዲከናወን ያደርጋል፤

44/ ሐይቆችን በመጠበቅ እና በመንከባከብ ረገድ የራሳቸው ድርሻ ያላቸውን አካላት ይደግፋል፣ ይከታተላል፣ ያበረታታል፤

45/ የክልሉን የአካባቢ ሁኔታ ዘገባ በየወቅቱ እያዘጋጀ ለመንግሥትም ሆነ ለሕዝብ እንዲሰራጭ ያደርጋል፤

46/ በጣና ሐይቅ እና በሌሎች የውኃ አካላት ጥበቃ እና እንክብካቤ ዙሪያ ከሚሠሩ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር የሥራ ግንኙነቶችን ይፈጥራል፤

47/ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን የአካባቢን የሕይወት ጥራት የሚቀንሱ የድምፅ ብክለቶች እንዳይኖሩ ይሠራል፣ ለአፈፃፀሙም መመሪያ ያወጣል፣ መጠናቸውን ይቆጣጠራል፣ ችግር ሲያጋጥም እርምጃ ይወስዳል።

## 43. የመንግሥት ኮሚዩኒኬሽን ቢሮ

በሌሎች ሕጎች አስቀድሞ የተደነገገው ወይም ወደ ፊት የሚደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ መንግሥት ኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች ቢሮ የሚከተሉት ዝርዝር ሥልጣን እና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1/ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችን እና ሕጎችን ያመነጫል፣ ለአፈፃፀሙ ከክልሉ የልማት አቅጣጫዎች ጋር የተጣጣመ ዝርዝር መርሃ ግብር ያዘጋጃል፣ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

42/ Conducts studies and research enablibg to the sustainable protection, restoration and use of wetlands and rivers associated with lakes, and prepares and implements management plans;

43/ Being with relevant bodies, makes an integrated watershed development and conservation works enabling to ensure existence of lakes to be implemented;

44/ Supports, monitors and encourages bodies that have a role to play in protecting and maintaining lakes;

45/ Causes for dissemination of regional environmental status report to the government and the public on a regular basis by preparing same;

46/ Establishes working relationships with international organizations working on the protection and care of Lake Tana and other water bodies;

47/ Works with relevant body to prevent noise pollution that reduces the quality environmental life, issues directive for its implementation, monitors their amounts, and takes action when problems arise.

## 43. Bureau of Government Communication

Without prejudice to the existing or subsequent provision of other laws, the Regional Bureau of Government Communication shall, pursuant to this proclamation, have the following specific powers and duties:

1/ Generates policies, strategies and laws, prepares a detailed program for their implementation in line with the development directions of the region, and implements them upon approval;

CamScanner

2/ የክልሉ መንግሥት ዋና ቃል አቀባይ በመሆን ይሠራል፤ መንግሥታዊ መልዕክቶችን ያሰራጫል፤ በክልላዊ ጉዳዮች ላይ የክልሉን መንግሥት ውሳኔዎች እና አቋሞች ለሕዝብ ይፋ ያደርጋል፤

3/ በክልሉ መንግሥት አቋሞች እና አሠራሮች ላይ የሚሰነዘሩ ትችቶች እና የሚሰጡ አስተያየቶችን በንቃት ይከታተላል፤ የሕዝብ አስተያየቶችን በማሰባሰብ እና በመተንተን ውጤቱን ጉዳዩ ለሚመለከታቸው የክልሉ መንግሥት አካላት ያሰራጫል፤

4/ የክልሉን ሕዝብ እና መንግሥት ጥቅም ለማስጠበቅ የሀገር ውስጥ እና የውጭ መገናኛ ብዙኃን የዕለት ተዕለት የሚዲያ ዳሰሳ ያደርጋል፤ ይተነትናል፤ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው የክልሉ መንግሥት አካላት ያሳውቃል፤

5/ በክልሉ መንግሥት ፖሊሲዎች እና ስትራቴጂዎች ዙሪያ ተገቢውን ግንዛቤ ለማስያዝ እና ግልፅነትን ለማስፈን ሕዝባዊ የውይይት እና የምክክር መድረኮችን ያዘጋጃል፣ ያስተባብራል፤

6/ በክልሉ መንግሥት ስም የመረጃ መረብ ሥራዎችን ያከናውናል፤ የድረ-ገጽ ልውውጦችን ያካሂዳል፤

7/ የክልሉን ሕዝብ እና መንግሥት ሁነቶች አስመልክቶ ለክልሉ፣ ለሀገር ውስጥም ሆነ ለውጭ ሀገር ጋዜጠኞች በየወቅቱ መግለጫዎችን ይሰጣል፤

8/ የክልሉን ሕዝብ እና መንግሥት መልካም ገፅታ ለመገንባ የሚያስችሉ ተከታታይ ሥራዎችን ይሠራል፤ መረጃዎችን ይሰጣል፤ የሚሰራጩ የተሳሳቱ መረጃዎች በወቅቱ እንዲታረሙ ያደርጋል፤

9/ ከሚመለከተው አካላት ጋር በመሆን ከክልሉ ሕዝብ ባሕል፣ እሴት እና ታሪክ ውጭ በሆነ አግባብ በክልሉ ሕዝብ ላይ የሚነሡ የሐሰት ትርክቶች እንዲታረሙ ተገቢ የሆኑ ሥራዎችን ይሠራል፤ ሀሰተኛ ትርክቶችን ይከላከላል፣ ብሔራዊ ገዥ ትርክት እንዲሰርፅ ለማድረግ በትኩረት ይሠራል፤



2/ Works being as main spokesperson for the regional government, disseminates government messages, and publicizes the regional government's decisions and stands on regional issues;

3/ Actively monitors criticisms and comments on the regional government's stands and practices, collects and analyzes public opinions, and disseminates the results to relevant regional government bodies by collecting public opinions and analyzing them;

4/ Conducts daily media surveys and analyses of local and foreign media outlets to protect interests of the people and government of the region, and informs relevant regional government bodies about the issue;

5/ Organizes and coordinates public discussion and consultation forums to ensure appropriate understanding and transparency regarding policies and strategies of the regional government;

6/ Performs information network activities and conducts website exchanges in name of regional government;

7/ Provides regular statements to the regional, domestic and foreign journalists regarding events of the people and government of the region;

8/ Carries out continuous work to build good image of the people and government of the region, provides information, and makes incorrect disseminated information to be corrected;

9/ Being with relevant bodies, carries out appropriate work to correct false narrations raised against people of the region which are outside the culture, values and history of the people of the region, defends false narrations, works diligently to inculcate national governing narration;

CamScanner

10/ በመንግሥት እና በሕዝብ መካከል የሚደረጉ የተግባቦት ግንኙነትን ያስተዳድራል፤ በመንግሥት ባለሥልጣናት እና በኅብረተሰቡ መካከል ውይይቶች እንዲካሄዱ መድረኮችን ያመቻቻል፤

11/ የመንግሥት ተግባራትን እና የልማት ዕቅዶችን ለሕዝብ በትክክል ለማስገንዘብ ከሚዲያዎች ጋር ግንኙነቶችን ይፈጥራል፣ ጋዜጣዊ መግለጫዎችን ያደራጃል፣ ለተቋማት የሚዲያ ጥያቄዎች ወቅታዊ እና ተገቢ ምላሽ ይሰጣል፤

12/ በድንገተኛ ሁኔታዎች ወይም በቀውሶች ጊዜ የሰላም ጋዜጠኝነትን የሚያጎሉ የግንኙነት ስልቶችን ያዘጋጃል፣ ለሕዝቡ ትክክለኛውን መረጃ ያሳውቃል፣ የተሳሳቱ መረጃዎች ሲያጋጥሙ ለማረም በንቃት ይሠራል፤

13/ የመንግሥትን የልማት ውጥኖች እና ተነሣሽነቶች የሚያንፀባርቁ እና ሕዝባዊ ተሳትፎን የሚያበረታቱ መጣጥፎችን፣ ቪዲዮዎችን፣ ብሮሸሮችን እና የማኅበራዊ ሚዲያ ዘመቻዎችን ጨምሮ አሳታፊ ይዘቶችን ያዘጋጃል፣ ለኅብረተሰቡ ተደራሽ እንዲሆኑ ያደርጋል፤

14/ ሁሉም የተግባቦት ጥረቶች ከመንግሥት አጠቃላይ ተልዕኮ እና ከማኅበረሰቡ እሴቶች ጋር ተጣጥመው እንዲፈፀሙ ያደርጋል፤

15/ ለተለያዩ የመንግሥት አካላት በውጤታማ የተግባቦት ስልቶች እና የሚዲያ መስተጋብር ላይ የአቅም ግንባታ ሥልጠና ይሰጣል፣ መልዕክቶችን በግልፅ እና በውጤታማነት እንዲያስተላልፉ እገዛ ያደርጋል፤

16/ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት የኮሚዩኒኬሽን እና የመረጃ ስርጭትን በተመለከተ አንድ ወጥ አሠራር እንዲኖር ለማድረግ ሥርዓት ይዘረጋል፣ አፈፃፀሙንም ይከታተላል፤

17/ በመንግሥት ሴክተሮች ውስጥ የሚከናወኑ የተግባቦት ሥራዎችን ያቀናጃል፣ ይከታተላል፣ የሚቀርቡ ሪፖርቶችን ይገመግማል፣ ድጋፍ እና ክትትል ያደርጋል፤

10/ Manages communication relation between the government and the public; Facilitates forums for discussions between government officials and the public;

11/ Establishs relationships with the media to accurately inform the public about government activities and development plans, organizes press conferences, provides timely and appropriate responses to media inquiries from institutions;

12/ Develops communication strategies that enhance peace journalism in times of emergency or crisis, provides accurate information to the public, and actively works to correct misinformation when encountered;

13/ Develops participatory contents including articles, videos, brochures, and social media campaigns that reflect the government's development initiation and initiatives and encourage public participation; and makes accessible to the public;

14/ Makes all communication efforts to be implemented balanced with the government's overall mission and community values;

15/ Provides capacity building training to various government entities on effective communication strategies and media engagement, and assists them in conveying messages clearly and effectively;

16/ In coordination with relevant bodies, establishes a system to the existence of uniform procedure for communication and information dissemination, and monitors its implementation;

17/ Coordinates and monitors communication activities carried out in government sectors; evaluates reported submitted, supports and monitors;

CamScanner

18/ ለመንግሥት ኮሚዩኒኬሽን አመራሮች፣ ባለሙያዎች እና ሚዲያ የሥራ መነሻ የሚሆን አጀንዳ ይቀርፃል፣ አፈፃፀማቸውን ይከታተላል፤

19/ ከሚመለከተው የፌደራል መንግሥት አካል ጋር በመተባበር ሥርጭታቸው በክልሉ ውስጥ ለሆኑ እና ለንግድ ዓላማ የሚውሉ የሕትመት ሚዲያ እና ማስታወቂያ ሥራ ለሚሠማሩ አካላት ፈቃድ ይሰጣል፣ በሕግ መሠረት መሥራታቸውንም ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

20/ በክልሉ ውስጥ የሚታተሙ የውጭ ወይም የአደባባይ ማስታወቂያዎችን አስመልክቶ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ስታንዳርድ ያወጣል፣ ሥራ ላይ ያውላል፣ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

21/ በክልሉ ርዕሰ መስተዳድር በሚሰጠው ውክልና መሠረት ለክልሉን መንግሥት ተቋማት የሕዝብ ግንኙነት ዳይሬክተሮችን ይመድባል ፣ የሥራ አፈፃፀማቸውን ይከታተላል፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከኃላፊነት ያነሣል፤

22/ በክልሉ ውስጥ የውጭ ወይም የአደባባይ ማስታወቂያ የሚለጥፉ አካላት ፈቃድ ያላቸው መሆናቸውን ያረጋግጣል፣ ይቆጠራል፤

23/ ከሚመለከተው ጋር በመሆን የውጭ ወይም የአደባባይ ማስታወቂያዎች የህብረተሰቡን ባህል፣ እሴቶች እንዲሁም የተግባቦት መርሆች የጠበቁ መሆናቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ እርምጃ ይወስዳል፣ ያስወስዳል።

## 44. የእንስሳት እና ዓሣ ሀብት ቢሮ

በሌሎች ሕጎች አስቀድሞ የተደነገገው ወይም ወደ ፊት የሚደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ የእንስሳት እና ዓሣ ሀብት ቢሮ የሚከተሉት ዝርዝር ሥልጣን እና ተግባራት ይኖሩታል፦

18/ Formulates work commencement agenda for government communication leaders, professionals and media, and monitors their implementation;

19/ In cooperation with relevant federal government body, grants licenses to entities engaged in print media and advertising activities that are distributed within the region and are used for commercial purposes, and monitors and controls their operation in accordance with the law;

20/ In cooperation with relevant bodies, issues, implements, monitors and controls standards regarding external or public advertisements published in the region;

21/ In accordance with the delegation given by the Head of Regional Government, assigns public relations directors for regional government institutions, monitors their performance, and removes them from office when necessary;

22/ Ensures and controls that entities posting outdoor or public advertisements in the region are licensed;

23/ Being with concerned, monitors and controls whether outdoor or public advertisements comply with culture, values as well as principles of communication of the community; takes and causes to be taken actions.

## 44. Bureau of Animal and Fisheries Resources

Without prejudice to what has been previously or may be provided for in other laws, the Regional Animal and Fisheries Bureau shall have the following detailed powers and duties:

CS CamScanner

1/ የእንስሳት እና ዓሣ ሀብት ምርታማነትን በዘላቂነት የሚያሳድጉ እና የዘርፉን ተወዳዳሪነት የሚያረጋግጡ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችን፣ ፕሮግራሞችን፣ ፓኬጆችን እና የሕግ ማዕቀፎችን ይቀርፃል፤ በሚመለከተው አካል ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

2/ የእንስሳት እና ዓሣ ምርት እና ምርታማነትን በማሳደግ የምርት ተወዳዳሪነትን ለማረጋገጥ የቴክኖሎጂ እና ዘመናዊ አመራረት ስልት እንዲስፋፋ እና አጠቃቀሙ እንዲያድግ ያደርጋል፣ ውጤታማነቱን ያረጋግጣል፤

3/ ገበያ መር የኤክስቴንሽ አገልግሎት ሥርዓት ይዘረጋል፣ ያሻሽላል፤ ለአርሶ አደሩ፣ ለከፊል አርብቶ አደሩ እንዲሁም በእንስሳት እና ዓሣ ሀብት ልማት ለተሠማሩ ሌሎች አካላት ተገቢውን ሙያዊ ድጋፍ ይሰጣል፣ ውጤታማነቱን በየጊዜው ያረጋግጣል፤

4/ የግል ባለሀብቶች፣ ኢንተርፕራይዞች እንዲሁም የእርባታ እና ግብይት ኅብረት ሥራ ማኅበራት በዘርፉ የሚኖራቸው ተሳትፎ እና ሚና እንዲያድግ ለማድረግ ሥርዓት ይዘረጋል፤ ለአፈፃፀሙ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፣ ውጤታማነቱን ይከታተላል፤

5/ ለእንስሳት እና ዓሣ ሀብት ልማት ዘርፉ ተወዳዳሪነት አስፈላጊ የሆኑ ቴክኖሎጂዎችን እና ግብዓቶችን ፍላጎት፣ አቅርቦት፣ ሥርጭት እና አጠቃቀም የሚመራበትን ሥርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፣ ውጤታማነቱን ያረጋግጣል፤

6/ በክልሉ ውስጥ የሚገኙ የእንስሳት እና ዓሣ ሀብት ዝርያዎችን ይለያል፣ የዝርያ ማሻሻል ሥራ በስፋት እና በዘላቂነት እንዲሠራ ያደርጋል፣ የኮሜርሻል አሠራር ሥርዓትን በመዘርጋት ሀብቶቹ ገበያ አሸናፊ እና ኢንዱስትሪ መጋቢ በሆነ አግባብ እንዲለሙ ያደርጋል፣ አፈፃፀሙ ውጤታማ መሆኑን ይከታተላል፣ ይደግፋል፤

1/ Formulates policies, strategies, programs, packages and legal frameworks that sustainably increase productivity of livestock and fish resources and ensure competitiveness of the sector; implements them when approved by the relevant body;

2/ Causes for expansion and increased utilization of technological and modern production methods to ensure product competitiveness by increasing livestock and fish production and productivity, and ensures the effectiveness;

3/ Establishes and improves market-oriented extension service system; provides the appropriate professional support to farmers, semi-pastoralists and other entities engaged in animal and fishery resource development, periodically ensures its effectiveness;

4/ Establishes a system to increase participation and role of private investors, enterprises and farming and marketing cooperatives in the sector; creates conducive environment for its implementation, and monitors its effectiveness;

5/ Establish a system to manage the demand, supply, distribution and use of technologies and resources essential for the competitiveness of the livestock and fisheries development sector, ensure its implementation, and ensure its effectiveness;

6/ Identifies livestock and fisheries species in the region, makes breed improvement work is carried out extensively and sustainably, causes for development of the resources in market-winning and industry-friendly manner by establishing commercial procedural system, monitors and supports for effectiveness of the implementation;

CamScanner

7/ በሥጋ፣ በወተት፣ በእንቁላል ምርታማነታቸው እና በሽታን በመቋቋም አቅማቸው የተሻሉ ሀገር በቀል የእንስሳት ዝርያዎችን በጥናት ይለያል፣ ይመዘግባል፣ እንዲመረጡ፣ እንዲጠበቁ እና እንዲባዙ ያደረጋል፣ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፤

8/ የክልሉ ሕዝብ በዘርፉ ያለውን ፀጋ አውጥቶ በመጠቀም ከድህነት እና ከኋላ ቀርነት እንዲላቀቅ፣ ማዕዱ ሙሉ እና የተትረፈረፈ እንዲሆን እንዲሁም የእንስሳት እና ዓሣ ዘርፉ ለክልል ውስጥ ጠቅላላ ምርት የሚያበረክተው አስተዋፅዖ እንዲያድግ በትኩረት ይሠራል፤

9/ የክልሉ አርሶ አደሮች በየጊዜው እያደገ ከሚሄደው የእንስሳት እና የእንስሳት ተዋፅዖ ምርቶች ገበያ በጥረታቸው ልክ ተጠቃሚ እንዲሆኑ እንዲሁም በዘርፉ ሰፊ የሥራ ዕድል እንዲፈጠር የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፣ ውጤታማነቱን ይከታተላል፣

10/ የዲጂታላይዜሽን ሥርዓት በመዘርጋት የክልሉን የእንስሳት ሀብት ልማት ዓይነት እና ቁጥር ክብዜት፣ ከዝርያ ማሻሻል፣ ከጤና አገልግሎት እና መኖ ልማት ጋር የተያያዙ መረጃዎችን ያሰባስባል፣ ያደራጃል፣ ይተነትናል፣ የዘርፉን ውጤታማነት በሚያሳድግ አግባብ ጥቅም ላይ ያውላል፤

11/ ከምርምር ተቋማት ጋር በመተባበር የእንስሳት እና ዓሣ ሀብት ልማት፣ ጤና አጠባበቅ እና መኖ ልማት ቴክኖሎጂዎችን ይለያል፣ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፣ ያሻሽላል፣ ያስፋፋል፣

12/ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን በእንስሳት እና ዓሣ ሀብት ልማት ዘርፍ የሚሠማሩ አካላት የፋይናንስ አቅርቦት፣ የመሥሪያ እና የመሸጫ ቦታ እንዲያገኙ ያደርጋል፣ ሙያዊ የምክር አገልግሎት ይሰጣል፣ ይደግፋል፤

7/ Identifies, through research, better indigenous animal breeds in their meat, milk and egg productivity and disease resistance; registers, makes them to be selected, maintained and reproduced, provides the necessary support;

8/ Works diligently to make people of the region, by utilizing the resources available in the sector, to be free from poverty and backwardness, their meal is complete and surplus as well as to increase contribution of the livestock and fish sectors to the gross domestic production in the region;

9/ Establishes a system to enable farmers in the region to benefit from the ever-growing market of livestock and livestock products and to create extensive employment opportunities in the sector, and monitors its effectiveness;

10/ Establishes digitalization system Collects, organizes and analyzes information related to the type and number of livestock resources development in the region, breed improvement, health services and fodder development, and uses it in a manner that enhances efficiency of the sector;

11/ Identifies, implements, improves and disseminates technologies for livestock and fish resource development, health care and fodder development in collaboration with research institutions;

12/ Being with relevant body, makes entities to be engaged in the livestock and fisheries development sector get financial provision, working and saling space; provides professional advisory services, and support;

13/ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን የእንስሳት መጠጥ ውኃ እጥረት ባለባቸው የድርቅ ተጋላጭ አካባቢዎች እጥረቱን በዘላቂነት ለመፍታት የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፣ ውጤታማነቱን ይከታተላል፤

14/ የክልሉ አርሶ አደሮች እና በዘርፉ የተሠማሩ ሌሎች አካላት ከብዛት ይልቅ ጥራት እና ምርታማነት ላይ እንዲያተኩሩ ያደርጋል፤ የእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ ግብዓት በስፋት እና በጥራት ያመርታል፣ ያስመርታል፣ ጥቅም ላይ እንዲውል ያደርጋል፣ የእንስሳት ብዜት ማዕከላትን ያቋቁማል፣ ያደራጃል፣ ያስተዳድራል፤

15/ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን የተፈጥሮ ሀብት መራቆት በማያደርስ አግባብ ኅብረተሰቡ ከለሙ ደኖች እና ተፋሰሶች የእንስሳት መኖ ማምረት እንዲሁም የግጦሽ መሬት አያያዝ እና አጠቃቀምን ማሻሻል የሚያስችለው ምቹ ሁኔታ እንዲፈጠርለት ሥርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊነቱን ያረጋግጣል፣ ውጤታማነቱን ይከታተላል፤

16/ የተለያዩ የመኖ ማልሚያ ስልቶችን እና የአሠራር ማዕቀፎችን በመቀየስ የግል ዘርፉ ለአገር ውስጥ እና ለውጭ ገበያ የሚቀርብ መኖ በስፋት እና በጥራት እንዲያመርት አስፈላጊውን ሙያዊ ድጋፍ ይሰጣል፣ በተመረጡ አካባቢዎች የመኖ ባንክ እንዲቋቋም ያደርጋል፤

17/ የቁም እንስሳት ጤንነት እና ምርታማነት እንዲያድግ፣ የቆዳ እና ሌጦ ምርት ጥራቱ ተጠብቆ ለገበያ እንዲቀርብ የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፣ ውጤታማ መሆኑንም ይከታተላል፤

18/ በግል እንስሳት መድኃኒት እና የክሊኒክ አገልግሎት ንግድ ሥራዎች ለሚሠማሩ አካላት የሙያ ፈቃድ ይሰጣል፣ ያድሳል፣ ይሰርዛል፤



13/ Being with relevant body, establishes a system to sustainably address the shortage of drinking water for livestock in drought-prone areas, and monitors its effectiveness;

14/ Makes farmers of the region and other entities engaged in the sector focus on quality and productivity rather than quantity; produces and causes for the production of animal breeding improvement input extensively and qualitatively; makes to be utilized, establishes, organizes and manages animal reproduction centers;

15/ Being with relevant bodies, establishes a system to create conducive environment for the society to produce animal fodder from cultivated forests and watersheds in a manner that does not lead to degradation of natural resources as well as to improve management and use of grazing land, ensures its implementation, monitors its effectiveness;

16/ Provides the necessary professional support to the private sector to produce fodder widely and qualitatively for domestic and foreign markets by developing various fodder production strategies and operational frameworks, causes for establishment of fodder banks in selected areas;

17/ Establishes a system of procedures enabling to improve the health and productivity of livestock and hides and skins is marketed maintaining the quality; and monitors the effectiveness

18/ Issues, renews and revokes professional licenses for entities to be engaged in business of private veterinary medicine and clinical services;

CamScanner

19/ የእንስሳት እና ዓሣ በሽታዎችን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፤ የበሽታ አሰሳ እና ቁጥጥር ያካሂዳል፤ መከላከልን መሠረት ያደረገ የጤና አገልግሎት ይሰጣል፤ በሽታን ለመከላከል አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የእንስሳት እና ዓሣ ከቦታ ቦታ የሚደረግ እንቅስቃሴን ይገድባል፤ በዚሁ ዘርፍ የሚደረጉ የጥናት እና ምርምር ሥራዎችን ይደግፋል፤ ያስተባብራል፤

19/ Establishes a system to prevent and control animal and fish diseases, conducts disease surveillance and control, provides prevention-based health services, restricts movement of animals and fish from one place to another when necessary to prevent disease, supports and coordinates research and development activities in this sector;

20/ ለኅብረተሰቡ የጤና ስጋት የሆኑ ከእንስሳት ወደ ሰው የሚተላለፉ አደገኛ በሽታዎችን ለመቆጣጠር የሚረዳ አሠራር ይዘረጋል፤ በአዲስ እና በማገርሸት ለሚከሰቱ ድንገተኛ የእንስሳት እና ዓሣ ሀብት የበሽታ ወረርሽኝ አፋጣኝ ምላሽ ይሰጣል፤

20/ Establishes a system to help control dangerous diseases transmitted from animals to humans that become health risk to the society, and provides prompt response to sudden outbreaks of animal and fish diseases that occur in new and recurring;

21/ የእንስሳት እና ዓሣ ሀብት ጤና አገልግሎት ጥራት እና ተደራሽነትን ለማሻሻል የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፤ መሠረተ ልማቶችን ያሟላል፤ ላቦራቶሪዎች፣ ክሊኒኮች፣ የክትባት ዲፖዎች፣ የመድኃኒት መጋዘኖች እንዲገነቡ ያደርጋል፣ ደረጃቸውን ያሻሽላል፣ አቅማቸውን ያሳድጋል፤

21/ Establishes a system to improve quality and accessibility of animal and fishery health services; fulfills infrastructures; construct laboratories, clinics, vaccine depots, and drug stores, improve their standards, and increase their capacity;

22/ በእንስሳት እና ዓሣ እርባታ እና ተዋፅዖ ልማት ለሚሠማሩ አካላት የጥራት መቆጣጠሪያ መመዘኛዎችን ያወጣል፣ የብቃት ምዘና ያደርጋል፣ ማስረጃ ይሰጣል፣ የእንስሳት ምርት እና ተዋፅዖ የዝውውር ሥርዓት መመሪያ ያወጣል፣ ያስፈፅማል፤

22/ Issues quality control standards for entities to be engaged in animal and fishery breeding and product development, undertakes competency assessments, provides certification, and issues and executes directives for transfer system of animal production and product;

23/ የእንስሳት እና ዓሣ ሀብት ልማት በክላስተር፣ በሞዴል መንደር እና በስፔሻላይዜሽን አሠራር መሠረት እንዲከናወን እና በገበያ እንዲመራ የአሠራር ስልቶችን ይቀይሳል፤ የሙያ ድጋፍ ይሰጣል፣

23/ Designs operational strategies for animal and fishery development to be carried out on the basis of clusters, model villages and specialization systems and to be market-led; provides professional support;

24/ ጥራቱን የጠበቀ የእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ ግብዓት ወደ ክልሉ በማስገባት፣ በማምረት እና በማባዛት አገልግሎት ላይ እንዲውል ያደርጋል፤

24/ Causes for the utilization through importing quality animal breeding improvement into the region, producing reproducing;

CamScanner

25/ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን የእንስሳት ተዋፅዖ ምርት ብክነትን በመከላከል በዘርፉ የተሠማሩ አካላትን ተጠቃሚነት ለማሳደግ የምርት ማሰባሰቢያ፣ ማከማቻ እና ማቀዝቀዣ ግብዓቶች እና መሠረተ ልማቶች እንዲሟሉ ያደርጋል፣ ያስፋፋል፣ ገበያ ያመቻቻል፣ ይከታተላል፤

26/ በእንስሳት እና ዓሣ ሀብት ልማት የተሠማሩ እና ወደ ፊት የሚሠማሩ ፕሮጀክቶች እና ፕሮግራሞች ሀብታቸው፣ እውቀታቸው እና አሠራራቸው የዘርፉን ምርት እና ምርታማነት ለማሳደግ በሚያስችል እና እሴት በሚጨምር አግባብ ጥቅም ላይ እንዲውል ይከታተላል፣ ይገመግማል፤

27/ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን ወደ ሀገር በሚገቡትም ሆነ ከአገር በሚወጡት የቁም እንስሳቶች፣ የእንስሳት እና ዓሣ ቴክኖሎጂዎች፣ ግብዓቶች ተዋፅዖ ምርቶች ላይ ምዝገባ እና ቁጥጥር ያደርጋል፤

28/ የእንስሳት መድኃኒቶች እና መኖ ጥራት እንዲሁም የእንስሳት ሕክምና አገልግሎት አሰጣጡን የሚያዘምን ሥርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊ እንዲሆን ይከታተላል፣

29/ የእንስሳት እና ዓሣ ምርት እና ተዋፅዖ የጥራት ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን የሚያስችሉ ቴክኖሎጂዎችን በምርምር በመለየት ወደ ተጠቃሚው ማኅበረሰብ እና ወደ ገበያ የሚገቡበትን ሥርዓት ያመቻቻል፣ ይመራል፣ ያስተባብራል፣

30/ የእንስሳት እና የእንስሳት ተዋፅዖ ምርቶች እንዲሁም የዓሣ ምርት በሀገር ውስጥ እና በውጭ ገበያ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ የሚያስችል ዘመናዊ የአመራረት ሥርዓት ይዘረጋል፣ ይተገብራል፣ ውጤታማነቱን ይከታተላል፤

31/ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ለኅብረተሰቡ ከበሽታ ነፃ የሆነ እና ጥራቱን የጠበቀ ሥጋ እንዲቀርብለት ለማድረግ በቄራዎች የሥጋ ምርመራ እንዲካሄድ ያደርጋል፤ ደረጃቸውን የጠበቁ የኤክስፖርት እና መለስተኛ ቄራዎች እንዲገነቡ ሙያዊ ድጋፍ ያደርጋል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

25/ Being with relevant body, ensures that the collection, storage and refrigeration inputs and infrastructures to be fulfilled in order to increase beneficiary of entities engaged in the sector by preventing wastage of animal products; expandeds, facilitates and monitors marketing;

26/ Monitors and evaluates projects and programs engaged and to be engaged in development of livestock and fish resources to ensure that their resources, knowledge and practices are utilized in a manner enabling to increase the production and productivity of the sector and adds value;

27/ Being with the relevant body, registers and controls on imported and exported livestocks, animal and fish technologies, inputs and by-products;

28/ Establishes a system modernizing quality of animal medicines and fodder as well as the provision of veterinary services, and monitors its implementation;

29/ Identifies technologies, through research, enabling animal and fish products and by-products maintain the quality standard, and facilitates, leads and coordinates a system for their introduction to the consumer society and the market;

30/ Establishes and implements modern production system enabling livestock and animal by-products as well as fish products to be competitive in domestic and foreign markets; monitors its effectiveness

31/ In cooperation with relevant bodies, causes meat inspection to be conducted at abattoirs to ensure that disease-free and quality meat is provided to the society; provides professional support for the construction of standardized export medium abattoirs; and minors its implementation;

32/ ለእንስሳት እና ዓሣ ምርት እና ተዋፅዖ ልማት አስፈላጊ የሆኑ ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችን ለተጠቃሚዎች ያስተዋውቃል፤ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፤ ውጤታማነታቸውን ይከታተላል፤

33/ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን የእንስሳት ምርት እና ተዋፅዖ ደኅንነት ለመጠበቅ የሚያስችል የዝውውር ሥርዓት ይዘረጋል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

34/ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን የእንስሳት ዝውውር፣ የእንስሳት እርድ፣ የዓሣ ማስገር፣ በንብ እርባታ አካባቢ የሚካሄድ የኬሚካል ርጭት ሥራዎችን እንዲሁም የመኖ ዘር፣ የክትባቶች እና የመገልገያ መሳሪያዎችን ጥራት ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

35/ የእንስሳት እና ዓሣ ሀብት ምርት እና ተዋፅዖ ለውጭ ገበያ ማዘጋጃ እና ማቀነባበሪያ ፋብሪካዎች ዓለም አቀፍ እና ሀገር አቀፍ መስፈርት እና ደረጃቸውን ጠብቀው እንዲቋቋሙ እና ሥራቸውን እንዲያከናውኑ ሙያዊ ድጋፍ ያደርጋል፤

36/ በክልሉ ውስጥ የእንስሳት ንግድ የጉዞ መስመሮችን በመለየት በሕግ እንዲታወቁ እና ተገቢውን ጥበቃ እንዲያገኙ ያደርጋል፣ የኳራንቲን እና የፍተሻ ማዕከላትን ያደራጃል፣ ከአጎራባች ክልሎች እና ከፌዴራል መንግሥት አካላት ጋር በትብብር ይሠራል፤

37/ ክልሉ በማር እና ሰም ልማት በገበያ ተወዳዳሪ እንዲሆን ለማድረግ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፣ ፀጋ ያላቸውን አካባቢዎች ለይቶ ይሠራል፣ አርሶ አደሩ እና በዘርፉ የተሠማሩ አካላት ዘመናዊ የንብ ማነብ አሠራሮችን እንዲተገብሩ ያደርጋል፣ ውጤታማነቱን ይከታተላል፤



32/ Introduces modern technologies necessary for the development of livestock and fish production and products to users, makes them to be utilized, and monitors their effectiveness;

33/ Being with concerned body, establishes transfer system enabling to maintain safety of livestock production and products, and monitors its implementation;

34/ Monitors and controls, in cooperation with relevant body, the transfer of livestock, animal slaughtering, fishing, chemical spraying activities in beekeeping areas as well as the quality of fodder seeds, vaccines, and equipments;

35/ Provides professional support for the establishment of factories to the production and processing of livestock and fish products for export markets maintaining international and national standards, and operate their work;

36/ Makes animal trade routes within the region and get properly protection by identifying and legalizing same, organizes quarantine and inspection centers, and works in cooperation with neighboring regions and federal government bodies;

37/ Establishes a system to make the region market competitive in honey and wax production, works identifying areas with potential, ensures farmers and entities engaged in the sector implement modern beekeeping practices, monitors the effectiveness;

CamScanner

38/ ለውጭ እና ለሀገር ውስጥ ገበያ ለሚቀርቡ እንስሳት የማቆያ ቦታዎችን ያቋቁማል፣ መሠረተ ልማቶችን ያሟላል፣ የመጓጓዣ ዘዴዎች እንዲመቻቹ አግባብ ካላቸው አካላት እና ድርጅቶች ጋር በትንጅት ይሠራል።

## 45. የኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ቢሮ

በሌሎች ሕጎች አስቀድሞ የተደነገገው ወይም ወደ ፊት የሚደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ ኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ቢሮ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ዝርዝር ሥልጣን እና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1/ ብሔራዊ የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ እና ኢኖቬሽን እንዲሁም የሀገሪቱን የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ፖሊሲዎች እና ስትራቴጅዎችን መሠረት በማድረግ ከክልሉ ነባራዊ ሁኔታ ጋር የተጣጣመ ስትራቴጂ ይነድፋል፣ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

2/ ከሀገራዊ እና ክልላዊ ፖሊሲዎች እና ስትራቴጂዎች ጋር የሚጣጣሙ ውጤታማ የሆኑ ቴክኖሎጂዎችን ያፈላልጋል፣ እንደ አግባብነታቸው ወደ ክልሉ የሚገቡበትን፣ የሚላመዱበትን እና የሚለሙበትን ሥርዓት ያዘጋጃል፤

3/ የመንግሥት እና የሕዝብ አገልግሎት አሰጣጥን ዘመናዊ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ ለማድረግ የክልሉ መንግሥት ተቋማት አሠራር በቴክኖሎጂ እንዲደገፍ ያደርጋል፤

4/ ከሳይንስ፣ ኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ሥራዎች ጋር በተያያዘ የክልሉን መንግሥት ያማክራል፤

5/ የመረጃ እና መገናኛ ቴክኖሎጂን መሠረት ያደረገ ክልላዊ የቴክኖሎጂ መረጃ ማዕከል ያደራጃል፣ ደኅንነቱ እንዲጠበቅ ይሠራል፣ ይቆጣጠራል፤

6/ በክልሉ ውስጥ የተቀናጀ የሳይበር ደኅንነት አስተዳደር ሥራ ይሠራል፣ ደኅንነቱ የተጠበቀ የመረጃ ልውውጥ እንዲኖር እና ጥቃት እንዳይፈፀም የበይነ መረብ ደኅንነት ቁጥጥር ያደርጋል፣ ጥቃት ሲከሰት አስቸኳይ የመፍትሔ እርምጃ ይወስዳል፤



38/ Establishes holding areas for animals supplied to foreign and domestic markets, fulfills infrastructures, and works in coordination with appropriate bodies and organizations to facilitate transportation methods.

## 45. Bureau of Innovation and Technology

Without prejudice to what has been previously or may be provided for in other laws, the Regional Innovation and Technology Bureau shall have the following detailed powers and duties under this Proclamation:

1/ Formulates a strategy in line with the existing situation of the region based on the national science, technology and innovation as well as the country's information and communication technology policies and strategies, and implements it upon approval;

2/ Searches effective technologies that are consistent with national and regional policies and strategies, and prepares a system for their introduction, adaptation, and development in the region as appropriate;

3/ Makes operations of the regional government institutions to be supported by technology to make government and public service delivery modern, efficient and effective;

4/ Advises the regional government related to science, innovation and technology;

5/ Organizes regional information technology center based on information and communication technology; works safety of same to be maintained, controls;

6/ Implements integrated cybersecurity management in the region, monitors internet security to ensure secure information exchange and prevent attacks, takes immediate remedial action when an attack occurs;

CamScanner

7/ በክልሉ ሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ እና ኢኖቬሽንን መፍጠር እና መጠቀም የሚችል የሠለጠነ እና በቂ የሰው ኃይል በማፍራት በሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ እና ኢኖቬሽን የመጠቀም ባሕሉ የጎለበተ ማኅበረሰብ እንዲፈጠር ለማድረግ ይሠራል፤

8/ ክልሉን በአገር አቀፍ እና በዓለም ደረጃ ተወዳዳሪ እና ቀዳሚ የሚያደርገውን ቴክኖሎጂ ከወዲሁ የመለየት፣ የመጠቀም፣ የማሻሻል፣ የመፍጠር እና የማልማት አቅም ለመገንባት ይሠራል፤

9/ ለሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ምርምር እንዲሁም ለኢኖቬሽን መደላድል ለመፍጠር የሚያስችሉ መሠረተ ልማቶችን ያለማል፣ የሀገር በቀል ቴክኖሎጂዎችን ለመጠቀም እና ለማሳደግ የሚያስችል ስርዓት ይዘረጋል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

10/ የሀገር በቀል ዕውቀቶችን በማልማት ጥቅም ላይ ማዋል የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት በመፍጠር የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ እና ኢኖቬሽን ባሕል እንዲጎለብት ያደርጋል፤

11/ የክልሉን የልማት ፍላጎት የሚያሟሉ የሳይንስ፣ የቴክኖሎጂ እና የኢኖቬሽን ምርምሮችን ያከናውናል፣ እንዲከናወኑ ያደርጋል፣ የምርምር ውጤቶች ወደ ማኅበረሰቡ መሸጋገራቸውን እና ጥቅም ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፤

12/ ስትራቴጂያዊ ተፈላጊነት ባላቸው የቴክኖሎጂ መስኮች የግል እና የመንግሥት አጋርነት ሥርዓት ይዘረጋል፣ ኢኖቬተሮችን እና ኢንተርፕረነሮችን ለማበረታታት የግሉ ዘርፍ በምርምር ተግባራት የሚሳተፍበት የድጋፍ እና የማበረታቻ ማዕቀፍ ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤

7/ Works to create a society with a culture of using science, technology and innovation by producing a skilled and sufficient human resource in the region that can create and use science, technology and innovation;

8/ Works to build the capacity to identify, use, improve, create and develop technology that will make the region competitive and leading at the national and global levels;

9/ Develops infrastructures used as bushing for science and technology research as well as innovation, establishes a system for the use and development of indigenous technologies, and monitors its implementation;

10/ Causes for development of culture of science, technology and innovation by creating a system for the development and utilization of indigenous knowledge;

11/ Conducts and causes for the conduction of science, technology and innovation research which meet the development needs of the region, and monitors the transfer and utilization of research results to the society;

12/ Establishes a system of private and public partnerships in technological fields of strategic importance, prepares a framework of support and incentives for the private sector to participate in research activities to encourage innovators and entrepreneurs; implements same upon approval;

CS CamScanner

13/ በክልሉ ቴክኖሎጂን መሠረት ያደረጉ በሀገር እና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሆኑ ኢንተርፕራይዞችን ለመፍጠር ይሠራል፣ በቴክኖሎጂ ልማት የተሠማሩ ኢንተርፕራይዞችን በልዩ ሁኔታ ይደግፋል፣ ይከታተላል፣ የማበረታቻ ሥርዓት ይዘረጋል፤

14/ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን ለሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ እና ኢኖቬሽን ልማት ተደራሽ፣ አካታች እና ቀልጣፋ የፋይናንስ አቅርቦት ሥርዓት እንዲዘረጋ ያደርጋል፣

15/ ለሳይንሳዊ ምርምር፣ ለቴክኖሎጂ ልማት እና ለኢኖቬሽን እንዲሁም ለቴክኖሎጂ ግብይት የሚውሉ ፋውንዴሽኖችን እና ፈንዶችን ያቋቁማል፣ ውጤታማ እንዲሆኑ ይከታተላል፣ ይደግፋል፤

16/ ከሚመለከታቸው የፌደራል እና የክልል አካላት ጋር በመሆን ሀገር በቀል ዕውቀቶች እና በኢንዱስትሪያዊ አመላካች የሚገለፁ ሀብቶችን በጥናት ይለያል፤ በአዕምሯዊ ንብረት ጥበቃ ሥርዓት ውስጥ እንዲካተቱ እና የእውቀቱ እና የሀብቱ ባለቤቶች የጥቅሙ ተጋሪ እንዲሆኑ ሥርዓት ይዘረጋል፣ ይከታተላል፤

17/ በክልሉ ሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ እና ኢኖቬሽን ለአካታች ማኅበራዊ ልማት እና ባሕላዊ ጠቀሜታ ያለውን ሚና ለማሳደግ ይሠራል፤ የቴክኖሎጂ አጠቃቀም፣ ደኅንነት እና ቁጥጥር በማኅበረሰብ ውስጥ ባሕል እንዲሆን የግንዛቤ ማሳደጊያ ሥራዎችን ይሠራል፤

18/ የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ እና ኢኖቬሽን ልማት እንቅስቃሴ ከማኅበራዊ እና ባሕላዊ እሴቶች ጋር ተጣጥመው የሚሄዱበትን የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፣ ውጤታማነቱን ይከታተላል፤

19/ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን ተግባር ተኮር የሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ትምህርት ሥነ ምሕዳር እንዲፈጠር ያደርጋል፤ በሥርዓተ ትምህርት በሚደገፍ የሳይንስ እውቀት ቴክኖሎጂን ሕዝባዊ ለማድረግ የሚያግዙ ሥራዎችን ይሠራል፣ ውጤታማነቱን ይከታተላል፤



13/ Works to create technology-based enterprises competitive at the national and international levels in the region; supports, in special way, enterprises engaged in technology, monitors, and establishes incentive systems;

14/ Being with the relevant body, causes for establishment of an accessible, inclusive and efficient financial provision system for the development of science, technology and innovation;

15/ Establishes foundations and funds used for scientific research, technology development and innovation as well as technology marketing; monitors and supports them to be effective;

16/ In collaboration with relevant federal and regional bodies, identifies indigenous knowledge and resources that can be expressed in industrial indicators through research; establishes and monitors a system for their inclusion in intellectual property protection system and owners of the knowledge and resources to share in the benefits;

17/ Works to enhance the role of science, technology and innovation for inclusive social development and cultural significance in the region, and carries out awareness-raising activities so that the use, safety and control of technology become culture in society;

18/ Establishes system of operations in which science, technology and innovation development activities are aligned with social and cultural values, and monitors its effectiveness;

19/ Being with the relevant body, makes an ecosystem for action-oriented science and technology education to be created; undertakes activities that help popularize technology through scientific knowledge supported by curriculum, monitors its effectiveness;

CamScanner

20/ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን ለክልሉ ልማት መፋጠን ስትራቴጂያዊ ጠቀሜታ ያላቸውን የመጭውን ጊዜ የሰው ኃይል ፍላጎት በመለየት ልዩ ሥልጠና ይሰጣል፣ እንዲሰጥ ያደርጋል፤ በዘርፉ ልዩ ተሰጥኦ ላላቸው ምቹ ሁኔታ በመፍጠር ያበረታታል፤

21/ በክልሉ ሁለንተናዊ ልማትን ለማፋጠን በግብርና፣ በአምራች ኢንዱስትሪ እና አገልግሎት ዘርፎች የቴክኖሎጂ ሽግግር እንዲፈጠር ይሠራል፣ ይደግፋል፤ በኢኮኖሚ እና በሥልጣኔ ተወዳዳሪነትን ለማሳደግ እና ድህነትን ትርጉም የለሽ ለማድረግ ለዘርፎች ልማት መነቃነቅ በሚያግዝ ቴክኖሎጂ ላይ በትኩረት ይሠራል፤

22/ በክልሉ በሳይንሳዊ እውቀት እና ሥልት የሚመራ የቴክኖሎጂ ጥናት እና የዲጂታላይዜሽን ተወዳዳሪነት ማበልፀጊያ፣ ጥገና እና ፍተሻ ማዕከል ያቋቁማል፤ አቅም እንዲገነባ ያደርጋል፤ ይደግፋል፣ ይከታተላል፤

23/ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን በቴክኖሎጂ ዘርፍ ጀማሪ ቴክኖሎጂ ፈጣሪዎችን እና የኢኖቬሽን ሥርዓተ ምሕዳር ገንቢዎችን የፋይናንስ፣ የቴክኒክ፣ የመሥሪያ ቦታ እና ተያያዥ ድጋፎች እንዲመቻቹላቸው ያደርጋል፤

24/ የዲጂታል መሠረተ ልማት እና አስቻይ ሥርዓቶችን በመዘርጋት ለክልሉ የዲጂታል ኢኮኖሚ ግንባታ ምቹ መደላድሎችን ይፈጥራል፤

25/ ለሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ እና ኢኖቬሽን ልማት ተደራሽ፣ አካታች እና ቀልጣፋ የፋይናንስ አቅርቦት አማራጮች እንዲኖሩ ምቹ ሁኔታዎችን ለመፍጠር ከሚመለከተው አካል ጋር ይሠራል፤

26/ አካባቢን እና ማኅበራዊ ደኅንነትን መሠረት ያደረገ የቴክኖሎጂ ልማት እና ቁጥጥር ሥርዓት ይዘረጋል፤ በአጠቃላይ አሉታዊ ጉዳት የሚያደርሱ ቴክኖሎጂዎች የአወጋገድ ሥርዓት ይዘረጋል፣ ይተገብራል፤

20/ Being with the relevant body, identifies the future needs of human power which are strategically important for acceleration of development of the region and provides and causes for provision of special training; encourages by creating favorable condition to those with special talents in the sector;

21/ Works and supports for creation of technological transfer in the agricultural, manufacturing industry and service sectors to accelerate overall development in the region; works focusing on technology that will help stimulate development of sectors to increase economic and civilization competitiveness and make poverty meaningless;

22/ Establishes an incubation center for technological research and digitalization competitiveness led by scientific knowledge and method in the region; makes capacity to be built; supports and monitors;

23/ Being with the relevant body, causes for the creation of conditions of financial, technical, work space and related support to early stage technology creators and innovation ecosystem developers in technology sector;

24/ Creates favorable conditions for the construction of the digital economy in the region by establishing digital infrastructure and enabling systems;

25/ Works with the relevant body to create favorable conditions for accessible, inclusive and efficient financing provision options for the development of science, technology, and innovation;

26/ Establishes a system for technological development and control based on environmental and social safety; establishes a system for eliminating technologies that cause negative harm in general and implements same;

27/ ተቋማት የተሰጣቸውን ተግባር እና ኃላፊነት በብቃት ለመወጣት ይቻላቸው ዘንድ ፍላጎታቸውን ማዕከል በማድረግ ሲስተሞችን ያለማል፣ በሌሎች እንዲለሙ ያደርጋል፣ ስለ አጠቃቀማቸውም ሥልጠና ይሰጣል፤

28/ በክልሉ ቀጣይነት ያለው የቴክኖሎጂ ዕድገት እውን ለማድረግ የሚያስችሉ ስልቶችን ይቀይሳል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፣ ይከታተላል፣ ለፈጣን የቴክኖሎጂ ዕድገት መሠረት ይጥላል፤

29/ መሠረታዊ የማሽን ቴክኖሎጂን፣ የኃይል ምንጭን፣ የግብዓት እና የአመራረት ሥርዓትን በቴክኖልጂ ለማስተሳሰር ሥልት ይቀይሳል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፣ ይከታተላል፤

30/ በኢኮኖሚ፣ በማኅበራዊ እና በመንግሥት አገልግሎቶች በሚተገበረው የዲጂታል ቴክኖሎጂ ዘርፍ አቅም ለመፍጠር ሥርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፣ ይከታተላል፤

31/ በክልሉ በማሽን ቴክኖሎጂ፣ በአማራጭ የኃይል አቅርቦት፣ በስትራቴጂካዊ ግብዓት፣ በዘረ መል እና በዲጂታል ቴክኖሎጂ ሁሉን አቀፍ እና አስተማማኝ የቴክኖሎጂ ሽግግር እንዲረጋገጥ ያደርጋል፣ ይከታተላል፤

32/ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን በፋብሪካ ምሕንድስና እና በዲጂታል ቴክኖሎጂ የበቃ እና በሳይንሳዊ እውቀት የበለፀገ ወጣት ትውልድ ለመፍጠር ይሠራል፤ በተግባር ሥልጠና የሚደገፍ የፋብሪኬሽን ኢንጂነሪንግ እና ኢኖቬሽን ንቅናቄ እንዲፈጠር ያደርጋል፤

33/ በቴክኖሎጂ ቀዳሚ እውቀት እና ተሞክሮ ካላቸው አካላት እና በውጭ ከሚኖሩ የክልሉ ተወላጆች እና ወዳጆች ጋር ትብብር በማድረግ ቴክኖሎጂን ለማልማት እና ለማሸጋገር ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፣ ይከታተላል፤



27/ Develops systems focusing on their needs to enable institutions effectively carry out their assigned tasks and responsibilities, makes them to be developed by others, and provides training on their use;

28/ Designs, implements and monitors strategies enabling to achieve continuous technological development in the region, and lays foundation for rapid technological development;

29/ Design, implement, and monitor strategies to integrate basic machine technology, energy sources, input and production systems with technology;

30/ Establishes, implements and monitors a system to create capacity in the digital technology sector being applied in the economy, social and government services;

31/ Ensures and monitors comprehensive and reliable technology transfer in machine technology, alternative energy supply, strategic resources, genetics and digital technology in the region;

32/ Works with relevant body to create young generation who are competent in factory engineering and digital technology and enrich in scientific knowledge; causes for the creation of manufacturing engineering and innovation movement supported by practical training;

33/ Creates and monitors favorable environment for the development and transfer of technology through collaborating with entities with prior knowledge and experience in technology and with the region's natives and friends living abroad;

34/ የተለያዩ የሳይንስ እና ቴክኖሎጂ እውቀቶች እና መረጃዎች በክልሉ የሥራ ቋንቋ እየተተረጐሙ ለተጠቃሚው ሕዝብ እንዲሰራጩ እና ጥቅም ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፤

35/ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን በተፈጥሮ ሳይንስ እና በሒሳብ ትምህርት የላቀ ውጤት ለሚያስመዘግቡ ተማሪዎች ወይም የፈጠራ ክህሎት ላላቸው መምህራን፣ ተመራማሪዎችና ሌሎች ግለሰቦች የማበረታቻ ሽልማት ይሰጣል፣ ይደግፋል።

## 46. <u>የኮንስትራክሽን ባለሥልጣን</u>

በሌሎች ሕጎች አስቀድሞ የተደነገገው ወይም ወደ ፊት የሚደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ የኮንስትራክሽን ባለስልጣን በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ዝርዝር ሥልጣን እና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1/ ዓለም አቀፋዊ እና ሀገራዊ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ኮድ፣ ስታንዳርድ እና ደረጃን መሠረት በማድረግ የክልሉን የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ኮድ፣ ስታንዳርድ እና ደረጃ ያዘጋጃል፣ ያስፈፅማል፤

2/ በሀገር ደረጃ የወጡ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ አዋጆች፣ ደንቦች፣ ኮዶች፣ ስታንዳርዶች፣ ደረጃዎች እና መመሪያዎች በክልሉ ውስጥ መተግበራቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤ የአቅም ግንባታ ሥራዎችን ያከናውናል፤

3/ በክልሉ ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነት እና ብቃት ያለው የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ እንዲፈጠር በዲዛይን፣ በጨረታ፣ በኮንትራት ይዘት እና አስተዳደር እንዲሁም በግንባታ ጥራት እና ቁጥጥር ግልፅ እና ተጠያቂነት ያለው የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፤ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤ ያረጋግጣል፣ ይቆጣጠራል፤

4/ በክልሉ ውስጥ የሚገነቡ ማንኛውንም የመንግሥት እና የግል የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶችን ይመዘግባል፣ ይቆጣጠራል፤



34/ Makes various scientific and technological knowledge and information to be translated into the working language of the region and disseminated to the public to be utilized;

35/ Being with relevant body, provides incentive awards to students who achieve excellent results in natural science and mathematics or to teachers, researchers and other individuals with creative skills, and supports same;

## 46. <u>Authority of Construction</u>

Without prejudice to what has been previously or may be provided for in other laws, the Regional Construction Authority shall have the following detailed powers and duties under this Proclamation:

1/ Prepares and implements the Regional Construction Industry Code,Standards and Grades based on international and national construction industry codes, standards and grades;

2/ Monitors and supervises the implementation of construction industry proclamations, regulations, codes, standards, grades and directives issued at national grade in the region; and carries out capacity building activities;

3/ Establishes transparent and accountable operating system in design, bidding, contract content and management as well as construction quality and control to create an internationally competitive and competent construction industry in the region; monitors, verifies and supervises its implementation;

4/ Records and supervises any government and private construction projects being constructed in the region;

CamScanner

5/ ለመሠረተ ልማት እና ኮንስትራክሽን ሥራዎች ግንባታዎች ሞዴል ስፔሲፊኬሽን፣ የልኬት ሥርዓት እና ማኑዋል ያዘጋጃል፣ ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፣ ይቆጣጠራል፤

6/ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን የመንግሥት ኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች ውል በተገባበት ዲዛይን፣ ዋጋ፣ ጥራት እና ጊዜ ተሠርተው ስለመጠናቀቃቸው እና ርክክብ ስለመደረጉ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ የእርምት እርምጃ ይወስዳል፤

7/ የግንባታ ፈቃድ አሰጣጥ፣ የቁጥጥር እና የምዝገባ ሥራ ግልፅነት እና ተጠያቂነትን የሚያረጋግጥ አሠራር ይዘረጋል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

8/ የኮንስትራክሽን ሥራዎች በአካባቢ፣ በሠራተኞች እና በኅብረተሰቡ ጤንነት እና ደኅንነት ላይ ጉዳት እንዳያደርሱ ለመከላከል የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፣ አፈፃፀማቸውን ይቆጣጠራል፤

9/ በኮንስትራክሽን ሥራ እና ግንባታ አደጋ ሲፈጠር ምክንያቱን እና የጉዳት መጠኑን ያጣራል፣ ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ያቀርባል፣ የሕግ ተጠያቂነት እንዲኖር ይሠራል፤

10/ የግንባታ ሞዴል ዋጋዎችን እና የግምት መሥሪያ ቀመሮችን ያዘጋጃል፣ በዚሁ መሠረት የዋጋ ግምቶች በአግባቡ ስለ መዘጋጀታቸው ያረጋግጣል፣ ይቆጣጠራል፤

11/ በኮንስትራክሽን ዘርፍ የሚሠማሩ ባለሙያዎችን ይመዘግባል፣ የሙያ ፈቃድ ይሰጣል፣ ያድሳል፣ ይሰርዛል፣ ይቆጣጠራል፤ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን የኮንስትራክሽን ባለሙያዎች የሙያ ብቃት ምዘና እንዲካሄድ ያደርጋል፤

12/ ለሥራ ተቋራጮች፣ አማካሪዎች እና በዘርፉ ለሚሳተፉ ሌሎች ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፣ ያግዳል፣ ይሰርዛል፣ ይቆጣጠራል፤



5/ Prepares, monitors, verifies and controls model specifications, measurement systems and manuals for infrastructure and construction works;

6/ Being with relevant body, monitors, controls and takes corrective action to ensure that government construction projects are completed and handed over in accordance with the design, cost, quality and time agreed upon;

7/ Establishes a system to ensure transparency and accountability in the issuance of construction license, supervision and registration work, and monitors its implementation;

8/ Establish a system to prevent construction works from causing harm to an environment, health and safety of workers and the society, and monitor their implementation;

9/ In the event of an accident in construction work and building, investigates the cause and extent of the damage, submits a report to relevant body, and works to ensure legal liability;

10/ Prepares construction model prices and estimation formulas, ensures that price estimations are prepared appropriately on this basis, and supervises them;

11/ Registers professionals to be engaged in the construction sector, issues professional licenses, renews, cancels, and supervises them; causes for undertaking of professional competency assessments of construction professionals being with relevant body;

12/ Issues, suspends and cancels competency certificates for contractors, consultants and other organizations involved in the sector; and controls same;

CamScanner

13/ ለኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ቁጥጥር የሚያገለግል መረጃ ይሰበስባል፣ የመረጃ ቋት ያቋቁማል፣ ወቅታዊ እና ተደራሽ ያደርጋል፤

14/ የኮንስትራክሽን ግብዓቶችን ደረጃ ያዘጋጃል፣ ያሻሽላል፣ አፈጻፀሙን ይቆጣጠራል፤

15/ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን ከውጭ የሚገቡ የግንባታ ግብዓቶች በሀገር ውስጥ መተካት የሚያስችል አሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፣ አፈጻፀሙን ይቆጣጠራል፤

16/ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን በመንግሥት ኮንስትራክሽን ሥራዎች የሚፈጠሩ የውል አለመግባባቶች አማራጭ የግጭት መፍቻ ዘዴ በመጠቀም በወቅቱ መፍትሔ እንዲያገኙ ያደርጋል፤

17/ የመንግሥት ኮንስትራክሽን ፕሮጀክት አፈጻፀም ከጊዜ፣ ከጥራት እና ወጭ አንፃር ክንውኑን ኦዲት ያደርጋል፣ በሚገኙ ክፍተቶች ላይ የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፤

18/ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪውን ለማዘመን እና ማነቆዎቹን ለመፍታት የሚያስችሉ የጥናት እና ምርምር ሥራዎችን ይሠራል፤

19/ ዘመናዊ የኮንስትራክሽን ሥራዎች ግብዓት እና ውጤቶችን የጥራት መፈተሻ ላቦራቶሪ በተመረጡ ቀጠናዎች ያቋቁማል፤ የክልሉን የኮንስትራክሽን መሣሪያዎችን ጨምሮ የተለያዩ የላቦራቶሪ ምርመራ አገልግሎት ይሰጣል፣ በበላይነት ያስተዳድራል፤ የኮንስትራክሽን ግብዓቶች በላቦራቶሪ ተመርምረው ለግንባታ አገልግሎት መዋላቸውን ያረጋግጣል፣ ለሚሰጠው አገልግሎት በመስተዳድር ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ መሰረት ክፍያ ያስከፍላል፤

20/ በክልሉ መንግሥት በጀት እና በግሉ ዘርፍ ለሚገነቡ ማናቸውም ግንባታዎች የሚያስፈልጉ ዲዛይኖችን መርምሮ ያፀድቃል፣ የግንባታ ፈቃድ ይሰጣል፤ ከፍትሕ ቢሮ ጋር በመሆን የመንግሥት የግንባታ ሥራ ውሎች በአግባቡ መዘጋጀታቸውን ክትትል እና ቁጥጥር ያደርጋል፤



13/ Collects information used for supervision of the construction industry, establishes database, makes it up-to-date and accessible;

14/ Prepares, improves and monitors grade of construction resources;

15/ Being with relevant body, establishes a system to replace imported construction resources with domestic ones, monitors its implementation;

16/ Being with relevant body, ensures that contractual disputes arising from government construction projects to be resolved in time using alternative dispute resolution methods;

17/ Audits performance of government construction projects in terms of time, quality and cost, and takes corrective action on any gaps found;

18/ Conducts research activities to modernize the construction industry and address bottlenecks;

19/ Establishes quality testing laboratory in selected zones for modern construction works inputs and outputs; provides various laboratory testing services including the regional construction equipment, manages on top of it; ensures that construction inputs are tested by the laboratory and used for construction purposes, and charges fee for the services it provides in accordance with a regulation to be issued by the Government Council;

20/ Examines and approves designs required for any constructions constructed by the regional government budget and the private sector, and issues construction licenses; being with the Bureau of Justice, monitors and controls the proper preparation of government construction contracts;

CamScanner

21/ በክልሉ ውስጥ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው አቅም እንዲያድግ ተፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፣ የግንባታ ቴክኖሎጅዎች እንዲስፋፉ ያበረታታል፤

22/ በክልሉ ውስጥ ተፈፃሚነት የሚኖራቸውን የኮንስትራክሽን ፖሊሲዎችን እና ስትራቴጅዎችን ይነድፋል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

23/ የዲዛይን ለውጥን እና ተያያዥ ምክንያቶችን ተከትሎ የሚፈጠር ተጨማሪ የግንባታ ሥራዎች እና ተጨማሪ ዋጋ ሲያጋጥም የሚቀርብለትን ጥያቄ አጣርቶ ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፤ ሲፈቀድለትም በሕጉ መሠረት ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤

24/ በሚመለከተው ተቋም ሲጠየቅ የመንግሥት የግንባታ ፕሮጅክቶችን ለማካሄድ የሚዘጋጁ ቴክኒካል መመዘኛ ሰነዶችን፣ ዲዛይኖችን እና የሥራ ዝርዝሮችን ግምገማ ያካሂዳል፣ ያረጋግጣል፤

25/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፳፬) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በየደረጃው በሚገኝ ከፍተኛ የመንግሥት የበላይ አመራር አስቀድሞ በሚሰጥ አቅጣጫ መሠረት መንግሥት የሚያካሂዳቸውን ክልላዊ ፋይዳ ያላቸው ከፍተኛ የግንባታ ፕሮጀክት የጨረታ ሁኔታ ግምገማ ያካሂዳል፤ በሴክተሮች የተካሄዱትን የከፍተኛ ፕሮጀክቶች የጨረታ ሁኔታ በማስቀረብ ይመረምራል፣ ያረጋግጣል፣ ያፀድቃል፤

26/ የኮንስትራክሽን መሣሪያዎች እና የሰው ኃይል ወቅታዊ ዋጋ አጥንቶ በማቀናጀት ሴክተሮች እንዲያውቁት እና ሥራ ላይ እንዲያውሉት ያደርጋል፤

27/ በኮንስትራክሽን ዘርፍ ውስጥ የኅብረተሰቡ ተሳትፎ እንዲረጋገጥ ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፣ ሥራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

28/ በየደረጃው የሕንፃ ሹም ጽሕፈት የሥራ ክፍሎችን ቤት ያደራጃል፣ ይመራል፣ ይቆጣጠራል፣

21/ Provides the necessary support to the construction industry in the region to grow its capacity, encourages expansion of construction technologies;

22/ Formulates construction policies and strategies that will be applicable in the region, implements them when approved, and monitors its implementation;

23/ Examines and submits to the relevant body of any requests for additional construction works and additional costs arising from design changes and related factors; when approved, ensures that they are implemented in accordance with the law;

24/ When requested by relevant institution, reviews and verifies technical specifications, designs, and list of quantity prepared for government construction projects;

25/ Without prejudice to the provision of Sub-article (24) of this Article, conducts an evaluation of bidding status of major construction projects of regional importance undertaken by the government in accordance with a direction to be given in advance by top government leader at each level; and examines, verifies and approves bidding status of major projects undertaken by sectors;

26/ Studies and integrates current prices of construction equipments and human power and makes sectors to be awared of them and implement;

27/ Creates favorable environment for ensuring public participation in construction sector, monitors and supervises its implementation;

28/ Organizes, leads and controls departments of Office of Construction at each level;

29/ የክልሉ የግንባታ ተቋራጮች፣ አርክቴክተሮች፣ አማካሪዎች እና ሌሎች በኮንስትራክሽን ሥራ ላይ የተሠማሩ አካላት በዘርፉ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፣ ተገቢውን ድጋፍ ይሰጣል፤

30/ የኮንሥትራክሽን ማሽነሪ እና የግንባታ መሣሪያዎች አቅርቦት ፈቃድ ይሰጣል፣ ያድሳል፤ ጉድለት ካለ አስፈላጊውን የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፣ እንዲወሰድ ያደርጋል፤

31/ የኮንስትራክሽን ዘርፉ በክልሉ ጥቅል ምርት ውስጥ የሚኖረው ድርሻ እንዲያድግ እና ለክልሉ ዕድገት እና ልማት የሚጠበቅበትን ሚና መወጣት እንዲችል ለማድረግ ስልቶችን ይቀይሳል፣ በልዩ ትኩረት ይሠራል፣ ይደግፋል፤

32/ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን የኮንስትራክሽን እቃዎች ግዥ በጥራት እንዲፈፀም የጥራት ቁጥጥር ያደርጋል።

## ክፍል ስድስት

## ስለ ሌሎች አስፈፃሚ አካላት፣ ተጠሪ ተቋማት እና በቢሮ ወይም ሌላ አስፈጻሚ አካል እና በተጠሪ ተቋማት መካከል ስለሚኖር ግንኙነት

### 47. የኅብረት ሥራ ኮሚሽን

1/ የኅብረት ሥራ ኮሚሽን ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የክልሉ መንግሥት አስፈፃሚ አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤

2/ የኮሚሽኑ አደረጃጀት፣ ሥልጣን እና ተግባራት በመስተዳድር ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ ይወሰናል።

29/ Establishes and implements a system making construction contractors, architects, consultants and other entities engaged in construction work in the region to be competitive in the sector, and provides appropriate support;

30/ Issues and renews licenses for supply of construction machinery and equipments; takes and causes to be taken the necessary corrective action if there is defect;

31/ Devise strategies to make the construction sector to increase its share in the regional gross domestic product and to fulfill its expected role in the growth and development of the region; works with special attention and supports same;

32/ Being with relevant body, undertakes quality control to ensure procurement of construction materials is carried out with quality.

## PART SIX

## Other Executive Bodies, Accountable Institutions and the Relationship Between Bureau or Other Executive Organ and Accountable Institutions

### 47. Cooperative Commission

1/ The Cooperative Commission is hereby established as an executive organ of the regional government with independent legal personality;

2/ The organization, powers and duties of the Commission shall be determined by a regulation to be issued by the Government Council.

## 48. የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት

1/ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የክልሉ መንግሥት አስፈፃሚ አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤

2/ የኢንስቲትዩቱ አደረጃጀት፣ ሥልጣን እና ተግባራት በመስተዳድር ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ ይወሰናል።

## 48. Institute of Agricultural Research

1/ The Agricultural Research Institute is hereby established as an executive organ of the regional government with independent legal personality;

2/ The organization, powers and duties of the Institute shall be determined by a regulation to be issued by the Government Council.

## 49. የግብርና ጥራትና ቁጥጥር ባለሥልጣን

1/ የግብርና ጥራትና ቁጥጥር ባለስልጣን ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የክልሉ መንግስት አስፈፃሚ አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤

2/ የባለስልጣኑ አደረጃጀት፣ ሥልጣን እና ተግባራት በመስተዳድር ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ ይወሰናል።

## 49. Authority of Agricultural Quality and Quarantine

1/ The Agricultural Quality and Quarantine Authority is hereby established as an executive organ of the regional government with independent legal personality;

2/ The organization, powers and duties of the Authority shall be determined by a regulation issued by the Executive Council.

## 50. የአደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን

1/ የአደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የክልሉ መንግስት አስፈፃሚ አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤

2/ የኮሚሽኑ አደረጃጀት፣ ሥልጣን እና ተግባራት በመስተዳድር ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ ይወሰናል።

## 50. Commission of Disaster Risk Management

1/ The Disaster Risk Management Commission is hereby established as an executive body of the regional government with independent legal personality;

2/ The organization, powers and duties of the Commission shall be determined by a regulation to be issued by the Government Council.

## 51. የመንግሥታት ግንኙነት እና ከክልሉ ውጭ ያሉ ጉዳዮች ማስተባበሪያ ኮሚሽን

1/ የመንግሥታት ግንኙነት እና ከክልሉ ውጭ ያሉ ጉዳዮች ማስተባበሪያ ኮሚሽን በዚህ አዋጅ ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የክልሉ መንግስት አስፈፃሚ አካል ሆኖ ተቋቁሟል፤

## 51. The Commission for Coordination of Intergovernmental Relations and Extra Regional Affairs

1/ Inter-Governmental Relations and Extra-Regional Affairs Coordination Commission is hereby established as an executive body of the Regional Government with independent legal personality;

CamScanner

2/ የኮሚሽኑ አደረጃጀት፣ ሥልጣን እና ተግባራት በመስተዳድር ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ ይወሰናል።

## 52. የአማራ ክልል ስቴት ዩኒቨርሲቲ

1/ የአማራ ክልል ስቴት ዩኒቨርሲቲ ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የክልሉ መንግሥት አስፈፃሚ አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤

2/ የዩኒቨርሲቲው አደረጃጀት፣ ሥልጣን እና ተግባራት እንዲሁም ዩኒቨርሲቲው ሌላ ሥያሜ እንዲኖረው ከተፈለገ በመስተዳድር ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ ይወሰናል።

## 53. የአማራ ክልል ኢንቨስትመንት ሆልዲንግ

1/ የአማራ ክልል ኢንቨስትመንት ሆልዲንግ ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የክልሉ መንግሥት አስፈፃሚ አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤

2/ የሆልዲንጉ ዓላማ በክልሉ በተለያዩ ሕጎች እና የአደረጃጀት ማዕቀፎች የተቋቋሙ እና በመንግሥት ሙሉ ወይም ከፊል ባለቤትነት የተያዙ የልማት ድርጅቶች፣ የፋይናንስና ኢንሹራንስ ድርጅቶች፣ የአክሲዮን ድርሻዎች፣ ሕንፃዎች፣ በመንግሥት ስር የሚገኙ ሌሎች ሀብቶች፣ በንጋት የዘለቄታ በጎ አድራጎት ድርጅት እና በጋፋት ኢንዶውመንት ድርጅት፣ ድርጅቱ በሚያስተዳድራቸው የኢንቨስትመንት ተቋማት ስር ያሉ የንግድ ሀብቶችን በባለቤትነት ማስተዳደር፤ የመንግሥት ንግድ እና ኢንቨስትመንት ሀብት በንግድ ሥራ በተቃኘ ስትራቴጂያዊ አሠራር እንዲመራ በማድረግ የኢንቨስትመንቶችን ውጤታማነት ማረጋገጥ፤ ለአገር ውስጥ እና የውጭ ባለ ሀብቶች ምቹ የኮርፖሬት ምሕዳር በመፍጠር ተጨማሪ የኢንቨስትመንት ዕድሎችን ማስፋት እና የመንግሥት ስትራቴጂያዊ ኢንቨስትመንት መሣሪያ ሆኖ ማገልገል ነው፤



2/ Organization, powers and duties of the Commission shall be determined by regulation to be issued by the Government Council.

## 52. The Amhara Region State University

1/ The Amhara Region State University is hereby established as an executive body of the regional government with independent legal personality;

2/ The organization, powers and duties of the university as well as any other name the university may wish to have, shall be determined by a regulation to be issued by the Government Council.

## 53. The Amhara Region Investment Holding

1/ The Amhara Region Investment Holding is hereby established as an executive body of the regional government with an independent legal personality;

2/ The purpose of the holding is to administer development organizations established and held completely or partially by the government in various laws and organizational frame works in the region, financial and insurance organizations, shareholdings, buildings, other resources found under government, trade resouyrces in Nigat Charitable Endowment and Gafat Endowment organizations and institutions administered by the organization; to ensure the effectiveness of investments by leading the government's commercial and investment resource in strategical operation in line with business; to expand additional investment opportunities through creating favorable corporate environment for domestic and foreign investors, and to serve as a strategic investment tool for the government;

መ) በስሩ አዳዲስ የንግድ እና ኢንቨስትመንት ተቀጥላ ድርጅቶችን ያቋቁማል፤ በባለቤትነት በያዛቸው ተቀጥላ ድርጅቶች የካፒታል ዕድገት ወይም ቅነሳ፣ ሽያጭ፣ ጥምረት፣ ክፍፍል ወይም ሌላ የአደረጃጀት ጉዳይ ላይ ይወስናል፤

ሠ) ሆልዲንጉም ሆነ በስሩ የሚያስተዳድራቸው ተቀጥላ ድርጅቶች ዓለም አቀፍ የኢንቨስትመንት መልካም አስተዳደር መርሆችን እንዲተገብሩ ያደርጋል፤ የመንግሥትን ሀብት በብቃት ለማስተዳደር የሚያስችል ዘመናዊ የኮርፖሬት አስተዳደር እና ፋይናንስ ሥርዓት እንዲዘረጋ በማድረግ ቀጣይነት ላለው የኢኮኖሚ ዕድገት አስተዋፅዖ ያደርጋል፤

ረ) ሀብት እና ጥሪትን ለትውልድ ማስተላለፍ የሚችል የክልሉ የሉዓላዊ ሀብት ፈንድ ተቋም ሆኖ ያገለግላል፤

7/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (2) መሠረት በሆልዲንጉ ስር የሚታቀፉ የንግድና ኢንቨስትመንት ተቋማትን የሚያስተዳድር የበጎ አድራጎት ድርጅትን በማፍረስ ሂደት የሚያልፈው በክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ውሳኔ መነሻነት ይሆናል፤

8/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (7) መሠረት የበጎ አድራጎት ድርጅት እንዲፈርስ ሲወሰን የፍትሕ ቢሮ የሒሳብ ማጣራት ሥራው ገንዘብ ቢሮ በሚመድበው ባለሙያ እንዲከናወን ያሳውቃል፤

9/ አግባብነት ባለው የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ሕግ ላይ የተደነገገው ቢኖርም በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (7) መሠረት የሚፈጸም ሂደት የንግድና ኢንቨስትመንት ድርጅቶቹን እና ሀብቶችን መፍረስ ሳያስከትል ይከናወናል፤



D) Establishes new commercial and investment subsidiary organizations under it, decides on capital increase or decrease, sale, merger, dividend or other organizational matters of subsidiaries it owns;

E) Ensures that both the holding and the subsidiary organizations it manages implement international investment good governance principles; contributes to sustainable economic growth by establishing a modern corporate governance and finance system that enables efficient management of government resources;

F) Serves as the regional sovereign wealth fund institution that can transfer wealth and resources to future generations;

7/ The process of dissolution of charitable organization administering the trade and investment institutions embraced under the holding pursuant to Sub-article (2) of this Article shall pass through initiation decision of the regional head of government;

8/ Whene a charitable organization dissolves based on Sub-article (7) of this Article, the Justice Bureau shall notify to the Finance Bureau so that the account verification to be conducted by a preofessional assigned by the latter;

9/ Notwithstanding to the provision of pertinent civic society organizations law, the process implemented based on Sub-article (7) of this Article shall be conducted without casing the dissolution of trade and investment organizations and their resources;

CamScanner

10/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (7) እና (8) መሠረት በንብረት አጣሪ የሚከናወን የንብረት ዝርዝር፣ ግመታ እና ኦዲት ሪፖርት አዘገጃጀት እና ሌሎች በማጣራት ሂደት የሚፈጸሙ ተግባራት አሠራር ዝርዝር በገንዘብ ቢሮ ይወሰናል፤

11/ የፍትሕ ቢሮ ከገንዘብ ቢሮ በሚቀርብለት የአጣሪ ሪፖርት መሠረት በሀብት እና እዳ ማስተላለፍ ጉዳይ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ያስተላልፋል፤

12/ በሌላ ሕግ የተደነገገው ቢኖርም ሆልዲንጉ የራሱን እና የተቀጥላ ድርጅቶችን የሰው ኃይል አስተዳደር፣ የፋይናንስ እና የግዥ ፖሊሲዎችን፣ አሠራሮችን እና ደንቦችን ይቀርፃል፣ ያስፀድቃል።

## 54. የባሕል፣ ኪነ ጥበብ እና ዝክረ ታሪክ ጽሕፈት ቤት

1/ የባሕል፣ ኪነ ጥበብ እና ዝክረ ታሪክ ጽሕፈት ቤት ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የክልሉ መንግሥት አስፈፃሚ አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤

2/ የጽሕፈት ቤቱ አደረጃጀት፣ ሥልጣን እና ተግባራት በመስተዳድር ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ ይወሰናል።

## 55. የፕላን ኢንስቲትዩት

1/ የፕላን ኢንስቲትዩት ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የክልሉ መንግሥት አስፈፃሚ አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤

2/ የኢንስቲትዩቱ አደረጃጀት፣ ሥልጣን እና ተግባራት በመስተዳድር ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ ይወሰናል።



10/ Detailed procedural functions of report preparation of list of property, valuation and audit, and other functions implemented in the liquidation process by asset liquidator based on Sub-articles (7) and (8) of this Article shall determined by Finance Bureau;

11/ The Justice Bureau shall pass the Final Decision in transfer of asset and liability based on liquidator report submitted to it by the Finance Bureau;

12/ Notwithstanding provision in another law, the Holding shall formulate and approve its own and its subsidiary organizations' human resource management, financial and procurement policies, procedures and regulations.

## 54. The Office of Culture, Arts and Memorial History

1/ The Office of Culture, Arts and Memorial History is hereby established as an executive body of the regional government with independent legal personality;

2/ The organization, powers and duties of the Office shall be determined by a regulation to be issued by the Government Council.

## 55. The Planning Institute

1/ The Planning Institute is hereby established as an executive organ of the regional government with independent legal personality;

2/ The organization, powers and duties of the Institute shall be determined by a regulation to be issued by the Government Council.

CamScanner

## 56. የፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት

1/ የፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የክልሉ መንግሥት አስፈፃሚ አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤

2/ የኢንስቲትዩቱ አደረጃጀት፣ ሥልጣን እና ተግባራት በመስተዳድር ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ ይወሰናል።

## 57. የኅብረተሰብ ተሳትፎ ማስተባበሪያ ጽሕፈት ቤት

1/ የኅብረተሰብ ተሳትፎ ማስተባበሪያ ጽሕፈት ቤት ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የክልሉ መንግሥት አስፈፃሚ አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤

2/ የጽሕፈት ቤቱ አደረጃጀት፣ ሥልጣን እና ተግባራት በመስተዳድር ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ ይወሰናል።

## 58. የገጠር መንገዶች ኮንስትራክሽን ኤጀንሲ

1/ የገጠር መንገዶች ኮንስትራክሽን ኤጀንሲ በአዲስ ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የክልሉ መንግሥት አስፈፃሚ አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤

2/ የኤጀንሲው አደረጃጀት፣ ሥልጣን እና ተግባራት በመስተዳድር ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ ይወሰናል፤

## 59. የኮንስትራክሽን ባለሥልጣን

1/ የኮንስትራክሽን ባለሥልጣን ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የክልሉ መንግሥት አስፈፃሚ አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤

2/ የዚህ አዋጅ አንቀጽ 46 ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ የባለሥልጣኑ አደረጃጀት እና ዝርዝር ሥልጣንና ተግባራት በመስተዳድር ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ ይወሰናል፤



## 56. The Policy Research Institute

1/ The Policy Research Institute is hereby established as an executive body of the regional government with an independent legal personality;

2/ The organization, powers and duties of the institute shall be determined by a regulation to be issued by the Government Council.

## 57. Public Participation Coordination Office

1/ The Public Participation Coordination Office is hereby established as an executive body of the regional government with an independent legal personality;

2/ The organization, powers and duties of the office shall be determined by a regulation to be issued by the Government Council.

## 58. The Rural Roads Construction Agency

1/ The Rural Roads Construction Agency is hereby established as a new executive body of the regional government with an independent legal personality;

2/ The organization, powers and duties of the agency shall be determined by a regulation to be issued by the Government Council.

## 59. The Construction Authority

1/ The Construction Authority is hereby established as an executive body of the regional government with an independent legal personality;

2/ Without prejudice to the provisions of Article 46 of this Proclamation, the organization and detailed powers and duties of the authority shall be determined by a regulation to be issued by the Government Council;

CamScanner

## 60. ለርዕሰ መስተዳድር ተጠሪ የሆኑ አካላት

የሚከተሉት አስፈፃሚ አካላት ተጠሪነት ለብሔራዊ ክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ይሆናል፡-

1/ የካቢኔ ጉዳዮች እና የርዕሰ መስተዳድር ጽሕፈት ቤት፤

2/ የአማራ ክልል ፖሊስ ዋና ጠቅላይ መምሪያ፤

3/ የአማራ ክልል ስቴት ዩኒቨርሲቲ፤

4/ የአደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን፤

5/ የኅብረት ሥራ ኮሚሽን፤

6/ የኮንስትራክሽን ባለሥልጣን፤

7/ የፕላን ኢንስቲትዩት፤

8/ የአማራ ክልል ኢንቨስትመንት ሆልዲንግ፤

9/ የሥነ ምግባር እና ፀረ ሙስና ኮሚሽን፤

10/ የታላቁ ሕዳሴ ግድብ ማስተባበሪያ ጽሕፈት ቤት፤

11/ የሙያ ብቃት ምዘና እና ማረጋገጫ ባለስልጣን፤

12/ የመንግሥታት ግንኙነት እና ከክልሉ ውጭ ያሉ ጉዳዮች ማስተባበሪያ ኮሚሽን፡፡

## 61. ለግብርና ቢሮ ተጠሪ የሆኑ አካላት

የሚከተሉት አስፈፃሚ አካላት ተጠሪነት ለክልሉ ግብርና ቢሮ ይሆናል፡-

1/ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት፤

2/ የግብርና ጥራትና ቁጥጥር ባለሥልጣን፤

3/ የቆቦ ጊራና ሸለቆ ልማት ፕሮግራም ማስተባበሪያ ጽሕፈት ቤት፤

4/ የቆጋ መስኖ ልማት ፕሮግራም ማስተባበሪያ ጽሕፈት ቤት፤

5/ የክልሉ የአፈር ምርመራ እና ለምነት ማሻሻያ ማዕከላት፤

6/ የክልሉ የዕፅዋት ተባይ ቅኝት ጥናት እና ምርምር ማዕከላት፤



## 60. Bodies Accountable to the Head of Government

The following executive bodies shall be accountable to the Head of Government of the National Region:

1/ Cabinet Affairs and Office of the President;

2/ The Amhara Region Police Chief Supreme Department;

3/ The Amhara Region State University;

4/ Disaster Risk Management Commission;

5/ Cooperatives Commission;

6/ Construction Authority;

7/ Planning Institute;

8/ The Amhara Region Investment Holding;

9/ The Ethics and Anti-Corruption Commission;

10/ The Grand Renaissance Dam Coordination Office;

11/ The Professional Qualification Assessment and Certification Authority;

12/ The Intergovernmental Relations and Extra-Regional Affairs Coordination Commission.

## 61. Bodies Accountable to the Bureau of Agriculture

The following executive bodies shall be accountable to the Regional Bureau of Agriculture:

1/ The Agricultural Research Institute;

2/ The Agricultural Quality and Control Authority;

3/ The Kobo Girana Valley Development Program Coordination Office;

4/ The Koga Irrigation Development Program Coordination Office;

5/ The Regional Soil Testing and Fertility Improvement Centers;

6/ The Regional Plant Pest Survey and Research Centers;

CamScanner

7/ የቲሹ ካልቸር ማዕከላት፤

8/ የአማራ ምርጥ ዘር ኢንተርፕራይዝ፤

9/ በክልሉ መንግሥት ስር ያሉ የኖራ ፋብሪካዎች።

7/ The Tissue Culture Centers;

8/ The Amhara Seed Enterprise;

9/ The Lime factories under the regional government.

### 62. ለባሕል፣ ቱሪዝም እና ስፖርት ቢሮ ተጠሪ የሆነ አካል

የባሕል፣ ኪነ ጥበብ እና ዝክረ ታሪክ ጽሕፈት ቤት ተጠሪነት ለክልሉ የባሕል፣ ቱሪዝም እና ስፖርት ቢሮ ይሆናል።

### 62. Accountable body for the Culture, Tourism and Sports Bureau

The Culture, Arts and Memorial History Office shall be accountable to the Regional Culture, Tourism and Sports Bureau.

### 63. ለንግድ እና ገበያ ልማት ቢሮ ተጠሪ የሆነ አካል

የባሕር ዳር የግብርና ምርቶች መዳረሻ ገበያ ማዕከል ተጠሪነት ለክልሉ የንግድ እና ገበያ ልማት ቢሮ ይሆናል።

### 63. Accountable body for the Trade and Market Development Bureau

The Bahir Dar Agricultural Products Terminal and Market Center shall be accountable to the Regional Trade and Market Development Bureau.

### 64. ለኢንዱስትሪ እና ኢንቨስትመንት ቢሮ ተጠሪ የሆኑ አካላት

የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ተጠሪነት ለኢንዱስትሪ እና ኢንቨስትመንት ቢሮ ይሆናል።

### 64. Bodies Accountable to the Bureau of Industry and Investment

The Industrial Parks Development Corporation shall be accountable to the Bureau of Industry and Investment.

### 65. ለፕላን እና ልማት ቢሮ ተጠሪ የሆኑ አካላት

የሚከተሉት አስፈፃሚ አካላት ተጠሪነት ለፕላን እና ልማት ቢሮ ይሆናል፡-

1/ የሲቪል እና ቤተሰብ ምዝገባ አገልግሎት፤

2/ የፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት።

### 65. Bodies Accountable to the Bureau of Planning and Development

The following executive bodies shall be accountable to the Bureau of Planning and Development:

1/ The Civil and Family Registration Service;

2/ The Policy Research Institute.

### 66. ለመንገድ፣ ትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ ቢሮ ተጠሪ የሆነ አካል

የገጠር መንገዶች ኮንስትራክሽን ኤጀንሲ ተጠሪነቱ ለክልሉ የመንገድ፣ ትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ ቢሮ ይሆናል፡፡

### 66. Accountable Body to the Road, Transport and Logistics Bureau

The Rural Roads Construction Agency shall be accountable to the Regional Road, Transport and Logistics Bureau.

CamScanner

## 67. ለእንስሳት እና ዓሣ ሀብት ቢሮ ተጠሪ የሆኑ አካላት

የሚከተሉት አስፈፃሚ አካላት ተጠሪነት ለክልሉ እንስሳትና ዓሣ ሀብት ቢሮ ይሆናል፡-

1/ የክልሉ የበግ ብዜት ማዕከላት፤
2/ የባሕር ዳር ዳልጋ ከብት ሰው ሠራሽ ዝርያ ማዳቀል ማዕከል፤
3/ የክልሉ የእንስሳት በሽታ ቅኝትና ጥናት ላቦራቶሪ ማዕከላት፤
4/ የሰቆጣ ዶሮ ብዜት ማዕከል፤
5/ የኮምቦልቻ ዶሮ ሀብት ልማት ኢንተርፕራይዝ፤
6/ የላልይበላ ብሔራዊ የንብ ሙዚየም፤
7/ የክልሉ የፈሳሽ ናይትሮጂን ማምረቻ ማዕከላት፤
8/ የክልሉ የእናት ንብ ማባዣ እና ማሠልጠኛ ማዕከላት፤
9/ የቻግኒ የዳልጋ ከብት ብዜት እና ጥበቃ ማዕከል።

## 68. ለጤና ቢሮ ተጠሪ የሆኑ አካላት

የሚከተሉት አስፈፃሚ አካላት ተጠሪነት ለክልሉ ጤና ቢሮ ይሆናል፡-

1/ የኅብረተሰብ ጤና ኢንስቲቲዩት፤
2/ በክልሉ መንግሥት ስር ያሉ የጤና ሳይንስ ኮሌጆች፤
3/ በክልሉ መንግሥት ስር ያሉ የኦክስጅን ፕላንቴሽን ማምረቻ እና ማከፋፈያ ማዕከላት፤
4/ በክልሉ መንግሥት ስር ያሉ የደም ባንኮች፤
5/ የአካል ድጋፍ እና ተሐድሶ ማዕከላት
6/ በክልሉ መንግሥት ስር የሚተዳደሩ ሆስፒታሎች።

## 67. Bodies Accountable to the Bureau of Animal and Fisheries Resources

The following executive bodies shall be accountable to the Bureau of Animal and Fisheries Resources:

1/ The Regional Sheep Reproduction Centers;
2/ The Bahir Dar Cattle Artificial Breeding Reproduction Center;
3/ The Regional Animal Disease Surveillance and Research Laboratory Centers;
4/ The Sekota Chicken Reproduction Center;
5/ The Kombolcha Poultry Resources Development Enterprise;
6/ The Lalibela National Bee Museum;
7/ The Regional Liquid Nitrogen Production Centers;
8/ The Regional Queen Bee Reproduction and Training Centers;
9/ The Chagni Cattle Breeding and Conservation Center.

## 68. Bodies Accountable to the Health Bureau

The following executive bodies shall be accountable to the Regional Health Bureau:

1/ The Public Health Institute;
2/ The Health Science Colleges under the Regional Government;
3/ The Oxygen Plantation Production and Distribution Centers under the Regional Government;
4/ The Blood Banks under the Regional Government;
5/ The Physical Support and Rehabilitation Centers;
6/ The Hospitals managed under the Regional Government.

CamScanner

## 69. ለሥራ እና ክህሎት ቢሮ ተጠሪ የሆኑ አካላት

የክልሉ የፖሊቴክኒክ ኮሌጆች ተጠሪነታቸው ለክልሉ የሥራ እና ክህሎት ቢሮ ይሆናል፡፡

## 69. Bodies Accountable to the Employment and Skills Bureau

The regional polytechnic colleges shall be accountable to the regional employment and skills bureau.

## 70. ለፍትሕ ቢሮ ተጠሪ የሆነ አካል

የክልሉ ማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን ተጠሪነት ለክልሉ የፍትሕ ቢሮ ይሆናል፡፡

## 70. A Body Accountable to the Justice Bureau

The regional prisons commission shall be accountable to the regional justice bureau.

## 71. ለሰላም እና ፀጥታ ቢሮ ተጠሪ የሆነ አካል

የክልሉ ሚሊሻ ኮሚሽን ተጠሪነት ለሰላም እና ፀጥታ ቢሮ ይሆናል፡፡

## 71. A Body Accountable to the Peace and Security Bureau

The regional militia Commission shall be accountable to the Peace and Security Bureau.

## 72. ለትምህርት ቢሮ ተጠሪ የሆኑ አካላት

የሚከተሉት አስፈፃሚ አካላት ተጠሪነት ለክልሉ ትምህርት ቢሮ ይሆናል፡-

1/ በክልሉ መንግሥት ስር የሚተዳደሩ የመምህራን ኮሌጆች፤

2/ የትምህርት ግብዓቶች ክዘና ማዕከላት፡፡

## 72. Bodies Accountable to the Education Bureau

The following executive bodies shall be accountable to the Regional Education Bureau:

1/ Teachers' Colleges managed under the Regional Government;

2/ Educational Materials Warehouse Centers.

## 73. ለውኃ እና ኢነርጂ ቢሮ ተጠሪ የሆነ አካል

የውኃ ፈንድ ጽሕፈት ቤት ተጠሪነት ለውኃ እና ኢነርጂ ቢሮ ይሆናል፡፡

## 73. A Body Accountable to the Water and Energy Bureau

The Water Fund Office shall be accountable to the Water and Energy Bureau.

## 74. ለገንዘብ ቢሮ ተጠሪ የሆነ አካል

የኅብረተሰብ ተሳትፎ ማስተባበሪያ ጽሕፈት ቤት ተጠሪነቱ ለገንዘብ ቢሮ ይሆናል፡፡

## 74. A Body Accountable to the Finance Bureau

The Community Participation Coordination Office shall be accountable to the Finance Bureau.

## 75. በቢሮዎች ወይም ሌላ አስፈፃሚ አካል እና በተጠሪ ተቋም መካከል ስለሚኖር ግንኙነት

1/ ለቢሮ ወይም ለሌላ አስፈፃሚ አካል ተጠሪ የሆነ ተቋም በሕግ የተቋቋመ ራሱን የቻለ ተቋም በመሆኑ ቢሮው ወይም ሌላ አስፈፃሚ አካል የተጠሪ ተቋሙን ሥራዎች ከመምራት፣ ከማስተባበር እና ከመደገፍ ውጪ በእለት ከእለት እንቅስቃሴው ላይ ጣልቃ አይገባም፡፡

## 75. Relationship between the Bureaus or Other Executive Body and Accountable Institution

1/ The bureau or other executive body shall not interfere in the day-to-day activities of the institution except to direct, coordinate and support its activities of an institution accountable to a bureau or other executive body as it is an independent institution established by law.

2/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም የቢሮው ወይም ሌላው አስፈፃሚ አካል ዕቅድ እና ሪፖርት የተጠሪ ተቋሙንም ዕቅድ እና ሪፖርት የያዘ መሆን ይኖርበታል፡፡

3/ በሕግ በሚዘረጋ ሥርዓት መሠረት ቢሮው ወይም ሌላው አስፈፃሚ አካል የተጠሪ ተቋምን የሰው ኃይል አስተዳደር፣ የፋይናንስ አስተዳደር እና መሰል ሥራዎችን ሊያከናውን ይችላል፡፡

4/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (1) አፈፃፀም "መምራት፣ ማስተባበር እና መደገፍ"፡-

ሀ) የተጠሪ ተቋማትን ዕቅድ እና የአፈፃፀም ሪፖርት አጠቃላይ አፈፃፀም መከታተልን፣

ለ) አደረጃጀቶቻቸውን እንዲሁም የልማት ሥራ ፕሮግራሞቻቸውን፣ ፕሮጀክቶቻቸውን እና በጀቶቻቸውን መገምገም እና ለሚመለከተው የመንግሥት አካል ማቅረብን፣

ሐ) በሕግ የተሰጧቸውን ተግባር እና ኃላፊነቶች በአግባቡ መወጣት እንዲችሉ መደገፍን፣

መ) ከፌዴራል ወይም ከሌሎች ክልሎች ተቋማት ጋር ግንኙነት የሚፈጥሩበትን ሁኔታ ማመቻቸት እና መደገፍን፣

ሠ) የተጠሪ ተቋማትን እና የተጠሪ ተቋማት ባለሙያዎችን አቅም መገንባትን ይጨምራል፡፡

## 76. ስለ ሌሎች አስፈፃሚ አካላት እና ተቋማት

የብሔራዊ ክልላዊ መንግሥቱ ሌሎች አስፈፃሚ አካላት እና ተቋማት በየተቋቋሙበት ሕግጋት በተደነገገው መሠረት ይቀጥላሉ፡፡

## 77. የስያሜ ለውጥ

1/ በደንብ ቁጥር 119/2006 የሙያ ብቃት ምዘና እና ማረጋገጫ ኤጀንሲ ተብሎ የነበረው በዚህ አዋጅ የሙያ ብቃት ምዘና እና ማረጋገጫ ባለሥልጣን በሚል የስያሜ ለውጥ ተደርጓል፤

2/ Notwithstanding the provision of Sub-article (1) of this Article, the plan and report of the bureau or other executive body shall also include the plan and report of the institution accountable to it.

3/ The bureau or other executive body may, in accordance with the procedure established by law, perform the human resources management, financial management and similar functions of the institution accountable to it.

4/ For the implementation of Sub-article (1) of this Article, "Direct, coordinate and support":

A) Monitoring the overall implementation of plans and performance reports of the accountable institutions,

B) Evaluating their organizations as well as their development work programs, projects and budgets, and submitting to the relevant government body,

C) Supporting them in properly carrying out their duties and responsibilities assigned by law,

D) Facilitating and supporting the establishment of relations with federal or other regional institutions,

E) Including capacity building of the accountable institutions and professionals of the accountable institutions.

## 76. Other Executive Bodies and Institutions

Other executive bodies and institutions of the National Regional State shall continue based on the provision of their respective laws.

## 77. Change of Nomenclature

1/ The nomenclature of the Professional Qualification Assessment and Certification Agency as per Proclamation No. 119/2014 has been changed to the Professional Qualification Assessment and Certification Authority by this Proclamation;

CamScanner

2/ በአዋጅ ቁጥር 216/2006 መሠረት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፖሊስ ኮሚሽን ተብሎ ይጠራ የነበረው በዚህ አዋጅ የአማራ ክልል ፖሊስ ዋና ጠቅላይ መምሪያ በሚል የስያሜ ለውጥ ተደርጓል፤

3/ በአዋጅ ቁጥር 280/2014 አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ (6) ስር የስያሜ ለውጥ ተደርጎለት የነበረው የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባ አገልግሎት የሲቪል እና ቤተሰብ ምዝገባ አገልግሎት በሚል የስያሜ ለውጥ ተደርጓል።

4/ በአዋጅ ቁጥር 280/20014 (ከአዋጅ ቁጥር 81/1995 ዓ.ም እንደተሻሻለ) መሠረት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሚሊሻ ጽሕፈት ቤት ተብሎ ይጠራ የነበረው በዚህ አዋጅ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሚሊሻ ኮሚሽን በሚል የስያሜ ለውጥ ተደርጓል።

2/ Name of the Amhara National Regional State Police Commission as per Proclamation No. 216/2014 has been changed to the Amhara Regional Police Chief Supreme Department by this Proclamation;

3/ The Vital Events Registration Service, which was renamed under Article 40, Sub-Article (6) of Proclamation No. 280/2022 has been renamed as the Civil and Family Registration Service.

4/ The Amhara National Regional State Militia Office as per Proclamation No.280/2022 (as amended from Proclamation No. 81/2003) has made nomenclature change as the Amhara National Regional State Militia Commission.

### 78. <u>አስፈፃሚ አካላት በየደረጃው የሚቋቋሙ ስለ መሆናቸው</u>

የክልሉ አስፈፃሚ አካላት በክልሉ ውስጥ እንደ አስፈላጊነቱ እስከ ታችኛው የመንግሥት አስተዳደር እርከን አደረጃጀታቸውን ሊዘረጉ ይችላሉ።

### 78. <u>Executive Bodies to be Established at each Level</u>

Executive bodies of the region may extend their organization to the lower levels of government administration within the region, as necessary.

## <u>ክፍል ሰባት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

## <u>PART SEVEN</u>

## <u>MISCELLANEOUS PROVISIONS</u>

### 79. <u>አስፈፃሚ አካላትን ስለ ማደራጀት</u>

የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት የክልሉን አስፈፃሚ አካላት አደረጃጀት አስመልክቶ በጥናት ላይ የተመሠረቱ ለውጦችን ከማድረግ ባሻገር አዳዲስ ተቋማትን የመመሥረት፣ ተግባር እና ኃላፊነታቸውን የመወሰን፣

እንደኛውን ከሌላው ጋር የማዋሐድ፣ እንዲሁም በሕግ መሠረት ሥልጣን እና ተግባራቸውን የማንሳት ሥራዎችን እንዲያከናውን በዚህ አዋጅ ቋሚ የውክልና ሥልጣን ተሰጥቶታል።

### 79. <u>Organizing Executive Bodies</u>

The Regional Government Council has been given permanent deligation authority by this proclamation to establishing new institutions, determining their duties and responsibilities, merging one with another, as well as revoking their powers and functions in accordance with with the law in addition to making research-based changes to the organization of the executive bodies of the region.

CamScanner

## 80. ስለ ተሻሩ እና ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች

1/ የክልሉ አስፈፃሚ አካላት ማቋቋሚያ፣ ሥልጣን እና ተግባራት መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 280/2014 ተሽሮ በዚህ አዋጅ ተተክቷል፤

2/ የኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ቢሮ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 296/2017 በዚህ አዋጅ ተሽሯል፤

3/ የአማራ አመራር አካዳሚ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 221/2007 በዚህ አዋጅ ተሽሯል፤

4/ የእፅዋት ዘር እና ሌሎች የግብርና ግብዓቶች ጥራት ቁጥጥር እና ኳራንታይን ባለስልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 208/2006 በዚህ አዋጅ ተሽሯል

5/ የክልሉ አደጋ መከላከል ምግብ ዋስትና ፕሮግራም እና ልዩ ድጋፍ የሚሹ አካባቢዎች ማስተባበሪያ ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 101/1996 በዚህ አዋጅ ተሽሯል፤

6/ የኅብረት ሥራ ማኅበራት ማስፋፊያ ኤጀንሲ ማቋቋም አዋጅ ቁጥር 124/1998 በዚህ አዋጅ ተሽሯል፤

7/ የአማራ ብሔራዊ ክልል የግብርና ምርምር ተቋምን ለማቋቋም የወጣው አዋጅ ቁጥር 48/1992 እና የአዋጁ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 118/1997 በዚህ አዋጅ ተሽረዋል፤

8/ የአማራ ሕዝቦች ሰማዕታት መታሰቢያ ሐውልት ጽሕፈት ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 160/2001 እና የሙሉ ዓለም ባሕል ማዕከል ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 24/1996 በዚህ አዋጅ ተሽረዋል፤

## 80. Repealed and Inapplicable Laws

1/ Proclamation No. 280/2022 for the Establishment, and Determination of Powers and Duties of the Regional Executive Bodies is hereby repealed and replaced by this Proclamation;

2/ Proclamation No. 296/2025 for the Establishment of the Innovation and Technology Bureau is hereby repealed;

3/ Proclamation No. 221/2015 for the Establishment of the Amhara Leadership Academy is hereby repealed;

4/ Proclamation No. 208/2014 for the Establishment of the Plant Seeds and Other Agricultural Inputs Quality Control and Quarantine Authority is hereby repealed;

5/ Proclamation No. 101/2004 for the Establishment of the Regional Disaster Prevention Food Security Program and Areas in Need of Special Assistance Coordination Commission is hereby repealed;

6/ Proclamation No. 124/2006 for the Establishment of the Cooperative Extension Agency is hereby repealed;

7/ Proclamation No. 48/2000 for the Establishment of the Amhara National Region Agricultural Research Institute and its Amendment Proclamation No. 118/2005 are hereby repealed;

8/ Proclamation No. 160/2009 for the Establishment of the Amhara People's Martyrs' Memorial Office and Regulation No. 24/2004 for the Establishment of the Mulualem Cultural Center are hereby repealed;

CamScanner

9/ የከተሞች ፕላን ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 147/1999 በዚህ አዋጅ ተሽሯል፤

10/ የጣና ሐይቅ እና አካባቢው ሕይወተ ክልል ስፍራ አከላለል እና አስተዳደር መወሰኛ ደንብ ቁጥር 125/2007 እና የጣና ሐይቅና ሌሎች የውኃ አካላት ጥበቃ እና ልማት ኤጀንሲ ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 180/2011 በዚህ አዋጅ ተሽሯል፤

11/ የእንስሳት እና ዓሣ ሀብት ልማት ማስፋፊያ ኤጀንሲ ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 81/2003 በዚህ አዋጅ ተሽሯል፤

12/ የቅርሶች ጥበቃ እና የቱሪዝም ልማት ፈንድ ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 128/2007 በዚህ አዋጅ ተሽሯል፤

13/ የክልሉ ትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ ባለሥልጣን ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 199/2014 በዚህ አዋጅ ተሽሯል፤

14/ የገጠር መንገዶች ኮንስትራክሽ ኤጀንሲን ለማቋቋም የወጣው አዋጅ ቁጥር 235/2008 እና የገጠር መንገዶች ኮንስትራክሽ ኤጀንሲን ለማሻሻል የወጣው አዋጅ ቁጥር 247/2009 በዚህ አዋጅ ተሽረዋል፤

15/ የአሠሪ እና ሠራተኛ ጉዳይ ባለሥልጣንን ለማቋቋም እና ሥልጣን እና ተግባራትን ለመወሰን የወጣው ደንብ ቁጥር 200/2014 በዚህ አዋጅ ተሽሯል፤

16/ የመንግሥት ልማት ድርጅቶች አመሠራረት፣ አደረጃጀት፣ አመራር እና ድጋፍ አሰጣጥን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ቁጥር 236/2008 እና በአዋጅ ቁጥር 280/2014 አንቀጽ 40 ንዑስ-አንቀጽ (4) ሥር የሥያሜ ለውጥ ተደረጎለት የነበረው የመንግሥት የልማት ድርጅቶች አስተዳደር በዚህ አዋጅ ተሽሯል፤



9/ Proclamation No. 147/2007 for Establishment of the Urban Planning Institute is hereby repealed;

10/ Regulation No. 125/2015 for the Determination of Demarcation and Management of Lake Tana and its Surrounding Areas Bio-Zone, and Regulation No. 180/2019 for the Establishment of Lake Tana and Other Water Bodies Conservation and Development Agency are hereby repealed;

11/ Regulation No. 81/2011 ,for the Establishment of Livestock and Fisheries Development Agency is hereby repealed;

12/ Regulation No. 128/2015 for the Establishment of Heritage Conservation and Tourism Development Fund is hereby repealed;

13/ Regulation No. 199/2022 for the Establishment of the Regional Transport and Logistics Authority is hereby repealed;

14/ Proclamation No. 235/2016 for the Establishment of the Rural Roads Construction Agency and Proclamation No. 247/2017 for the Amendment of the Rural Roads Construction Agency are hereby repealed;

15/ Regulation No. 200/2022 for the Establishment of the Employment and Labour Authority and Determination of its powers and duties is hereby repealed;

16/ Proclamation No. 236/2016 issued to establish the Establishment, Organization, Management and Support Provision of the Public Development Organizations, and the Public Development Organizations Administration which was renamed under Article 40, Sub-Article (4) of Proclamation No. 280/2022 are hereby repealed;

17/ በአዋጅ ቁጥር 236/2008 የተቋቋመውን የመንግሥት የልማት ድርጅቶች አስተዳደር ተከትሎ የወጡ ደንቦች እና መመሪያዎች በዚህ አዋጅ መሠረት ተሽረዋል፤

17/ Regulations and directives issued pursuant to the Public Development Organizations Administration established by Proclamation No. 236/2016 are hereby repealed;

18/ የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት ከጥቅምት 30/2012 ዓ/ም እስከ ሕዳር 1/2012 ዓ/ም ባካሄደው አምስተኛ ዙር አምስተኛ ዓመት የሥራ ዘመን አስራ አራተኛ መደበኛ ጉባኤ ጥረት ኮርፖሬትን በተመለከተ ባደረገው ሞሽን መሠረት ጥረት ኮርፖሬት ለክልሉ ምክር ቤት ተጠሪ እንዲሆን በማለት እና የቦርድ አሰያየምን ላይ ያስተላለፈው ውሳኔ በዚህ አዋጅ መሠረት ተሽሯል፤

18/ The decisions made the Amhara Tiret Corporate to be accountable to the Region Council and Appointment of Board in accordance with the motion made regarding the Tiret Corporate by the Amhara National Region Council, in its Fifth Round, Fifth Year of its working term, held from November 10/2019 to November 11/2019 are hereby repealed;

19/ ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የተለመደ አሠራር በዚህ አዋጅ ውስጥ በተሸፈኑት ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

19/ Any law, regulation, directive or customary practice inconsistent with this Proclamation shall not apply to the matters covered by this Proclamation.

## 81.መብቶችን እና ግዴታዎችን ስለ ማስተላለፍ

## 81. Transfer of Rights and Obligations

1/ በአዋጅ ቁጥር 280/2014 መሬትን በተመለከተ ለክልሉ መሬት ቢሮ እና ለከተማ እና መሠረተ ልማት ቢሮ ተሰጥተው የነበሩ መብቶች እና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ አዲስ ለተቋቋመው መሬት ቢሮ ተላልፈዋል፤

1/ The rights and obligations granted to the Regional Land Bureau and Urban and Infrastructure Development Bureau regarding to land under Proclamation No. 280/2022 are hereby transferred to the newly established Land Bureau;

2/ በአዋጅ ቁጥር 280/2014 አንቀጽ 40 ንዑስ-አንቀጽ (4) ስር የስያሜ ለውጥ ከተደረገለት የመንግሥት ልማት ድርጅቶች አስተዳደር የሚመነጩ መብቶች እና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው የገንዘብ ቢሮ ተላልፈዋል፤

2/ The rights and obligations arising from the administration of government development organizations, which made change of nomenclature under Article 40, Sub-Article (4) of Proclamation No. 280/2022, are hereby transferred to the Finance Bureau established under this Proclamation;

3/ በአዋጅ ቁጥር 280/2014 ለከተሞች እና መሠረተ ልማት ቢሮ ተሰጥተው የነበሩት ከመሬት እና ከኮንስትራክሽን ከሚመነጩ መብቶች እና ግዴታዎች በስተቀር በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው የከተማ እና መሠረተ ልማት ቢሮ ተላልፈዋል፤

3/ Rights and obligations granted to Urban and Infrastructure Development Bureau under Proclamation No. 280/2022, except for rights and obligations arising from land and construction, are transferred to Urban and Infrastructure Development Bureau established by this Proclamation;

CamScanner

4/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 29 ንዑስ-አንቀጽ (24) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በአዋጅ ቁጥር 280/2014 ከኢንቨስትመንት ፈቃድ ከመስጠት የሚመነጩ መብቶች እና ግዴታዎች በስተቀር ለክልሉ ማዕድን ሀብት ልማት ቢሮ ተሰጥተው የነበሩት በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው የማዕድን ቢሮ ተላልፈዋል፤

5/ በአዋጅ ቁጥር 280/2014 መሠረት ለክልሉ ፍትሕ ቢሮ ተሰጥተው የነበሩ መብቶች እና ግዴታዎች በዚህ በአዋጅ መሠረት ለተቋቋመው የፍትሕ ቢሮ ተላልፈዋል፤

6/ ከካፒታል በጀት መደልደያ ቀመር እና መስፈርት ዝግጅት ከሚመነጩ መብቶች እና ግዴታዎች በስተቀር በአዋጅ ቁጥር 280/2014 ለገንዘብ ቢሮ ተሰጥተው የነበሩት ተግባራት እና ኃላፊነቶች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው የገንዘብ ቢሮ ተላልፈዋል፤

7/ በአዋጅ ቁጥር 280/2014 ለክልሉ ሥራ እና ሥልጠና ቢሮ ተሰጥተው የነበሩት መብቶች እና ግዴታዎች እንዲሁም በደንብ ቁጥር 200/2014 ለአሠሪ እና ሠራተኛ ጉዳይ ባለሥልጣን ተሰጥተው የነበሩት መብት እና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ በአዲስ ለተቋቋመው የሥራ እና ክህሎት ቢሮ ተላልፈዋል፤

8/ በአዋጅ ቁጥር 280/2014 ለክልሉ ሰላም እና ፀጥታ ቢሮ ተሰጥተው የነበሩት መብቶች እና ግዴታዎች ከፖሊስ እና ከማረሚያ ቤት ከሚመነጩ ተግባራት ውጭ በዚህ አዋጅ መሠረት ለተቋቋመው የሰላም እና ፀጥታ ቢሮ ተላልፈዋል፤

9/ በአዋጅ ቁጥር 280/2014 መሠረት ለሴቶች፣ ሕፃናት እና ማኅበራዊ ጉዳይ ቢሮ ተሰጥተው የነበሩት መብቶች እና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ መሠረት ለተቋቋመው የሴቶች፣ ወጣቶች እና ማኅበራዊ ጉዳይ ቢሮ ተላልፈዋል፤



4/ Without prejudice to the provision under Sub-article (24) of Article 29 in this proclamation, the rights and obligations granted to the Regional Mineral Resources Development Bureau under Proclamation No. 280/2022, except for the rights and obligations arising from issuance of investment licenses, are transferred to the Mining Bureau established by this Proclamation;

5/ The rights and duties assigned to the Regional Justice Bureau under Proclamation No. 280/2022 are hereby transferred to the Justice Bureau established under this Proclamation;

6/ The duties and responsibilities assigned to the Finance Bureau under Proclamation No. 280/2022, except for the rights and duties arising from preparation of capital budget allocation formula and criteria, are hereby transferred to the Finance Bureau established under this Proclamation;

7/ The rights and duties assigned to the Regional Employment and Training Bureau under Proclamation No. 280/2022 and the rights and duties assigned to the Employment and Labor Authority under Regulation No. 200/2022 are hereby transferred to the newly established Labor and Skills Bureau;

8/ The rights and obligations granted to the Regional Peace and Security Bureau under Proclamation No. 280/2022, except for functions arising from Police and Prisons, have been transferred to the Peace and Security Bureau established under this Proclamation;

9/ The rights and obligations granted to the Women, Children and Social Affairs Bureau under Proclamation No. 280/2022 have been transferred to the Women, Youth and Social Affairs Bureau established under this Proclamation;

CamScanner

10/ በአዋጅ ቁጥር 280/2014 መሠረት ለወጣቶች እና ስፖርት ቢሮ ተሰጥተው ከነበሩት መብቶች እና ግዴታዎች ውስጥ የወጣቶች ጉዳይ ለሴቶች፣ ወጣቶች እና ማኅበራዊ ጉዳይ ቢሮ እንዲሁም ስፖርትን የሚመለከቱ ተግባራት በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው የባሕል፣ ቱሪዝም እና ስፖርት ቢሮ ተላልፈዋል፤

11/ በበአዋጅ ቁጥር 280/2014 መሠረት ለሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ተሰጥተው የነበሩት መብቶች እና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ አዲስ ለተቋቋመው የሲቪል ሰርቪስ እና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ ተላልፈዋል፤

12/ በአዋጅ ቁጥር 280/2014 መሠረት ለፕላን እና ልማት ቢሮ ተሰጥተው የነበሩት መብቶች እና ግዴታዎች እንዲሁም የካፒታል በጀት መደልደያ ቀመር እና መስፈርት ዝግጅት በዚህ አዋጅ መሠረት ለተቋቋመው የፕላን እና ልማት ቢሮ ተላልፈዋል፤

13/ በአዋጅ ቁጥር 280/2014 መሠረት ለመንግሥት ኮሚዩኒኬሽን ቢሮ ተሰጥተው የነበሩ መብቶች እና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ መሠረት ለተቋቋመው የመንግሥት ኮሚዩኒኬሽን ቢሮ ተላልፈዋል፤

14/ የጣና ሐይቅ እና አካባቢው ሕይወተ ክልል ስፍራ አከላለል እና አስተዳደር፣ የጣና ሐይቅ እና ሌሎች የውኃ አካላት ጥበቃ እና ልማት ኤጀንሲ እንዲሁም ለአካባቢ እና ደን ጥበቃ ባለሥልጣን ተሰጥተው የነበሩት መብቶች እና ግዴታዎች ከደን ልማት ሥራዎች በስተቀር ሌሎቹ በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ተላልፈዋል፤

15/ በአዋጅ ቁጥር 280/2014 መሠረት ለክልሉ ንግድ እና ገበያ ልማት ቢሮ ተሰጥተው የነበሩ መብቶች እና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው የንግድ እና ገበያ ልማት ቢሮ ተላልፈዋል፤



10/ Among the rights and obligations granted to the Youth and Sports Bureau under Proclamation No. 280/2022, the Youth Affairs to the Women, Youth and Social Affairs Bureau, and Sports-related activities have been transferred to the Culture, Tourism and Sports Bureau established by this Proclamation;

11/ The rights and duties assigned to the Civil Service Commission under Proclamation No. 280/2022 are hereby transferred to the newly established Civil Service and Human Resources Development Bureau;

12/ The rights and duties assigned to the Planning and Development Bureau under Proclamation No. 280/2022 as well as Preparation of the Capital Budget Allocation Formula and Criteria, are hereby transferred to the Planning and Development Bureau established under this Proclamation;

13/ The rights and duties assigned to the Government Communications Bureau under Proclamation No. 280/2022 are hereby transferred to the Government Communications Bureau established under this Proclamation;

14/ The rights and obligations of Lake Tana and its Surrounding Bio-Zoning Area Demarcation and Management, the Lake Tana and Other Water Bodies Conservation and Development Agency as well as the Environment and Forest Conservation Authority, except for forest development activities, are transferred to Environmental Conservation Authority established by this Proclamation;

15/ The rights and obligations of the Regional Trade and Market Development Bureau under Proclamation No. 280/2022 are hereby transferred to Trade and Market Development Bureau established by this Proclamation;

CamScanner

16/ በአዋጅ ቁጥር 280/2014 መሠረት ለኢንዱስትሪ እና ኢንቨስትመንት ተሰጥተው የነበሩ ኢንዱስትሪን እና በሌሎች አካላት ሲከናወኑ የነበሩትን ጨምሮ ማናቸውንም የኢንቨስትመንት ሥራዎች የሚመለከቱ መብቶች እና ግዴታዎች በአዲስ ለተቋቋመው የኢንዱስትሪ እና ኢንቨስትመንት ቢሮ ተላልፈዋል፤

17/ በአዋጅ ቁጥር 280/2014 መሠረት ኮንስትራክሽንን አስመልክቶ ለክልሉ ከተሞች እና መሠረተ ልማት ቢሮ ተሰጥተው የነበሩ መብቶች እና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ አዲስ ለተቋቋመው የኮንስትራክሽን ባለሥልጣን ተላልፈዋል፤

18/ በአዋጅ ቁጥር 280/2014 ለመስኖ እና ቆላማ አካባቢዎች ልማት ቢሮ ተሰጥተው የነበሩ ሁሉም ተግባራት፣ ለአደጋ መከላከል እና ምግብ ዋስትና ኮሚሽን ተሰጥተው የነበሩ የምግብ ዋስትና ተግባራት፣ ለአካባቢ እና ደን ጥበቃ ባለሥልጣን ተሰጥተው የነበሩ የደን ልማትን የሚመለከቱ ሥራዎች እንዲሁም ለግብርና ቢሮ ተሰጥተው የነበሩት መብቶች እና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ መሠረት ለተቋቋመው የግብርና ቢሮ ተላልፈዋል፤

19/ በአዋጅ ቁጥር 280/2014 ለጤና ቢሮ ተሰጥተው የነበሩት መብቶች እና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ መሠረት ለተቋቋመው የጤና ቢሮ ተላልፈዋል፤

20/ በአዋጅ ቁጥር 280/2014 ለትምህርት ቢሮ ተሰጥተው የነበሩት መብቶች እና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ መሠረት ለተቋቋመው የትምህርት ቢሮ ተላልፈዋል፤

21/ በደንብ ቁጥር 81/2003 ዓ/ም ለእንስሳት እና ዓሣ ሀብት ልማት ማስፋፊያ ኤጀንሲ ተሰጥተው የነበሩት መብቶች እና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ መሠረት በአዲስ ለተቋቋመው የእንስሳት እና ዓሣ ሀብት ቢሮ ተላልፈዋል፤



16/ Rights and obligations related to any investment activities, including industry and activities carried out by other entities, which were previously assigned to Industry and Investment under Proclamation No. 280/2022, have been transferred to the newly established Industry and Investment Bureau;

17/ The rights and obligations assigned to the Regional Urbans and Infrastructure Development Bureau in relation to Construction under Proclamation No. 280/2022 are hereby transferred to the newly established Construction Authority;

18/ All duties assigned to the Irrigation and Lowland Development Bureau, duties assigned to the Disaster Prevention and Food Security Commission in relation to food security, duties assigned to the Environment and Forest Conservation Authority in relation to forest development as well as rights and obligations assigned to the Agriculture Bureau under Proclamation No. 280/2022 are hereby transferred to the newly established Agriculture Bureau;

19/ The rights and obligations granted to the Health Bureau under Proclamation No. 280/2022 are transferred to the Health Bureau established pursuant to this Proclamation;

20/ The rights and obligations granted to the Education Bureau under Proclamation No. 280/2022 are transferred to the Education Bureau established pursuant to this Proclamation;

21/ The rights and obligations granted to the Animal and Fisheries Development Extension Agency in Regulation No. 81/2011 are transferred to the newly established Animal and Fisheries Bureau by this Proclamation;

CamScanner

22/ በደንብ ቁጥር 128/2007 ለቅርሶች ጥበቃ እና የቱሪዝም ልማት ፈንድ ጽሕፈት ቤት እና በአዋጅ ቁጥር 280/2014 ለቱሪዝም ቢሮ ተሰጥተው የነበሩት መብቶች እና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ መሠረት በአዲስ ለተቋቋመው ባሕል፣ ቱሪዝም እና ስፖርት ቢሮ ተላልፈዋል፤

23/ በአዋጅ ቁጥር 280/2014 ለውኃ እና ኢነርጂ ቢሮ ተሰጥተው የነበሩት መብቶች እና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ መሠረት ለተቋቋመው የውኃ እና ኢነርጂ ቢሮ ተላልፈዋል፤

24/ በአዋጅ ቁጥር 296/2017 ለኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ቢሮ ተሰጥተው የነበሩት መብቶች እና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ መሠረት በአዲስ ለተቋቋመው የኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ቢሮ ተላልፈዋል፤

25/ በአዋጅ ቁጥር 280/2014 መሠረት ለገቢዎች ቢሮ ተሰጥተው የነበሩት መብቶች እና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው የገቢዎች ቢሮ ተላልፈዋል፤

26/ በአዋጅ ቁጥር 221/2007 መሠረት ለአማራ አመራር አካዳሚ ተሰጥተው የነበሩ መብቶች እና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ በአዲስ ለተቋቋመው የአማራ ክልል ስቴት ዩኒቨርሲቲ ተላልፈዋል፤

27/ በአዋጅ ቁጥር 101/1996 መሠረት ከምግብ ዋስትና ሥራዎች ከሚመነጩ መብቶች እና ግዴታዎች በስተቀር ለአደጋ መከላከል እና ምግብ ዋስትና ኮሚሽን ተሰጥተው የነበሩት መብቶች እና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ በአዲስ ለተቋቋመው የአደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን ተላልፈዋል፤

28/ በአዋጅ ቁጥር 160/2001 መሠረት ለአማራ ሕዝብ ዝክረ ታሪክ ማዕከል ተሰጥተው የነበሩ መብቶች እና ግዴታዎች እንዲሁም በደንብ ቁጥር 24/1996 ለተቋቋመው የሙሉዓለም የባሕል ማዕከል ተሰጥተው የነበሩት ተግባራት በዚህ አዋጅ በአዲስ ለተቋቋመው የባሕል፣ ኪነጥበብ እና ዝክረ ታሪክ ጽሕፈት ቤት ተላልፈዋል፤

22/ The rights and obligations granted to the Heritage Protection and Tourism Development Fund Office under Regulation No. 128/2015 and to the Tourism Bureau in Proclamation No. 280/2022 have been transferred to the newly established Culture, Tourism and Sports Bureau pursuant to this Proclamation;

23/ The rights and obligations granted to the Water and Energy Bureau under Proclamation No. 280/2022 are transferred to the Water and Energy Bureau established under this Proclamation;

24/ The rights and obligations granted to the Innovation and Technology Bureau under Proclamation No. 296/2025 are transferred to the newly established Innovation and Technology Bureau under this Proclamation;

25/ The rights and obligations granted to the Revenues Bureau under Proclamation No. 280/2022 are transferred to the Revenue Bureau established under this Proclamation;

26/ The rights and obligations granted to the Amhara Leadership Academy under Proclamation No. 221/2015 are transferred to the newly established Amhara Region State University in this Proclamation;

27/ The rights and duties assigned to the Disaster Prevention and Food Security Commission, except for the rights and duties arising from food security activities, pursuant to Proclamation No. 101/2004, are hereby transferred to the newly established Disaster Risk Management Commission;

28/ The rights and duties assigned to the Amhara People Memorial History Center pursuant to Proclamation No. 160/2009 and duties assigned to Mulualem Cultural Center established pursuant to Proclamation No. 24/2004 are transferred to the newly established Office of Culture, Arts and Memorial History;

29/ በአዋጅ ቁጥር 147/1999 መሠረት ለክልሉ ከተሞች ፕላን ኢንስቲትዩት ተሰጥተው የነበሩ መብቶች እና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ አዲስ ለተቋቋመው የፕላን ኢንስቲቲዩት ተላልፈዋል፤

30/ በአዋጅ ቁጥር 124/1998 የኅብረት ሥራ ማኅበራት ማስፋፊያ ኤጀንሲ እና በአዋጅ ቁጥር 280/2014 አንቀጽ 37 ንዑስ-አንቀጽ (3) ፊደል ተራ (መ) ሥር የኅብረት ሥራ ማኅበራት ማስፋፊያ ባለሥልጣን እየተባለ ሲጠራ ለነበረው አስፈፃሚ አካል ተሰጥተው የነበሩ መብቶች እና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ በአዲስ ለተቋቋመው የኅብረት ሥራ ኮሚሽን ተላልፈዋል፤

31/ በአዋጅ ቁጥር 208/2006 ለተቋቋመው የእፅዋት ዘር እና ሌሎች የግብርና ግብአቶች ጥራት ቁጥጥር እና ኳራንታይን ባለሥልጣን ተሰጥተው የነበሩ መብቶች እና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ አዲስ ለተቋቋመው የግብርና ጥራትና ቁጥጥር ባለሥልጣን ተላልፈዋል፤

32/ በአዋጅ ቁጥር 101/1996 ለተቋቋመው እና በአዋጅ ቁጥር 280/2014 አንቀጽ 37 ንዑስ-አንቀጽ (3) ፊደል ተራ (ሀ) ሥር የአደጋ መከላከል እና ምግብ ዋስትና ኮሚሽን እየተባለ ሲጠራ ለነበረው አስፈፃሚ አካል ተሰጥተው የነበሩ መብቶች እና ግዴታዎች ከምግብ ዋስትና ሥራዎች ከሚመነጩት መብቶች እና ግዴታዎች በስተቀር በዚህ አዋጅ በአዲስ ለተቋቋመው የአደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን ተላልፈዋል፤

33/ በአዋጅ ቁጥር 48/1992 ከተቋቋመው እና በአዋጅ ቁጥር 118/1997 ለተሻሻለው የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ተሰጥተው የነበሩ መብቶች እና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ በአዲስ ለተቋቋመው የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ተላልፈዋል፤



29/ The rights and obligations granted to the Regional Urbans Planning Institute under Proclamation No. 147/2007 are hereby transferred to the newly established Planning Institute;

30/ The rights and obligations granted to the Cooperative Extension Agency under Proclamation No. 124/2006 referred as the Cooperative Extension Authority executive organ under Proclamation No. 280/2022, Article 37, Sub-Article (3), Letter (D) are hereby transferred to the newly established Cooperative Commission;

31/ The rights and obligations granted to the Plant Seeds and Other Agricultural Inputs Quality Control and Quarantine Authority established by Proclamation No. 208/20014 are hereby transferred to the newly established Agricultural Quality and Quarantine Authority;

32/ The rights and obligations granted to the executive body referred as Disaster Prevention and Food Security Commission established by Proclamation No. 101/2004 and under Proclamation No. 280/2022, Article 37, Sub-Article (3), Letter (A), except for the rights and obligations arising from food security activities, are hereby transferred to the newly established Disaster Risk Management Commission;

33/ The rights and obligations granted to the Agricultural Research Institute established by Proclamation No. 48/2000 and amended by Proclamation No. 118/2005 are transferred to the newly established Agricultural Research Institute by this Proclamation;

CS CamScanner

34/ በአዋጅ ቁጥር 280/2014 መሠረት ለመንገድ ቢሮ ተሰጥተው የነበሩት መብቶች እና ግዴታዎች እንዲሁም በደንብ ቁጥር 199/2014 ለትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ ባለሥልጣን ተሰጥተው የነበሩት መብቶች እና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው የመንገድ፣ ትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ ቢሮ ተላልፈዋል፤

35/ በአዋጅ ቁጥር 235/2008 ዓ.ም እና በዚሁ አዋጅ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 147/2009 ዓ.ም ለክልሉ ገጠር መንገዶች ኮንስትራክሽን ኤጀንሲ ተሰጥተው የነበሩ መብቶችና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ በአዲስ ለተቋቋመው የገጠር መንገዶች ኮንስትራክሽን ኤጀንሲ ተላልፈዋል፤

36/ የክልሉ ምክር ቤት ጥረት ኮርፖሬትን በተመለከተ ለክልሉ ምክር ቤት ተጠሪ እንዲሆን እና የቦርድ አሰያየምን አስመልክቶ ያስተላለፈው ውሳኔ የሥራ አመራር ቦርድ አባላትን መሰየምን እና ሥልጣንና ተግባራትን መወሰንን ጨምሮ በዚህ አዋጅ ለክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ተላልፏል።

## 82. አለመግባባቶች ስለሚፈቱበት ሁኔታ

1/ የክልሉ አስፈፃሚ አካላት የክልሉን ሁለንተናዊ ልማት ለማፋጠን የጋራ እና ተናጠላዊ ኃላፊነቶቻቸውን በመወጣት፣ በትብብር እና በፉክክር መካከል ሚዛን ጠብቀው መሥራት ይገባቸዋል፤

2/ አስፈፃሚ ተቋማት ተግባራቸውን በብቃት ለመፈፀም የሌሎች ተቋማት ተሳትፎ በሚያስፈልግበት ጊዜ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ስምምነት በመፈራረም በጋራ መሥራት ይችላሉ።

3/ በአስፈፃሚ አካላት መካከል አለመግባባት ሲፈጠር በመጀመሪያ የሁሉንም ፍላጎት የሚያሟላ እና የክልሉን መንግሥት ፍላጎት የሚያሳካ መፍትሔ በጋራ መፈለግ ይገባቸዋል፤

4/ አለመግባባት የፈጠሩ አካላት በጋራ መፍትሔ መፈለግ ካልቻሉ ጉዳዩ ለርዕሰ መስተዳድሩ ቀርቦ ውሳኔ የሚሰጥበት ይሆናል።

## 83. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

1/ ቀደም ሲል በአዋጅ ቁጥር 280/2014 መሠረት ተቋቁመው ከነበሩ አስፈፃሚ አካላት ተግባር ተቀንሶ በአዲስ እንዲቋቋሙ ለተደረጉ ነገር ግን በዚህ አዋጅ ተግባር እና ኃላፊነት ላልተሰጣቸው አስፈፃሚ አካላት የተሰጡ ተግባራት ወደፊት በሕግ ተግባር እና ኃላፊነት እስኪሰጣቸው ድረስ ሥራው ቀደም ሲል ሲሠራ በነበረበት ተቋም አማካኝነት መከናወኑን ይቀጥላል፤ ሆኖም ይህ አዋጅ በክልሉ ምክር ቤት ከጸደቀ ከአራት ወራት በኋላ ድንጋጌው ተፈፃሚነት አይኖረውም፤



34/ The rights and obligations granted to the Roads Bureau under Proclamation No. 280/2022 as well as rights and obligations granted to the Transport and Logistics Authority under Proclamation No. 199/2022 are hereby transferred to the Roads, Transport and Logistics Bureau established by this Proclamation;

35/ The rights and obligations granted to the Regional Rural Roads Construction Agency under Proclamation No. 235/2015 and its amendment Proclamation Proclamation No. 147/2017 are hereby transferred to the newly established Rural Roads Construction Agency.

36/ The decision passed by the Region Council concerning Tiret Corporate to be accountable to it and designation of board members is transferred to Head of the Regional Government including designation of executive officer members and determination of powers and duties hereby this proclamation.

## 82. Methods of Dispute Resolution

1/ The executive bodies of the region shall work in a balanced manner between cooperation and competition, fulfilling their collective and individual responsibilities to accelerate the overall development of the region;

2/ Executive institutions may work together by signing agreements with relevant bodies when participation of other institutions is necessary to carry out their functions effectively;

3/ When disagreement between and among executive organs is arised, first, they need to find a common solution meeting their needs and achieving needs of the regional government;

4/ If the disagreeing bodies cannot find common solution, the case shall be submitted to and decided by the Head of Government.

## 83. Transitional Provision

1/ The duties assigned to the executive bodies previously established under Proclamation No. 280/2022 and cascaded to newly established, but the duties are not assigned under this Proclamation, shall continue to be performed by the institution in which the work was previously been performed until such time as the duties and responsibilities to be assigned to them by law; however, this provision shall not come into effect four months after the approval of this Proclamation by the Region Council;

CamScanner

2/ በሌሎች ሕጎች የተቋቋሙ እና ስያሜያቸው በዚህ አዋጅ የተሻሻሉ አስፈጻሚ አካላት ስያሜያቸው በዚህ አዋጅ በተገለፀበት አግባብ ተሻሽሎ ሥልጣን እና ተግባራቸው በተቋቋሙበት ሕግ እና እንደ አግባብነታቸው በሌሎች ሕጎች በተደነገገው መሠረት መከናወናቸውን ይቀጥላሉ፤ ሆኖም ተግባር እና ኃላፊነታቸው በአዲስ ሲሻሻል የተሻሻለውን ተግባር እና ኃላፊነት ይዘው ይቀጥላሉ፡፡

## 84. ደንብ የማውጣት ሥልጣን

የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ለዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ሙሉ ተፈጻሚነት የሚያስፈልጉትን ደንቦች ሊያወጣ ይችላል፡፡

## 85. መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 19 ንዑስ-አንቀጽ (1) ፊደል ተራ (ሰ) ድንጋጌ ሥር ለክልሉ አስፈጻሚ አካላት የተሰጠው የወል ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ ርዕሰ መስተዳድሩ ይህንን አዋጅ እና በአዋጁ መሠረት የሚወጡትን ደንቦች በተሟላ ሁኔታ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉትን ዝርዝር መመሪያዎች ሊያወጣ ይችላል፡፡

## 86. አዋጁ ስለሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በክልሉ ምክር ቤት ከፀደቀበት ከሐምሌ 21 ቀን 2017 ዓ/ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**ባሕር ዳር**

**ሐምሌ 21 ቀን 2017 ዓ/ም**

**አረጋ ከበደ ለጋስ**

**የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፕሬዚደንት**



2/ Executive bodies established by other laws and whose nomenclatures have been amended by this Proclamation shall continue to exercise their powers and duties in accordance with the law by which they were established and as prescribed by other laws, as appropriate; however they shall continue having the amended duties and responsibilities when same are newly amended.

## 84. Power to Issue regulations

The Regional Government Council may issue regulations necessary for the full implementation of the provisions of this Proclamation.

## 85. Power to Issue Directives

Without prejudice to the general authority granted to the executive organs of the region under the provision of Article 19, Sub-Article (1), Letter (G) of this Proclamation, the Head of Government may issue detailed directives necessary for the full implementation of this Proclamation and the regulations to be issued pursuant to it.

## 86. Effective date of the proclamation

This proclamation shall come into force on 28th July, 2025 since the date of its approval by the Regional Council.

**Done at Bahir Dar,**

**28th July, 2025**

**Arega Kebede Legas**

**The Amhara National Regional State President.**

CamScanner